እስከ ፣ ዮም ፣ እስከሚጽፍበት ።

ፀ ፣ ዳዊትኒ ፣ ይቤ ፣ ለትኩናሙ ፣ ግዕዶሙ ፣ መሥገርተ ፣ በቅድሜሆሙ ።
ዳዊትም ፣ ግዕድ ፣ ትምህርታቸው ፣ ከባቢ ፣ አሽከላ ፣ ትሹንባቸው ፣ ብሎ ፣ ተናግሯል ፤ (ሐተታ ፣) ግዕድ ፣ አላት ፣ ትምህርት ፣ ግዕድን ፣ ከበው ፣ እንዲማገቡት ፣ ትምህርትንም ፣ ከበው ፣ ይማሩታልና ፣ ለግዕድ ፣ እንዲጠባበቁለት ፣ ለትምህርትም ፣ ይጠባበቁለታልና ፣ ለግዕድ ፣ እንዲመራረጡት ፣ ለትምህርትም ፣ ይመራረጡለታልና ።

ለፍዳሆሙ ፣ መለዕቅፍቶሙ ፣ (መዝ ፣ ፷፱ ፣ ፳፫ ፣ ፳፱) ።
ፍዳ ፣ ልታመጣባቸው ፣ ዕቅፍት ፣ ነፍስ ፣ ልትቸነክባቸው ።

ፐ ፣ ይጽለግ ፣ አዕይንቲሆሙ ፣ ወኢያርአዩ ።
ዓይን ፣ ልቡናቸው ፣ ይጥፉ ፤ ወኢያርአዩ ፣ ምሥጢር ፣ አይዩ ።

ወይትቀጸዕ ፣ ዘባናቲሆሙ ፣ በዘሉ ፣ ጊዜ ።
ተስፋ ፣ ትንሣኤ ፣ ይጡ ፣ (ሐተታ ፣) እንስሳትን ፣ አስነንብሶ ፣ መፍጠሩ ፣ ተስፋ ፣ ትንሣኤ ፣ የለቸውም ፣ ሲል ፣ ነው ። ሰውን ፣ ግን ፣ አቅንቶ ፣ መፍጠሩ ፣ ተስፋ ፣ ትንሣኤ ፣ አለው ፣ ሲል ፣ ነው ፤ አሊህንም ፣ ተስፋ ፣ ትንሣኤ ፣ ይጡ ፣ ሲል ፣ ወይትቀጸዕ ፣ ዘባናቲሆሙ ፣ በዘሉ ፣ ጊዜ ፣ አለ ።

(አንድም ፣ መልስ) ፣) ዳዊትኒ ፣ ይቤ ፣ ለትኩን ፣ ግዕዶሙ ፣ መሥገርተ ፣ በቅድሜሆሙ ።
ግዕድ ፣ ምክራቸው ፣ ከባቢ ፣ አሽከላ ፣ ትሹንባቸው ፣ ብሎ ፣ ዳዊት ፣ ተናግሯል ፤ (ሐተታ) ፣ ግዕድ ፣ ማለት ፣ ምክርን ፤ ግዕድን ፣ ከበው ፣ እንዲማገቡት ፣ ምክርንም ፣ ከበው ፣ ይመክሩታል ፤ ለግዕድ ፣ እንዲጠባበቁለት ፣ ለምክርም ፣ ይጠባበቁለታልና ፤ ለግዕድ ፣ እንዲመራረጡት ፣ ለምክርም ፣ ይመራረጡለታልና ።

ለፍዳሆሙ ፣ መለዕቅፍቶሙ ።
ፍዳ ፣ ልታመጣባቸው ፣ ዕቅፍት ፣ ነፍስ ፣ ልትቸንባቸው ።

ይጽለግ ፣ አዕይንቲሆሙ ፣ ወኢያርአዩ ።
ዓይን ፣ ልቡናቸው ፣ ይጥፉ ፣ ወኢያርአዩ ፣ ምሥጢር ፣ አይዩ ።

ወይትቀጸዕ ፣ ዘባናቲሆሙ ፣ በዘሉ ፣ ጊዜ ።
ጀርባቸው ፣ በጥመሰ ፣ መንደልቶ ፣ ይበዋ ፣ ይጉበዋ ።

(አንድም ፣ መልስ) ዳዊትኒ ፣ ይቤ ፣ ለትኩን ፣ ግዕዶሙ ፣ መሥገርተ ፣ በቅድሜሆሙ ።
በቁሙ ፣ ግዕዳቸው ፤ ከባቢ ፣ አሽከላ ፣ ትሹንባቸው ።

ለፍዳሆሙ ፣ መለዕቅፍቶሙ ።
ፍዳ ፣ ልታመጣባቸው ። ዕቅፍት ፣ ነፍስ ፣ ልትቸንባቸው ።

ይጽለግ ፣ አዕይንቲሆሙ ፣ ወኢያርአዩ ።
ዓይናቸው ፣ በቀጠና ፣ ይጥፉ ።

www.zeyeneta.com

ወይትቀጻዕ ፡ ዘባናቲሆሙ ፡ በዙሉ ፡ ጊዜ ።

ያርባቸው ፡ በስልት ፤ ይበጥ ፡ ይጉበጥ ።

ያጌ ፡ ኣብል ፡ እንከ ፡ ተዐቅፉኑ ፡ ዝሙ ፡ ይደቅ ።

እስራኤል ፡ ከዘስፋው ፡ እንደዋው ፡ ሊቀሩ ፡ ከተስፋው ፡ ወው ፡ እሳለሁን ።
ሐለ ። (አልልም ።)
አኮኑ ፡ በእንተ ፡ ተዐቅፎሙ ፡ ኮነ ፡ ሕይወት ፡ ላዕለ ፡ አሕዛብ ።

እንዲህግ ፡ እንዳልል ፡ የእስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ መውጣት ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ኾኖ ፡ ያለግን ።
(ግብ ፡ሐዋ ፡ ፲፫ ፡ ፵፮ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፲፱)

ያፀ ፡ ሶበ ፡ ስሒተ ፡ ዚአሆሙ ፡ ብዕለ ፡ ኮነ ፡ ለአሕዛብ ፡ወጌጋየ ፡ ዚአሆሙ ፡ ሣህለ ፡ ኮነ ፡ ለዓለም ፡ እፎ ፡ እንጋ ፡ ኢምኮኑ ፡ ቋጸሚሆሙ ።

ሶበ ፡ ስሒተ ፡ ዚአሆሙና ፡ ወጌጋየ ፡ ዚአሆሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ብዕለ ፡ ኮነና ፡ ሣህለ ፡ ኮነ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የእስራኤል ፡ ስሕተታቸው ፡ በደላቸው ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ከኾነ ፡ ሕግ ፡ መፈጸማቸው ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።

እንድም ፡ ሰሒታ ፡ መንፈቅ ፡ ይላል ።

የከሉቶቹ ።እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ መውጣት ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ከኾነ ፡ መሳፍ ፡ ለእስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ ወጥተው ፡ ቢኾን ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።

አንድም ፡ የሐዋርያት ፡ አብዳን ፡ ዝንጉዓን ፡ ስሑታን ፡ ጊጉያን ፡ መባል ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ከኾነ ፡ ፍጹማን ፡ መባላቸው ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ፤ አንድም ፡ መንፈቆ ፡ ይላል ፡ የኩሉቶቹ ፡ ሐዋርያት ፡ አብዳን ፡ ዝንጉዓን ፡ ስሑታን ፡ ጊጉያን ፡ መባል ፡ ጥቅም ፡ ከኾነ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የሚኑ ፡ መላው ፡ ሐዋርያትማ ፡ አብዳን ፡ ዝንጉዓን ፡ ስሑታን ፡ ጊጉያን ፡ ቀርቷው ፡ ቢሆን ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።

ክፍል ፡ ፲፩ ።

፲፫ ፡ ነክሙ ፡ አብል ፡ ለአሕዛብ ።
ለእናንት ፡ ለአሕዛብ ፡ እገዲሃ ፡ እሳልው ።

አምጣነሰ ፡ ሐዋርያሆሙ ፡ እነ ፡ እሴብሓ ፡ ለሙልእከትየ ።

የአሕዛብስ ፡ ሐዋርያቸው ፡ ከኾንኽ ፡ ሹመቱን ፡ እንልጣታለሁ ፡ እሊያን ፡ ሔሩ ፡ መመሀሩ ፡ አንዳላቸው እኔንም ፡ ሔር ፡ ከመ ፡ ትጸር ፡ ስምየ ፡ ብውስተ ፡ አሕዛብ ፡ ብሉኒልኒ ። እንድም ፡ ትምህርቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለአሕዛብ ፡ ያደርጋል ፡ አኛን ፡ ዘመደቹን ፡ እይወደንም ፡ ላሉት ፡ እመጣ ፡ ያሕዛብ ፡ መምህራቸው ፡ ከኾንሁ ፡ እስራኤል ፡ ባሙኝ ፡ ያግኙኝ ፡ ብዬ ፡ ትምህርቱን ፡ እገልጣታለሁ ።

፲፬ ፡ አመቦ ፡ ከመ ፡ አትንያሙ ፡ በዝንቱ ፡ ለአዝማድየ ፡ ወለሕዝብየ ።

ወገኖቼ ፡ ዘመዶቼ ፡ እስራኤልን ፡ በቂሙ ፡ አቅኔናቸውና ፡ እንዲኾኑ ፡ ብዬ ፡ አንድም ፡ የማልቅናቸው ፡ ማስቀናት ፡ እንዳለ ፡ ብዬ ፤ ወአድኅን ፡ አለ ፡ ኮኑ ፡ አምኔሆሙ ። (፩ ፡ ጴጥ ። ፪ ፡ ፲ ።)

ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ የተመለሱትን ፡ አድናቸው ፡ እንዲኽን ፡ ብዬ ፡ የማድናቸው ፡ ግዳን ፡ እንዳለ ፡ ብዬ ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ ፀአተ ፡ ዚአሆሙ ፡ ሣህለ ፡ ኮነ ፡ ለዓለም ።

የእስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ መውጣት ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ኾኗልና ። እፎ ፡ ፈድፋደ ፡ ግንኛ ።
እፎ ፡ ፈድፋደ ፡እ ምኮነ ፡ ተመይጦቶሙ ፡ ሕይወት ፡ እምውታን ።

የእስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ መውጣት ፡ ለአሕዛብ ፡ ጥቅም ፡ ከኾነ ።
(ተመይጦሙ ፡ ሕይወትን) ዘሙታን ፡ ሕሊና ፡ ተለይተው ፡ ሕይወት ፡ የሚሆን ፡ መመለሳቸው ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።

አንድም ፡ (ተመይጦቶሙ ፡ ሕይወተ ፡) ወደሕይወት ፡ መመለሳቸው ፡ እንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።
አንደምን ፡ በጠቀመ ፡ ነበር ።

አንድም ፡ (እፎ ፡ አምኮነ ፡ ሕይወተ ፡ ተመይጦቶሙ ፡ አሙታን) ፡ ከሙታን ፡ ሕሊና ፡ ተለይተው ፡ መመለሳቸው ፡ እንደምን ፡ ጥቅም ፡ በኾነ ፡ ነበር ።

www.zeyeneta.com

፲፯ ፡ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ቀዳሚሃ ፡ ቅድስተ ፡ ወብሑዕኒ ፡ ቅዱስ ፡ ከማሁ ።
ዘመዶችህ ፡ ናቸውና ፡ እንጂ ፡ ታነጣጣቸዋለህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እርሶው ፡ ቢያምር ፡ ዳቦው ፡ ያምራል
ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሥርዋ ፡ ቅዱስ ፡ ከማሁ ፡ አዕጹቂሃኒ ፡ ቅዱስ ።
ሥሩ ፡ ጣፋጣ ፡ ቢሆን ፡ ጫፉም ፡ ጣፋጣ ፡ ይኾናል ፡ አምን ፡ እኮ ፡ የጥንተ ፡ ተንሥ ፡ የመምለኬ ፡ እግ
ዘአብሐር ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ።
እንድም ፡ ቢነደው ፡ ቢቆጨው ፡ እርሶው ፡ ቢያምር ፡ ዳቦው ፡ ያምር ፡ ነበር ፡
ሥሩ ፡ ጣፋጣ ፡ ቢሆን ፡ ጫፉም ፡ ጣፋጣ ፡ ይኾን ፡ ነበር ፡ እሊህ ፡ መሪራን ፡ አዕጹቅ ፡ ከመዪት ፡ ተገኝ
ተዋል ፡ ይላል ።

፲፰ ፡ ወለእመ ፡ ተሰብሩ ፡ እምአዕጹቂሃ ፡ ኪያከ ፡ እውልዐ ፡ ገዳም ፡ ተከሉ ፡ በመካኖሙ ።
አዕጹቅ ፡ ቢሰበሩ ፡ እንተን ፡ የበዳውን ፡ ዘይት ፡ በቤት ፡ ዘይት ፡ ስፍራ ፡ ተክለውሃል ።
ወኀበርከ ፡ ሥርወ ፡ ምስሌሆሙ ።
ከቤት ፡ ዘይት ፡ ጋራ ፡ በሥር ፡ እንድ ፡ ኾነሃል ።
ወኮንከ ፡ ዘይተ ፡ ከማሆሙ ፡ (ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ፡ ኤር ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ።)
እንደነሱ ፡ ዘይት ፡ ተብለሃል ።

፲፱ ፡ ወኢትዘሀር ፡ ላዕለ ፡ አዕጹቅ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በአዕጹቅ ፡ አትታበይ ።
ወእመሰ ፡ ተዘሀርከ ፡ እኮ ፡ እንተ ፡ ዘትጸውሮ ፡ ለሥርው ።
ብትታበይ ፡ ግን ፡ ጫፉ ፡ እንተ ፡ ሥሩን ፡ የምትሸከመው ፡ አይደለህም ።
አላ ፡ ሥርው ፡ ይጸውረከ ፡ ለከ ፡ (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፪ ።)
ሥር ፡ እሱ ፡ ጫፉን ፡ አንተን ፡ ይሸከመሃል ፡ እንጂ ።

አንድም ፡ (መልስ) ፡ ወለእመ ፡ ተሰብሩ ፡ እምአዕጹቂሃ ፡ ኪያከ ፡ እውልዐ ፡ ገዳም ፡ ተከሉ ፡ በመካኖሙ ።
እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ ቢወጡ ፡ ተሰፋ ፡ ያልተነገረልህ ፡ እንተን ፡ በእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ አግብተውሃል ።
ወኀበርከ ፡ ሥርወ ፡ ምስሌሆሙ ።
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ በተስፋ ፡ አንድ ፡ ኾነሃል ።
ወኮንከ ፡ ዘይተ ፡ ከማሆሙ ።
እንደነሱ ፡ ባለተስፋ ፡ ተብለሃል ።
ወኢትዘሀር ፡ ላዕለ ፡ አዕጹቅ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በአዕጹቅ ፡ በእስራኤል ፡ አትታበይ ።
ወእመሰ ፡ ተዘሀርከ ፡ እኮ ፡ እንተ ፡ ዘትጸውሮ ፡ ለሥርው ።
ብትታበይ ፡ ግን ፡ እስራኤል ፡ ባንተ ፡ ተስፋ ፡ የገቡ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ ሥርው ፡ ይጸውረከ ፡ ለከ ።
እንተ ፡ በእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ገብተሃል ፡ እንጂ ።

፳፪ ፡ ትብልኑ ፡ ተሰብሩ ፡ እምአዕጹቂየ ፡
እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ እንደወጡ ፡ ሊቀሩ ፡ ከተስፋው ፡ ወጡ ።
ወሕነ ፡ ኮንኩ ፡ ዐጽቀ ፡ ዘይት ፡ ህየንቴሆሙ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፫ ፡ ፵፮ ።)
እኔ ፡ በእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ገባው ፡ ትላለህን ፡

፳ ፡ ርቱዕ ፡ ይሰበሩ ።
መኾንስ ፡ ከተስፋው ፡ ሊወጡ ፡ ይገባል ።
እስመ ፡ ኢአምኑ ።
አላመኑምና ።
ወአንተሰ ፡ ቆምከ ።
እንተ ፡ ግን ፡ ከተሰፋው ፡ ገብተሃል ።
እሙ ፡ አመንከ ።
አምነሃልና ።
ፍሩሀ ፡ ንዜር ፡ እንከ ፡ ወኢታዕቢ ፡ ርእሰከ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ ፈርተህ ፡ ኑር ፡ አትታበይ ፡
አንድም ፡ መልስ ፡ ርቱዕ ፡ ይሰበሩ ።
(ርቱዕን ፡ ይሰበሩ) ፡ እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ እንደወጡ ፡ ሊቀሩ ፡
ይገባልን ።
እስመ ፡ ኢአምኑ ።
አላመኑምና ።

www.zeyeneta.com

ወእንተሰ ፡ ቆምከ ።

አንተሳ ፡ ከተስፋው ፡ ገብተሃል ፡ ገብተሃላ ።

አስሙ ፡ አመንከ ።

አምነሃልና ።

ፍሩሀከ ፡ ንበር ።

ዋ ፡ ፈርተህ ፡ ኑር ።

ወኢታዕቢ ፡ ርእሰከ ።

አትታበይ ።

ጸንፅ ፡ ሶበ ፡ ለአልከቱ ፡ እለ ፡ ፍጥረቶሙ ፡ ዘይት ፡ አሙንቱ ፡ ኢመሐኮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪያከኑ ፡ ይምሕከ ።

ጥንቱን ፡ የቤት ፡ ዘይት ፡ ለነበሩ ፡ ለእሊያ ፡ ካላዘነላቸው ፡ ላንተ ፡ ያዝንልሃልን ።

አንድም ፡ ጥንቱን ፡ ባለተስፋ ፡ ለነበሩ ፡ ለእስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ ካላዘነላቸው ፡ ተስፋ ፡ ላልተነገረልህ ፡ ላንተ ፡ ያዝንልሃልን ።

ጸጽ ፡ ርኢ ፡ አንከ ፡ ምሕረቶሂ ፡ ወአጥብያቶሂ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ምሕረቱንም ፡ ቁርጥ ፡ ፍርዱን ፡ አይ ፡ አለ ፡ አጥብያቶ ፡ አስራኤልን ፡ ከተስፋው ፡ ማውጣቱን ፤ ምሕረቶ ፡ አንተን ፡ በአስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ማግባቱን ።

ለእለሰ ፡ ወድቁ ፡ አውቀዮሙ ።

ከሃይማኖት ፡ የወጡትንስ ፡ ከተስፋው ፡ ለይታቸዋል ።

ወለከሰ ፡ ምሕረከ ፡ ለአመ ፡ ነበርከ ፡ በዘመሐረከ ።

ለአንተ ፡ ግን ፡ ባስተማረህ ፡ ትምህርት ፡ ብትጸና ፡ አዝኖልሃል ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ኪያከኒ ፡ ያወቅየከ ። (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ፡ ፅብ ፡ ፫ ፡ ፲፭) ።

ያለዚያ ፡ ግን ፡ ባትጸና ፡ አንተንም ፡ ከተስፋው ፡ ይለይሃል ።

ጸር ፡ ወሎሙኒ ፡ ይተከሎሙ ፡ ለአመ ፡ አምኑ ፡ ይከል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተኪሎቶሙ ፡ ዳግመ ፡ (ፍ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፮) ።

ተኪሎቶሙና ፡ ይተክሎሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ቢያምኑ ፡ ዳግመኛ ፡ አነሱንም ፡ ወደተስፋው ፡ ሊመልሳቸው ፡ ይቻለዋል ።

ጸፀ ፡ ኪያከ ፡ ጥቀ ፡ አውልዓ ፡ ገዳም ፡ ገዘመከ ፡ እምፍጥረትከ ፡ ወተከለከ ፡ ውስተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍጥረትከ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ዘይት ።

ውስተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍጥረትከና ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ዘይት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እንተን ፡ የበዳውን ፡ ዘይትስ ፡ እንኳ ፡ ከበቀልህበት ፡ ቆርጠ ፡ አምጥቶ ፡ ባልበቀልህበት ፡ በቤት ፡ ዘይት ፡ ሥፍራ ፡ ተክሎሃል ።

አፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ሎሙ ፡ ይክል ፡ ተኪሎቶመ ፡ አለ ፡ ዘይት ፡ እሙንቱ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ (ኤር ፡ ፲፩ ፡ ፲፯) ።

ጥንቱን ፡ የቤት ፡ ዘይት ፡ የሚኾኑ ፡ እኒያንማ ፡ ወደቦታቸው ፡ መልሶ ፡ ሊተክላቸው ፡ እንደምን ፡ አይ ቻለውም ።

(አንድም ፡ መልስ) ፡ ኪያከ ፡ ጥቀ ፡ አውልዓ ፡ ገዳም ፡ ገዘመከ ፡ አምፍጥረትከ ፡ ወተከለከ ፡ ውስተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ፍጥረትከ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ዘይት ።

ተስፋ ፡ ያልተነገረልህ ፡ አንተን ፡ አሕዛብንስ ፡ እንኳ ፡ ከመገንህ ፡ ለይቶ ፡ ባልተነገረልህ ፡ በእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ አግብቶሃል ።

አፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ሎሙ ፡ ይክል ፡ ተኪሎቶሙ ፡ ውስተ ፡ ፍጥረቶሙ ፡ እለ ፡ ዘይት ፡ እሙንቱ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ (ኤር ፡ ፲፩ ፡ ፲፯) ።

ጥንቱን ፡ ባለተስፋ ፡ የነበሩ ፡ እስራኤልንማ ፡ ወደተስፋው ፡ ሊመልሳቸው ፡ አንደምን ፡ አይቻሰውም ። (ሐተታ) ፡ የቤት ፡ ዘይት ፡ ሲያረጅ ፡ ቅብዕ ፡ ልምላሜ ፡ ያጣል ፤ የበዳውን ፡ ዘይት ፡ ቆርጠው ፡ ልጡን ልጠው ፡ ትተው ፡ የቤት ፡ ዘይትን ፡ ልጡን ፡ መርምረው ፡ ሳይቀጡ ፡ እንጨቱን ፡ ቆርጠው ፡ ጥለው ፡ የበዳውን ፡ ዘይት ፡ እንጨት ፡ አግብተው ፡ በቤት ፡ ዘይት ፡ ልጥ ፡ አስረው ፡ ይተመታል ። ይህስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የቤት ፡ ዘይትን ፡ ከመካከል ፡ ቆርጠው ፡ ጥለው ፡ እንደመጣጫ ፡ ይፈለፍሱታል ፤ አፈር ፡ ይደለድ ሉበታል ፤ የ በዳውን ፡ ዘይት ፡ ብቃያውን ፡ አምጥተው ፡ ተክለው ፡ ውኃ ፡ ያጠጡታል ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ሥር ፡ ይሰዳል ፡ ወደላይ ፡ ያድጋል ፤ ቅብዕ ፡ ልምላሜ ፡ ከቤት ፡ ዘይት ፤ ኃይል ፡ ጽንዕ ፡ ከበዳ ፡ ዘይት ፡ ኾኖ ፡ ታድሶ ፡ ይኖራል ፤ እንደዚህም ፡ ኹሉ ፡ ተስፋ ፡ ትንቢት ፡ ከእስራኤል ፤ ሃይማኖት ፤ ልጅነት ፡ ከአሕዛብ ፡ ኾኖ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉና ፤ የሌለ ፡ የሌላቸውን ፡ ሰጥቶ ፤ አድሎ ፡ መ ናገር ፡ ነው ፡ አንጂ ፡ ኹሉም ፡ በኹሉ ፡ አለ ።

www.zeyeneta.com

፩ ፡ መእረቅድ ፡ ለከሙ ፡ አኀዊነ ፡ ታአምሩ ፡ ዘንተ ፡ ምክረ ።
ሞጎድኖንችን ፡ ይህነን ፡ ትምህርት ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ፡ ዝ ፡ ምክሮሙ ፡ ወዝ ፡ ግብሮሙ ፡ ይሠሣር ፡ መሮኔፍ ፡ አንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፴፰ ።)

፪ ፡ ኢትበሉ ፡ ወጠቢባን ፡ ንሕነ ።
እየቆች ፡ ነን ፡ እንዳትሉ ፡ ታአምሩ ።

እሴሙ ፡ ውረተ ፡ ልብ ፡ ረከቦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ መከፈልቶሙ ።
እናውቃለን ፡ በግለት ፡ የእስራኤል ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ ጽዋዕ ፡ ተርታቸው ፡ ድንቁርና ፡ ኾኗልና ። (አንድም ፡ መከፈልቶሙ ፡ ለእስራኤል) ። እናውቃለን ፡ በግለት ፡ እኩሌቶቹን ፡ እስራኤልን ፡ ድንቁርና ፡ አግኝቷቸዋልና ።

እስከ ፡ አመ ፡ ይበውኡ ፡ ሙሉ ፡ እሕዛብ ፡ (ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፮) ።
እሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ተከተው ፡ ወደተስፋው ፡ እስኪገቡ ፡ ድረስ ።

፳፮ ፡ ወእምዝ ፡ የሐይዉ ፡ ሙሉ ፡ እስራኤል ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ቢያምኑ ፡ ይድናሉ ።

በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ እምጽዮን ፡ ይወፅእ ፡ መድኀን ።
መድኀን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይወጣል ።

ወያእትት ፡ ኃጢአተ ፡ እምያዕቆብ ፡ (ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፱ ፡ ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፶፱ ፡ ፳ ፡ መዝ ፡ ፻፱ ፡ ፯) ።
ከያዕቆብ ፡ ኃጢአትን ፡ ያስተሰርያል ።

፳፯ ፡ ወቦቱ ፡ ይረክቡ ፡ ተስፋሆሙ ፡ አመ ፡ አዕተትኩ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ (ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፴፬—፴፬) ።
ኃጢአታቸውን ፡ ባስተሰረይሁ ፡ ጊዜ ፡ በሱ ፡ ተስፋውን ፡ ያገኛሉ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ እምዝ ፡ የሐይዉ ።

፳፰ ፡ እመንገለ ፡ ወንጌልሰ ፡ ፀርነ ፡ እሙንቱ ፡ በእንቲአክሙ ።
ትወዳቸዋለህና ፡ እንጂ ፡ ታነሣሣቸዋለህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ በወንጌልስ ፡ በኩል ፡ ጠላቶቻችን ፡ ኖቸው ፡ አለ ፡ እኛ ፡ ብንወዳቸው ፡ እነሱ ፡ እይወዱንም ፡ (በእንቲአከሙ ፡) እናንተን ፡ ስላስተማርነ ።
ወእመንገለ ፡ ኅሬሰ ፡ አኀዊነ ፡ እሙንቱ ፡ በእንተ ፡ አበዊነ ።
በኀሬ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ከአብርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ስለተወለድን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ናቸው ፡

፳፱ ፡ አስሙ ፡ አልቦ ፡ ንስሓ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ።
በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንጌል ፡ ቅርብ ፡ ቀረባ ፡ የለምና ፤ እምዝ ፡ የሐይዉ ።

፴ ፡ በከመ ፡ አንትሙ ፡ ቀዲሙ ፡ ዐለውክምዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ቀድሞ ፡ እናንት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምፃችሁት ፡ እንደነበረ ።
ወይእዜሰ ፡ ተሣሃለክሙ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ብሏችኋል ፡ (ትችት) ።

፴፩ ፡ እስመ ፡ እሙንቱሂ ፡ ዐለውም ፡ በከመ ፡ አንትሙ ፡ ዐለውክምዎ ፡ ከግሁ ፡ እሙንቱሂ ፡ ዐለውም ፡ ይእዜ ።
አለውምና ፡ አለውክምዎ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ቀድሞ ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዐምፃችሁት ፡ እንደኋበረ ፡ እነሱም ፡ ዛሬ ፡ ዐምፀውታልና ።
ከመ ፡ ለሙኒ ፡ ይሣሃልሙ ።
እናንተን ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ፡ እነሱንም ፡ ዛሬ ፡ ይቅር ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንጌል ፡ ቅርብ ፡ ቀረቦ ፡ የለምና ፡ እምዝ ፡ የሐይዉ ።

፴፪ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘግሐ ፡ ለኵሉ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአት ፡ ከመ ፡ ይሣሃል ፡ ለኵሉ ፡ (ገላት ፡ ፫ ፡ ፳፪ ፤ ሮሞ ፡ ፲፩ ፡ ፴ ።)
እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በኃጢአት ፡ በረት ፡ ዘግቶት ፡ ስለነበረ ፡ ኹሉን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ይቅር ፡ ይልሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቦ ፡ ንስሐ ።

፴፫ ፡ ኦ ፡ ዕሙቀ ፡ ብዕሉ ፡ ለብዕለ ፡ ጥበቢሁ ፡ ወአእምሮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ፡ ዕውቀቱ ፡ የጥበቡ ፡ ምላት ፡ ስፋት ፡ ምን ፡ ይረቀ ፡ ምን ፡ ይጠልቅ ፡ ኦ ፡ ወዮ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ረቂት ፡ ነው ፤ ለጥበቡ ፡ ምላት ፡ ስፋት ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ።

ወአልቦ ፡ ውሮ ፡ ለፍናቲሁ ።
ባሕርዩ ፡ እይመረመርምና ።

www.zoyeneta.com

ወአልቦ ፡ ዘያአምሮ ፡ ለፍትሑ ፡ (ም ፡ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፲ ፡ ፭) ።
ፍርዱን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፤ እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ ይውጡ ፡ አሕዛብ ፡ በተስፋው ፡ ይግቡ ፡ ብሎ ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

፶፱ ፡ ወመኑ ፡ የአምር ፡ ሕሊናሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን ፡ ነገሩን ፡ ማን ፡ ያውቃል ።

ወመኑ ፡ ተማከሮ ፡ (ኢዮ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፲፫ ፡ ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፲፰ ፡ ፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፮) ።
እስራኤል ፡ ከተስፋው ፡ ይውጡ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ተስፋው ፡ ይግቡ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ መከረው ።

፶፭ ፡ ወመኑ ፡ ለቅሐ ።
የምክር ፡ ብድራት ፡ ማን ፡ አበደረው ።

ወተፈድዮ ። (ኢዮ ፡ ፵፩ ፡ ፪) ።
እንደመከርሁህ ፡ ምክረኝ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ ተከፈለው ።

ወአልቦ ፡ ዘየአምሮ ፡ ለፍትሑ ።
ድኅነት ፡ ዓለም ፡ በኔ ፡ ካሣ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ የፈረደበትን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ወመኑ ፡ የአምር ፡ ሕሊናሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ፡ ነገሩን ፡ ማን ፡ ያውቃል ።

ወመኑ ፡ ተማከሮ ።
ሰው ፡ ኹን ፡ ሥጋ ፡ ልበስ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ መከረው ።

ወመኑ ፡ ለቅሐ ።
የፍቅር ፡ ብድራት ፡ ማን ፡ አበደረው ።

ወተፈድዮ ።
እንደወደድሁህ ፡ ውደደኝ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ ተከፈለው ።

(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወአልቦ ፡ ዘየአምሮ ፡ ለፍትሑ ፡ በዲያብሎስ ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ወመኑ ፡ የአምር ፡ ሕሊናሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን ፡ ነገሩን ፡ ማን ፡ ያውቃል ።

ወመኑ ፡ ተማከሮ ።
ሰማይን ፡ ዝቅ ፡ ምድሩን ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ ፍጠር ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ መከረው ።

ወመኑ ፡ ለቅሐ ።
የሚፈጥርበትን ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ማን ፡ አበደረው ።

ወተፈድዮ ።
እንዳበደርኸህ ፡ ከፈለኝ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ ተከፈለው ፡

፷፮ ፡ እስመ ፡ ዚአሁ ፡ እምኔሁ ።
ኹሉ ፡ ከሱ ፡ የተገኘ ፡ ነውና ።

ወዚአሁ ፡ በእንቲአሁ ።
ኹሉ ፡ እሱን ፡ ስለማገልገል ፡ ነውና ።

ወዚአሁ ፡ ቦቱ ።
ኹሉ ፡ በሱ ፡ አምኖ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ለዘለዓለሙ ፡ ከብር ፡ ምስጋና ፡ ግንዘቤ ፡ የሚኾን ።

አሜን ።
በውነት ፡ እንበለ ፡ ሐሰት ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፪ ።

ክፍል ፲፱ ።

፩ ። እስተወድሶ ። አኀዊነ ፣ በማህሉ ፣ ለእግዚአብሔር ።

ወይድኅንዎን ፣ ብርሃናትን ፣ ማመላለሱን ፣ ማየትን ፣ ማፍሰሱን ፤ ነፋሳትን ፣ ማንፈሱን ፤ መዓልትና ፣ ሌሊትን ፣ በጋና ፣ ክረምትን ፣ ማፈራረቁን ፤ ማላጅ ፣ አድርጌ ፣ እማልዳችኋለኹ ። እንድም ፣ ሥጋዊውን ፣ ማላጅ ፣ አድርጌ ፣ እማልዳችኋለኹ ።

ረድዩ ፣ ነፍስተከሙ ፣ መሥዋዕተ ፣ ቅዱሰ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ (ም ፣ ፮ ፣ ፲፫ ።)

(በሀብት ፣ ተቃንተዋል ፣ በመሌሊት ፣ እየመሰለ ፣ ለመንገር ፣ ያመጣዋል) ፣ ሰውነታችኹን ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ከቡር ፣ መሥዋዕት ፣ እድርጉ ፣ ብዬ ፣ አስተበቍዐከሙ ፣ (ሐተታ) ፣ መቃናት ፣ ምኑን ፣ መሥዋዕት ። አለመቃናት ፣ ከቡር ፣ መሥዋዕት ፣ ኑውና ።

መሕያው ።

ሕያው ፣ መሥዋዕት ፣ ታደርጉ ፣ ዘንድ ፣ አድርጉ ፣ ብዬ ፣ እማልዳችኋኹ ፣ መቃናት ፣ ምውት ፣ መሥዋዕት አለመቃናት ፣ ሕያው ፣ መሥዋዕት ፣ ነውና ።

ወሥሙረ ፣ ወኀሩየ ፣ ይኩን ፣ ቍርባንከሙ ፣ (፩ ፣ ጴጥ ፣ ፪ ፣ ፭ ፣)
ቍርባናችሁ ፣ ያማረ ፣ የተወደደ ፣ ይኾን ፣ ዘንድ ።

ወቅኔከሙ ፣ ነባቢ ።

እግዚአብሔር ፣ አባታችን ፣ መንግሥተ ፣ ሰማይ ፣ ርስታችን ፣ ብላችሁ ፣ የምትገዙት ፣ አገዛዝ ፣ ያማረ የተወደደ ፣ ይኾን ፣ ዘንድ ፣ ይኹን ፣ ብዬ ፣ እግልዳችኋለሁ ። አንድም ፣ ነባቤ ፣ ይላል ፣ የምትገዙት ፣ አገዛዝ ፣ ተካሰ ፣ ዋጋችሁን ፣ የሚያሰጣችሁ ፣ ይኾን ፣ ዘንድ ፣ ይኹን ፣ ብዬ ፣ አስተበቍዐከሙ ።

ኢታፍቅርዎ ፣ ለዝ ፣ ዓለም ፣ ወሐድሱ ፣ ልበከሙ ። (ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፳፫ ፣)
ይህን ፣ ዓለም ፣ አትውደዱ ፣ ልቡናችሁን ፣ በዕውቀት ፣ አድሱ ፣ መቃናት ፣ ብሌት ፣ አለመቃናት ፣ ተሐድሶ ፣ ነውና ።

ወአመክሩ ፣ ዘይፈቅድ ፣ እግዚአብሔር ። (ኤፌ ፣ ፭ ፣ ፲ ፣ ፲፯ ።)
እግዚአብሔር ፣ የሚወደውን ፣ ሥራ ፣ መርምራችሁ ፣ ያዙ ፣ (ሐተታ) ። መመርመር ፣ ከመጻሕፍት ፣ ከመምህራን ፣ ከልቡና ።

ዘሠናይ ።

የከፉውን ፣ ትታችሁ ፣ የበጎውን ፣ ያዙ ።

ወዘጽድቅ ፣

የሐሰቱን ፣ ትታችሁ ፣ የውነቱን ።

ወዘፍጹም ።

የወጣኒውን ፣ ትታችሁ ፣ የፍጹሙን ፣ ያዙ ።

፫ ። ወእነግረከሙ ፣ ሰሉልከሙ ፣ በጸጋ ፣ እግዚአብሔር ፣ ዘተውህበ ፣ ሊተ ።

ለኹላችሁም ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ በተሰጠኝ ፣ ሐዋርያነት ፣ እነግራችኋለኹ ።

ከመ ፣ ኢትትዐበዩ ።

እንዳትታበዩ ፣ እትታበዩ ፣ ብዬ ።

ወኢተሐልዩ ፣ ትዝህርተ ።

ትዝህርትን ፣ እንዳትይዙ ፣ አትያዙ ፣ ብዬ ።

ሐሊዮ ፣ በዘታነጽሑ ፣ ርእሰከሙ ፣ እምዝሙት ።

ስውነታችሁን ፣ ከዝሙት ፣ በምትለዩት ፣ ገንዘብ ፣ የምትለዩበትን ፣ ሥራ ፣ ሥሩ ፣ እንጂ ፣ አስ ፣ ትሕትና ፣ ያዙ ፣ እንጂ ፣ ኢተሐልዩ ።

መጠነ ። ዘከመ ፣ ከፈለ ፣ እግዚአብሔር ፣ በመሰፈርተ ፣ ሃይማኖቱ ፣ (ሮሜ ፣ ፲፪ ፣ ፲፩ ፣ ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፯ ።)
ጌሉም ፣ እንደ ፣ ሃይማኖቱ ፣ መጠን ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዳደለው ፣ እንዳደሰው ፣ ጸጋ ፣ ይኑር ።

፬ ። ዘከመ ። ዘውስተ ፣ አሐዱ ፣ ነፍሰትን ፣ ብዙኅ ፣ መለያልይ ፣ ብነ ።

ግንድ ፣ አካላችን ፣ ብዙ ፣ ሕዋስ ፣ እንዳለን ።

መዘዘኢኮ ፣ ምክፋሉ ። (ኤፌ ፣ ፬ ፣ ፳፭ ፣)
ሥራውም ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ እንደኾነ ፣ ያይን ፣ ግየት ፣ የጆሮ ፣ መስማት ፣ የእግር ፣ መሔድ ፣ የእጅ ፣ መዳሰስ ፣ እንደኾነ ።

www.zeyeneta.com

ፍ ፡ ከማሁ ፡ ዘልእነ ፡ እንዘ ፡ ብዙኃን ፡ አሐዱ ፡ ሥጋ ፡ ንሕነ ፡ በክርስቶስ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።)
እንደዚህም ፡ ብዙ ፡ ስንኾን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ነን ፡ (ሐተታ) ፡ ይሖት ፡ እንደ ፡ መጣው ፡ አንድ ፡ ስን ኾን ፡ ብዙ ፡ ነን ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበር ፡ ወይ ፡ ምሥጢር ፡ ሒዶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ፌ ፡ ወብክሙ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ።
እንደዚህም ፡ ክኾነ ፡ ክእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠ ፡ ልጅነት ፡ አላችሁ ። ወዘዘአዙ ፡ ጸጋሁ ።
ህብቱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኔው ።

ዘሂ ፡ ይትኔበይ ፡ በሐሳበ ፡ ሃይማኖቱ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ።)
መጻእያትን ፡ የሚናገር ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ መጻእያትን ፡ የሚናገር ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡ መጻአያትን ፡ የሚናገሩ ፡ ነቢያት ፡ ናቸው ፡ በዓይን ፡ ይመሰላሉ ።

ፂ ፡ ወዘሂ ፡ ይትለአክ ፡ በመልእክቱ ።
የሚረዳም ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ የሚረዳ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡ የውስጥ ፡ አርድእት ፡ ናቸው ፡ በእጅ ፡ ይመሰላሉ ።
ወዘሂ ፡ ይሜህር ፡ በትምህርቱ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲-፲፩ ።)
የሚያስተምርም ፡ አንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ የሚያስተምር ፡ በዚ ያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። ተሾመው ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፡ በአፍ ፡ ይመሰላሉ ።

ፃ ፡ ወዘሂ ፡ ይትፌሣሕ ፡ በፍሥሓሁ ።
ሳይሾም ፡ የሚያስተምር ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ።
ሳይሾሙ ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፡ በእፍንጫ ፡ ይመሰላሉ ።
ወዘሂ ፡ ይሠየም ፡ ክሙ ፡ ያስልጥ ፡ መልእክቶ ።
ተልእኮውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ የሚሾም ፡ አለ ፡ የሚረዳ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ የሚረዳ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። የእፍአ ፡ አርድእት ፡ ናቸው ፡ በእግር ፡ ይመሰላሉ ፡ የላይኛውን ፡ የውስጥ ፡ አርድእት ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ የአፍአ ፡ አርድእት ፡ የላይኛ ውን ፡ የእፍአ ፡ አርድእት ፡ ያሉ ፡ አንደ ፡ ኾነ ፡ ይህን ፡ የውስጥ ፡ አርድእት ፡ ማለት ፡ ነው ።
ወዘሂ ፡ ይምሕር ፡ በምሕሮቱ ፡ (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፷ ፡ ፪ ። ፱ ፡ ፯ ።)
ሰሰው ፡ የሚያዝን ፡ የሚራራ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ነው ፤ እንደ ሃይማኖቱ ፡ መጠን ፡ ለሰው ፡ የሚያዝን ፡ የሚራራ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። ለሰው ፡ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ ባለጸጎች ፡ ናቸው ፡ በልብ ፡ ይመሰላሉ ።

፱ ፡ ተፋቀሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።)
ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ይጠቅምን ፡ እይጠቅም ፡ ሳትሉ ፡ አንድም ፡ ኃጥእ ፤ ጻድቅ ፡ እሚ ፡ መናፍቅ ፡ ላትለያዩ ፡ ፍቅርን ፡ ያዙ ።
ተገሐሡ ፡ እምእኩይ ፡ ወትልዉ ፡ ሠናየ ። (መዝ ፡ ፴፬ ፡ ፲፬ ፤ ፻፲ ፡ ፲ ።)
ክፉውን ፡ ትታችሁ ፡ በጎውን ፡ ያዙ ።

፲ ፡ ወአድልዉ ፡ ለጽድቅ ።
ለጽድቅ ፡ አብልጡ ።
አፍቅሩ ፡ ቢጸክሙ ።
በሃይማኖት ፡ የመሰላችሁ ፡ ወንድማችሁን ፡ ውደዱ ።
ወኩኑ ፡ መሐርያነ ።
ለሰው ፡ የምታዝኑ ፡ የምትራሩ ፡ ኹኑ ።
ተካበሩ ፡ በበይናቲክሙ ። (ሬሌጵ ፡ ፪ ፡ ፫ ።)
እርሰ ፡ በርሳችሁ ፡ ተረዳዱ ፡ ክብት ፡ ለሌለው ፡ ክብት ፡ ጉልበት ፡ ለሌለው ፡ ጉልበት ፡ ኾናችሁ ።
ወአክብሩ ፡ መኳንንቲክሙ ።
መምህሮቻችሁንም ፡ አርዱ ።

፲፩ ፡ ወለጸህቅ ፡ ኢትትሀከዩ ።
የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አትበሉ ።
ለመንፈስ ፡ ተሐይዉ ።
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ አንደ ፡ ኾነ ፡ በነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ትኾናላችሁ ።
ለእግዚአብሔር ፡ ተቀነዩ ። (ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ፤ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ።)
ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ።

www.zeyeneta.com

፲፭ ፤ ለተስፋክሙ ፣ ተፈጸሙ ።
ተስፋችሁንም ፣ ለማግኘት ፣ ደሰ ፣ ይበላችሁ ።
ለሕማምክሙ ፣ ተዐገሡ ።
መከራውን ፣ ታግሣችሁ ፣ ተቀበሉ ።
ለጸሎትክሙ ፣ ተጸመዱ ። (፩ ፣ ተሰ ፣ ፭ ፣ ፲፯ ።)
ለጸሎት ፣ ጽሙዳን ፣ ኹኑ ።

፲፫ ፣ ለግብረ ፣ ቅዱሳን ፣ ተሳተፉ ።
እስተዋዕእውን ፣ ለማወጣጣት ፣ እንድ ፣ ኹኑ ።
አፍቅሮ ፣ ንግድ ፣ እትልዉ ። (ዘፍጥ ፣ ፲፰ ፣ ፫ ፣ ፲፱ ፣ ፪ ፣ ፫ ፣ ዕብ ፣ ፲፫ ፣ ፪ ።)
እንግዳ ፣ መቀበልን ፣ ውደዱ ፣ እትጉዉ ።

፲፬ ፣ ድኅርዎሙ ፣ ለአሰ ፣ ይሰድዱክሙ ።
ሀገር ፣ አስጥለው ፣ የሚያሳድዷችሁንም ፣ መርቁ ። ከቦታችሁ ፣ አያናውጣችሁ ፣ ከመንግሥት ፣ ሰማይ ፣ እያወጣችሁ ፣ ብላችሁ ።
ደኅሩ ፣ ወኢትርግሙ ። (ማቴ ፣ ፭ ፣ ፵፬ ፤ ግብ ፣ ሐዋ ፣ ፯ ፣ ፶፱ ፣ ፩ ፣ ቆሮ ፣ ፬ ፣ ፲፪ ።)
መርቁ ፣ እንጂ ፣ እትራገሙ ።

፲፭ ፣ ምስለ ፣ ዘይትፌሣሕ ፣ ተፈሥሑ ።
ሀብት ፣ ስርየት ፣ አግኝተ ፣ ደስ ፣ ከሚሉው ፣ ጋራ ፣ ደስ ፣ ይበላችሁ ።
ወምስለ ፣ ዘይብኪ ፣ ብክዩ ። (መዝ ፣ ፴፭ ፣ ፲፫ ፣ ግቴ ፣ ፳፭ ፣ ፴፮ ።)
ሀብት ፣ ስርየት ፣ እጥቶም ፣ ከሚያዝን ፣ ከሚያለትስ ፣ ጋራ ፣ እዘኑ ፣ አልቅሱ ፣ (ታሪክ) ፣ እንደ ፣ ኹሰት ፣ አጋው ፣ ሰተልእኮ ፣ በወጡበት ፣ እንዱን ፣ ድቀት ፣ አግኝቶት ፣ አድሯል ፣ በነጋው ፣ ወንድሜ ፣ እኔ ፣ ድቀት ፣ አግኝቶኛልና ፣ እንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ታመልሼ ፣ ከዚያ ፣ ገዳም ፣ እልሑድም ፣ ዓለሙን ፣ መስዬ ፣ እናራለሁ ፣ አለው ። እኔም ፣ እንጂ ፣ አግኝቶኛል ፤ ይልቁንስ ፣ ሐደን ፣ ኃጢአታችንን ፣ ለመሆሪ ፣ ንስሐችን ፣ ነግረን ፤ ቀኖናችንን ፣ ተቀብለን ፣ እንደ ቀደሙው ፣ ኾነን ፣ እንናራለን ፣ ብሎ ፣ አጽናንቶ ፣ ይዞት ፣ ሐደ ። ሐደው ፣ ለመሆሪ ፣ ንስሐቸው ፣ ነግረው ፣ ቀኖናቸውን ፣ ተቀብለው ፣ ፩ ሱባዔ ፣ ቀኖና ፣ እንዳደረ ፣ ሪሱ ፣ ለረይኩ ፣ ለከ ፣ በእንተ ፣ ዘኢገብረ ፣ እጉከ ፣ የሚል ፣ ድምፅ ፣ አለምቶታል ፣ (ዜና ፣ እበው) ።

፲፮ ፣ ወከመዝ ፣ ሐልዩ ፣ ምስለ ፣ ቢጽክሙ ። (ም ፣ ፲፭ ፣ ፭) ።
በሃይማኖት ፣ ከመሰሏችሁ ፣ ወንድሞቻችሁ ፣ ጋራ ፣ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ያለውን ፣ ሥራ ፣ ሥሩ ።
ወትዕቢተሰ ፣ ኢተሐልዩ ።
ትዕቢትን ፣ ግን ፣ እትያዙ ።
ወከመ ፣ ዘያቈሕት ፣ ርእሶ ፣ ተመሰሉ ።
ትሕትናን ፣ የያዘውን ፣ ሰውም ፣ ምሰሉ ፣ ሙሴን ፣ ጴጥሮስን ፤ ራሱን ፤ እሰጢፋኖስን ።

፲፯ ፣ ወኢትበሉ ፣ ጠቢባን ፣ ንሕነ ። (ኢሳ ፣ ፭ ፣ ፳፩ ።)
እዋቆች ፣ ነን ፣ እትበሉ ።
ወኢትፍድይዎ ፣ እኩየ ፣ ለዘአሕሰመ ፣ ለክሙ ።
የበደላችሁንም ፣ እንደ ፣ በደለን ፣ እንበድሰው ፣ አትበሉ ።
ሠናየ ፣ ተናገሩ ፣ ምስለ ፣ ቢጽክሙ ። (፩ ፣ ተሰሎ ፣ ፭ ፣ ፲፭ ፣ ፳፪ ።)
በጎይማኖት ፣ ከመሰሏችሁ ፣ ወንድሞቻችሁ ፣ ጋራ ፣ በጎ ፣ በንውን ፣ ነገር ፣ ተጨዋወቱ ።

፲፰ ፣ ወእመሰ ፣ ይትከሀለክሙ ፣ ምስለ ፣ ኵሉ ፣ ሰብእ ፣ ተአኅዉ ። (ማር ፣ ፱ ፣ ፶ ፣ ዕብ ፣ ፲፪ ፣ ፲፬ ።)
ሰሬቻላችሁስ ፣ ከኹሉ ፣ ጋር ፣ ወንድሜ ፣ ወንድሜ ፣ ተባባሉ ።

፲፱ ፣ ወኢትትበቀሉ ፣ ለሊክሙ ።
እናንት ፣ እንበቀላለን ፣ እትበሉ ።
አኅዊነ ፣ አኅልፍዎ ፣ ለመዓት ።
ወንድሞቻችን ፣ ቂምን ፣ እርቋት ፣ (ሐተታ) ፣ እንደ ፣ ዋርካ ። ዋርካ ፣ በቡታያንቷ ፣ ሳለች ፣ አንድ ፣ ብላቴና ፣ ነቅሎ ፣ ይጥሏታል ። ካደገች ፣ ከንነች ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ ብዙ ፣ ሰው ፣ ብዙ ፣ ምሳር ፣ ብዙ ፣ መጫኛ ፣ ታስፈልጋለች ። ቂምም ፣ የዋለች ፣ ያደረች ፣ እንደኾነ ፣ ከቀቷል ፣ ታደርሳለች ፣ ከቀቷልም ፣ ከደረሰች ፣ ፍዳዋ ፣ ይጸናልና ። አንድም ፣ ከሀደትን ፣ ከናንተ ፣ እርቋት ፣ መዓተ ፣ እርዮስ ፣ እንዲል ።

www.zeyeneta.com

እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እነ ፡ እትቤቀል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእነ ፡ እትፈደይ ። (ዘሌዋ ፡ ፲፱፡ ፲፰ ። ግቴ ፡ ፭ ፡ ፴፪ ። ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፴፭ ።)

እኔ ፡ እበቀላለሁ ፡ ፍዳ ፡ ኃጢአትንም ፡ እከፈላለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏልና ፡ እኅልፍዋ ።

ኛ ፡ ወእመኒ ፡ ርኀበ ፡ ጸላኢከ ፡ አብልኦ ።

እንተስ ፡ ጠላትህ ፡ ቢራብ ፡ አብላው ።
ወለእመኒ ፡ ጸምዐ ፡ አስትዮ ።
ቢጠማም ፡ አጠጣው ።

ወዘንተ ፡ ለአመ ፡ ገበርከ ፡ አፍሓመ ፡ እሳት ፡ ታስተጋብአ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ (ምሳ ፡ ፳፭ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ግቴ ፡ ፭ ፡ ፴፬ ።)

ይህን ፡ ያደረግህ ፡ እንደሆነ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፍሓመ ፡ እሳትን ፡ ትቋበሳለህ ፡ አለ ፡ እኔ ፡ ስጠላው ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ቢፈራኝ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ቢል ፤ አፍሓመ ፡ ገሃነምን ፡ ታስፈርድበታለህ ። እኔ ፡ ስጠላው ፡ እርሱ ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርግልኝ ፡ የበለጠች ፡ መንግሥት ፡ ስማይ ፡ አንዳለች ፡ እንጂ ፡ ቢያውቅ ፡ ነው ፡ ቢል ፤ አፍሓመ ፡ ፍቅርን ፡ ታሳድርበታለህ ። ቃሉ ፡ ቃለ ፡ ሰሎሞን ፡ ነው ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ ተናግሮታል ። (ምሳ ፡ ፳፭ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።)

ኛ፩ ፡ ወኢትግእ ፡ ለአኩይ ፡ በእኩይ ።

ክፉውን ፡ ስው ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ ድል ፡ እንጣዋለሁ ፡ ክፉውን ፡ ግብር ፡ በክፉ ፡ ግብር ፡ አጠፋዋለሁ ፡ አትበል ።

አላ ፡ ግእ ፡ ለአኩይ ፡ በገቢረ ፡ ሠናይ ።

ክፉውን ፡ ግብር ፡ በበጎው ፡ ግብር ፡ አጥፋው ፡ እንጂ ፤ ክፉውን ፡ ስው ፡ በበጎ ፡ ግብር ፡ ድል ፡ ንጣው ፡ እንጂ ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ፡ ለኵሉ ፡ ነፍስ ፡ መኳንን ፡ ተኩነኑ ።

አክብሩ ፡ መኳንንቲከሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ። ያውስ ፡ ቢኾን ፡ ለመኳንን ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ለክርስቶስ ፡ ለመኳንንተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ለሐዋርያት ፡ እንዛለን ፡ እንጂ ፡ ለኹሉ ፡ እንዛለን ፡ (እንዳይሉት) ፡ ገሠጽ ፡ ለኾነ ፡ ኹሉ ፡ ተገዙ ፡ ለንጉሥ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። (፩ ጴጥ ፡ ፪፡ ፭)

እስመ ፡ ኢይሠየም ፡ መኰንን ፡ በእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ። (ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። ምሳ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ።)

ገዢ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አይሾምምና ። አእምር ፡ ከመ ፡ ልዑል ፡ ይኬንን ፡ መንግሥተ ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወለዘፈቀደ ፡ ይሁብ ፡ እንዲል ፡ (ዳን ፡ ፬ ፡ ፳፱ ።) እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይፈንምሙ ፡ ካለ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ።)

ወእምኀመስ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ ብውሕ ፡ ለቱ ።

መሾሙስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከኾነ ፡ ኹሉ ፡ ሊገዛለት ፡ ይገባል ። አንድም ፡ ነፍጡ ፡ መርቡጡ ፡ እሳቱ ፡ ስለቱ ፡ መቅጫው ፡ በእጁ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቀጣችኋል ። አንድም ፡ የወዲሁም ፡ የወዲያውም ፡ ዓለም ፡ ፍርድ ፡ የሱ ፡ ነው ፡ ይፈርድባችኋል ፡ (ሐተታ) ፡ የወዲሁስ ፡ ይኹን ፡ የወዲያው ፡ እንደምነው ፡ ቢሉ ፡ በወዲሁ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ በወዲያው ፡ የሚያስፈርድባቸው ፡ ስለኾነ ፡ ተዝለት ፡ ሳልኋችሁ ፡ ለማ ፡ ያልተገዛችሁ ፡ ብሎ ፡ እስመ ፡ ዘኩሉ ፡ ለቱ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫።)

፪ ፡ ወዘሰ ፡ አበየ ፡ ተኩንኖ ፡ ለመኰንን ፡ ትእዛዘ ፡ ኦግዚአብሔር ፡ አበየ ።

ገዥ ፡ ለኾነው ፡ ኹሉ ፡ እልገዛም ፡ ያለ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አፈረሰ ፡ ዘሰ ፡ አበዮ ፡ ለቂሮስ ፡ ኪያየኒ ፡ ዓበየ ፡ እንዲል ።

ወእሰሰ ፡ አበዩ ፡ ተኩንኖ ፡ ዙኒኔ ፡ ያመጽኡ ፡ ለርእሶሙ ።

እንገዛም ፡ ያሉስ ፡ ለርእሶሙ ፡ ራሳቸውን ፡ ለመጉዳት ! አንድም ፡ በርእሶሙ ፡ በራሳቸው ፡ ፍዳን ፡ ያመጣሉ ።

፫ ፡ ወመኳንንትሰ ፡ ኢኮኑ ፡ ግሩማነ ፡ ለዘይገብር ፡ ሠናየ ።

መኳንንትማ ፡ እንጂ ፡ እንዳንገዛላቸው ፡ ግሩማን ፡ ናቸው ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ የመኳንንትስ ፡ ግሩማንነታቸው ፡ ለፈቃደኛ ፡ እይደለም ።

www.zeyeneta.com

ዘእንበለ ፡ ለዘእኩይ ፡ ምግባሩ ።
ግብሩ ፡ ክፉ ፡ ለኾነ ፡ ሰዐመፀኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወእመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ኢትፍርሆሙ ፡ ለመኳንንት ፡ ግበር ፡ ሠናየ
መኳንንትን ፡ ላትፈራቸው ፡ ከወደድህስ ፡ ንብር ።

ወዓዲ ፡ እሙንቱ ፡ ያእዙቱከ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።)
ዳግመኛ ፡ እነሱም ፡ ግምጃ ፡ አውራጃ ፡ ሹመት ፡ ሽልማት ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሰጥተው ፡ ያከብሩሃል ።
ወያእዙትምሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለሠናይት ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ እንድ ፡ ነው ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።)

እስመ ፡ ላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሙንቱ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ታሠኒ ፡ ምግባረከ ።
እንት ፡ ሥራህን ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሹመዋልና ።

ወእመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ኢትፍራህ ፡ ግበር ፡ ሠናየ ።
ላትፈራ ፡ ከወደድህስ ፡ ንብር ።

ወዘእኩ ፡ ለከንቱ ፡ እኩነንምሙ ፡ መጥባሕተ ።

ዓይን ፡ በፍላት ፡ እጅ ፡ እግር ፡ በስለት ፡ ላይሠሩ ፡ ላይቀጡ ፡ ፍትሐ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ያሠለጠናቸው ፡ አይደለምና ።

እስመ ፡ ላእካኑ ፡ እሙንቱ ፡ ከመ ፡ ይትበቀልዎ ፡ ለገባሬ ፡ እኪት ። (መዝ ፡ ፹፰ ፡ ፮ ።)
እመዐኖን ፡ ዓይን ፡ በፍላት ፡ እጅ ፡ ግር ፡ በስለት ፡ ሊሠሩ ፡ ሊቀጡ ፡ ተሹመዋል ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ይኩንንዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለእኪት ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ እንድ ፡ ነው ።

፮ ፡ ወይእዜኒ ፡ በግብር ፡ ተኩነኑ ።
አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ በግድ ፡ ተገዙ ።

ወእከ ፡ ዳእሙ ፡ ለዘእኩይኒ ፡ ምግባሩ ።
መገዛታችሁም ፡ ግብሩ ፡ ክፉ ፡ ለኾነ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ዓዲ ፡ ለዘሠናይኒ ፡ ምግባሩ ። (ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫)።
ግብሩ ፡ በጎ ፡ ለኾነም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ (ሐተታ) ፡ ከዚህ ፡ ዓዲ ፡ ለዘሠናይኒ ፡ ምግባሩ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ፡ እላ ፡ ለእኩያንኒ ፡ አለ ፤ እንደምነው ፡ ቢሉ ፤ ከዚያ ፡ ለበጎዎቹ ፡ ተገዝተው ፡ ለክፉዎቹስ ፡ እንገዛም ፡ ብለዋልና ፡ እላ ፡ ለእኩያንኒ ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ ከክፉዎቹን ፡ ፈርተው ፡ ተገዝተው ፡ ለበጎዎቹስ ፡ እንገዛም ፡ ብለዋልና ፡ ዓዲ ፡ ለዘሠናይኒ ፡ ምግባሩ ፡ አለ ። እንድም ፡ ኹሉም ፡ እንደአባትነታቸው ፡ ይጽፋሉ ።

፯ ፡ ወበእንተዝ ፡ ታገብኡ ፡ ሎሙ ፡ ጸባሕተ ።
ስለዚህ ፡ የጎመት ፡ ግብር ፡ ትገብሩላቸዋላችሁ ።

እስመ ፡ ላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሙንቱ ።
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተሹመዋልና ።

፰ ፡ ወለዝ ፡ ግብር ፡ ተሠይሙ ።

ዓመዐኖን ፡ ዓይን ፡ በፍላት ፡ እጅ ፡ እግር ፡ በስለት ፡ ለመቅጣት ፡ ፈቃደኛን ፡ ለመሾም ፡ ለመሸለም ።
ወሎሱ ፡ በዘይረትዕ ፡ ግበሩ ። ኹሉን ፡ በሚገባ ፡ ሥሩ ።
(እንድም ፡ ወለሎሱ ፡ በዘይረትዕ ፡ ግበሩ) ። ለኹሉ ፡ የሚገባውን ፡ ሥሩ ።
ወለዘኒ ፡ ጸባሕተ ፡ ጸብሑ ።

ለሚገባው ፡ ግብሩን ፡ ስጡ ። እንድም ፡ ወለዘኒ ፡ ጸባሕት ፡ ጸብሑ ፡ ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ስጡ ።
ወለዘኒ ፡ ጸባሕት ፡ ጸባሕተ ፡ ጸብሑ ። ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ግብሩን ፡ ስጡ ።
ወለዘኒ ፡ ዓሥራት ፡ ዐሥሩ ።
ያጨ ፡ ቆሎ ፡ ለሚገባው ፡ ስጡ ።

ወለዘኒ ፡ ዐሥራተ ፡ ዐሥሩ ።

ለሚገባው ፡ ያጨ ፡ ቆሎውን ፡ ስጡ ። ወለዘኒ ፡ ዐሥራት ፡ ዐሥራተ ፡ ዐሥሩ ። ያጨ ፡ ቆሎ ፡ ለሚገባው ፡ ያጨ ፡ ቆሎውን ፡ ስጡ ።

ወለዘኒ ፡ ብነት ፡ በንቱ ። (ማቴ ፡ ፭፪ ፡ ፭፭ ፡ ግር ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ።)

ወለዘኒ ፡ ብነት ፡ እንቍጣጣሽ ፡ ለሚገባው ፡ ስጡ ። ወለዘኒ ፡ ብነት ፡ በንቱ ፡ ለሚገባው ፡ እንቍጣጣሹን ፡ ስጡ ። ወለዘኒ ፡ ብነት ፡ ብነተ ፡ በንቱ ፤ እንቍጣጣሽ ፡ ለሚገባው ፡ እንቍጣጣሹን ፡ ስጡ ።

www.zeyeneta.com

ጅ ፡ ወለዘሂ ፡ ፍርግተ ፡ ፍርሁ ።

መፈራት ፡ የሚገባውንም ፡ ፍሩ ፡ ባልንጀራ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ አፈር ፡ ስንፈጭ ፡ ውኃ ፡ ስንራጭ ፡ አድ ፡ ገናል ፡ ብሉ ፡ መናቅ ፡ አይገባም ፡ መፍራት ፡ ይገባል ።

ወለዘሂ ፡ ከብረ ፡ እክብሩ ።

ክብር ፡ የሚገባውንም ፡ አክብሩ ፡ ተሹሞ ፡ የነበረ ፡ በተሻረ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ሲመጣ ፡ ይታጠቁለት ፡ ይፈቱለት ፡ ሲሔድ ፡ ይሸኙት ፡ ያንበረውን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ አይገባም ፡ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ማክበር ፡ ይገባል ።

ወአልቦ ፡ ዘይበቍዐክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ አፍቅሮ ፡ ቢጽክሙ ።

ይህ ፡ ዅሉ ፡ ኾኖ ፡ ከፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ በቀር ፡ የሚረባችሁ ፡ የሚጠቅማችሁ ፡ የለም ።

ወዘሰ ፡ አፍቀረ ፡ ቢጾ ፡ ዅሉ ፡ ሕገ ፡ ፈጸመ ፡ ገቢረ ፡ (ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።) ወንድሙንም ፡ የወደደ ፡ ሕጉን ፡ ዅሉ ፡ ፈጸመ ።

፱ ፡ አስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ በአሪት ፡ ኢትሑር ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ።

በአሪት ፡ ኢትሑር ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ ብሏልና ፡ ከወደደው ፡ ወደ ፡ ሚስቱ ፡ አደሪድበትም ።

ወኢትቅትል ፡ ነፍሰ ።

ነፍስ ፡ አትግደል ፡ ብሏልና ፡ ከወደደው ፡ አይገድለውም ።

ወኢትስርቅ ።

የሰው ፡ ከብት ፡ አትስረቅ ፡ ብሏልና ፡ ከወደደው ፡ አይሰርቅበትም ።

ወኢትኩን ፡ ሰምዐ ፡ በሐሰት ።

በሐሰት ፡ አትመስክር ፡ ብሏልና ፡ ከወደደው ፡ በሐሰት ፡ አይመስክርበትም ። ወኢትፍቱ ።

የሰው ፡ ከብት ፡ እትመኝ ፡ ብሏልና ፡ ከወደደው ፡ ገንዘቡን ፡ አይመኝበትም ።

ወዓዲ ፡ ባዕድኒ ፡ ቦቱ ፡ ትእዛዝ ።

ነግግለትና ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የታዘዘ ፡ ትእዛዝ ፡ አለ ።

ወርእሱ ፡ ለዅሉ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ። (ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።)

የዅሉ ፡ ግን ፡ ፍጻሜው ፡ የሚሆ ፡ ፍልጥ ፡ ማሰሪያው ፡ ልጥ ፡ እንዲሉ ፤ ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ነው ።

፲ ፡ ዘያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ኢይገብር ፡ እኩየ ።

ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ።

ተሩቅሮስ ፡ ፍጹም ፡ ሕግ ፡ ውኑቱ ። (ማቴ ፡ ፭፪ ፡ ፶፱ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፭ ።)

ፍቅርስ ፡ ፍጹም ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ ወዘኒ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ዘጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ለነቂህ ፡ እምንዋም ፡ (ኤፌ ፡ ፭፩ ፡ ፲፬ ። ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፭፩ ፡ ፮ ፡ ፯ ።)

ከንቶ ፡ ሐኬት ፡ የምንነቃበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ይህን ፡ ታውቃላችሁ ፡

ይእዜሰ ፡ አልጸቀት ፡ ሕይወትነ ፡ እንተ ፡ ተሰፈውናሃ ። (ዕብ ፡ ፮ ፡ ፱ ።)

ዛሬ ፡ ግን ፡ አለችን ፡ ያልናት ፡ ተስፋ ፡ ያደረግናት ፡ ልጅነት ፡ ተሰጠች ።

፲፪ ፡ ወኃለፈት ፡ ሌሊት ፡ ወመጽአት ፡ መዓት ፡ (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፰ ።)

አሪት ፡ ድንቁርና ፡ አልፋ ፡ መንፈል ፡ ፅውቶት ፡ ተሰጠች ።

ወንግድፍ ፡ እምሳዕሌነ ፡ ምግባረ ፡ ጽልመት ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ።)

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ የአሪትን ፡ የድንቍርናን ፡ ሥራ ፡ ትተን ።

ወንልበስ ፡ ወልታ ፡ ብርሃን ።

የፅውቶት ፡ የመንፈልን ፡ ሥራ ፡ እንሥራ ።

ንልበሰ ፡ ካለ ፡ ወልታ ፡ ዘንድ ፡ ግሥ ፡ ነው ።

፲፫ ፡ ከመ ፡ ናንሶሱ ፡ በምግባረ ፡ ጽድቅ ።

በምግባር ፡ በትርፋት ፡ አንናር ፡ ዘንድ ፡ (ሐተታ) ፡ አላባሽ ፡ ጋሻ ፡ የያዘ ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ መዲያ ፡ መዲህ ፡ ሲል ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ በዚያ ፡ ግሥ ፡ ተናግሮታል ።

www.zeyeneta.com

ወአኮ ፡ በተውኔት ፡ ወበግጥሌት ፡
ናንሶሱ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ በዘፈን ፡ በጨዋታ ፡ አይጀለም ።
ወበሕግታይ ።
በመብል ፡ በመጠጥ ፡ አይደለም ።
ወበዝሙት ፡ ወበምርዓት ።
በዝሙት ፡ በድርዓት ፡ አይደለም ።
ወአኮ ፡ በተሐምሞ ፡ ወበቅንዓት ። (ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፴፬ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ።)
በቅንዓት ፡ በምቀኝነት ፡ አይደለም ።

፲፬ ፡ ልበስዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ገላት ፡ ፫ ፡ ፳፯ ።)

ይህንስ ፡ ትታችሁ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ምስሉት ፡ ምስሉት ፡ አንጂ ፡ አኮ ፡ ለተውኔት ፡ ወኢተሐልዩ ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋክሙ ።

ሥጋዊ ፡ ፈቃዳችሁን ፡ አብዝታችሁ ፡ እትሥሩ ፡ (ሐተታ) ፡ እንደባዛ ፡ መሬት ፡ ባዛ ፡ መሬት ፡ ዝናም ፡ የበዛበት ፡ እንደ ኾነ ፡ ዘሩን ፡ ችክ ፡ አድርጎ ፡ ይይዘዋል ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድም ፡ የበዛ ፡ እንደኾነ ፡ ኃጢአቱን ፡ ችክ ፡ አድርጎ ፡ ይይዘዋልና ፡ እንድም ፡ እንደ አርባጫ ፡ መሬት ፡ አርባጫ ፡ መሬት ፡ ዝናም ፡ የበዛበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጎርፉ ፡ ዘሩን ፡ ጠራርጎ ፡ ይዞት ፡ ይሔዳል ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድም ፡ የበዛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ኃጢአት ፡ ጨልጦ ፡ ገርኝቶ ፡ ይዞ ፡ ይሔዳል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ወለዘኒ ፡ ድኩም ፡ የይግኖቱ ፡ ጸርዎ ፡ ወአጽንዕዎ ፡

የሚበላና ፡ የማይበላ ፡ በማየ ፡ አይጎ ፡ ጊዜ ፡ ታውቋል ፡ ኖኅን ፡ ከሚበሉ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ይዘህ ፡ ግባ ብሎታል ፡ አምስቱን ፡ ሰምግብ ፡ ኹሉቱን ፡ ሰዘር ። ከማይበሉ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ይዘህ ፡ ግባ ፡ ብሎታል ።
ከኖኅም ፡ አስቀድሞ ፡ በአዳም ፡ ጊዜ ፡ ታውቋል ። የሚበሉት ፡ አየሔዱ ፡ ብላን ፡ ይሉት ፡ ነበር ።
ከኖኅም ፡ በኋላ ፡ በሙሴ ፡ ጊዜ ፡ ታውቋል ። መልአከ ፡ ገጽ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ብሉ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አትብሉ ፡ እያለ ፡ ይነግረው ፡ ነበር ። (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፪—፵፫ ።) ቤት ፡ ሠርቶ ፡ በጉልላት ፡ ይጨርሱ ፡ እንዲሉ ።
የተጣሉበትን ፡ በመጨረሻ ፡ አመጣው ፡ ይህ ፡ ከኾነ ፡ እስከአሁን ፡ ለምን ፡ ያልተናገረው ፡ ቢሉ ፡ እስከአሁን ፡ ሲናገረው ፡ የመጣ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የሚያመጣው ፡ ምግባር ፡ ነው ፡ ሃይማኖት ፡ ይቅደመኝ ፡ ምግባር ፡ ይከተለኝ ፡ ለማለት ፡ አሚንስ ፡ መሠረት ፡ ይኣቲ ፡ ወካልኣኒሃ ፡ ሕንጻ ፡ ወንድቅ ፡ እሙንቱ ፡ አንዲል ፡ (አፈ ፡ ወርቅ) ።
ሃይማኖት ፡ ደካማ ፡ አይሁዳዊን ፡ (ጸርዎ) ፡ ታገሡት ፡ (ወአጽንዕዎ) ፡ በትዕግሥቱ ፡ አጽኑት ፡ አንድም (ጸርዎ) ፡ መብሉን ፡ ተዉለት ፡ (ወአጽንዕዎ) ፡ በመተዉ ፡ አጽኑት ፡ (እንድም ፡ አጽንዕዎ ፡ ወጸርዎ) ፡ (አጽንእዎ) ፡ አምኖ ፡ ቢበሉት ፡ ምን ፡ ያስጎዳል ፡ በሉት ፡ (ወጸርዎ) ፡ አምቢ ፡ ቢል ፡ ተዉለት ።

ወኢትግበሩ ፡ ለአድልዎ ፡ (ም ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፱ ።)
የምትሠሩትንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ለግብዝነት ፡ አታድርጉ ፡ (ሐተታ) ፡ ወዲህ ፡ ሰውነታችን ፡ ይጠቅመን ፡ ወዲህ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ይጸናልን ፡ ብላችሁ ።

፪ ፡ ዘሰ ፡ የአምን ፡ ከመ ፡ ዙሉ ፡ ብውሕ ፡ ዙሎ ፡ ሊይብላዕ ፡ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ።)
ኹሉን ፡ መብላት ፡ አንዲገባ ፡ የሚያምነስ ፡ ኹሉን ፡ ይብላ ፡ አንድም ፡ አማኒስ ፡ ኹሉንም ፡ መብላት ፡ እንደሚገባው ፡ መጠን ፡ ኹሉን ፡ ይብላ ።
ወዘሰ ፡ ይናፍቅ ፡ ሐምለ ፡ ለይሴስይ ።
የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እህል ፡ ይብላ ፡ ብላዕ ፡ ግዕረ ፡ ገዳም ፡ እንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፴ ።)

፫ ፡ ወዘኒ ፡ ይብልዕ ፡ ኢይመንኖ ፡ ለዘኢይበልዕ ።
የሚበላ ፡ አረማዊ ፡ የማይበላ ፡ አይሁዳዊን ፡ እይንቀፈው ፡ ይህ ፡ ግብዝ ፡ ብሎ ።

ወዘኒ ፡ አይበልዕ ፡ ኢይግዕዞ ፡ ለዘይበልዕ ፡ (ቆላስ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።)

የማይበላ ፡ አይሁዳዊም ፡ ይሚበላ ፡ አረማዊን ፡ አይንቀፈው ፡ ይህ ፡ ኹሉን ፡ ባረ ፡ ብሎ ።

እስመ ፡ ለዙሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አእመሮሙ ።
የኹሉንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቅላቸዋልና ፡ አረማዊ ፡ ዙሉ ፡ ዘቦአ ፡ ውስተ ፡ አፍ ፡ አያረክሰ

www.zeyeneta.com

ለሰብአ ፣ ያለውን ፣ ይዘ ፣ አንደሆነ ፣ (ግቴ ፣ ፲፭ ፣ ፲፯ ።) አይሁዳዊም ፣ ኢቅብልኡ ፣ ዘክልኡ ፣ ጥረቢው ፣ መዘጽፋት ፣ ለኩናሁ ፣ ያለውን ፣ ይዘ ፣ አንደጅኑ ፣ (ዘሴሞ ፣ ፲፭ ፣ ፰-፲፫ ።)
አአመሮሙ ፣ ባለው ፣ አአመናሙ ፣ ይላል ፣ ኹሉንም ፣ አግዚአብሔር ፣ በሃይማኖት ፣ አንድ ፣ አድርጎ ቸዋልና ።

፪ ፣ ምንትኑ ፣ አንተ ፣ ዘትግዕዝ ፣ ነባሬ ፣ ባዕድ ፤ አንዘ ፣ ለአግዚኡ ፣ ይቀውም ፣ (ግቴ ፣ ፯ ፣ ፩ ፣ ያዕ ፣ ፬ ፣ ፲፫ ፣ ፲፪ ።)
አንዲሀ ፣ ከኾነ ፣ በልቶ ፣ ጠጥቶ ፣ ጌታውን ፣ ሲያገለግል ፣ የጌታን ፣ ቤተ ፣ ሰብእ ፣ ያምትነቅፍ ፣ አንተ ምንድነህ ፣ መንግሥት ፣ ተበላሻውን ፣ ነህ ፤ ወረኛን ፣ ተነሥተኃል ፤ ምስለኔን ፣ ነህ ፣ (ሐተታ) ፣ ባዕድ ፣ አለው ፣ ፈጣሪ ፣ ከፍጡር ፣ በማብርም ፣ በአነዋርም ፣ ልዩ ፣ ነውና ።

እመኒ ፣ ወድቀ ፣ ለአግዚኡ ፣ ይቀውም ።
በመብል ፣ ምክንያት ፣ ቢሰነካከል ፤ የተሰነካከለ ፣ ቢመስልህ ፣ በልቶ ፣ ጠጥቶ ፣ ጌታውን ፣ ለማገልገል ፣ ይጸናል ።

ይክል ፣ እግዚአ ብሔር ፣ አቅሞቶ ።
እግዚአብሔር ፣ በልቶ ፣ ጠጥቶ ፣ እንዲያገለግለው ፣ ማድረግ ፣ ይቻለዋል ።

አንድም ፣ እመኒ ፣ ወድቀ ፣ ለአግዚኡ ፣ ይቀውም ።
በጋጠአት ፣ ምክንያት ፣ ቢሰነካከል ፣ የተሰነካከለ ፣ ቢመስልህ ፣ በንስሓ ፣ ተመልሶ ፣ ጌታውን ፣ ለማገልገል ፣ ይጸናል ።

ይክል ፣ እግዚአብሔር ፣ አቅሞቶ ።
እግዚአብሔር ፣ በንስሓ ፣ መልሶ ፣ እንዲያገለግለው ፣ ማድረግ ፣ ይቻለዋል ።

አንድም ፣ እመኒ ፣ ወድቀ ፣ ለአግዚኡ ፣ ይቀውም ።
በሞት ፣ ምክንያት ፣ ቢሰነካከል ፣ የተሰነካከለ ፣ ቢመስልህ ፣ በትንሣኤ ፣ ተነሥቶ ፣ ጌታውን ፣ ለማገልገል ፣ ይጸናል ።

ይክል ፣ እግዚአብሔር ፣ አቅሞቶ ።
እግዚአብሔር ፣ አሰነሥቶ ፣ እንዲያገለግለው ፣ ማድረግ ፣ ይቻለዋል ።

፭ ፣ አሰመቦ ፣ ዘይትሔረም ፣ አምዕለት ፣ ዕለተ ።
አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ የሚከለከል ፣ ባሕታዊ ፣ አለና ፣ ዘኒ ኢይበልዕ ፣ አይግብ ፣ ለዘይበልዕ ወቦ ፣ ዘይትሔረም ፣ በዙሉ ፣ መዋዕል ፣ (ገላት ፣ ፬ ፣ ፲ ።)
አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ ሰድስት ፣ ቀን ፣ የሚከለከል ፣ ባሕታዊ ፣ አለና ፣ ዘኒ ፣ ይበልዕ ፣ አይመንኖ ፣ ለዘ አይበልዕ ።
(ሐተታ) ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ በሚከለከል ፣ ባሕታዊ ፣ አረማዊን ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ ሰድስት ፣ ቀን ፣ በሚከለከል ፣ ባሕታዊ ፣ አይሁዳዊን ፣ መስሎ ፣ ይናገራል ።

ወባሕቱ ፣ ለዙሉ ፣ በከመ ፣ አዘዘ ፣ ልቡ ።
ነገር ፣ ግን ፣ ኹሉም ፣ ልቡ ፣ እንደወደደ ፣ እንደወደደው ፣ ያድርግ ።

፮ ፣ ዘሂ ፣ ተሐረመ ፣ በበዕለቱ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ተሐረመ ።
አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ የተከለከለ ፣ ባሕታዊ ፣ እግዚአብሔር ን ፣ ለማገልገል ፣ ተከልክሏል ።

ወዘሂ ፣ ተሐረመ ፣ በዙሉ ፣ መዋዕል ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ተሐረመ ።
አንድ ፣ ቀን ፣ በልቶ ፣ ሰድስት ፣ ቀን ፣ የተከለከለ ፣ ባሕታዊ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ለማገልገል ፣ ተከልክሏል ።

ወዘሂ ፣ በላዐ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ በልዐ ።
እንደዚህም ፣ የበላ ፣ አረማዊ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ለማገልገል ። በልቷል ።

ወየአኵቶ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ (ዘዳግ ፣ ፰ ፣ ፲ ፣ ፩ ፣ ቆሮ ፣ ፲ ፣ ፴፩ ።)
በልቶ ፣ ጠጥቶ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ያመሰግነዋል ፣ ይህን ፣ የሰመሸኝን ፣ አያለ ።

ወዘኒ ፣ ኢበልዐ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ኢበልዐ ።
የተከለከለም ፣ አይሁዳዊ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ለማገልገል ፣ ተከልክሏል ።

ወየአኵቶ ፣ ለእግዚአብሔር
እግዚአብሔርን ፣ ያመሰግነዋል ፣ ከአረማዊ ፣ የምለይበትን ፣ ሕግ ፣ የሠራህልኝ ፣ ብሎ ።

፯ ፣ ወአልቦ ፣ እምውሰቴትነ ፣ ዘለርእሱ ፣ የሐዩ ።
ከኛ ፣ ወገን ፣ ራሱን ፣ ለማገልገል ፣ ከመብል ፣ የሚከለከል ፣ የለም ።

www.zeyeneta.com

ወዘለርእሱ ፡ ይመውት ።
በመብልም ፡ የሚኖር ፡ የለም ።

፳ ፡ ወእመኒ ፡ ሐየውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሐዩ ። ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንመውት ፡ እመኒ ፡ ሐየውን ፡ ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንሕነ ።

እመኒ ፡ ሐየውንና ፡ እመኒ ፡ ነሐዩ ፡ እመኒ ፡ ሞትንና ፡ እመኒ ፡ ንመውት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ብንከለከልም እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ በመብልም ፡ ብንኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።
(አንድም ፡ መልስ) ።

ወአልቦ ፡ እምውስቴትን ፡ ዘለርእሱ ፡ የሐዩ ።
ከኛ ፡ ወገን ፡ ራሱን ፡ ለማገልገል ፡ ከመብል ፡ የሚከለከል ፡ የለም ።

ወዘለርእሱ ፡ ይመውት ።
በመከልከሉም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ ሐየውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሐዩ ።
ብንከለከልም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንመውት ።
በመከልከሉም ፡ ጸንተን ፡ ብንኖር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።
(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወአልቦ ፡ እምውስቴትን ፡ ዘለርእሱ ፡ የሐዩ ።
ከኛ ፡ ወገን ፡ ራሱን ፡ ለማገልገል ፡ ከኃጢአት ፡ የሚከለከል ፡ የለም ።

ወዘለርእሱ ፡ ይመውት ።
በመከልከሉም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ ሐየውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሐዩ ።
ከኃጢአት ፡ ብንከለከል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሞትን ።
በመከልከሉም ፡ ጸንተን ፡ ብንኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።
(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወአልቦ ፡ እምውስቴትን ፡ ዘለርእሱ ፡ ይመውት ።
ከኛ ፡ ወገን ፡ እራሱን ፡ ለማገልገል ፡ በሰማዕትነት ፡ የሚሞት ፡ የለም ።

ወዘለርእሱ ፡ የሐዩ ።
በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ የሚኖር ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለ እግዚአብሔር ፡ ንመውት ።
በሰማዕትነትም ፡ ብንሞት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ሐየውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሐዩ ።
በሕይወት ፡ ሥጋም ፡ ብንኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።
(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወአልቦ ፡ እምውስቴትን ፡ ዘለርእሱ ፡ ይመውት ።
ከኛ ፡ ወገን ፡ ራሱን ፡ ለማገልገል ፡ በሰማዕትነት ፡ የሚሞት ፡ የለም ።

ወዘለርእሱ ፡ የሐዩ ።
የሚኖሣም ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ ሞትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንመውት ።
በሰማዕትነትም ፡ ብንሞት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ሐየውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሐዮነ ።
ብንኖሣም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

፱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወሐይወ ፡ ከመ ፡ ይኩንን ፡ ሕያዋን ፡ ወምውታን ፡
(ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፵፪ ፦)
ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕያዋንን ፡ ሙታንን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ሞቶ ፡ ተነሣ ። እንድም ፡ በሕያዋን ፡ በሙታን ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሞቶ ፡ ተነሣ ።

፲ ፡ ምንትኑ ፡ እንተ ፡ አንከ ፡ ዘትሜዕዝ ፡ ቢጸከ ።
እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ወንድምህ ፡ አረማዊን ፡ ስዎን ፡ በላ ፡ ብለህ ፡ የምትነቅፈው ፡ አንተ ፡ ምንድነህ ፡ ወንግሥት ፡ ተበላላጭን ፡ ነህ ፤ ዎ ስለኔን ፡ ነህ ፤ ወረኛን ፡ ተነሥተሃል ።

www.zoyeneta.com

ወምንትኑ ፡ አንተ ፡ ዘትሜንን ፡ ቢጸከ ።
አንተስ ፡ መብሉን ፡ አልተውሰት ፡ ብለህ ፡ ወንድምህን ፡ አይሁዳዊን ፡ የምትነቅፈው ፡ አንተ ፡ ምን ድነህ ።
አንዘ ፡ ህለወን ፡ ዙልን ፡ ንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ምኩናኑ ፡ ለክርስቶስ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፭ ፡ ፴፩ ፡ ግቴ ፡ ፳፩ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ።)
ዙላችንም ፡ ክርስቶስ ፡ በሚፈርድበት ፡ ዐደባባይ ፡ እንቆም ፡ ዘንድ ፡ ሳለን ።
፲፩ ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ አነ ።
እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡ ብሏልና ።
እስመ ፡ ሊተ ፡ ይሰግድ ፡ ዙሉ ፡ ብርክ ። (ኢሳ ፡ ፵፭ ፡ ፳፫ ፡ ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡)
ብርክ ፡ መላእክት ፡ ብርክ ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ፡ ለኔ ፡ ይሰግዳል ።
ወሊቶኒ ፡ ይገኒ ፡ ዙሉ ፡ ልሳን ።
አንደበት ፡ ዙሉ ፡ በኔ ፡ ያምናል ፡ ለኔ ፡ ይገዛል ፡ ብሏልና ።
፲፪ ፡ ናሁ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ ህለወን ፡ ዙልን ፡ ንትሐተት ፡ ዘንበ ፡ እግዚአብሔር ። (ገላ ፡ ፮ ፡ ፭ ።)
እነሆ ፡ ዙላችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አንመረመር ፡ ዘንድ ፡ እንዳለን ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ።
ወኢንግአዝ ፡ አንከ ፡ ቢጸን ።
አንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ወንድማችን ፡ አረማዊን ፡ ለምን ፡ በላ ፡ ብለን ፡ አንንቀፍ ።
ወዘንተ ፡ ዳዕሙ ፡ ነሐሲ ፡ በዘኢንግአዝ ፡ ቢጸነ ። (ግቴ ፡ ፲፭ ፡ ፮ ።)
ወንድማችን ፡ አረማዊን ፡ በማንነቅፍ ፡ ገንዘብ ፡ የማንነቅፍበትን ፡ ሥራ ፡ እንሥራ ፡ አንጂ ።
፲፫ ፡ ወአአምር ።
ኢትብልው ፡ ዘከልኤ ፡ ጥረሲሁ ፡ ወዘጽፋቅ ፡ ለኩናሁ ፡ ያለውን ፡ እንጂ ፡ ባታውቅ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ አአምር ፡ አውቃለሁ ።
ወእትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ እልቦ ፡ ዘይማስን ፡ በእንቲአሁ ።
ነገር ፡ ግን ፡ አምኖ ፡ ቢበሉት ፡ እንዳያስነዳ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምናለሁ ።
ለሙሱን ፡ ዳዕሙ ፡ ዙሉ ፡ ይማስን ። (ግቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፭ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።)
ለሙሱን ፡ ልብ ፡ ላንት ፡ ዙሉ ፡ የሚያስነዳ ፡ ይመስልሃል ፡ እንጂ ።
፲፮ ፡ ወእመሰ ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ፡ ተሐይሶ ፡ ለቢጽከ ፡ አልብከኬ ፡ ተፋቅሮ ።
በመብል ፡ ምክንያት ፡ ለምን ፡ በላ ፡ ብለህ ፡ ወንድምህ ፡ አረማዊን ፡ የምትነቅፈው ፡ ከኾነ ፡ ፍቅር፡ የለህም ፡ የለህማ ።
፱ኑ ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ፡ ይትሃከል ፡ ዝኩ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ።
(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፩-፲፫ ።)
ክርስቶስ ፡ ስለርሱ ፡ የሞተለት ፡ ወንድማችን ፡ አረማዊ ፡ አንተ ፡ ለምን ፡ በላ ፡ ብለህ ፡ ብትነቅፈው ፡ ይሳሻልን ፡ እይነዳም ።
፲፯ ፡ ኢትዕርፉ ፡ እንከ ፡ ላዕለ ፡ ሠናይ ፡ ዘጸገወነ ፡ እግዚእነ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
አንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ጌታችን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ አትበሉ ።
(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወኢንግዐዝ ፡ እንከ ፡ ቢጸነ ።
መብሉን ፡ አንተው ፡ ብለን ፡ ወንድማችን ፡ አይሁዳዊን ፡ አንንቀፍ ።
ወዘንተ ፡ ዳዕሙ ፡ ነሐሲ ፡ በዘኢንግዕዝ ፡ ቢጸነ ።
ወንድማችንን ፡ በማንነቅፍ ፡ ገንዘብ ፡ የማንነቅፍበትን ፡ ሥራ ፡ እንሥራ ፡ እንጂ ።
ወአአምር ።
ዙሉ ፡ ዘቦአ ፡ ውስተ ፡ አፍ ፡ ኢያረኩሶ ፡ ለሰብእ ፡ ያለውን ፡ እንጂ ፡ ባታውቅ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ አአምር ፡ አውቃለሁ ።
ወእትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይማስን ፡ በእንቲአሁ ።
እንዳንተም ፡ አምኖ ፡ ቢበሉት ፡ እንዳያስነዳ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምናለሁ ።
ለሙሱን ፡ ዳዕሙ ፡ ዙሉ ፡ ይማስን ።
ስዚያ ፡ ለሙሱን ፡ ልብ ፡ አይሁዳዊ ፡ ዙሉ ፡ የሚያስነዳ ፡ ይመስለዋል ። እንጂ ።
ወእመሰ ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ፡ ተሐይሶ ፡ ለቢጽከ ።
መብሉን ፡ አልተው ፡ ብለህ ፡ ወንድምህ ፡ አይሁዳዊን ፡ የምትነቅፈው ፡ ከኾንክ ።
አልብከኬ ፡ ተፋቅሮ ።
ፍቅር ፡ የለህም ፡ የለህማ ።

www.zeyeneta.com

ቦኑ ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ፡ ይትጋደል ፡ ዝኩ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ።
ክርስቶስ ፡ ስለሱ ፡ የሞተለት ፡ ወንድማችን ፡ አይሁዳዊ ፡ መብሉን ፡ አልተውለት ፡ ብለህ ፡ ይነዳ ፡ እሬ ተውለት ።

ኢትፅርፉ ፡ እንከ ፡ ላዕለ ፡ ሠናይ ፡ ዘጸገወነ ፡ እግዚእነ ። (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
ደቂቅየ ፡ ተሩቀሩ ፡ ብሎ ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ አታፍርስ ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መብልዐ ፡ ወመስቴ ።
መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ አትሰብክምና ።

ዘእንበሰ ፡ ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ወፍሥሓ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። (ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍቅርን ፡ ተስፋን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

(አንድም ፡ መልስ ፡) እስመ ፡ ኢኮነ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መብልዐ ፡ ወመስቴ ።
መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፤ ወንጌል ፡ መብልን ፡ መጠጥን ፡ ለያዘ ፡ ሰውነት ፡ አትነገርምና ።

ዘእንበሰ ፡ ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ወፍሥሓ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። (ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍቅርን ፡ ተስፋን ፡ ለያዘ ፡ ሰውነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

(አንድም ፡ መልስ) ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መብልዐ ፡ ወመስቴ ።
መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ መብል ፡ መጠጥን ፡ ለያዘ ፡ ሰውነት ፡ አትወረስምና ።

ዘእንበለ ፡ ጽድቅ ፡ ወሰላም ፡ ወፍሥሓ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። (ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኾን ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍቅርን ፡ ተስፋን ፡ ለያዘ ፡ ሰውነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፰ ፡ ወዘሰ ፡ ከመዝ ፡ ይትቀነይ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሥሙር ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኅሩይ ፡ በኀበ ፡ ሰብእ (፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።)
እንዲህ ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍቅርን ፡ ተስፋን ፡ በያዘ ፡ ሰውነት ፡ ኾኖ ፡ ለክርስቶስ ፡ የሚገዛ ፡ በሰውም ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነው ።

ወይእዜኒ ፡ ንትልዋ ፡ ለሰላም ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ቢጸን ፡ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ።)
እንዲሁም ፡ ከኾነ ፡ ወንድማችን ፡ አረማዊ ፡ ሕንጻ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚኾን ፡ ገንዘብ ፡ ፍቅርን ፡ አጽንተን ፡ እንያዝ ።

ወኢንሥዐር ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ።
ለምን ፡ በላ ፡ ብለን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ አንበል ።

ወባሕቱ ፡ ዅሉ ፡ ንጹሕ ፡ ለንጹሕ ።
ለንጹሕ ፡ እንጂ ፡ ዅሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

ወአኩይስ ፡ ለሰብአ ፡ በኑፋቄ ፡ በሊዕ ። (ቊ ፡ ፲፬ ።)
ሰውንስ ፡ የሚጎዳው ፡ እየተጠራጠሩ ፡ መብላት ፡ ነው ።

(አንድም ፡ መልስ) ፡ ወይእዜኒ ፡ ንትልዋ ፡ ለሰላም ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ቢጸን ።
ወንድማችን ፡ አይሁዳዊ ፡ ሕንጻ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚኾን ፡ ገንዘብ ፡ ፍቅርን ፡ አጽንተን ፡ እንያዝ ።

ወኢንሥዐር ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንበይነ ፡ መብልዕ ።
መብሉን ፡ እንተው ፡ ብለን ፡ ደቂቅየ ፡ ተሩቀሩ ፡ ብሎ ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ አናፍርስ ።

ወባሕቱ ፡ ዅሉ ፡ ንጹሕ ፡ ለንጹሕ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ለንጹሕ ፡ ዅሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

ወአኩይስ ፡ ለሰብእ ፡ በኑፋቄ ፡ በሊዕ ።
ሰውንስ ፡ የሚጎዳው ፡ እየተጠራጠሩ ፡ መብላት ፡ ነው ።

፳፩ ፡ ይኄይስ ፡ ኢበሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወኢሰትየ ፡ ወይን ፡ እምአዕቅፎ ፡ ቢጽ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ።)
እንዲሁም ፡ ከኾነ ፡ ሥጋ ፡ አለመብላት ፡ ወይን ፡ አለመጠጣት ፡ (ወኢያዕቅፎ ፡ ቢጽ) ፡ ወንድምንም ፡ አለመንቀፍ ፡ በጎ ፡ ሕግ ፡ ነው ።
(አንድም ፡) ወንድምን ፡ ከመንቀፍ ፡ ሥጋ ፡ አለመብላት ፡ ወይን ፡ አለመጠጣት ፡ ይሻላል ።

፳፪ ፡ ወአመኒ ፡ ሃሌ ፡ ሃይማኖቅ ፡ አጽንዕ ፡ ርእሰከ ፡ በቲአምኖትከ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
አማኒስ ፡ ክኾንህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ በሃይማኖትህ ፡ ጽና ።

www.zeyeneta.com

ወብፁዕ ፡ ዘይዘልፍ ፡ ርእሶ ፡ በዘረክበ ፡ እንዎሮተ ። (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።)
በተሰጠው ፡ እንዎሮ ፡ ራሱን ፡ የሚዘልፍ ፡ ሰው ፡ ንውድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።
(እንድም ፡) እንዎሮን ፤ ባገኘ ፡ ግንዘቤ ፡ ራሱን ፡ የሚዘልፍ ፡ ሰው ፡ ንውድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

ፀፀ ፡ ወዘሰ ፡ ይናፍቅ ፡ እመ ፡ በልዐ ፡ ይትኬነን ።
የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ ቢበላ ፡ ይጎዳል ።

እሰመ ፡ ኢኮነ ፡ በእሚን ።
መብላቱ ፡ በሃይማኖት ፡ አይደለምና ።

ወኵሉ ፡ ዘይከውን ፡ ዘእንበለ ፡ አሚን ፡ ኃጢአት ፡ ወጌጋይ ፡ ውእቱ ። (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፮ ።)
ያለሃይማኖት ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ዕዳ ፡ ነው ፡ ይጐዳል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ክፍል ፡ ፩፩ ።

ወርቱዕሰ ፡ እንትሙ ፡ ጽኑዓን ፡ ትጼርዎሙ ፡ ድካሞሙ ፡ ለሰውናን ። (ም ፡ ፲፬ ፡ ፩ ።)
እገባብስ ፡ እናንት ፡ ሃይማኖተ ፡ ጽኑዓን ፡ አሕዛብ ፡ ሃይማኖተ ፡ ድኩማን ፡ አይሁድን ፡ ልትታገሷቸው ፡ ይገባል ።

(ሐተታ ፡)እንደ ፡ በጎ ፡ ሽማግሌ ፡ ተናገረ ፡ በጎ ፡ ሽማግሌ ፡ እንተም ፡ ተው ፡ አንተም ፡ ተው ፡ ሲል ፡ መጥቶ ፡ ይልቁንም ፡ እገሌ ፡ ተው ፡ እንዲል ።

ወኢናድሉ ፡ ለርእስነ ።
ለራሳችን ፡ አናብልዋ ።

፪ ፡ ወኵልነ ፡ ናድሉ ፡ ለጽድቅ ፡ ወለግብር ፡ ሠናይ ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ቢጽነ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ፡ ፳፬፡፴፪)
ወንድማችን ፡ አይሁዳዊ ፡ ሕንጻ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚኾን ፡ ግንዘብ ፡ ለሃይማኖት ፡ ለፍቅር ፡ አናድላ ፡ እንጂ ።

፫ ፡ ከርስቶስኒ ፡ እኮ ፡ ለርእሱ ፡ ዘአድለወ ።
ክርስቶስም ፡ እንጂ ፡ ከርሰቶስም ፡ እኮን ፡ ራሱን ፡ ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡ አልወደደም ።
ጸዕሙ ፡ በክመ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ትዕይርቶሙ ፡ ለእሰ ፡ ይትዔየሩከ ፡ ወድቀ ፡ ላዕሌየ ፡ (መዝ ፡ ፷፱ ፡ ፲ ።)
እንተን ፡ የተገዳደሩህ ፡ ተግዳሮት ፡ በኔ ፡ ደረሰ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ ሰሰው ፡ የሚገባውን ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ እንጂ ፡ እኮ ፡ ለርእሱ ፡ ዘአድለወ ።

እንድም ፡ እንተን ፡ የተገዳደሩህ ፡ ተግዳሮት ፡ በኔ ፡ ደረሰ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ አብን ፡ የተገዳደሩትን ፡ የአይሁድን ፡ ተግዳሮት ፡ ተቀበለ ፡ እንጂ ። (ሐተታ) ፡ ምን ፡ ብለው ፡ ተገዳደረውታል ፡ ቢሉ ልብን ፡ በኩፊብ ፡ ዕጕልተ ፡ ላሕም ፡ አቁመው ፡ ተገዳደረውታል ። (ዘፀአ ፡ ፴፪ ፡ ፩-፲፭ ።)

እሱንም ፡ እምሰማይ ፡ ወረድኩ ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ቢሉኞው ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፴፰ ።)በእር ፡ ይብለን ፡ እምሰማይ ፡ ወረድኩ ፡ ዘሰሊን ፡ ነእምር ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ አኮኑ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ ብለው ፡ ተገዳደረውታልና ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፵፪ ።)

አንድም ፡ አብን ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርዶ ፡ ውኃ ፡ ከደንጊያ ፡ አፍልቆ ፡ ቢመግባቸው ፡ ከዚህ ፡ ሰማዩ ፡ ዝቅ ፡ ምድሩ ፡ ብቅ ፡ ካለበት ፡ ቢሆን ፡ ውርጩን ፡ እያረጋ ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርጂ ፡ ውኃ ፡ ከደንጊያ ፡ አፍልቂ ፡ መገብኋችሁ ፡ ይለናል ፡ እንጂ ፡(ይከልኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠሪዓ ፡ ማዕድ ፡ በገዳም) ፡ በረሀማ ፡ አውርዶ ፡ መመገብ ፡ ይቻለዋልን ፡ ብለው ፡ ተገዳደረውታል ። (ዘፀአ ፡ ፲፮ ፡ ፪-፬ ። መዝ ፡ ፴፰ ፡ ፲፱ ።)
እሱንም ፡ እሁበከሙ ፡ ትብልዑ ፡ ሥጋየ ፡ ቢሉኞው ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፩)
በእር ፡ ይከል ፡ የሀበነ ፡ ሥጋሁ ፡ ንብላዕ ፡ ብለው ፡ ተገዳደረውታልና ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፪ ።)

ወኵሉ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለተግሣጸ ፡ ዚአነ ፡ ተጽሕፈ ።
ይህንማ ፡ ጽርዓውያን ፡ በመጡባቸው ፡ ጊዜ ፡ መታብያን ፡ እንዲጸልዩት ፡ ተግልጾለት ፡ ዳዊት ፡ ተናግሮት የሰም ፡ እንዲሉት ፡ እውቆ ፡ አመጣ ፡ እንዲሉትም ፡ አውቆ ፡ ማምጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ።
ጌታ ፡ ብፁዓን ፡ ብውዓን ፡ እያለ ፡ ቢያስተምራቸው ፡ አሪት ፡ ነቢያትን ፡ ሊያሳልፋቸው ፡ መጥቷል፡

www.zeyeneta.com

እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ ኢመጻእኩ ፡ እሥዐሮሙ ፡ እንዳለ ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።)
ከዚያም ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እስመ ፡ ኢተነድጋ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ለነፍስየ ፡ እያለ ፤ ቢያስተምራቸው ፡ ይሆንማ ፡ ዳዊት ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮት ፡ የለም ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ አብብእ፡ ታብሑኒሁ ፡ እንግርከሙ፡ ዘእንተ ፡ ዳዊት ፡ ርእስ ፡ እበው ፡ ከመኒ ፡ ሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወመቃብሪሁኒ ፡ ሀሎ ፡ ኀቤነ ፡ እንዳለ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፳፱-፴ ።)

ከዚያም ፡ ትውልደ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ቢላቸው ፡ አብርሃምን ፡ ያህል ፡ አባት ፡ እያለን ፡ ትውልደ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ይሰናል ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ እብለከሙ ፡ ከመ ፡ ይክል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንሥአ ፡ ውሉደ ፡ እምእላንቱ ፡ አእባን ፡ ለአብርሃም ፡ እንዳለ ፡ (ማቴ ፡ ፫ ፡ ፭-፮ ።)
የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ለኛ ፡ ምክር ፡ እዝናት ፡ ሊኾን ፡ ተጽፏል ።

ከመ ፡ በትዕግሥትነ ፡ ወበተወክሎ ፡ መጻሕፍት ፡ ንርክብ ፡ ተስፋነ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ።)
መከራውን ፡ በመታገሣችን ፤ መጻሕፍትም ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ በማመናችን ፡ ተስፋችንን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ።

፩ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወአቡሃ ፡ ለምሕረት ፡ የሀበነ ፡ ነሐሲ ፡ ዘዚአሁ ፡ በሱልን ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ፊልጵ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።)
የተስፋ ፡ ባለቤት ፡ የምሕረት ፡ መገኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ (የሀበነ ፡ ነሐሲ ፡ ዘዚአሁ ፡)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብነትነት ፡ ኹላችንም ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ማስቡን ፡ ይስጠን ። (ሐተታ፡) ልጅ ፡ ካባቱ ፡ እንዲገኝ ፡ ምሕረትም ፡ ከርሱ ፡ ትገኛለችና ፡ አቡሃ ፡ ለምሕረት ፡ አለ ።

፪ ፡ ከመ ፡ ዙልን ፡ በአሐዱ ፡ አፍ ፡ ንስብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ።
ኹላችንም ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መከረ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኾነን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሐርነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግነው ፡ ዘንድ ።
ወይእዜኒ ፡ ተመከሩ ፡ ቢጸክሙ ።
አሁንም ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ ተቀበሉ ።

፯ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመክፈክሙ ፡ ውስተ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።
ክርስቶስ ፡ ዘኪያክሙ ፡ ተመክፈ ፡ ኪያየ ፡ ተመክፈ ፡ ወዘኪያየ ፡ ተመክፈ ፡ ተመክፎ ፡ ለዘፈነወኒ ፡ ባለው፡ ተመክፎ ። ባባቱ ፡ ጌትነት ፡ እንደተቀበላችሁ ፡ እናንተም ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ ተቀበሉ ።

፰ ፡ እብል ፡ እንከ ፡ ክርስቶስ ፡ ላእከ ፡ ኮነ ፡ ለግዝረት ። (ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፳፬ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፳፫ ።)
ወይእዜኒ ፡ ተመክፉ ፡ ቢጸክሙ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመክፈክሙ ፡ ውስተ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ክርስቶስ ፡ ለግዝረተ ፡ ሥጋ ፡ ምክንያት ፡ ኾነ ፡ አላለው ።
ለጽድቀ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘኢተገዝረ ፡ ከተማ ፡ ነፍስቱ ፡ አመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ ለትሠሮ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ለማስረዳት ። (ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ።)
ወክሙ ፡ ያጽንዓ ፡ ለተስፋ ፡ አበዊነ ።
ከቤታ ፡ ግዙራንም ፡ እመለዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያናገረውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ።

፱ ፡ ወአሕዛብሰ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
አሕዛብ ፡ ግን ፡ ሳይገዘሩ ፡ ያምኑበታል ።

እስመ ፡ ተግሃልሙ ።
በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ይቅር ፡ ብሏቸዋልና ።

(አንድም ፡ መልስ) ።

እብል ፤ እንከ ፡ ክርስቶስ ፡ ላእከ ፡ ኮነ ፡ ለግዝረት ።
ምንትኑ ፡ ረባሕ ፡ ለተይዞዶ ፡ ወምንትኑ ፡ ሥላጤሃ ፡ ለግዝረት ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ መምህሩ ፡ ግዙር ፡ እሱ ፡ ግዙር ፡ ግዝረትን ፡ ይነቅፋልሳ ፡ እንዳይሉት ፡ (አብልኦ ፡) ፡ ክርስቶስ ፡ ግዘረተ ፡ ሥጋውን ፡ ቁም፡ ነገር ፡ ብሎት ፡ ተገዘረ ፡ እላለሁን ።

ለጽድቀ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
(አሳ ፡ ለጽድቀ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።)

ዘኢተገዝረ ፡ ከተማ ፡ ነፍስቱ ፡ አመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ፡ እንጂ።
ወክሙ ፡ ያጽንዓ ፡ ለተስፋ ፡ አበዊነ ።

www.zeyeneta.com

ከቤተ ፡ ግዙራን ፡ እመለዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያናገረውንም ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መአሕዛብስ ፡ ይሴብሕም ፡ ለእግዚአብሔር ።
አሕዛብም ፡ ሳይገዙሩ ፡ ያምኑበታል ።

እስመ ፡ ተሣሃሎሙ ።
በሃይማኖት ፡ ብፅ ፡ ይቅር ፡ ብሏቸዋልና ።

(አንድም ፤ መልስ) ፡ አብል ፡ እንከ ፡ ከርስቶስ ፡ ላእከ ፡ ኮነ ፡ ለግዝረት ።

ከርስቶስ ፡ እንከ ፡ ግእከላየ ፡ ኮነ ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ። (ቁርሉ) ፡ ከርስቶስ ፡ ለግዝረት ፡ ሥጋ ፡ ለግዝረት ፡ ነፍስ ፡ ምክንያት ፡ ኾነ ፡ ፡ አላለሁ ።

ለጽድቀ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
በዘርዕከ ፡ ይትባረኩ ፡ ሁሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ያናገረውን ፡ ተስፋ ፡ ለማበረዳት ፡ ለግዝረት ፡ ነፍስ ፡ ላለው ፡፡

ወከመ ፡ ያጽንዓ ፡ ለተስፋ ፡ አበዊነ ።
ከቤተ ፡ ግዙራንም ፡ እመለዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያናገረውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ ለግዝረት ፡ ሥጋ ፡ ምክንያት ፡ ኾነ ፡ አላለሁ ። ግዝረት ፡ ሥጋ ፡ ላለው ።

መአሕዛብሰ ፡ ይሴብሕም ፡ ለእግዚአብሔር ።
እንኪያስ ፡ ሕዝብም ፡ አሕዛብም ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ያምኑበታል ።

እስመ ፡ ተሣሃሎሙ ።
በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ኹሉንም ፡ ይቅር ፡ ብሏቸዋልና ።

እስመ ፡ ከማሁ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ በእንተዝ ፡ አገኒ ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ።
በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አገዛልሃለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለስምከ ፡ (ም ። ፲፩ ፡ ፴ ፤ መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፶፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፱ ።)
ለስምህም ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፲ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ተፈሥሑ ፡ አሕዛብ ፡ ምስለ ፡ ሕዝቡ ። (ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፵፫ ።)
ዳግመኛም ፡ አሕዛብ ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

፲፩ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ ።
አሕዛብ ፡ ኹላችሁም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

ወይሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ። (መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፩ ።)
ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑታል ። ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ ተሣሃሎሙ ፡ (ሐተታ) ፡ ባስል ዮሰ ፡ በሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ወርቅ ፡ አድርጎ ፡ ወስዶታል ።
ከዚህም ፡ እንደጊዜ ፡ ገድሉ ፡ ወርቅ ፡ አድርጎ ፡ አመጣው ።

፲፪ ፡ ኢሳይያስኒ ፡ ይቤ ፡ ይቀውም ፡ ሥርወ ፡ ዕሤይ ። (ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፲ ። ራዕ ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፭ ።) ፡ (ይቀውም ፡) ይነግሥ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ኢሳይያስም ፡ ሥርወ ፡ ዕሤይ ፡ ከርስቶስ ፡ ይነግሣል ፡ አለ ።

ወዘተሠይመ ፡ እምኔሁ ፡ ይከውን ፡ ንጉሠ ፡ ለአሕዛብ ።
(እምኔሁ ፡ ለዕሤይ) ፡ ከዕሤይ ፡ የተወለደ ፡ ከርስቶስ ፡ ለአሕዛብም ፡ ንጉሥ ፡ ይኾናል ። አለ ።

(አንድም ፡ መልስ) ፡ ኢሳይያስኒ ፡ ይቤ ፡ ይቀውም ፡ ሥርወ ፡ ዕሤይ ።
ትውልደ ፡ ዕሤይ ፡ ነገደ ፡ ዕሤይ ፡ ምእመን ፡ ጽንዐ ፡ ነፍስን ፡ አግኝቶ ፡ ይጸናል ፡ አለ ።

ወዘተሠይመ ፡ እምኔሁ ፡ ይከውን ፡ ን ጉሠ ፡ ለአሕዛብ) ።
እምኔሁ ፡ ሰሥርው ፡ ከምእሪን ፡ ወገን ፡ የነገሠው ፡ ከርስቶስም ፡ ለአሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾናል ። እሱ ፡ እሙንቱ ፡ ትእምርተ ፡ ሚመት ፡ እንዲል ። (አረ ፡ ወ)

ወሕዝብ ፡ ይትዌከሉ ፡ ቦቱ ።
ሕዝቡም ፡ ያምኑበታል ፡ አንዳለ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ይሴብሕም ፡ አለ ።

፲፫ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ተስፋ ፡ ይፈጽም ፡ ለከሙ ፡ ኵሎ ፡ ፍሥሓ ።
(እንዲህም ፡ ከኾነ) ፡ የተስፋ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋውን ፡ ኹሉ ፡ ይፈጽምላችሁ ።

ወሰላም ፡ በአሚን ። (ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ።)
በሃይማኖት ፡ አንድነት ን ፡ ይፈጽምላችሁ ።

www.zoyeneta.com

ከመ ፤ ያዘዘኸው ፤ በተስፋው ፤ ለመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ወበኃይሉ ። (ም ፤ ፩ ፤ ፲፯ ።)

ጎያሴ ፤ ሕይወቱ ፤ በሚኾን ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ፍጹማን ፤ ያደረጋችሁ ፤ ዘንድ ። አንድም ፤ በተስፋው ፤ መንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ አሠውጥ ፤ እምነ ፤ መንፈስየ ፤ ዲበ ፤ ሐሎ ፤ ዘሥጋ ፤ ብሎ ፤ ባናገረው ፤ ተስፋ ፤ መንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ (ወበኃይሉ) ፤ በከሐሊነቱ ፤ ፍጹማን ፤ ያደርጋችሁ ፤ ዘንድ ፤ ይፈጽም ፤ ለከሙ ።

ክ ፍ ል ፤ ፳፪ ።

፲፪ ፤ መእትአመነክሙ ፤ አነሂ ፤ አኅዊነ ፤ ከመ ፤ ትፈጽሙ ፤ በዙሉ ፤ ምግባረ ፤ ሠናይ ።

እኔም ፤ ወንድሞቻችን ፤ በሃውን ፤ ነገር ፤ ኹሉ ፤ እንድትፈጽሙ ፤ አምናችኋለሁ ።

ወጽጉባን ፤ አንትሙ ፤ በዙሉ ፤ ጥበብ ፤ ፤ በግእዝ ፤ ቦታ ፤ የኀባ ፤ ነው ፤ አንተስ ፤ ኢቀባዕከኒ ፤ ርእሰየ በዘይት ፤ (ሉቃ ፤ ፯ ፤ ፵፮ ።) ለምሁራን ፤ ልብ ፤ በጥበብ ፤ (መዝ ፤ ፶ ፤ ፲፪ ።)
ጥበብን ፤ ሁሉ ፤ የተመላችሁ ፤ እንደኾናችሁ ።

ወትክሉ ፤ ምህርቶሙ ፤ ለቢጽክሙ ። (፪ ፤ ጴጥ ፤ ፩ ፤ ፲፪ ። ፩ዮሐ ፤ ፪ ፤ ፳፩ ።)
ወንድሞቻችሁን ፤ ማስተማር ፤ እንዲቻላችሁ ፤ አምናችኋለሁ ።

፲፫ ፤ ወተነቢልየ ፤ ጸሐፍኩ ፤ ለክሙ ፤ አምአሐዱ ፤ ገጽ ።

ጥበብን ፤ የተመላን ፤ ወንድሞቻችንን ፤ ማስተማር ፤ የሚቻለን ፤ ከኾነ ፤ ምን ፤ ትለናለህ ፤ ትሉኝ ፤ እንደኾነ ፤፤ ከምሉ ፤ በከፍሉ ፤ ከብዙ ፤ በጥቂቱ ፤ ደፍሬ ፤ ጻፍሁላችሁ ። አንድም ፤ ከቢጽ ፤ ሐሳዊ ፤ አንድ ወገን ፤ ኹኑ ፤ ብዬ ፤ አንድ ፤ ወገን ፤ ኹኜ ፤ ደፍሬ ፤ ጻፍሁላችሁ ።

ዘእንተ ፤ ጸጋሁ ፤ ለእግዚአብሔር ፤ ዘረከብኩ ፤ (ም ፤ ፩ ፤ ፭ ፤ ፲፪ ፤ ፫ ።)
ዘእግዚአብሔር ፤ ዘንድ ፤ ስለተ ሾምሁ ት ፤ ሐዋርያነት ፤ ጸሐፍኩ ፤ ለክሙ ።

፲፬ ፤ ከመ ፤ እትለአክ ፤ ለኢየሱስ ፤ ክርስቶስ ፡ ውስተ ፤ አሕዛብ ።

(ኢየሱስ ፤ ክርስቶስን ፤ ለአሕዛብ ፤ አስተምር ፤ ዘንድ) ፤ አሕዛብን ፤ በማስተምር ፤ ኢየሱስ ፤ ክርስቶስን አገለግል ፤ ዘንድ ።

ወከሙ ፤ እትቀነይ ፤ ለትምህርተ ፤ እግዚአብሔር (፡ ም ፤ ፲፭ ፤ ፲፫ ፤ ፊልጵ ፤ ፪ ፤ ፲፯ ።)
(ትምህርተ) ፤ የእግዚአብሔር ፤ ሕግ ፤ ወንጌልን ፤ ለአሕዛብ ፤ አስተምር ። ዘንድ ።

ከመ ፤ ይኩን ፤ መሥዋዕቶሙ ፤ ለአሕዛብ ፤ ሥሙረ ፤ ወጎሩየ ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ በላዕሌየ ።

(መሥዋዕቶሙ ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ሥሙረ ፤ ይኩን ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ) ፤ በኔ ፤ ትምህርት ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ልጆች ፤ ኾነው ፤ ያቀረቡት ፤ መሥዋዕት ፤ በመንፈስ ፤ ቅዱስ ፤ ያማረ ፤ የተወደደ ፤ ይኾን ዘንድ ።

፲፮ ፤ መሊተስ ። ኢየሱስ ፤ ክርስቶስ ፤ ምክሕየ ፤ ለኀበ ። እግዚአብሔር ።

በላዕሌየ ፤ ብሎ ፤ ነበርና ፤ ለእኔስ ፤ በእግዚአብሔር ፤ ዘንድ ፤ መመኪያ ፤ ኢየሱስ ፤ ክርስቶስ ፤ ነው ።

፲፯ ፤ መእትኅበል ፤ እንግር ፤ ዘኅብረ ፤ ሊቶ ፤ ክርስቶስ ፤ በዘየእምኑ ፤ አሕዛብ ።

አሕዛብ ፤ በሚያምኑ ፤ በሚድኑ ፤ ገንዘብ ፤ ክርስቶስ ፤ ለኔ ፤ ያደረገልኝን ፤ ነገር ፤ ልናገር ፤ አወዳለሁ ። ቃል ፤ (ዘኅብረ ፤ ሊቶ ፤ በቃል) ።
በቃል ፤ ያደረገልኝን ፤ ነገር ፤

መበምግባር ። (፪ ፤ ቆሮ ፤ ፫ ፤ ፭ ፤ ፮ ፤ ፭ ።)

በሥራ ፤ ያደረገልኝን ፤ ሥራ ፤ ልናገር ፤ አወዳለሁ ፤፤ በቃል ፤ በምግባር ፤ ብሎ ፤ ኹለት ፤ አርእስት ፤ ተናግሯል ፤ ለሁለቱም ፤ ያመጣል ።

ኀይል ፤ ቊጥር ።
ምክር ፤ ላለው ፤ አመጣ ፤ በኀይል ፤ ምውት ፤ በማስነሣት ።

መቅድሚያ ።
ድመቀ ፤ ፀመረመስ ።

መበመንፈስ ።
ጋዜን ፤ በማመላት ፤ ያደረገልኝን ፤ ነገር ፤ ልናገር ፤ አወዳለሁ ።

በኀይል ፤ መንፈስ ፤ ቅዱስ ። (ግር ፤ ፲፭ ፤ ፲፯ ።)
መንፈስ ፤ ቅዱስን ፤ አሳድሮ ፤ ጽንዕ ፤ በማናገር ፤ ቃል ፤ ላለው ፤ ይህስ ፤ አንድ ፤ ወገን ፤ ነው ፤ ብሎ ፤ ምክር ፤ ላለው ።

www.zeyeneta.com

ወዘከመ ፡ መሀርኩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አስከ ፡ እድያሚሃ ፡ ለኢያሪኮ ።

በኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ኢያሪኮ ፡ አውራጃ ፡ ድረስ ፡ እንዳስተማርሁ ፡ (ቃል ፡ ላለው) ፡ (ሐተታ) ምነው ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ በጽሐ ፡ ጳውሎስ ፡ ሀገረ ፡ ዕልዋሪቆን ፡ ዘውእቱ ፡ ጽንፈ ፡ ምድር ፡ ይል ፡ የለም፡ ቢሉ ፡ ይህች ፡ ኢያሪኮ ፡ አያይዛ ፡ ከጽንፈ ፡ ምድር ፡ የምታደርስ ፡ ስለኾነ ።

ወፈጸምኩ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ።

የክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ ከኹሉ ፡ አደረስሁ ።

ኵ ፡ ወፈድፋደ ፡ ተፈቅረት ፡ ትምህርቱ ።

ትምህርቱ ፡ ወንጌል ፡ ፈጽማ ፡ ተረዳች ።

ወኢሐርኩ ፡ ኀበ ፡ ተሰምየ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ኢይሕንጽ ፡ ዲበ ፡ መሠረተ ፡ ባዕድ ።

ሌላ ፡ በበገረው ፡ እንዳላንጽ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ ወደተጠራበት ፡ አልሔድሁም ፡ አለ ፡ ሌላ ፡ ያሉት ግረውን ፡ እንዳላስተምር ፡ (ሐተታ) ፡ ምነው ፡ አሁንስ ፡ እንኳ ፡ ጽር ፡ የሚሰድላቸው ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እንጅ ፡ አይደሉ ፡ ስለምን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ ወደተጠራበት ብቻ ፡ አልሔድሁም ፡ ሲል ፡ ነው ።

ጸፈ ፡ በከመ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ እሰ ፡ ኢዘነውዎሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ ያአምርዎ ፡ ሀለዎሙ ።

የሱን ፡ ነገር ፡ ነቢያት ፡ ነግረዋቸው ፡ ያላወቁት ፡ ሐዋርያት ፡ ነግረዋቸው ፡ ያውቁት ፡ ዘንድ ፡ አላቸው መእለኒ ፡ ኢሰምዕዎ ፡ ይለብውም ። (ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፲፭ ።)

ሐዋርያት ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ ነግረዋቸው ፡ ያልሰሙትም ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የሚነሡ ፡ መምህራን ፡ ነግረዋቸው ፡ ያውቁት ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ አንደተናገረ ፡ ወኢሐርኩ ።

ጸፀ ፡ ወዘልፈ ፡ እፈቅድ ፡ እምጸእ ፡ ኀቤክሙ ።

ሁልጊዜ ፡ ወደናንት ፡ ልመጣ ፡ እወዳለሁ ።

ወይሰእነኒ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።)

ስወድም ፡ ይሳነኛል ።

ጸ፫ ፡ ወይእዜ ፡ ባሕቱ ፡ እስመ ፡ ሶበጥኩ ፡ በዝ ፡ በሐውርት ፡ ኦስመ ፡ እጽህቅ ፡ እምጸእ ፡ ኀቤክሙ ፡ እምጉንዴይ ፡ ዕሰት ። (ም ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።)

ነገር ፡ ግን ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወደእናንት ፡ አመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንድወድ ፡ ስወድም ፡ እንዲሳነኝ ፡ ይሰእነኒ ፡ ያልሁበትን ፡ ምክንያት ፡ በዚህ፡ ከታላ ፡ በመጀመሪያው፡ አንቀጽ ፡ ወለእመኒሰ ፡ ከመ ፡ እርከብ ፡ ዕሜትየ ፡ በሳዕሌክሙ ፡ ከመ ፡ በላዕለ ፡ አሕዛብኒ ፡ ወላዕለ ፡ አረማኒ ፡ ብዙ፡ ፍጽሚ፡ ተናግሬአለሁ ።(ም፡፩፡፲፫) (ሐተታ) ፡ ደግ ፡ መጽሐፍ ፡ በጀመረበት ፡ መጨረስ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ወዘልፈ ፡ እፈቅድ ፡ እምጸእ ፡ ኀቤክሙ ፡ ወይስእነኒ ፡ አለ ፡ በሐውርት ፡ አለው ፡ በሀገር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንዲኖር ፡ በአንቀጽም ፡ ብዙ ፡ ምሥጢር ፡ ይገኛልና ፡ (በሐውርት ፡ አለ) ፡ በከመ ፡ ይነግር ፡ ብሒረ ፡ መሳፍንት ፡ እንዲል ። እንቀጸ ፡ መሳፍንት ፡ ሲል ፡ (አፈ ፡ ወር) ።

ጸ፬ ፡ ወእንዘ ፡ አሐውር ፡ ሠገግሰ ፡ እስጳንያ ፡ እሴፎ ፡ እርአይክሙ ፡ ሕሊፈ ።

ወደ ፡ ሲባንያም ፡ ስሔድ ፡ እግር ፡ መንገዴን ፡ ላያችሁ ፡ እወዳለሁ ።

ወእምኀቤክሙ ፡ እትፈኖ ፡ ሀየ ፡ እምከመ ፡ ቀደምኩ ፡ ተፈሣሕኩ ፡ ምስሌክሙ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፮ ።)

አስቀድሜ ፡ ከናንት ፡ ጋራ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ካደረግሁ ፡ በኋላ ፡ ከናንት ፡ ወደዚያ ፡ (እሔድ ፡ ዘንድ) ፡ እወዳለሁ ፡ አንድም ፡ እሔዳለሁ ።

ጸ፭ ፡ ወይእዜሰ ፡ አሐውር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመልእክተ ፡ ቅዱሳን ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮፡ ፳፭ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ፡ ፳ ፡ ፳፪)

ዛሬ ፡ ግን ፡ አስተዋዕአውን ፡ ለመስጠት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሔዳለሁ ።

ጸ፮ ፡ እስመ ፡ ኀብሩ ፡ መቄዶንያ ፡ ወአካይያ ፡ ያስተዋዕኡ ፡ ለነዳያን ፡ እለ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወለቅዱሳን ፡ ወሠምሩ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፩ ፡ ፬ ።)

በመቄዶንያ ፡ ፊልጵስዩስና ፡ በአካይያ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ነዳያን አስተዋዕአውን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ እንድ ፡ ኾነው ፡ ወደዋልና ።

ጸ፯ ፡ እስመ ፡ ርቱዕ ፡ ሎሙ ።

የሚገባቸው ፡ ስለሆነ ።

www.zeyeneta.com

እምከመሰ ፡ ተሳተፍዎሙ ፡ ለእሕዛብ ፡ በግብር ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ርቱዕ ፡ ይትለአከዎሙ ፡ በዘይትፈቅድ ፡ ለነፍሰቶሙ ። (ም ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ።)

እሕዛብን ፡ በመንፈሳዊው ፡ ግብር ፡ ከመሰሏቸው ፡ ለሥጋቸውም ፡ በሚያሻቸው ፡ ሊረዱዋቸው ፡ የሚገባ ፡ ሰልኾነ ። (አንድም) ፡ እሕዛብን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ግብር ፤ ከመሰሏቸው ፡ ለሥጋቸውማ ፡ በሚያሻቸው ሊረዱዋቸው ፡ እንደምን ፡ አይገባ ፡ አምከመሰ ፡ ጎብሩ ፡ በዘኢይማስን ፡ እፎ ፡ በዘይማስን ፡ እንዲል (ቊናዶ) ።

ፍጽ ፡ መዘንተ ፡ ፈጺምየ ፡ ውኑቲምየ ፡ አሐልፍ ፡ እንተ ፡ ጎቤከሙ ፡ ለሲባንያ ፡ (ፈጺምየ ፡ አስተዋዕአውን ፡ አመጣጥቼ ፡ ጎቲምየ) ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አድርሼ ፡ (ፈጺምየ) ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አድርሼ ፡ (ሐቲምየ) ፡ በልቡ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቆልፌ ፡ በናንት ፡ በኩል ፡ ወደ ሲባንያ ፡ እሔዳለሁ ።

ፍ፱ ፡ ወእትአመን ፡ ባሕቱ ፡ ከመ ፡ እምጸአ ፡ ጎቤከሙ ፡ ለፍጻሜ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፲፩።)

የክርስቶስን ፡ ትምህርት ፡ መንጌልን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደናንተ ፡ ልመጣ ፡ እወዳለሁ ፡ እንድመጣ ፡ እምናለሁ ፡ (ሐተታ) ፡ ምን ፡ ቀርቶታል ፡ ቢሉ ፡ ሞት ፡ (አንድም ፡ ጌታ ፡ የራሱን ፡ ነገር ፡ ሲያስተምር፡ እንደሞተ ፡ አሱም ፡ የጌታን ፡ ነገር ፡ ሲያስተምር ፡ ይሞታልና፡ (አንድም) ፡ መካነ ፡ ሞቱ ፡ ናትና ፡ በፍቅር ፡ ለመሳብ ።

ክፍል ፡ ፳፫ ።

፩ ፡ ወአስተበቍዓከሙ ፡ አኀዊነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወንድሞቻችን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ማላጅ ፡ አድርጌ ፡ ወበፍቅረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ፍቅር ፡ ማላጅ ፡ አድርጌ ፡ እማልዳችኋለሁ ።

ትሰአሉ ፡ ሊተ ፡ በጸሎትክሙ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር። (፪ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፳፯፡፪ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፩)

(በጸሎትክሙ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር) ፡ (ትሰአሉ ፡ ሊተ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ ወደ ፡ እግዘ አብሔር ፡ ትሰምኑልኝ ፡ ዘንድ ፡ እማልዳችኋለሁ ። (ሐተታ) ፡ ፍጹሙ ስለትሕትና ፡ ወጣንያኑን ፡ ትሰእሉ ፡ ሊተ ፡ በጸሎት ከሙ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ አንድም ፡ አጵ ተብቍዖ ፡ ለማስተማር ፡ ለማለበም ፡ ጸሎተ ፡ ማጎበርም ፡ ይጠቅማልና ።

፪፩ ፡ ከመ ፡ ያድኅንኒ ፡ እምዐላውያን ፡ አለ ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ ።

በብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ካሉ ፡ ከዓላውያን ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ።

ከመ ፡ አሥምሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ አለ ፡ በኢየሩሳሌም ።

በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ አገለግላቸው ፡ ዘንድ ።

፴፪ ፡ ከመ ፡ እምጸአ ፡ ጎቤክሙ ፡ በፍሥሓ ።

ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ወደእናንት ፡ እመጣ ፡ ዘንድ ።

ወአዕርፍ ፡ ምስሌክሙ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በፈቅድልኝ ፡ ከናንት ፡ ጋር ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ አዐርፍ ፡ ቢል ፡ አርፋለሁ ።

፴፫ ፡ ወአምላከ ፡ ሰላም ፡ የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፳ ።)

የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ። አሜን ።

ይሁን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ፡ እግኅሠንኩከሙ ፡ ፌቤንሃ ፡ እኅተነ ፡ እንተ ፡ ትትለአክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘክንክርኤስ ።

ክንክርኤስ ፡ ክንክራያስ ፡ ይላል ፡ አመ ፡ ምኔትነት ፡ ተሹማ ፡ እንድም ፡ ዓሥራት ፡ በሑራት ፡ አያወጣም ፡ ጠንዘቢ ፡ በክንክርኤስ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ የምትረዳ ፡ ፌቤንን ፡ ሰማይ ፡ ዕሩቅ ፤ አደራ ፡ ጥብቅ ፡ እንዲሉ ፡ አደራ ፡ አላችኋለሁ ።

፪ ፡ ወትትወከፍዋ ፡ በእግዚእነ ።

(እግኅሠንኩከሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ትትወከፍዋ ፡ በእግዚእነ) ፡ ዘኪያከሙ ፡ ተወክፈ ፡ ኪያየ ፡ ተወከፈ መጽኪያ ፡ ተወከፈ ፡ ተወከር ፡ ለዘፈነወኒ ፡ ባለው ፡ በጌታችን ፡ ተወከር ፡ ትቀበሏት ፡ ዘንድ ፡ ጌታችንን ፡ ማላጅ ፡ አድርጌ ፡ አማልዳችኋለሁ ።

በከሙ ፡ ይደልዎ ፡ ለቅዱሳን ።

ቅዱሳንን ፡ ሊቀበሏቸው ፡ እንዲገባ ፡ አንድም ፡ ለቅዱሳን ፡ ለሳውን ፡ መቀበል ፡ እንዲገባቸው ።

www.zeyeneta.com

ወሥርዕዋ ፡ ውስተ ፡ ዘፈቀድክሙ ፡ ለትካዝክሙ ፡
ግዳጃችሁንም ፡ ለመፈጸም ፡ በምትሹት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እዘጂት።
እስመ ፡ አሥለጠት ፡ ለብዙኃን ።
ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ግዳጅ ፡ ትፈጽማለችና ፡ አለ ፡ ዓሥራት ፡ በሱራት ፡ እያወጣች ።
ወሊተኒ ።
ለኔም ፡ የጠም ፡ ቆሎ ፡ የባል ፡ ዶሮ ፡ ብላኛለችና ።
አንድም ፡ መልስ ፡ እስመ ፡ አሥለጠት ፡ ለብዙኃን ።
ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ግዳጅ ፡ ፈጽማለችና ፡ ክታብ ፡ ወስዳ ፡ በማስታረቅ ።
ወሊተኒ ።
እኔንም ፡ ብዑዓን ፡ ገባርያን ፡ ሰላም ፡ ከተባሉት ፡ እስቈጥራኛለችና ።

፫ ፡ እምኁ ፡ ጽርስቅላሃ ፡ ወአቂላሃ ፡ እለ ፡ ኀብሩ ፡ ምስሌየ ፡ በግብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፪ ፡ ፳፮ ።)
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሚኾኑ ፡ አቂላን ፡ ጽርስቅላን ፡ ቸር ፡ እላችሁን ፡ በሉ ።

፬ ፡ እለ ፡ መጠዉ ፡ ክሣዶሙ ፡ በእንተ ፡ ነፍስየ ።
ስለእኔ ፡ ስሙነታቸውን ፡ ለመክራው ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡ ፡
ወእኩ ፡ ፡እን ፡ ባሕቲተየ ፡ ዘአእኩቶሙ ።
የማመሰግናቸውም ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ።
ዓዲ ፡ ኵሎሙ ፡ እብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘአሕዛብ ።
ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ያመኑ ፡ ምእመናንም ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኗቸዋል ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወእምኁ ፡ ማኅበረ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ቤቶሙ ። (፩ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ።)
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ያሉ ፡ ቤተ ፡ ሰብአቻቸውንም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ስም ፡ ስማቸውን ፡ ይጠራል ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ማኅበር ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ቤቶሙ ፡ እለ ።
ወእምኁ ፡ ኤጴኔጦሃ፡ እኁየ ፡ ዘውእቱ ፡ ጥንቶሙ ፡ ለእስያ ፡ በክርስቶስ ።

(እኁየ ፡ በክርስቶስ ፡ ጥንቶሙ ፡ በክርስቶስ) ፤ በክርስቶስ ፡ ወንድሜ ፡ የሚኾን ፡ ለእስያ ፡ ሰዎች ፡ በክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ፊታውራሪያቸው ፡ እበጋዛቸው ፡ የሚኾን ፡ ኤጴኔጦንን ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ በሉ ።

፮ ፡ እምኁ ፡ ማርያ ፡ እንተ ፡ ብዙኀ ፡ ሠርሐት ፡ ለክሙ ።
በሃይማኖት ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ የተቀበለች ፡ ማርያን ፡ ቸር ፡ አለሽን ፡ በሉ ።

፯ ፡ እምኁ ፡ እንድራኒቆን ፡ ወዩልያን ፡ እለ ፡ እምአዝማድየ ፡ ወተጸወዉ ፡ ምስሌየ ።
ከኔ ፡ ጋራ ፡ በወንጌል ፡ ያመኑ ፡ ዘመዶቼ ፡ የሚኾኑ ፡ ዩልያንን ፡ እንድራኒቆንን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ
ወያአምርዎ ፡ ሐዋርያት ፡ ከመ ፡ ቀዲሙኒ ፡ ተልእኩ ፡ ለክርስቶስ ። (፩ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።)
በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከጌታ ፡ እንደተማሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ያውቋቸዋል ።
፰ ፡ አምኁ ፡ ጵልያጦንሃ ፡ እኁየ ፡ በክርስቶስ ።

(እኁየ ፡ በክርስቶስ ፡ አምኁ ፡ በክርስቶስ) ፤ በክርስቶስ ፡ ወንድሜ ፡ የሚኾን ፡ ጵልያጦንን ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ በሉ ።

፱ ፡ እምኁ ፡ ኡርባኖን ፡ ዘነኀብር ፡ በግብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ወስንጣክን ፡ እኁየ
የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ አንድ ፡ የምንኾን ፡ ኡርባኖንን ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ በሉ ።
ወንድሜ ፡ ስጣክንንም ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ በሉ ።

፲ ፡ እምኁ ፡ ኤጤሌን ፡ ኅሩዮ ፡ በክርስቶስ ።

(አምኁ ፡ በክርስቶስ ፡ ኅሩዮ ፡ ለክርስቶስ) ፡ ክርስቶስ ፡ የመረጠው ፡ ኤጤሊንን ፡ በክርስቶስ ፡ ሰላምታ ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ በሉ ።

እምኅዎሙ ፡ ለእለ ፡ እርስጠበሉ ።
ስመ ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ ከእርስጣባሉ ፡ ወገን ፡ የሚኾኑትን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።
፲፩ ፡ አምኁ ፡ ሄሮድያና ፡ ዘእምእዝማድየ ።
ከዘመዶቼ ፡ ወገን ፡ የምትኾን ፡ ሄሮድያናን ፡ ቸር ፡ አለሽን ፡ በሉ ።
አምኁ፡ እለ ፡ እምውስተ ፡ ቤተ ፡ ንርቁሱ ፡ ኦስ ፡ በክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ከንርቃሱ ፡ ወገን ፡ የሚኾኑትን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

www.zeyeneta.com

፲፪ ፡ አምኑ ፡ እል ፡ ጢሮፌሞና ፡ ወጢሮፌሞስ ፡ አለ ፡ የመዉ ፡ በእግዚአነ ።
ፈጺታችን ፡ አምነው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ ጢሮፌሞናንና ፡ ጢሮፌሞስን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

አምኑ ፡ ወርሲዳ ፡ እኅትነ ፡ እንተ ፡ ብዙኃ ፡ የመወት ፡ በእግዚአነ ።
ፈጺታችን ፡ አምና ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ የተቀበለች ፡ እኅታችን ፡ ጠርሴዳን ፡ ቸር ፡ አለሽን ፡ በሉ ።

፲፫ ፡ አምኑ ፡ ሩፎን ፡ ኅሩዮ ፡ ለእግዚአነ ፡ (ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፩ ።)
(አምኑ ፡ በእግዚአነ ፡ ኅሩዮ ፡ ለእግዚአነ) ፡ ጌታችን ፡ የመረጠው ፡ ሩፎንን ፡ በጌታችን ፡ ሰላምታ ፡ ቸር ፡ አለሀን ፡ በሉት ።

ወእሞ ።
እናቲን ።

ወሊተኒ ፡ አምየ ።
ለእም ፡ እናቴ ፡ (ሐተታ) ፡ ሐዋርያት ፡ ወንድ ፡ ወንዱን ፡ ሽማግሌውን ፡ አባታችን ፡ ሕፃን ፡ ሕፃኑን ፡ ወንድማችን ፤ ሴት ፤ ሴቲን ፤ ባልቴቲቱን ፤ እናታችን ፤ ሕፃን ፡ ሕፃኑን ፤ እኅታችን ፤ ማለት ፡ ልማዳቸው ነውና ፡ ወሊተኒ ፡ እምየ ፡ አለ ። (እንድም) ፡ ከቤተ ፡ ገማልያል ፡ ሲማር ፡ ትረዳው ፡ ነበርና ፡ ወሊተኒ ፡ እምየ ፡ አለ ።

፲፬ ፡ አምኑ ፡ አስቀሪጦን ፡ ወአፍልሰንጳ ፡ ወሄርሜን ፡ ወጳጥሮባን ፡ ወሄርማን ።
አስቀሪጦንን ፡ አፍልሰንጳን ፡ ሄርሜንን ፡ ጳጥሮባን ፡ ሄርማንን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

ወአኃዊነ ፡ አለ ፡ ምስሌሆሙ ።
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ወንድሞቻችንንም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

፲፭ ፡ አምኑ ፡ ፊሎሎን ፡ ወዮልያ ፡ ወኔርያ ።
ፊሎሎንን ፡ ዮልያን ፡ ኔርያን ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

ወአኅቶ ፡ ወአልንጦን ።
ስሟ ፡ ነው ፡ ብሉ ፡ አኅቶን ፡ እንድም ፡ አኅቱን ፡ ዋልጦንን ፡ ቸር ፡ አለሽን ፡ በሉ ።

ወሁሉሙ ፡ ቅዱሳነ ፡ አለ ፡ ምስሌሆሙ ።
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንንም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።

፲፮ ፡ ወተአምኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።)
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ከይሁዳ ፡ ከኤሳው ፡ ከዲያብሎስ ፡ በተሰየ ፡ ሰላምታ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ተባባሉ ።

ወአምኑክሙ ፡ ሁሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቲሁ ፡ ለክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይሏችኋል ።

፲፯ ፡ አስተበቍዐክሙ ፡ አኀዊነ ፡ ተዓቀብዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ሀክከ ፡ ወያመጽኡ ፡ ካሕዶ ፡ ላዕለ ፡ ትምህር ትክሙ ፡ ዘተመሀርክሙ ፡ ትግበሩ ፡ ባቲ ። (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ። ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፲ ።)
ባቲ ፡ ኪያሃ ፡ ሲል ፡ ነው፡ ወንድሞቻችን፡ እሷን ፡ ትሠሪት ፡ ዘንድ ፡ በተማራችኋት፡ ትምህርት፡ ወንጌል፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ክርክርን ፡ የሚያመጡ

አንድም ፡ ትግበሩ ፡ ባቲ ፡ በተማራችኋት ፡ ትምህርት ፡ በወንጌል ፡ ላይ ፡ የአሪትን ፡ ሥራ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ አሪት ፡ ዋምቅት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ እያሉ ፡ ጠብ፡ ክርክርን ፡ በሚያመጡ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ እወቁባቸው ፡ ብዬ ፡ እግልዳችኋለሁ ።

ወተግሕሥሙ ።
ተለዩአቸው ።

፲፰ ፡ እሰመ ፡ ለክርሞሙ ፡ ይትቀነዩ ፡ ወእኩ ፡ ለእግዚአነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ፊልጵ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።)
ለጌታችን ፡ ያይደሰ ፡ ኾድ ፡ እምላኩ ፡ ናቸውና ።

ወቍጹሓን ፡ ንኁሂ ፡ ወበተየውሆ ፡ ያስሕትዎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ የዋሃን ፡ (ሕዝ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፱ ።)
ወነገር ፡ ግታለል ። በመለዘብ ፡ ያልተማሩ ፡ ብዙዎችን ፡ ሰዎች ፡ ያስታቸዋልና ፡ የዋሕ ፡ ብእሲ ፡ ሁሉ ፡ ወነገርዎ ፡ የሐምን ፡ እንዲል ። (ምሳ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።)

፲፱ ፡ ወንፈረ ፡ ጌአክሙሰ ፡ ተሰምዐ ፡ በሁለሄ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፰ ።)
እዋንትም ፡ ትሳዙን ፡ ብዬ ፡ እናንተስ ፡ እንዳትሳዙ ፡ የናንተ ፡ ነገር ፡ በሀራቱ ፡ መዓዝን ፡ ተሰምቷል ።

ወአትረግሕ ፡ ፀእንቲአክሙ ።
ብኩሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ስናንቱ ፡ ደስ ፡ ይሰኛል ።

www.zeyeneta.com

ወአፈቅድ ፡ ለከሙ ፡ ትጥበቡ ፡ ለሠናይ ፡ ወትትግኃሥዎ ፡ ለእኩይ ፡ (፮ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ።)

ከፉውን ፡ ትታችሁ ፡ ለበጎው ፡ ልትራቀቁ ፡ አወዳለሁ ፡ ለከፉ ፡ መራቀቅ ፡ አለና ፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ ትጥበቡ ፡ ለሠናይ ፡ አለ ፡ ለእከይሰ ፡ ጠቢባን ፡ እሙንቱ ፡ አንዲል ።

፳ ፡ ወአምላከ ፡ ሰላም ፡ ይቀጥቅጠ ፡ ለሰይጣን ፡ በታሕተ ፡ እገሪከሙ ፡ ፍጡነ

የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአኖ ሔር ፡ ሰይጣንን ፡ በእጃችሁ ፡ ጭብጥ ፡ በአግራችሁ ፡ አርግጥ አድርጎ ፡ ያጥፋላችሁ ፡ (ሐተታ) ፡ ይህ ፡ በተነበበ ፡ ጊዜ ፡ የላይ ፡ ፈሪ ፡ የታች ፡ ፈሪ ፡ አያስ ፡ ሲያጣላ ቸው ፡ የነበረ ፡ ሰይጣን ፡ እንደጠሰ ፡ ተኖ ፡ አንደትቢያ ፡ በኖ ፡ ጠፍቷል ።

ጸጋሁ ፡ ለእግዚአነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌከሙ (፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፴፫ ።)

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ይደረግላችሁ ።

፳፩ ፡ ይኤምኃከሙ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ዘነኃብር ፡ ግብረ ፡ ምስሌሁ ፡(ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ። ፊሊጵ ፡ ፪ ፡ ፲፱።)

ከሱ ፡ ጋራ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ አንድ ፡ የምንኾን ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይላችኋል ።

ወሉቂዮስ ፡ ወኢያሶን ፡ ወሱሲ ፤ጴጥሮስ ፡ አለ ፡ አዝማድየ ።

ሉቅዮስ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይላችኋል ፡ ኢያሶን ፡ ከዘመዶቼ ፡ ወገን ፡የሚኾኑ ፡ ሱሲ ፡ ጴጥሮስም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይላችኋል ። (ሱሲ ፡ ፀሐይ ፡ ማለት ፡ ነው ።)

፳፪ ፡ ወአማኅኩክሙ ፡ አነ ፡ ጠርጥዮስ ፡ ዘጸሐፍኩዋ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ በእግዚእነ ።

በጌታችን ፡ አምጌ ፡ ይህችን ፡ ከታብ ፡ የጻፍኋት ፡ እኔ ፡ ጠርጤዎስም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ አላችኋለሁ ፤ ጥቂ ፡ ዳሀ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስለትሕትና ፡ አነ ፡ ጠርጤዎስ ፡ አለ ፡ አንድም ፡ ያልታወቀ ፡ ነው ፡ በመንገድ ስትሄድ ፡ አግኝቷት ፡ ለኔም ፡ ይህን ፡ ወስደሽ ፡ ስጭኝልኝ ፡ ብሏት ፡ ወስዳ ፡ ሰጥታለታለች ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን፡ መጥቶ ፡ የነበረ ፡ ፈረንጅ ፡ አሊህን ፡ ኹሉ ፡ አውቃቸዋለሁ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አላውቀውም ፡ ብሏል

፳፫ ፡ አምኃከሙ ፡ ጋይዮስ ፡ ዘያኃድረኒ ፡ በንግዶትየ ።

በአንግድነቴ ፡ ጊዜ ፡ ዘመድ ፡ ዘመጅ ፡ ያለኝ ፡ ጋይዮስም ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይላችኋል ።

ወኵሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ (፮ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ።)

ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይሏችኋል

አምኑክሙ ፡ አርስጦስ ፡ መጋቤ ፡ ሀገር ፡ ወቍአስጥሮስ ፡ አኑነ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ።)

ሀገር ፡ አሳዳሪ ፡ አርስጦስ ፡ ወንድማችን ፡ ቍአስጥሮስ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይሏችኋል ።

፳፬ ፡ ውእቱ ፡ ዘይክል ፡ ያጽንዕክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ስብክት ፡ ዘእሰብክ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ስለጌታችን ፡ ስለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማስተምራት ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ሊያጸናችሁ ፡ የሚቻለው ፡ አሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ አንድም ፡ አሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጽናችሁ ።

ዘኅቡዕ ፡ ኅርመታ ፡ አምቅድመ ፡ ዓለም ፡ (ኤፌ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ። ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፱ ።)

ሥጋዌው ፡ ቅድመዓለም ፡ ኅቡዕ ፡ የሚኾን ፡ (ሐተታ) ፡ ኅቡዕ ፡ አለ ፡ በስው ፡ ዘንድ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ታውቆ ፡ ያለ ።

፳፭ ፡ ወአስተርአየ ፡ በዝ ፡ መዋዕል ፡ አምቃለ ፡ ነቢያት ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፪ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ።)

አምስት ፡ ሽህ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ አስቲፈጸም ፡ በነቢያት ፡ ቃል ፡ የተነገረ ።

ወበትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለዓለም ።

አምስት ፡ ሽህ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ ሐሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ባሰው ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ።

ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ዅሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወይእመኑ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።

አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ተምረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ በሚኾን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያምኑ ዘንድ ፡ አለ ፡ (ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ) ፡ እንደሆነ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ።

፳፮ ፡ ወያአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ።

ክብር ፡ ጌትነት ፡ ግንዘቡ ፡ የሚኾን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያውቁት ፡ ዘንድ ።

www.zeyeneta.com

መጽሐፉ ፡ መቢብ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ (፩ጠሞ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ ይሁ ፡ ፳፩ ፡)

ለዘልዓለሙ ፡ እዋቂ ፡ የሚኾን ፡ (ሐተታ) ፡ አብን ፡ ጠቢብ ፡ አለው ፡ አሕዛብ ፡ እንጨት ፡ ጠርበው ፡ ድንጊያ ፡ አለዝበው ፡ ጣዖት ፡ ቢያመልኩ ፡ ግዙፍ ፡ እምላክ ፡ ከሹ ፡ በግዘፍ ፡ ይታይላቸው ፡ ብሎ ፡ ለጅን ፡ በሥጋ ፡ ስዶላቸዋልና ፡ ጠቢብ ፡ አለው ፡ እስመ ፡ አሕዛብ ፡ አፍቀሩ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ እምዕፀው ፡ ዘጸረብዎ ፡ ጸረብት ፡ ወበአንተዝ ፡ ኮነ ፡ ወልድከ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ ያስተርእዮሙ ፡ ለግባርያን ፡ አርአያ ፡ ወአምሳል ፡ እንዲል ፤ (ጎርጎስ) ፡ አንድም ፡ ጠቢብ ፡ ብሎ ፡ ለወልድ ፡ ቀጠለ ፡ ዲያብሎስ ፡ ከሥጋ ፡ ከይሲ ፡ ተሠውሮ ፡ ቢያስት ፡ አሱም ፡ በሥጋ ፡ ብእሲ ፡ ሥጣው ፡ ኾኖ ፡ አድኖበታልና ፡ ጠቢብ ፡ አለው ፡ ወበከመ ፡ ኮነ ፡ እንከ ፡ ተኃብአ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ፡ ከይሲ ፡ በጉሕሉት ፡ ከማሁ ፡ ኮነ ፡ ድኅነትን ፡ በተሠውሮተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘመድን ፡ እንዲል ፡ (መቅድመ ፡ ወንጌል) ፡ አሜን ፡

በውነት ፡ ያለሐሰት ፡

ጸጋ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሀለ ፡ ምስለ ፡ ዅልክሙ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ጸጋሁ) ፡ ሀበት ፡ ወልድና ፡ ሕይወተ ፡ ልቡና ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ስርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ይደረግላችሁ ፤

አሜን ፡

በውነት ፡ ይኹን ፡

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ዘተጽሕፈት ፡ በቆሮንቶስ ፡ ወተፈነወት ፡ በእደ ፡ ፈቤን ፡ እንተ ትትለአኮሙ ፡ ለማኅበረ ፡ ክንክርኤስ ፡

በቆሮንቶስ ፡ የተጻፈች ፡ በክንክርኤስ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ በምትረዳ ፡ በፈቤን ፡ እጅ ፡ ለሮም ፡ ሰዎች ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ክታብ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ፡

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡

አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡

****

www.zeyeneta.com

ምክንያተ ፡ መልእክተ ፡ ጳውሎስ ፡
ካልእ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ።

እስመ ፡ በብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ኮኑ ፡ ሶበ ፡ ተመክፍዋ ፡ ለመልእክቱ ፡ ቅዳሚት ፡ ተከዙ ፡ ጥቀ ፡ እንዘ ፡ ይኔስሑ ፡ እምኀጢአቶሙ ፡ ለእሊ ፡ ነሥኡ ፡ ማዕርገ ፡ ሢመቶሙ ፡ ለመምህራን ፡ ወነዘኑ ፡ በእንተ ፡ ዘተሐየዩ ፡ ወኢንብሩ ፡ ኀቢኤ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ኃጢአት ።

ወዓዲ ፡ ተባየጽምሙ ፡ ለቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ አለ ፡ ያመጽኡ ፡ ምክንያተ ኃፅዝ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ያከብርዋ ፡ ለመጽሐፈ ፡ አሪት ፡ ወይመንንዋ ፡ ለሥርዓት ፡ ክርስቶስ ፡ ወይረስይዋ ፡ ክሙ ፡ ወኢምንት ።

ወእጽንኑ ፡ ልቦሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ በተእዝዞተሙ ፡ ለእሉ ፡ እምድኅረ ፡ እስ ተሐመሙ ፡ ዘሠናይ ፡ ጸሕቅ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ ዘይፈንውዎ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ።

ወነገሮ ፡ ዘንተ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ረድኡ ፡ እመ ፡ ኀብእ ፡ ኀቤሁ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በፈል ጵስዩስ ፡ ዘመቄዶንያ ።

ወፈነዎ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ፡ ክሙ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ለዙሉሙ ፡ በታሉ ፡ ክመ ፡ እይ ትወክፍዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ሐዋርያተ ፡ ሐሰት ።

ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ቲቶ ፡ ተወክፍዎ ፡ ዙሉሙ ፡ ወመሀሮሙ ፡ ክሙ ፡ ኢይትወክፍዎሙ ፡ እስከ ፡ ዐበይዎሙ ፡ ወገብኡ ፡ ኀበ ፡ ጸሕቆሙ ፡ ዘቀዳሚ ።

ወተአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ በፍርኃት ፡ ወበረዓድ ።
ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ቲቶ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ የእዙቶሙ ፡ ወይትዌከፍ ፡ ሥላጤሆሙ ።

ወነገሮ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘከሙ ፡ ተእ ዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ወእፈድፈዱ ፡ ጸሕቀ ፡ እምቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ ዘይፈንውዎ ፡ ኀበ ፡ ቅዱሳን ።

ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሐፈ ፡ ሎሙ ፡ ዳግመ ፡ መልእክተ ፡ እንዘ ፡ ያቀድም ፡ወድ ሶቶሙ ፡ ለእሉ ፡ እሰ ፡ ሰደድዎ ፡ ለዝኩ ፡ ዘተዐደመ ፡ ሥርዓተ ፡ ትእዛዝ ፡

ጳውሎስ ፡ ኹለተኛ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡
የጸፈው ፡ ከታብ ፡ ምክንያት ።

የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ የፈተኗይዙን ፡ ከታቡን ፡ በተቀበሏት ፡ ጊዜ ፡ የመምህሮቻቸውን ፡ ሹመት ፡ የተሾሙትን ፡ ሰዎች ፡ ስለዚች ፡ ኃጢአታቸው ፡ ጉባኤ ፡ አድርገው ፡ ሳይለይዋቸው ፡ በመቅረታቸው ፡ ቸል ፡ በማለታቸው ፡ እየተጠጠቱ ፡ እጅግ ፡ እር ገው ፡ አዝነው ፡ ተከዘው ፡ ነበረ ።

ጳጉሜኖም ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ እንደ ፡ ኢምንት ፡ እድርገው ፡ ንቀው ፡ እታለው ፡ አሪትን ፡ ያከብሯት ፡ ዘንድ ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ አሪት ፡ ጥቅት ፡ እንበለ ፡ ግዘረት ፡ አትረባም ፡ እትጠቅም ፡ እያሉ ፡ ጠብ ፡ ክርክርን ፡ የሚፈ ጥሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ጓደኞች ፡ እድርገዋቸው ፡ ነበርና ።

በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ የሚሰጹ ትን ፡ እስተዋዕዶውን ፡ ለማወጣጣት ፡ ብቡን ፡ ሐሳብ ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ ከደከሙ ፡ በኋላ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ለነዚህ ፡ በመታዘዛቸው ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደዚህ ፡ ግብር ፡ እዘንብለው ፡ ነበርና ።

ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እንሱን ፡ ጠይቆ ፡ ወደርሱ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ የመቄዶንያ ፡ ክፍል ፡ በምትኾን ፡ በፈልጵስዩስ ፡ ላለ ፡ ይህን ፡ ነገረው ።

ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ቲቶን ፡ እኒህን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳ ውያንን ፡ እንዳይቀበሏቸው ፡ በታል ፡ ይመክራቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ከታብ ፡ ሳይጽፍ ፡ በታል ፡ ላከው ።

ቲቶም ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ዙሉም ፡ አክብረው ፡ ተቀበሉት ፡ እሱም ፡ ወደቀ ደመ ፡ ትሩፋታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ቢጽ ፡ ሐሳው ያንን ፡ እንቀበላችሁም ፡ እስኪሏቸው ፡ ድረስ ፡ መላልሶ ፡ እስተግራቸው ።

ፈርተው ፡ ተንቀጥቅጠው ፡ ታዘዙለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቲቶ ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸማቸውን ፡ አይቶ ፡ እያመሰገናቸው ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ።

ለጳውሎስም ፡ ለርሱ ፡ መታዘዛቸውን ፡ ለም እመናን ፡ በሰሚልኩት ፡ እስተዋዕዶ ፡ ማወጣጣትም ፡ ከተደመው ፡ ይልቅ ፡ እብልጠው ፡ መትጋታቸውን ፡ ነገረው ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተሾመውን ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የነግዙን ፡ ጉባኤ ፡ ሠርተው ፡ በመለየ ታቸው ፡ እንሱን ፡ እያመሰገነ ፡ ይህን ፡ ኹለተኛ ውን ፡ ከታብ ፡ ጸፈለቸው ።

www.zeyeneta.com

ዳግመኛም ፡ በዚች ፡ ክታብ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ መከራ ፡ እየተቀበለ ፡ የሚያስተምር ፡ እውነተኛ ፡ መምህር ፡ እንደኾነ ፡ እነዚያ ፡ ግን ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ እንደኾኑ ፡ ገለጠላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ቢመለስ ፡ ይቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ እንዲቀበሉት ፡ ለመናቸው ፡ ማለጸቸው ።

ይህን ፡ ክታብ ፡ የመቄዶንያ ፡ ክፍል ፡ በምት ኾን ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ሳለ ፡ ጽፎ ፡ በቲቶና ፡ በሉ ቃስ ፡ እጅ ፡ ላከላቸው ።

ወእርእዮሙ ፡ ካዕበ ፡ በዉስቴታ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይሰብክ ፡ በጽድቅ ፡ እንዘ ፡ የሐምም ፡ በብ ዙኅ ፡ መከራ ፡ ወውእቶሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ሐሳውያን ።

ወእምዝ ፡ ሰአሎሙ ፡ ወአስተብቍዖሙ ፡ ከመ ፡ ይትወክፍዎ ፡ ዲውኑቱ ፡ ብእሲ ፡ እመ ፡ ኃጢሐ ።

ወፈነወ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ፡ ወሉቃስ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ዘመቄዶንያ ።

www.zeyeneta.com

ቀዳማዊ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ካልእት ፡ እለ ፡ (ታሪክ ፡) ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በፈልጵስዩስ ፡ ኾኖ ፡ ቲቶን ፡ ጠይቅኖ ፡ ፍ ፡ ብሎ ፡ ሰዶታል ፡ ቢ ሐድ ፡ ለእስተዋዕአ ፡ ሲተጉ ፤ ለምግባር ፡ ልችሩት ፡ ቢርካከሩ ፡ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የንግው ። የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተቆጣውን ፡ ለይቱው ፡ አነ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወእነ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ወእነ ፡ ዘኬፋ ፡ ፤ ማለትን ፡ ትተው ፡ እነ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ልሉ ፡ አግኝቷቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ክሰው ፡ ጽንት ፡ አይ ታማምና ፡ ቢጽ ፡ ሐላውያን ፡ በመና ፡ በደመና ፡ ሲመኩ ፡ ስምተው ፡ ወደሶሪት ፡ እንመለስ ፡ ብለዋል ፡ ሐዲ ፡ ይሁን ፡ ነግሮታል ፡ ይሀን ፡ ስምቶ ፡ ሰዚህ ፡ ይጽፋል ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዙሁ ፡ ሰእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አቡሃ ፡ ለምሕረት ፡ ወእምላካ ፡ ለኵሳ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘእስተፍሥሐነ ፡ እምኵሉ ፡ ሕማምነ ፡ ከመ ፡ ንክሃል ፡ አስተፍሥሖቶሙ ፡ ለኵሉሙ ፡ ሕመማን ፡ በወእቱ ፡ ፍሥሓነ ፡ ዘእስተፍሥሐነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፫-፭ ።)

እስመ ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ አመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወአመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ። ጸድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ፡ ቃልነ ፡ ወኢተቶሐ ፡ እወ ፡ ወአልቦ ። እስመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንሕነ ፡ ሰበክነ ፡ ለክሙ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሰለዋናስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ኢኮነ ፡ እወ ፡ ወአልቦ ። ዳዕሙ ፡ እወ ፡ ኮነ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይላል ። (ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ እስከ ፡ ፳ ።)

ወበጺሕያ ፡ ጢርአዳ ፡ ውስተ ፡ ትምሀርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍናተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውሷተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕዙት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ። (ም ፡ ፬ ፡ ፯ ፡)

አፉነ ፡ ዘኮፈ ፡ ለኵሙ ፡ እ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወርትዑ ፡ ልብነ ፡ ይላል ። (ም ፡ ፮ ። ፲፪ ፡)

ከዚያም ፡ ወእንግረክሙ ፡ አኀዊነ ፡ እታ ፡ ኦጠስአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለቤሎ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመቄዶንያ ፡ ይላል ። (ም ፡ ፰ ፡ ፩ ።)

ወይእዜስ ፡ ግበሩኂ ፡ ወፈጽሙኂ ፡ ይላል ።(፰ ፡ ፲፩ ።)

እመስ ፡ ይኤድመክሙ ፡ አጽምእቶሙ ፡ ለአብዳን ፡ እንዘ ፡ ጠቢባን ፡ ወነባብያን ፡ አንትሙ ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።)

ክዚህ ፡ በኋላ ፡ እሱ ፡ እያጸናው ፡ በተቀበልው ፡ መክራ ፡ ሲመካ ፡ አልምቶ ፡ አሰፍቶ ፡ ይጽፋል ። ወእመሰ ፡ ይደሉ ፡ ተመክሖ ፡ አነኂ ፡ አትሜካሕ ፡ ይላል ። (ም ፡ ፲፩ ፡ ፴ ።)

ወናሁ ፡ ይረትዕ ፡ ሊተ ፡ ተመክሖ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ብሎ ፡ ንግባዕ ፡ ካዕበ ፡ ወንዘክር ፡ ራእየ ። ዘክሠተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ። (ም ፡ ፲፪ ፡ ፩ ።)

የጻፈበት ፡ ሀገር ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ክታብ ፡ ወሳጅ ፡ ቲቶና ፡ ሉቃስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ሐዋርያው ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።

በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንቼ ፡ ብኅኖ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክሾመኝ ።

እንድም ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ከማስ ፡ ቀምር ፡ ክኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ።

ወጢሞቴዎስ ፡ እኁነ ።

ከወንድማችን ፡ ከጢሞቴዎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ፡ (ሐተታ) ፡ በጽሕፈትም ፡ በድርሰትም ፡ አግዞት ፡ አይደለም ፡ ስለትሕትና ፡ ያነሣዋል ።

ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘማኅበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወገረ ፡ ቆሮንቶስ ።

ማኅበረ ፡ ቆውሎስ ፡ ማኅበረ ፡ አጵሎስ ፡ ማኅበረ ፡ ኬፋ ፡ ላይደሉ ፡ ማኅበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚ ፡ ባሉ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ትድረስ ፡ (ሐተታ) ፡ አንደቀዳማዊ ፡ ቆሮንቶስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪ ።)

ወሰሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ዐገረ ፡ ካይያ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፩ ።)

በአካይያ ፡ አውራጃ ፡ ላሉትም ፡ ኹሉ ፡ ትድረስ ።

www.zeyeneta.com

፪ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ።
ቸር ፡ አላችሁን ።

ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ መእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፯) ።
የእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ቸርነቱ ፡ ይደረ ግላችሁ ።

ፍ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

እቡየ ፡ ለምሕረት ።
የምሕረት ፡ መጎኖ ፡ (ሐተታ) ፡ ልጅ ፡ ከአባቱ ፡ እንዲኖኝ ፡ ምሕረትም ፡ ከርሱ ፡ ትገኖለችና ።

ወአምላካ ፡ ለሠላ ፡ ትፍሥሕት ፡ (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፭) ።
የፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ባልቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፮ ። ዘአስተፍሥሐን ፡ እምድሉ ፡ ሕግምን ፡ ከመ ፡ ንክህል ፡ አስተፍሥሖተ ፡ ለዝሉሙ ፡ ሕሙማን ፡ በውእቱ ፡ ፍሥሐን ፡ ዘአሥተፍሥሐን ፡ እግዚአብሔር ።

እኛን ፡ ደስ ፡ ባሰኘበት ፡ ደስታ ፡ ጎዙናንን ፡ ደስ ፡ ያሰኘቸው ፡ ዘንድ ፡ በመከራው ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ያሰ ኘን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ (ሐተታ) ፡ ባደባባይ ፡ ገፈው ፡ ጎርፈው ፡ ሲያሰወቁቸው ፡ እንደተ ቸሙ ፡ እንደተሸለሙ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ይሐዳሉና ፤ ወፅኡ ፡ እምፀውድ ፡ እንዘ ፡ ይትሄሥሑ ፡ እስመ ፡ ከፈ ሉሙ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ትጹብ ፡ ከመ ፡ ያኅሥርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፵፩) ።

እንድም ፡ እኛን ፡ ወደመከራው ፡ አግብቶ ፡ ከመከራው ፡ አውጥቶ ፡ ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ባሰኘበት ፡ ደስታ ፤ ጎዙናንን ፡ ወደመከራው ፡ አግብተን ፡ ከመከራው ፡ አውጥተን ፡ ጸጋውን ፡ አሰጥተን ፡ ደስ ፡ እናሰ ኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደመከራው ፡ አግብቶ ፡ ከመከራው ፡ አውጥቶ ፡ ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኘን ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፮ ፡ ወበከመ ፡ በዝኀ ፡ ሕማሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ላዕሌነ ፡ ከማሁ ፡ ይፈደፍድ ፡ ፍሥሓነ ፡ በክርስቶስ ፡ (መዝ ፡ ፸፪ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱) ።
የክርስቶስ ፡ መከራ ፡ በኛ ፡ እንደበዛ ፡ መጠን ፡ እንድም ፡ (ብዝኀ ፡ ሕማሙ ፡) እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ በክርስቶስ ፡ ደስታ ፡ ይበዛልና ።

፯ ፡ ወእመኒ ፡ ሐመምነ ፡ ከመ ፡ እንትሙ ፡ ትድኀኑ ፡ (ም ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯) ።
መከራም ፡ ብንቀበል ፡ እናንት ፡ ከመከራ ፡ ነፍሱ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ወትትፈሥሑ ።
እናንተን ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ተፈሣሕነ ፡ ንሕነ ፡ ከመ ፡ እንትሙ ፡ ትትፈሥሑ ።
እኛም ፡ በመከራው ፡ ደስ ፡ ቢለን ፡ እናንተንም ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

እንድም ፡ እኛ ፡ ወደመከራው ፡ ገብተን ፡ ከመከራው ፡ ወጥተን ፡ ጸጋውን ፡ አግኝተን ፡ ደስ ፡ ቢለንም ፡ እናተም ፡ ወደመከራው ፡ ገብታችሁ ፡ ከመከራው ፡ ወጥታችሁ ፡ ጸጋውን ፡ አግኝታችሁ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወትጸንኡ ፡ በትዕግሥቱ ፡ ለውእቱ ፡ ሕማም ፡ ዘቦቱ ፡ ነሐምም ፡ ንሕነኒ ።
መከራውን ፡ በመታገሥ ፡ ብንጸናም ፡ እናንተ ፡ እኛ ፡ ታግሠን ፡ የተቀበልነውን ፡ መከራ ፡ በመታ ገሥ ፡ ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፯ ፡ ወትውክልትነኒ ፡ ጽኑዕ ፡ በእንቲአክሙ ።
እናንተን ፡ ስለማስተምር ፡ ስለናንት ፡ ተስፋችን ፡ (ፍጹም) ፡ የተረጻ ፡ ነው ። ጽኑሕ ፡ ይላል ፡ ዋጋችን ፡ ይቆየናል ።

ወበከመ ፡ ኅረይክሙ ፡ ሕማመነ ፡ ከማሁ ፡ ተኀብሩ ፡ በፍሥሓነኒ ።
በመከራም ፡ እንደመሰላችሁን ፡ በክብርም ፡ ትመስሉናላችሁ ።

፰ ፡ ወእፈቅድ ፡ ታእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ በከመ ፡ ሐመምነ ፡ በዕስያ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫) ።
ሐመምን ፡ ሐመምን ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ግን ፡ ያውቅልሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፤
ወንድሞቻችን ፤ በእስያ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበልን ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ፡ ይህስ ፤ ያንዱን ፡ ላንዱ ፡ አያመጣም ፡ ብሎ ፡ በእስያ ፡ በተቀበልነው ፡ መከራ ፡ እንደመሰላችሁን ፡ በክብርም ፡ እንድትመ ስሉን ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ።

www.zeyeneta.com

እሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእምላነ ፡ ኃይልነ ፡ አመንደቡነ እስከ ፡ ቀበጽናሃ ፡ ሰሕይወትነ ፡ ወአጥባዕነ ፡ ሰሞቲት ። ወሕይወት ፡ እንናራሰን ፡ ማለትን ፡ ትተን ፡ እንሞታለን ፡ በማለት ፡ እስክንጸና ፡ ድረስ ፡ ደርሰን ፡ ኩሎችን ፡ የወጣ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አጽንተውብናልና ።

ኩሙ ፡ ኢንትአመን ፡ በርእስነ ፡ ዘእንበለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘያሐይዎሙ ፡ ሰምውታን ። ሙታን ፡ ሕሊናን ፡ ትንሣኤ ፡ ሕሊና ፤ ሙታነ ፡ ሥጋን ፤ ትንሣኤ ፡ ሥጋ ፡ በሚያስነሣቸው ። በእግዚአብሔር ፡ አንጂ ፡ በራሳችን ፡ አንዳንተማመን ፡ (ሐተታ) ፤ ፍጡር ፡ የእድሜውን ፡ ልክ ፡ ወውቃሰሁ ፡ ግሰት ፡ አሞታለሁም ፡ እለማለት ፡ በራስ ፡ መተማመን ፡ ነውና ።

፤ ፡ ዘእድኃንነ ፡ እመጠነዝ ፡ ሞት ።
ከዚህን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ ባዳነን ።

ወዓዲ ፡ ኪየሁ ፡ ንትአመን ፡ ክመ ፡ ያድኅነነ ። (ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፡)
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ከሚመጣው ፡ መከራ ፡ እንዲያድነን ፡ እናምናለን ።

እንዘ ፡ ትረድኡነ ፡ አንትሙኒ ፡ በጸሎትክሙ ።
በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ እናንተ ፡ እያዘናችሁልን ፡

፲፩ ፡ ከመ ፡ ንርከብ ፡ ሞገሰ ፡ በጸሎተ ፡ ብዙኃን ።
ባንድነት ፡ ማኅበር ፡ በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ ድኅነትን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ እንዘ ፡ ትረድኡነ ፡ በጸሎት ክሙ ፡ ላለው ፡ (ሐተታ) ፡ ፍጹሙ ፡ ስለትሕትና ፡ መጣንያኑን ፡ ትረድኡነ ፡ አለ ፡ አስተብቊዖ ፡ ሰማስ ተግር ፡ ለማለበም ፡ ጸሎተ ፡ ማኅበር ፡ ይጠቅማልና ።

ወአንትሙኒ ፡ ትትአኩቱ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ።
እናንተም ፡ በለው ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ለመመስገን ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ሰራሳቸው ፡ ተጠቅመው ፡ መምህሮቻቸውን ፡ ይጠቅማሉ ፡ ተብላችሁ ።

፲፪ ፡ አስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትምክህትነ ።
መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ።

ወሰምዓ ፡ ግእዛንነ ፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ፡)
የነጻነታችንም ፡ ምስክር ፡ ይህች ፡ ናትና ፤ እንድም ፡ ትምክህትነ ፡ ስምዓ ፡ ግዕዛንነ ፡ የነጸነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ ፡ እሰ ፡ ሃይማኖት ፡ ናትና ፡ ዓዲ ፡ ንትአመን ።

በምሕረቱ ፡ ወበተመይጦቱ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ። እንድም ፡ በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ የነፃነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ እለ ፡ ጸሎት ፡ ናትና ፡ ንርከብ ፡ ሞገሰ ፡ በጸሎተ ፡ ብዙኃን ፡ ላለው ፡ ወበጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውን ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ማንሻ ።

ወበ፫ጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውን ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወኢኮነ ፡ በትምህርተ ፡ ሥጋ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ የነጻነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ እለ ፡ ወንጌል ፡ ናትና ፡ እንሶሰውን ። እንድም ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ትምህርት ፡ አፊትን ፡ ያይደለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ኖርነ ።

ወፈድፋደስ ፡ በኀቤክሙ ።
ይልቁንም ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ እለ ፡ ወነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ዓመተ ፡ ወስደስተ ፡ አውራኃ ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ ።)
ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ኑሩዋልና ። እንድም ፡ ኹለት ፡ ክታብ ፡ ጽፏልና ።

እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትምክህትነ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ መመኪያችን ፡ የነፃነታችን ፡ ምስክር ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ እለ ፡ ማስተማር ፡ ዋጋ ፡ አለመብላት ፡ ናትና ።

ወበጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውን ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወኢኮነ ፡ በትምህርተ ፡ ሥጋ ።
እንበላበት ፡ እንጠጣበት ፡ ብለን ፡ ያይደለ ፤ በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በክንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በክንቱ ፡ ሀቡ ፡ ባለው ፤ ዋጋ ፡ ባለመብላት ፡ ኖርነ ።

ወፈድፋደስ ፡ በኀቤክሙ ።
ይልቁንም ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ እለ ፡ ከሌላ ፡ የመጣለትን ፡ እየበላ ፡ እስተምሩዋቸዋልና ። ወባዕደስ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሠጥኩ ፡ ወነሣእኩ ፡ ስሲሳይየ ፡ ክመ ፡ እትለአክሙ ፡ ወእመሂ ፡ ሀሎኩ ፡ ኀቤክሙ፡ እተሰቈጥ ፡ ንዋየክሙ ፡ ወኢተአድወተኒ ፡ ዛቲ ፡ ፍሥሓየ ፡ በደወለ ፡ እካይያ ፡ ብሎ ፡ እሁን ፡ እንዲያ መጣው ፡ (፪ኛ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።)

www.zeyeneta.com

፲፫ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘንጽሕፍ ፡ ጎቤክሙ ። የማታውቁትን ፡ የማትረዱትን ፡ የምንጽፍላችሁ ፡ አይደለምና ።
ዘእንበለ ፡ ዘታነብቡ ፡ ወዘተአምሩ ፡ ወዘይትዓወቀክሙ ። የምትመለከቱትን ፡ የምታውቁትን ፡ የሚረዳችሁን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘንጽሕፍ ፡ ጎቤክሙ ። እንድም ፡ ይህን ፡ እደርጉልን ፡ ብለን ፡ የምንጽፍላችሁ ፡ የለምና ።
ዘእንበለ ፡ ዘታነብቡ ፡ ወዘተአምሩ ፡ ወዘይትዓወቀክሙ ። የምትመለከቱትን ፡ የምታውቁትን ፡ የምትረዱትን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወእንዘ አመን ፡ ከመ ፡ ለዝሉፉ ፡ ተአምርዎ ፡ ለዝንቱ ። ይህንም ፡ ፈጽሞ ፡ እንድታውቁ ፡ እምናለሁ ።

፲፬ ፡ በክመ ፡ አእመርክሙነ ፡ እምእሐዱ ፡ ገጽ ። ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾናችሁ ፡ እንዳወቃችሁን ፡ መጠን ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ ዘንድ ፤ እንድም ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾነን ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ መጠን ፡ እንዳወቃችሁን ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ እንድታውቁት ፡ እምናለሁ ፡ ወከግሁ ፡ ማንሻ ።
ወከግሁ ፡ እንትሙሂ ፡ ምክህነ ፡ በፅሰተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።)
ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾናችሁ ፡ እንዳወቃችሁን ፡ መጠን ፡ እኛ ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ እናንተም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚመጣበት ፡ በፅሰተ ፡ ምጽአት ፡ መመኪያችን ፡ ናችሁ ፡ እኮ ፡ ሐምሰ ፡ መካልየ ፡ ወሀብክኒ ፡ ወናሁ ፡ ኀምስ ፡ መካልይ ፡ ዲቤሆን ፡ ዘረባሕኩ ፡ ብለን ፡ ስናበረ ከታችሁ ። (ማቴ ፡ ፭፩ ፡ ፭-፭፬ ።)

፲፭ ፡ ወበዝንቱ ፡ ፍሥሓ ፡ ተአሚንየ ፡ መከርኩ ፡ እምጸአ ፡ ኀቤክሙ ። በዚህም ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ እውቂ ፡ ወደናንት ፡ ልመጣ ፡ ወደድሁ ።
በቀዳሚ ፡ ከመ ፡ ትርከቡ ፡ ጸጋ ፡ ምክዕቢተ ። (በቀዳሚን ፡ አቆይ) ፡ እጽፍ ፡ ከብር ፡ ታግኙ ፡ ዘንድ ፡ አሰ ፡ ዅሉት ፡ ከታብ ፡ መጻፍ ፡ ማስተማር ፡ ዋጋ ፡ አሰመብላት ።

፲፮ ፡ ወእሑር ፡ መቄዶንያ ። (በቀዳሚ ፡ እሑር ፡ መቄዶንያ ፡ ብለሀ ፡ ግጠም) ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ እፈድ ፡ ዘንድ ።
ወእምህየ ፡ እመጥ ፡ ኀቤክሙ ። ከዚያም ፡ ወደናንት ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ።
ወአንትሙ ፡ ትፈንዉኒ ፡ ለምድረ ፡ ይሁዳ ። እናንተም ፡ ወደምድረ ፡ ይሁዳ ፡ ሸኝታችሁ ፡ ትሰዱኝ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ ዘንተ ፡ እንከ ፡ ዘመከርኩ ፡ ቦኑ ፡ እንጋ ፡ ከመ ፡ አብድ ፡ ዘገበርኩ ። ይህን ፡ የመከርሁ ፡ በውኑ ፡ ያላዋቂ ፡ ሥራ ፡ ሠራሁን ። እንድም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ኾንኩን ።
ወቦኑ ፡ ዘእመከር ፡ ሕገ ፡ ሰብእ ፡ እመክር ። ባስተምርስ ፡ የሰዉ ፡ ሥርዓት ፡ አስተምራለሁን ፡ ። እንድም ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አስተምራለሁን ።
እስመ ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ነገራችሁ ፡ እውነት ፡ ቢኾን ፡ እውነት ፡ ሐሰት ፡ ቢኾን ፡ ሐሰት ፡ ሲኾን ፡ ይገባል ፡ እኮን ፡ (አለ) ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ትሉት ፡ እንደኾነ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ትሉትም ፡ እንደኾነ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ልትሉት ፡ ይገባል ፡ እኮን ።

፲፰ ፡ ጸድቅ ፡ እግዚአብሔር ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
ልጀን ፡ በሥጋ ፡ ወሰኘ ፡ አሰዳለሁ ፡ ያሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።
ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ፡ ቃልነ ። የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ የምናስተምረውም ፡ ትምህርት ፡ ሐሰት ፡ አይደለም ።
ወኢ ተቶስሐ ፡ እወ ፡ ወእልቦ ። እንድ ፡ ጊዜ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማሰት ፡ አልተቀላቀለበትም ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንሕነ ፡ ሰበክነ ፡ ለክሙ ፡ አነ ፡ ጸወጽስ ፡ ወሰልዋናስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ኢክነ ፡ እወ ፡ ወእልቦ ።
(ዘንሕነ ፡ ጸወ ሉስ ፤ ወሰልዋናስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡) ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፤ ስልዋኖስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ያስተ

www.zeyeneta.com

ምርኖችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብሂል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ አይደለምና ።

ጸዕሙ ፡ አወ ፡ ኮነ ፡ በአንቲአሁ ።

ስለርሱ ፡ ወኢተቀስፈ ፡ አወ ፡ ወአልቦ ፡ እንጸልሁ ። የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ አጂ ።

ፍ ፡ እስመ ፡ ሙሉ ፡ ዘአስፈለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ በክርስቶስ ።

(ዘአስፈለ ፡ በክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ በክርስቶስ) ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ያናገረው ፡ ተስፋ ፡ በክርስቶስ ፡ ተፈጽሟልና ።

ወበአንተዝ ፡ ዐቂ ፡ ወበእንቲአሁ ፡ አሚነ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሀብ ። (ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ፡)

ዐቂና ፡ በእንቲአሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ስለዚህ ፡ በሱ ፡ አምነን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (አሚነ፡ ስብሐት) ፡ ምስጋና ፡ ያለው ፡ አዎታ ፡ (ስብሐተ ፡ አሚን) ፡ አዎታ ፡ ያለው ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ። አንድም ፡ ዐቂና ፡ በእንቲአሁ ፡ በየራሱ ፤ አሱ ፡ ስለካስልን ፡ በሱ ፡ አምነን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ያለው ፡ አዎታ ፤ አዎታ ፡ ያለው ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ።

ፍ፩ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዘያጸንዓን ፡ ምስሌክሙ ፡ በአሚን ፡ በክርስቶስ ።

ከእናንት፡ ጋራ ፡ በክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ የሚያጸናን ፡ አሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ነህብ ፡ ላለው ።

ዘቦቱ ፡ ቀብዐነ ።

አኛን ፡ ያከበረበት ።

ወዐተብነ ፡ (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፯ ።)

ከኢአማንያን ፡ የለየበት ፡ ራሱን ፡ ያስመሰለበት ።

ጽፍ ፡ ወወህበነ ፡ ዐረቦነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።)

የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፈለማ ፡ በልቡናችን ፡ የሣለበት ።

ጽ፫ ፡ ወአነ ፡ አስምዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በአንተ ፡ ነፍስየ ። (ም ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ፡ ሮሜ ፡፩፡ ፱ ።)

እኔ ፡ በሰውነቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምስክር ፡ እጠራበታለሁ ።

ከመ ፡ በምሒከ ፡ ዚአከሙ ፡ ኢመጸእኩ ፡ ቆሮንቶስ ።

ወደቆሮንቶስ ፡ ያልመጣሁ ፡ ለናንት ፡ በማዘን ፡ በመራራት ፡ እንዲኾነ ፡ (አለ) ፡ በነፋስ ፡ እንዳልሰቀላችሁ ፤ በሌጌዎን ፡ እንዳልነጻችሁ ፡ እንደኾነ ።

ጽ፬ ፡ ወአኮስ ፡ ዘናጌብረከሙ ፡ ትእመኑ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፤ ያላመናችሁ ፡ ኾኖ ፡ አንግዲህ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ የምንሳችሁ ፡ አይደለም ።

ጸዕሙ ፡ ንረድአከሙ ፡ ለገቢረ ፡ ፍሥሓከሙ ።

ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አናጸናችኋለን ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ በአሚን ፡ ቆምክሙ ።

በሃይማኖት ፡ ጸንታችኋልና ።

ወአዋዳዕከሙ ፡ በሃይማኖት ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፱ ።)

በሃይማኖት ፡ ጸንታችሁ ፡ መከራውን ፡ ስመቀበል ፡ ጨከናችኋልና ።

ምዕራፍ ፪ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ ወዘንተ ፡ አንክ ፡ መክርኩ ፡ በነፍስየ ፡ ኢይምጻእ ፡ ትኩዝየ ፡ ኀቤክሙ ።

ያዘንሁ ፡ የተከዝሁ ፡ ኾኜ ፡ ወደናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ በልቡናዬ ፡ ይህን ፡ መከርሁ ።

፪ ፡ ወአመሰ ፡ አነ ፡ አተኩዝኩክሙ ፡ መኑ ፡ ያስተፈሥሐኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአነ ፡ አተኩዝክዎ ።

ትኩዝየን ፡ ይዞ ፡ አንተ ፡ ሌላውን ፡ ብታሳዝን ፡ አንጂ ፡ አንተን ፡ ማን ፡ ያሳዝንሃል ፡ ትሉኝ ፡ አንደኾነ ፡ ባሳዝናችሁም ፡ እኔ ፡ ያሳዘንኋችሁ ፡ ማሳዘን ፡ ደስ ፡ ቢያሰኝልኝ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ደስ ፡ ያሰኝልኛል ፡ (አለ) ፡ ለአስተዋፅኦ ፡ እንድትተጉ ፤ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ እንድትፈካከሩ ፤ አነ ፡ ዘጸውሎስ፡ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፤ ግለትን ፡ እንድትተው ። ያባቴን ፡ ሚስት ፡ የነሣውን ፡ የመሐሩን ፡ ቹሎት ፡ የተሾመውን ፡ እንድትለዩ ፡ አድርጉ ። አንድም ፡ ኢይምጻእን ፡ ይዞ ፡ ብትመጣስ ፡ ባትመጣስ ፡

www.zeyeneta.com

ኃዘኑ ፡ ቀርቶልናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ባሳዘናችሁም ፡ ያሳዘንኋችሁ ፡ እኔ ፡ ደስ ፡ ባሰኛችሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ያለኝልኛል ።

፫ ፡ ወዘኒ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ መጺአየ ፡ ኢይርከበኒ ፡ ኃዘን ፡ በዘህለወኒ ፡ እትፈሣሕ ፤ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፭፩)
ይህንም ፡ የጻፍኩላችሁ ፡ ወደናንተ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ስለደስታዬ ፡ ፈንታ ፡ ኃዘን ፡ እንዳያገኘኝ ፡ ነው

ተአሚንየ ፡ በሁልክሙ ፡ ከመ ፡ ፍሥሓ ፡ ዚአየ ፡ ዘሁልክሙ ፡ ውእቱ ።
የኔ ፡ ደስታ ፡ የናንት ፡ ደስታ ፡ የኔ ፡ ኃዘን ፡ የናንት ፡ ኃዘን ፡ እንደኾነ ፡ ወውቂ ፡ ኢይርከቢኒ ።

፬ ፡ እስመ ፡ እምነ ፡ ብዙኅ ፡ ሕማም ፡ ወኀዘነ ፡ ልብ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ዘንተ ፡ በብዙኅ ፡ እንብዕ ።
ከብዙ ፡ መከራ ፡ ከብዙ ፡ ኃዘን ፡ የተነሣ ፡ ይህንን ፡ በብዙ ፡ ዕንባ ፡ ጽፌላችኋለሁ ፡ ፡ (አለ) ፡ ቀለሙን ፡ በዕንባው ፡ በጥብጦ ፡ ጽፎታልና ። አንድም ፡ እያለቀሰ ፡ ጽፎታልና ።

ወአኩ ፡ ከመ ፡ ትተክዙ ።
እንዲህም ፡ ማለቴ ፡ ታዝኑ ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ።

ጸዕሙ ፡ ከመ ፡ ታእምሩ ፡ እፍቀሮትየ ፡ ከመ ፡ ፈድፋደ ፡ አፈቅረክሙ ።
ፈጽሞ ፡ እንድወዳችሁ ፡ ጽና ፡ ፍቅሬን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወዘኒ ፡ አተከዘኒ ፡ እኩ ፡ ኪያየ ፡ ዘያቈክዝ ።
እኔንም ፡ ያሳዘነ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ ያሳዘነ ፡ አይደለም ።

ጸዕሙ ፡ ሁልክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ እሐዱ ፡ ጎብር ።
ከናንተ ፡ አንዱ ፡ ላይቀር ፡ ኹላችሁንም ፡ ያሳዘነ ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡ ከናንተ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከሚኾን ፡ ከቢጽ ፡ ሐላዊ ፡ በቀር ፡ ኹላችሁንም ፡ ያሳዘነ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወይእዜኒ ፡ ኢያክብድ ፡ ቃልየ ፡ ላዕሌክሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፩ ።)
አሁንም ፡ ሥርዓት ፡ እላጸናላችሁም ፡ ነገር ፡ እላበዛባችሁም ።

፮ ፡ ተአክሎ ፡ ለዘከመዝ ፡ ዛቲ ፡ ተግሣጽ ፡ እንተ ፡ ረከበቶ ፡ እምብዙኃን ።
(እንተ ፡ ረከበቶ ፡ እምብዙኃን ፡ ተግሣጽ ፡ እምብዙኃን ፡ ብለህ ፡ ግጠም) ፡ እንዲህ ፡ ላለው ፡ ሰው ፤ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተነሣ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ያገኘው ፡ መከራው ፡ ትቢቃዋለች ፤ መለየቱ ፡ ከብዙ ፡ ነውና ፡ ሲለዩት ፡ ብዙ ፡ ኾነው ፡ ነውና ።

፯ ፡ ወሚዲ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትስረዩ ፡ ሎቱ ፡ ወታስተፍሥሕም ፡
ዳግመኛ ፡ ታርቃችሁ ፡ ደስ ፡ ልታሰኙት ፡ ይገባል ።

ከመ ፡ ኢይሰጠም ፡ እምብዝኅ ፡ ኃዘን ፡ ዘከመዝ ።
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ባመጣው ፡ ኃዘን ፡ ባሕር ፡ እንዳይሰጠም ።

፰ ፡ ወበእንተዝ ፡ እስተበቍዐክሙ ፡ እጽንዑ ፡ ተፋቅሮ ፡ ምስሌሁ ።
ስለዚህ ም ፡ ታረቁት ፡ ብየ ፡ እግልዳችኋለሁ ።

፱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ እእምር ፡ ግዕዘክሙ ፡ ለእመሁ ፡ በሁሉ ፡ ትትኤዘዙኒ ።
ስለዚህም ፡ ለዩት ፡ ብላችሁ ፡ ትለዩት ፡ እንደኾነ ፡ ታረቁት ፡ ብላችሁ ፡ ትታረቁት ፡ እንደኾነ ።

እው ፡ አልቦ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።)
እንድ ፡ ጊዜ ፡ ታረቁት ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዩት ፡ ይለናልን ፡ ብላችሁ ፡ አይኾንም ፡ ትሉኝም ፡ እንደኾነ ፡ ግብራችሁን ፡ እውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጻፍኩላችሁ ።

፲ ፡ ወእመቦ ፡ ዘሰረይክሙ ፡ ሎቱ ፡ እነሂ ፡ ሰረይኩ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወእመኒቦ ፡ ዘኅደግሙ ፡ ሎቱ ፡ ኅደጉ ፡ ሰልየ ፡ በእንቲአክሙ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።)

እንታረቀውስ ፡ እንታረቀውስ ፡ እንተ ፡ ያለህ ፡ በፈልጵስዮስ ፡ እኛ ፡ ያለን ፡ በቆሮንቶስ ፡ ግንን ፡ ይዘን ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ የናንት ፡ መተው ፡ የኔ ፡ መተው ፡ የናንት ፡ መታረቅ ፡ የኔ ፡ መታረቅ ፡ ነው ።

እንድም ፡ እሱ ፡ ታርቆ ፡ የፅርቅ ፡ ዳረጎት ፡ ይልክብናል ፡ እንዳይሉት ፡ እኔስ ፡ የምተወው ፡ እናንት ፡ ብትተውት ፡ ነው ፡ የምታረቀውም ፡ እናንት ፡ ብትታረቁት ፡ ነው ።

በገጹ ፡ ለክርስቶስ ።
(አጸንው ፡ ተፋቅሮ ፡ ምስሌሁ ፡ በገጹ ፡ ለክርስቶስ) ፡ በክርስቶስ ፡ ግብር ፡ ታረቁት ፡ ብዬ ፡ እግልጻችኋለሁ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ሳጥናኤ ፡

፲፩ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ሰይጣን ። (ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፴፩ ።)
(በገጹ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ሰይጣን ፡ ብለህ ፡ ግጠም) ፡ በክርስቶስ ፡ ጻንነት ፡ ወንድ ፡ ግችነን ፡ ሰይጣን ፡ እንዳይቀማን ።

www.zeyeneta.com

ዘአኩ ፡ ንስሐቶ ፡ ሕሊናሁ ።
የሰይጣንን ፡ ነገሩን ፡ የምንስተው ፡ አይደለምና ፡ ከወንድሞቻችን ፡ አንዱንም ፡ አንዱን ፡ እየነጠቀ ፡ ወደገዩነም ፡ ለማውረድ ፡ እንደኾነ ፡ አንድም ፡ ቢመለስሳ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ግብሩን ፡ የምንስተው ፡ አይደለም ፡ ቢመለስም ፡ እንለየዋለን ።

ወበጸሐየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ውስተ ፡ ትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፮ ።)
ለእሙሁ ፡ በሎሌ ፡ ትትኤዘዙኒ ፡ አሁ ፡ አልቦ ፡ ብሎ ፡ ኀበርና ፡ እንታዘዝህስ ፡ አንታዘዝህስ ፡ አንተ ፡ ያለህ ፡ በፊልጵስዮስ ፡ እኛ ፡ ያለን ፡ በቆሮንቶስ ፡ ብትመጣ ፡ አልነበረምን ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እንዳል መጣስ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ጢሮአዳ ፡ በደረሰው ፡ ጊዜ ።

ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍናተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።)
ትምህርት ፡ ተሰጠኝ ፡ ዕዝነ ፡ ስማዕያን ፡ ተከፈተልኝ ።

፲፪ ፡ ወኢረከብኩ ፡ ዕረፍተ ፡ ለነፍስየ ።
ለሰውነቴም ፡ ዕረፍትን ፡ አላገኘሁም ።

እስመ ፡ ኢረከብክዎ ፡ ለቲቶ ፡ እኁየ ።
ስማዕያን ፡ በዝተው ፡ እኔ ፡ በቀኝ ፡ ብኾን ፡ እሱ ፡ በግራ ፡ እኔ ፡ በግራ ፡ ብኾን ፡ እሱ ፡ በቀኝ ፡ ኾኖ ፡ የሚያስተምርልኝ ፡ ቲቶ ፡ ወንድሜን ፡ አላገኘሁትምና ።

ወተፈለጥኩ ፡ እምኔሁ ።
ከሱ ፡ ተለይቼአለሁና ፡ ኢረከብኩ ።

ወሐርኩ ፡ መቄዶንያ ።
(በጸሐየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ሐርኩ ፡ መቄዶንያ ፡ ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍናተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።)

ወበጸሐየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ውስቴ ፡ ትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ።
ዉሮአዳ ፡ ደርሼ ፡ መቄዶንያ ፡ በኼድኩ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ተሰጠኝ ፤ ዕዝነ ፡ ስማዕያን ፡ ተከፈተልኝ። አንድም ፡ በቀዳሚ ፡ ኢሐር ፡ መቄዶንያ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያውስ ፡ ቢኾን ፡ በፊት ፡ ወደኛ ፡ ባልመጣህም ፡ ነበር ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ በፊት ፡ እንዳልመጣስ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ጢሮአዳ ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ፡ ፍናት ፡ ለኀበ ፡ አዙሁ ፡ አንቀጽ ፡ ዘመንገስ ፡ ወላዲሁ ፡ የሚባል ፡ ጌታ ፡ ተገለጠልኝ ፡ (አፈ ፡ ወር) ።

ወኢረከብኩ ፡ ዕረፍተ ፡ ለነፍስየ ።
ለሰውነቴም ፡ ዕረፍትን ፡ አላገኘሁም ።

እስመ ፡ ኢረከብክዎ ፡ ለቲቶ ፡ እኁየ ።
በማሉ ፡ የሚያስታርቅልኝ ፡ ከታብ ፡ ወስዶ ፡ የሚሰጥልኝ ፡ ቲቶ ፡ ወንድሜን ፡ አላገኘሁትምና ።

ኢረከብኩ ፡ ወተፈለጥኩ ፡ እምኔሁ ።
ዘሱ ፡ ተሰይቻለሁና ።

ወሐርኩ ፡ መቄዶንያ ።
(ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍናተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐርኩ ፡ መቄዶንያ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።)
ፍናት ፡ ለኀበ ፡ አዙሁ ፤ እንቀጽ ፡ ዘመንገለ ፡ ወላዲሁ ፡ የሚባል ፡ ጌታ ፡ በአምሳለ ፡ መኩንን ፡ መቄዶንያዊ ፡ ተገልጠ ፡ ኀልፍ ፡ እንተ ፡ መንገሌን ፡ ለመቄዶንያ ፡ ወነዓ ፡ ርድአነ ፡ አለኝ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ፡) (ሐርኩ ፡ መቄዶንያ) ፡ ወደመቄዶንያ ፡ ሐድሁ ።

፲፬ ፡ እኩት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘዘልፈ ፡ ደወቅበነ ፡ በእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹልጊዜ ፡ አናንተንም ፡ እኔንም ፡ የሚጠብቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ወተዐውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ መዓዛ ፡ አእምሮቱ ፡ በሎሌ ፡ በሐመርቅ ።
(ተዐውቀ ፡ በሎሌ) ፡ የዕውቀቱ ፡ ዕውቀት ፡ ብሪቱ ፡ መዓዝን ፡ በኛ ፡ ለኹሉ ፡ እንዲታወቅ ፡ ያደረገ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ መዓዛ ሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንሕነ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
ፅንጹቅ ፡ በመዓዛው ፡ እንዲታወቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የክርስቶስ ፡ መታወቂያው ፡ እኛ ፡ ነንና ።

በእንተ ፡ እለ ፡ ይድኅኑ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።)
አምነው ፡ ለሚድኑ ፡

ወእለሂ ፡ ይትኃጕሉ ።
ከደው ፡ ስለሚጐዱም ። ኹለቱም ፡ አርእስት ፡ ነው ፡ ለኹለቱም ፡ ያመጣል ።

www.zeyeneta.com

፲፯ ፡ እስመ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ መዓዛ ፡ ሞት ፡ ለሞት ።
ሞት ፡ ሊኾንባቸው ፡ ሞትን ፡ የሚያመጣ ፡ እውቅት ፡ የሚሰጣቸው ፡ እሉና ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይትጎሥሉ ወቦ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ።
ድኅነት ፡ ሊኾንላቸው ፡ ድኅነትን ፡ ሊያመጣላቸው ፡ ድኅነትን ፡ የሚያመጣ ፡ እውቀት ፡ የሚሰጣቸው እሉና ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይድኅኑ ፡ ላለው ።
ወመኑ ፡ ዘይደልዎ ፡ ዝንቱ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፬ ።)
ይህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ያለው ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ እንድም ፡ (ወለመኑ ፡ ይደሉ ፡ ዝንቱ) ፡ ይህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ያለው ፡ ለማን ፡ ይገባል ፡ (ወመኑ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዝንቱ) ፡ ለዚህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ላለው ፡ የሚቢቃ ፡ ማነው ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይትሜየንዎ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በካልእ ፡
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ሚተነኰሉ ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ አይደለንምና ።
ዳአሙ ፡ በንጽሕ ።
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ ከማለት ፡ ተከልክለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ። (እንድም) ።
እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይትሜየንዎ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በካልእ ።
አንድም ፡ ወንጌልን ፡ መባያ ፡ በማድረግ ፡ እንደሚተነኰሉ ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ አይደለንምና ።
ዳዕሙ ፡ በንጹሕ ።
ዋጋ ፡ ከመብላት ፡ ተከልክለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ።
ወከመ ፡ ዘመጽአ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ንኑግር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲፪)
ወበሳድስ ፡ ወርኀ ፡ ተፈነወ ፡ ገብርኤል ፡ መልአከ ፡ አምላበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ እንደመጣ ፡ አንደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፤ እሱ ፡ ወይሰመይ ፡ ወልደ ፡ አግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳልተማረ ። እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እናስተምራለን ። አንድም ፡ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ ዘተፈነወ ፡ አምላበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዲል ፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡) ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ እንደመጣ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ፤ እሱ ፡ ለልየ ፡ ርኢኩ ፡ ወአነ ፡ ሰማዕኩ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ወልዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፬ ፡)ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳስተማረ ፡ እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እናስተምራለን ።
አንድም ፡ ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመጻእኩ ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ ፡ እንዲል ፡ (ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፪ ፡) ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተልኮ ፡ እንደመጣ ፡ እንደራሱ ፤ እሱ ፤ ለምንት ፡ ትብሉኒ ፡ ትፀርፍ ፡ ለእመ ፡ አቤለከሙ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አነ ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴፮ ፡) ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳስተማረ ። እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ነቱን ፡ እናስተምራለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ፡ ኢኮነ ፡ ላለው ።

ም ዕ ራ ፍ ፫ ።

፩ ፡ አኃዊነ ፡ ንአኅዝኑ ፡ ካዕበ ፡ ይእዜ ፡ ንንግርከሙ ፡ ንመድኅ ፡ ርእሰነ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲፪ ።)
ወንድምቻችን ፡ ዳግመኛ ፡ አሁን ፡ ራሳችንን ፡ እያመሰገን ፡ እንነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ (ንአኅዝኑ) ፡ እንጀ ምራለን ? ። (ነአኅዝኑ) ፡ እንጀምርን ? ።
ወቦኑ ፡ ዘንፈቅድ ፡ ከመ ፡ እልክቱ ፡ ካልአን ።
ራሳችንንማ ፡ እያመሰገን ፡ እንነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ በውኑ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደሚያመሰግኑ ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ የምንሻው ፡ ነገር ፡ አለን ።?
እስከ ፡ ንጽሕፍ ፡ ጎቤከሙ ፡ በእንቲኣነ ፡ መጽሐፈ ።
እንድም ፡ ራሳችንን ፡ አመሰግንን ፡ ይህን ፡ እድርጉልን ፡ ብለን ፡ ከታብ ፡ እሰከመጻፍ ፡ ድፈስ ፡ ደር ሰን ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ የምንሻው ፡ ነገር ፡ አለን ፡
አው ፡ ከመ ፡ ትጽሐፉ ፡ እንትሙ ።
ወይስ ፡ እናንተ ፡ ትጽፉልን ፡ ዘንድ ፡ የኛማ ፡ መምህሮቻችን ፡ አዋቆች ፡ ጠንቃቆች ፡ ናቸው ፡ ብላችሁ ፡
፪ ፡ ወለነሰ ፡ መጽሐፍነ ፡ አንትሙ ፡ ይእቲ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፪ ።)
የኛስ ፡ መታወቂያችን ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ።

www.zeyeneta.com

መጽሐፍት ፡ ውስተ ፡ ልብነ ።
እናንት፡ በልቡናችን ፡ ታውቃችኋል ። ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ ይላል ፡ በልቡናችሁ ፡ ታውቀናል ።
ወትትዓወቅ ፡ ወያነብባ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።
ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ፡ ይመለከታችኋል ።

፫ ፡ ወየአምሩክሙ ፡ ከመ ፡ መልእክተ ፡ ክርስቶስ ፡ አንትሙ ፡ እንተ ፡ ተልእክናሃ ።
እኛ ፡ የፋቅናት ፡ የራመምናት ፡ የጻመጽናት ፡ የክርስቶስ ፡ የደብዳቤው ፡ መጻፊያ ፡ እንደኾናችሁ ፡
ሰው፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ፡ (አለ) ፡ እኛ ፡ ያስተማርናችሁ ፡ ያሳመናችሁ ፡ ያጠመቅናችሁ ፡ ያቈረብናችሁ፡
የክርስቶስ ፡ ማደሪያ ፡ እንደኾናችሁ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ።
ወጽሕፍት ፡ ይእቲ ።
ጽሕፈቱን ፡ ተናግሮ ፡ መጻፊያውን ፡ አልተናገረም ፡ ነበርና ፡ መጻፋችሁም ።
ወእኩ ፡ በማየ ፡ ሕመት ።
በጥቂር ፡ ቀለም ፡ እይደለም ።
ዘእንበለ ፡ በመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ።
የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ በሚኾን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀለምነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወዘኢኮነ ፡ ጽሌ ፡ ዘዕብን ። (ዘፀአ ፡ ፳፬ ፡ ፲፪ ።)
በደንጊያም ፡ ስሌዳነት ፡ አይደለም ።
ዘእንበለ ፡ ጽሌ ፡ ልብ ፡ ዘሥጋ ።
የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ በምትኾን ፡ በነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ሰሌዳነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እንድም ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የምትኾን ፡ የደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕይወት ፡ በምትኾን ፡ በነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ሰሌዳነት፡
ነው ፡ እንጂ ።

፬ ፡ ወብነ ፡ ባሕቱ ፡ ከመዝ ፡ ተስፋ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፮ ።)
በክርስቶስ ፡ ስላመነ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ስላስተማርነ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

፭ ፡ ወኢይደልወነ ፡ ነሐሊ ፡ ለሊነ ፡ ለርእስነ ፡ ወኢምንተኒ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ራሳችንን ፡ ልናመሰግን ፡ አይገባንም ።

፮ ፡ እስመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልነ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)
ኃይላችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ አለ ። ኃይላችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ (አንድም ፦)
ወብዙ ፡ ባሕቱ ፡ ዘከመዝ ፡ ተስፋ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ስላመነ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ስላስተማርን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።
ወኢይደልወነ ፡ ነሐሊ ፡ ለሊነ ፡ ለርእስነ ፡ ወኢምንተኒ ።
እንኪያስ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ስራሳችን ፡ ልናስብ ፡ አይገባንም ።
እስመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልነ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)
እውቅታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ (አለ) ፡ አውቆ ፡ ያደርግልናልና ። መበክሙ ፡ ብርቱ
ለኀበ ፡ ጸሐፊ ፡ ከማሁ ፡ ልብነሂ ፡ እመንገለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ (ማራ ፡ ይስ) ።

፯ ፡ ዘረሰየነ ፡ ሳእካነ ፡ ለሐዲስ ፡ ሕግ ።
ለሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ አገልጋዮች ፡ ያደረገን ።
እኩ ፡ በሕገ ፡ መጽሐፍ ።
አገልጋዮችም ፡ ያደረገን ፡ በሕግ ፡ ሥጋ ፡ በአሪት ፡ በንባብ ፤ አይደለም ።
እላ ፡ በሕገ ፡ መንፈስ ፡ (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፮ ።)
በሕገ ፡ ነፍስ ፤ በወንጌል ፤ በትሮጓሜ ፤ ነው ፡ እንጂ ።
እስመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይቀትል ።
ሕገ ፡ ሥጋ ፤ አሪት ፡ ንባብ ፤ ይጐዳልና ፡ እኩ ፡ በሕገ ፡ መጽሐፍ ።
ወመንፈስ ፡ ያሐዩ ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፷፫ ።)
ሕገ ፡ ነፍስ ፤ ወንጌል ፡ ትርጓሜ ፤ ይጠቅማልና ፡ እላ ፡ በሕገ ፡ መንፈስ ።

፮ ፡ ወሶበ ፡ ለእንታክቲ ፡ መልእክተ ፡ ሞት ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈት ፡ ባእብን ፡ ተገብረ ፡ ላቲ ፡ ስብሐት ።
በደንጊያ ፡ ስሌዳነት ፡ ስተጻፈች ፡ ለዚያች ፡ ለሕገ ፡ አሪት ፡ ክብር ፡ ከተደረገላት ።
እስከ ፡ ኢይክሉ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ነጽሮተ ፡ ገጹ ፡ ለሙሴ ፡ በእንተ ፡ ስብሐቱ ፡ ገጹ ፡ ኃላፊ ፡ (ዘፀአ ፡
፴፬ ፡ ፴ ።)
በፊቱ ፡ ኃላፊ ፡ ብርሃን ፡ ስለተሣለበት ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻላቸው ፡ እስኪኾን ፡ ድፈል ፡
ክብር ፡ ከተደረገላት ፡ (ተገልበብ ፡ ለነ ፡ ሙሴ ፡ ተገልበብ ፡ ለነ ፡ ብለውታልና) ።

www.zeyeneta.com

፫ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ይትገበር ፡ ፈድፋዶ ፡ ስብሐት ፡ ለመልእክተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ገላት ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላጸፋት ፡ ሕግ ፡ ለወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ ይደረግላት ፡ ይኾን ።

፬ ፡ ሶበ ፡ ለመልእክት ፡ እንተ ፡ ታኪንን ፡ ወታሐስብ ፡ ተገብረ ፡ ላቲ ፡ ስብሐት ፡ ብዙኅ ።
ሞትን ፡ ለምታስፈርድ ፤ ኃጢአትን ፡ ቈጥራ ፡ ቈጥራ ፡ ለምትናገር ፡ ለዚያች ፡ ለሕገ ፡ አሪት ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ ከተደረገላት ።

ሚመጠን ፡ ፈድፋዶ ፡ መልእክተ ፡ ጽድቅ ፡ ትሴባሕ ፡ ወትክብር ፡ (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።)
ሕይወት ፡ የሚገኝባት ፡ ሕገ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትክብር ፡ ይኾን ።

፲ ፡ አስከ ፡ ትከውን ፡ እንተ ፡ ተሰብሐት ፡ ከመ ፡ ዘኢተሰብሐት ፡ ሶበ ፡ ያስተዔርይዋ ፡ በዝንቱ ፡ ስብሐት ፡ ዓቢይ ።
በዚህ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ባንጸጸሯት ፡ ጊዜ ፡ ከብራ ፡ የነበረች ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ እንዳልከበረች ፡ እስከት ኾን ፡ ድረስ ።

፲፩ ፡ ሶበ ፡ ኃላፊ ፡ ዘይመጽእ ፡ ረከበ ፡ ስብሐተ ።
ኃላፊው ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ ክብር ፡ ካገኘ ።

እፎ ፡ ፈድፋዶ ፡ ዘይነብር ፡ ይረክብ ፡ ቀዋሚ ፡ ስብሐተ ።
(ዘይነብር ፡ ቀዋሚ) ፡ ባለማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረው ፡ ሕገ ፡ ወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ ያገኘ ፡ ይኾን ፡ እንድም ፡ (ኃላፊ) ፡ ይላል ፡ ኃላፊውን ፡ ሕገ ፡ አሪትን ፡ የያዘ ፡ ክብር ፡ ካገኘ ። (ቀዋሚ) ፡ ባለ ማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕገ ፡ ወንጌልንማ ፡ የያዘ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብርን ፡ ያገኘ ፡ ይኾን ፡ (ሐተታ)፡ ምነው ፡ በአሪቱ ፡ በሙሴ ፡ ግንባር ፡ ብርሃን ፡ ተሥሎበታል ። በወንጌል ፡ ቢፈቱ ፡ ብርሃን ፡ የተሣለበት ፡ የለም ፤ ስለምን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በወንጌልም ፡ የበቁት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳሉ ፡ ብርሃን ፡ ያያሉ ፡ በባሕረ ፡ ብርሃን ፡ ይዋኛሉ ፡ ያልበቁትም ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡ ረቂቅ ፡ የብርሃን ፡ ጦር ፡ ረቂቅ ፡ የብርሃን ፡ ጋሻ ፡ ሰዶላቸው ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ይገባሉና ፡ (ማሪ ፡ ይስ) ።

፲፪ ፡ ወእንዘ ፡ ብነ ፡ መጠነዝ ፡ ተስፋ ።
ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ ካለን ።

ርቱዕ ፡ ንቅረብ ፡ በገጽ ፡ ገሃደ ።
ገጸ ፡ ልቡናችንን ፡ ገልጸን ፡ ልንቀርብ ፡ ይገባናል ።

፲፫ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ። (ዘፀአ ፡ ፴፬ ፡ ፴፫ ፡ ፴፭)
(አኮ ፡ ከመ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል) ፡ ገጸ ፡ ልቡናችንንም ፡ ገልጸን ፡ መቅረባችን ፡ ሙሴ ፡ ፊቱን ፡ እንዳያዩት ፡ እንደሚሸፈንባቸው ፡ እንደ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ አይደለም ።

፲፬ ፡ ወባሕቱ ፡ ተጸለለ ፡ ልቦሙ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።
እስራኤልማ ፡ እንጂ ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻለው ፡ እስቲኾን ፡ ድረስ ፡ ልቡናቸው ፡ ደነቆረ ፡ ተገልበብ ፡ ስን ፡ ብስውታልና ።
(እንድም ፡ መልስ) ።

ወእንዘ ፡ ብነ ፡ መጠነዝ ፡ ተስፋ ።
ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ ሲኖረን ፡ ከተገኘን ።

ርቱዕ ፡ ንቅረብ ፡ በገጽ ፡ ገሃደ ።
ፊት ፡ ለፊት ፡ በባለሟልነት ፡ ልንቀርብ ፡ ይገባል ።

ወእከ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ።
ፊት ፡ ለፊት ፡ በባለሟልነት ፡ መቅረባችንም ፡ እስራኤል ፡ እንዳያዩት ። ፊቱን ፡ ይሸፍንባቸው ፡ እንደነበረ ፡ እንደሙሴ ፡ አይደለም ። (ሐተታ) ፡ ሙሴ ፡ ኹለቱን ፡ ፎቱን ፡ መጋረጃ ፡ ገብቶ ፡ ከዚያ ፡ አያልፍም ፡ ነበረ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ የምንገባ ፡ ኾነናልና ፡ ሙሴ ፡ በስውረተ ፡ አብን ፡ በሥጥቀተ ፡ዕፅ ፡ ያይ ፡ ነበር ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በኩነት ፡ ነውና ።

ወባሕቱ ፡ ተጸለለ ፡ ልቦሙ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።
እስራኤል ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻላቸው ፡ እስቲኾን ፡ ድረስ ፡ ልቡናቸው ፡ ደንቍሯልና ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ላለው ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ግላ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፡ ብሉይ ።
በብሉይ ፡ በአሪት ፡ ድንቁርና ፡ ጸንቶ ፡ ስለነበረ ።

አምጣነ ፡ ተነበ ፡ ወኢተክሥተ ።
ስለተነበበ ፡ ስላልተተረጐመ ። ተነበ ፡ ስላልተተረጐመ ፡ የተነበበ ፡ ያህል ። ያልተተረጐመ ፡ ያህል ።

www.zeyeneta.com

እስከ ፣ እጽርያ ፣ ከርስቶስ ። (ሮሜ ፣ ፲፩ ፣ ፳፭ ።)
ከርስቶስ ፣ እስከያላልፈው ፣ ድረስ ።

፲፭ ፣ ወእስከ ፡ የም ፡ ሶበ ፡ ያነቡ ፡ አሪተ ፡ ሙሴ ፡ ይገልም ፡ ልቦሙ ።
ገና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አሪትን ፡ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ ድንቁርና ፡ ልቡናቸውን ፡ ይሸፍነዋል ።

፲፮ ፡ ወእምከመ ፡ ተመይጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዐትት ፡ ውእቱ ፡ ግላ ፡ አምኔሆሙ ። (ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ፡ ፳፮ ።)
ወደእግዚአብሔር ፡ በተመለሱ ፡ ጌዜ ፡ ግን ፡ ድንቁርና ፡ ይርቅላቸዋል ፤

፲፯ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ ። (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፬ ።)
እግዚአብሔር ፡ ዕውቀት ፡ ስለኾነ ።

ወኀበ ፡ ሀሎ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ህየ ፡ ሀሎ ፡ ግእዛን ።
ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኝ ፡ እውቀት ፡ ካለ ፡ ዘንድ ። ከድንቁርና ነጻ ፡ መኾን ፡ ከዚያ ፡ አለና ።

፲፰ ፡ ወንሕነሰ ፡ ሙልኔ ፡ ከሚተነ ፡ ገጸነ ፡ ንነጽር ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንኪያስ ፡ ገጻ ፡ ልቡናችንን ፡ ገልጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያወርሰንን ፡ ክብር ፡ እንወቅ ።

ከመ ፡ ዘበመጽሔት ።
ፊቱን ፡ በመስታያት ፡ እንደሚያይ ፡ ሰው ።

ወንትመሰል ፡ በአርእያ ፡ ዚአሁ ።
ፊቱን ፡ በመስታወት ፡ የሚያየውን ፡ ሰው ፡ እንምሰለው ።

ከመ ፡ ንባእ ፡ እምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ።
ያ ፤ እንዱን ፡ እይቶ ፡ እንዱን ፡ እንዲያይ ፤ እኛም ፡ ከዕውቀት ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ።
በከመ ፡ ይሁበነ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ዕውቀትን ፡ እንደሰጠን ፡ መጠን ፡

ወንሕነሰ ፡ ሙልኔ ፡ ከሚተነ ፡ ገጸነ ፡ ንነጽር ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።
ፊት ፡ ለፊት ፡ በባለሟልነት ፡ ቀርበን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብሩን ፡ ጌትነቱን ፡ እንይ ።

ከመ ፡ ዘበመጽሔት ፡
በስቁረተ ፡ እብን ፡ በስዋቀተ ፡ ዕፅ ፡ ያይ ፡ እንደነበረ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ።

ወንትመሰል ፡ በአር እያ ፡ ዚአሁ ።
ሙሴን ፡ እንምሰለው ።

ከመ ፡ ንባእ ፡ እምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ።
እሱ ፡ እንዱን ፡ ኹለቱን ፡ መጋረጃ ፡ ገልጦ ፡ ይገባ ፡ እንደነበረ ፡ እኛም ፡ ከክብር ፡ ወደክብር ፡ እንሔድ ፡
ዘንድ ። ይህስ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ብሎታል ፡ ብሎ ።

ወንሕነሰ ፡ ሙልኔ ፡ ከሚተነ ፡ ገጸነ ፡ ንነጽር ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።
በስዋቀተ ፡ ዕፅ ፡ በስቁረተ ፡ ኰኵሕ ፡ ያይ ፡ እንደነበረ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ያይደለ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
በባለሟልነት ፡ ቀርበን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ክብሩን ፡ እንይ ።
ወንትመሰል ፡ በአርእያ ፡ ዚአሁ ።
በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ ክርስቶስን ፡ እንምሰለው ።

ከመ ፡ ንባእ ፡ እምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ።
እሱ ፡ ወደየማነ ፡ እብ ፡ ወደዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ እንዲሔደ ፡ (ውሳጤ ፡ መንጦላዕት) ፡ እንደገባ ፡ እኛም ፡
ከክብር ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ እንሔድ ፡ ዘንድ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ።

ከመ ፡ ይሁበነ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ከብሩን ፡ እንዲሰጠን ፡ መጠን ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ ፡ ብነ ፡ ዝንቱ ፡ መልእከት ፡ በከመ ፡ ምሕረቱ ፡ ዘጸገወነ ፡ (ም ፡ ፫ ፣ ፮ ።)
እንደቸርነቱ ፡ የሰጠን ፡ ይህ ፡ ሐዋርያነት ፡ አለንና ፡ ይህ ፡ ስላለን ።

ኢንትሐክይ ።
ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ እንበል ።
ወኢንትቈጣዕ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፩፭ ።)
መከራውን ፡ እንሰልች ፡ እንሰቀቅ ፡ እንመረር ።

www.zeyeneta.com

፪ ፡ አላ ፡ ንጎድጎ ፡ ለምግባረ ፡ ኀፍረት ፡ ዘኀቡዕ ።
ቀስ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ የሚሠሩትን ፡ የረበናትን ፡ ሥራ ፡ ትተን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ እንሥራ ፡ እንጂ ፡ ኢንትሐክይ ። መከራውን ፡ ታግሠን ፡ እንቀበል ፡ እንጂ ፡ ኢንትቈጣዕ ።

ወኢንሔር ፡ በትምይንት ።
በተንኰል ፡ እንዋርም ፡ እንኑር ።

ወኢንትመየኖ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ (፭ ተሰሎ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ እንበል ።
ወናቅም ፡ ርእሰነ ፡ በጽድቅ ፡ ገሀደ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ እንጽና ፡ እንጂ ።

እንበይነ ፡ ግእዘ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ዐሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ አብነት ፡ ስለመኾን ።
እንድም ፡ ወኢንትመየኖ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
ወንጌልን ፡ መባያ ፡ እናድርግ ።

ወናቅም ፡ ርእሰነ ፡ በጽድቅ ፡ ገሃደ ።
በጸጋ ፡ ዘነግእከሙ ፡ በጸጋ ፡ ህቡ ፡ በዘንቱ ፡ ዘነግእከሙ ፡ ዐዘንቱ ፡ ህቡ ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ ባለመ ብላት ፡ እንጽና ፡ እንጂ ።

እንቢይነ ፡ ግእዘ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
ስለቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ግብር ፡ ፈንታ ።

ወእመኒ ፡ ክዱን ፡ ትምህርትነ ፡ ክዱን ፡ ውእቱ ፡ ለኅርቱማን ፡ ወለንፉቃን ፡ በዘንቱ ፡ ዓለም ፡ (፭ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ።)
የሌላውን ፡ ንጎድጎ ፡ ለምግባረ ፡ ኃፍረት ፡ ዘኀቡዕ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ እንተስ ፡ የተገለጠ ፡ ታስተምራ ለኽን ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እኛስ ፡ ትምህርታችን ፡ የተሰወረ ፡ ቢኾን ፡ መሰወሩ ፡ ከመናፍቃን ፡ ነው ።
እንድም ፡ ከመናፍቃን ፡ መ ሰወሩ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ (በጽርዕ ፡ ምላሹ) ፡ መበዓለምሰ ፡ ዘይመጽእ ። ህሰምሙ ፡ ያአምርዎ ፡ መናፍቃን ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ።

እሊመ ፡ ጸለሎሙ ፡ ልቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘለዓለም ።
በያውቁት ፡ ክብር ፡ የማይጨመርለት ፡ ባያውቁት ፡ ክብር ፡ የማይጐልበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፅውቀ ቄን ፡ ነሥቷቸዋልና ።

ክሙ ፡ አይርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ ትምህርተ ፡ ስብሐተ ፡ ክርስቶስ ።
የክርስቶስ ፡ ጌትነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ የሚያውቁበትን ፡ ፅውቀት ፡ እንላያውቁ ፡ ፅውቀ ቄን ፡ ነሥቷቸዋልና ።

ዘውእቱ ፡ እርእያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (፩ብ ፡ ፭ ፡ ፫ ።)
ይኸውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ ነው ።

ፍ ፡ ወእኩ ፡ በርእስነ ፡ ዘንሰብክ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፭፬ ።)
ለራሳችን ፡ ማኅበር ፡ ልናበዛ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ልናስፋ ፡ የምናስተምር ፡ አይደለም ።
ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ልናበዛ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ልናስፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንድም ፡ (ወእኩ ፡ ሰር እስነ ፡ ዘንሰብክ) ፡ ለራሳችን ፡ እንበላበት ፡ እንጠጣበት ፡ ብለን ፡ የምናስተምር ፡ አይደለም ።

ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰር ፡ አብነት ፡ ስለኾነን ።

ወለክሙሰ ፡ እቅነይነ ፡ ርእሰነ ።
ለናንተስ ፡ እኛ ፡ ተገዝተናል ።

በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብነት ፡ ስለኾነን ።

፪ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ውእቱ ፡ አብርሀ ፡ ውስቱ ፡ ልብነ ፡ ብርሃነ ፡ እአምሮ ፡ ስብሓቲሁ ፡ በገጹ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ፲፱)
ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ግብር ፡ ጌትነቱን ፡ የምና

www.zeyeneta.com

ውቅበትን ፡ ዕውቀት ፡ በልቡናችን ፡ ሥሎብናልና ። አንድም ፡ ጌትነቱን ፡ የምናስመሰግንበትን ፡ ሥራ ፡ የምንሠራበትን ፡ ዕውቀት ፡ በልቡናችን ፡ ሥሎብናልና ። አሪት ፡ ሰይኩን ፡ ብርሃን ፡ ያለውን ። ኢሳይ ያስ ፡ ዘገብሮ ፡ ለብርሃን ፡ ምስሌ ፡ ጽልሞት ፡ ብሎታል ።

ኢሳይያስ ፡ ዘገብሮ ፡ ለብርሃን ፡ ምስለ ፡ ጽልመት ፡ ያለውንም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እስመ ፡ አግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ብሎ ፡ አነበበው ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፮ ፡ ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕዙት ። (ም ፡ ፭ ፡ ፮ ።)

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ውእቱ ፡ አብርሃ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ብርሃነ ፡ አእምሮ ፡ ለብሐቲሁ ፡ በገጹ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ውእቱ ፡ አብርሀ ፡ ያለውን ፡ ይተረጕማል ፡ አብርሀ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ያልከው ፡ እንደምነው ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ከ፬ቱ ፡ ባሕርያት በተፈጠረ ፡ በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ነፍስ ፡ አለችን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ ዘእምኀቤነ ። (፮ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፯ ።)

ክኖ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ። (አንድም ።)

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕዙት ።

ኢንትሐከይ ፡ ወኢንትቈጣዕ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ በሰውነታችን ፡ ልጅነት ፡ አለን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ክኖ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚኾን ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ይደረግልን ፡ ዘንድ ። (አንድም)

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕዙት ።

ከመ ፡ ንባእ ፡ አምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ በሚኾን ፡ በሥጋችን ፡ ትንሣኤ ፡ አለን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምአግዚአብሔር ።

ክኖ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ከብር ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፰ ፡ እንዘ ፡ በኵሉ ፡ ንሐምም ፡ ኢንትመነደብ ። (ም ፡ ፬ ፡ ፰ ፡ ፯ ።)

ስለዚህም ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ መከራ ፡ ስንቀበል ፡ አንጨነቅም ።

ንትሜነን ።

አንናቃለን ።

ወኢንኃሥር ።

አንዋረድም ።

፱ ፡ ንሰደድዜ ።

አገር ፡ አስጥለው ፡ ይበዱናል ።

ወኢንትገደፍ ።

አንጣልም ።

ንጼዐርዜ ።

ጭንቅ ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ያመጡብናል ።

ወኢንትጎኰል ። (መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፭፬ ፡ ፴፫ ።)

አንጠፋም ።

፲ ፡ ወዘልፈ ፡ ንጸውር ፡ ሞቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋነ ።

ክርስቶስ ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ችል ፡ ጊዜ ፡ በሥጋችን ፡ አንቀበላለን ።

ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሕይወቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ በላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ነፍስትነ ፡ መዊቲ ፡ (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፯) ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ በሚኾን ፡ በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ላይ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕይወቱ ፡ ሕይወትነቱ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ንሕነ ፡ ዘነሐዩ ፡ ወትረ ፡ ንትሜጠው ፡ ለሞት ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ ሕይወቱኒ ፡ ለኢየሱስ ፡ ይትዐወቅ ፡ በላዕለ ፡ ነፍስትነ ፡ መዊቲ ።

(ነሐዩ ፡ ወትረ ፡ ንትሜጠ ፡ ወትረ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ነ) ። የኢየሱስ ፡ ሕይወቱ ፡ ሕይወትነቱ ፡ በፈራሽ ፡

www.zeyeneta.com

በበስብሽ ፡ ሰውነታችን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ኋላ ፡ ሞተን ፡ ተነሥተን ፡ ልዘለዓለሙ ፡ ሕያው ፡ ኾነን ፡ የምንኖር እኛ ፡ ዛሬ ፡ ኹልጊዜ ፡ ለለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልሞት ፡ እንሰጣለን ፤ እስመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይቀትሉነ ፡ ዅሉ ፡ ዓሚረ ፡(መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፳፪) ፡ ዳንኤል ፡ ሞተ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜያተ ፡ በእንተ ፡ አምላኩ ፡ እን ዲል ፡ (ኦፈ ፡ ወርቅ) ።

፲፪ ፡ ወይእዜሰ ፡ ጸንዐ ፡ በላዕሌነ ፡ ሞት ።
ዛሬ ፡ መከራ ፡ ጸንቶብናል ።

አንዘ ፡ ሕይወት ፡ ኀቤነ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፱ ።)
ኋላ ፡ ሕይወት ፡ ሳለን ።
እንድም ፡ ለሌላው ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ሳለን ። በኛ ፡ መከራ ፡ ጸንቶብናል ።

፲፫ ፡ ወብነ ፡ አሐዱ ፡ መንፈሰ ፡ ዘሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ የምንናገርበት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አለን ።
እንድም ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አለን ፤ ይኸውም ፡ ሃይማኖትን ፡ የምንናገርበት ፡ ነው ።

በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ አመንኩ ፡ በዘነበብኩ ። (መዝ ፡ ፻፲፮ ፡ ፩)
በተናገርሁት ፡ አመነው ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ ብነ ፡ ፭ ፡ መንፈስ ፡ ዘሃይማኖት ፡ ላለው ፡ ወንሕነኒ ፡ ማንሻ ።

ወንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በዘነበብነ ።
ያፈ ፡ ሌላ ፡ የልቤ ፡ ሌላ ፡ ሳይኾን ፡ በተናገርሁት ፡ አመንሁ ፡ ብሎ ፡ መጽሐ ፍ ፡ እንደተናገረ ።

(ወንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በዘነበብነ ፡)
እኛም ፡ ያፋችን ፡ ሌላ ፡ የልባችን ፡ ሌላ ፡ ሳይኾን ፡ በተናገርነው ፡ እናምናለን ፡ (ሐተታ) ፡ በአፍ ፡ አምኖ ፡ በልብ ፡ ቢክዱ ፡ አንደ ፡ አርዮስ ፡ (በልብ ፡ አምኖ ፡ በአፍ ፡ ቢክዱ ፡ አንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ መኾን ፡ ነውና) ።

፲፬ ፡ ወነአምር ፡ ከመ ፡ ዘእንሥኦ ፡ ለኢየሱስ ፡ እግዚእነ ፡ ያነሥአነ ፡ ኪያነሂ ፡ ምስሌሁ ። (ገብ ፡ ሐዋ ፡ ፫፲፭)
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያስነሣው ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ተዋሕዶ ፡ ለመኖር ፡ እንደሱ ፡ እንዲያስነሣን ፡ እናውቃለን ።

ወያቀውመኒ ፡ ምስሌክሙ ፡ ኀቤሁ ።
አስነሥቶ ፡ ከናንት ፡ ጋራ ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ በባለሟልነት ፡ ያኖረናል ፡ እንዲያኖረን ፡ እናውቃለን ።

፲፭ ፡ አስመ ፡ ዅሉ ፡ በእንቲአክሙ ።
ኹሉ ፡ ስለናንት ፡ ነውና ፡ ምስሌክሙ ።

ከመ ፡ ትፈድፍድ ፡ ጸጋሁ ፡ በላዕለ ፡ ብዙኃን ።
ጸጋው ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዝታ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ።

ወይብዛኅ ፡ አኩቴቱ ፡ ለስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ።)
የእግዚአሔርም ፡ ጌትነቱ ፡ በዝቶ ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ (ያቀውመን) ፡ ምስሌክሙ ፡) እንድም ፡ ጸጋ ውን ፡ በዝታችሁ ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፤ ክብሩን ፡ ለመውረስ ፡ በዝታችሁ ፡ በሱ ፡ ቃል ፡ ትመሰገኑ ፡ ዘንድ ፡ ዅሉ ፡ በእንቲአክሙ ።

፲፮ ፡ ወበአንተዝ ፡ ኢንትቈጣዕ ።
ስለዚህ ፡ መከራን ፡ እንሰልች ፤ አንሰቀቅ ፤ አንመረር ።

ወኢንትሐከይ ።
ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አንበል ።

አስመ ፡ ዘእንተ ፡ እፍአነ ፡ ብእሲ ፡ በላዒ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፩ ።)
እፍአዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ኃላፊ ፡ ነውና ።

ወዘእንተ ፡ ውስጥነሰ ፡ ይትሐደስ ፡ ዅሉ ፡ አሚረ ። (ኦፈ ፡ ፫ ፡ ፲፮)
ውሳጣዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ግን ፡ ኹልጊዜ ፡ በተሐድሶ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ሕማምነ ፡ ዘለሰዓት ፡ ቀሊል ፡ ከብረ ፡ ወስብሐተ ፡ አፈድፈዶ ፡ ይገብር ፡ ለነ ። (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፭)
ለጥቂት ፡ ሰዓት ፡ የሚኾን ፡ መከራችን ፡ ክብርን ፤ የክብር ፡ ክብርን ፡ አብዝቶ ፡ የሚያመጣልን ፡ ስለኾነ ፡ ይትሐደስ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ኢንሴፎ ፡ ዘያስተርኢ ፤ አላ ፡ ዘኢያስተርኢ ። (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭)
የማይታየውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የሚታየውን ፡ ዓለም ፡ ተስፋ ፡ አናደርግምና ፤ ይትሐደስ ።

www.zeyeneta.com

እስመ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ውእቱ ¤
የሚታየው ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ስለኾነ ፡ (ኢንሴር ፡ ዘያስተርኢ ¤)
ወዘሰ ፡ ኢያስተርኢ ፡ ቀዋሚ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ውእቱ ¤
የሚታየው ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ባለማሰፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ስለኾነ ፡ (እላ ፡ ዘኢያስተርኢ) ¤

ም ዕ ራ ፍ ፫

፩ ፡ ወነእምር ፡ ከመ ፡ ለእመኒ ፡ ተነሥተ ፡ ቤተ ፡ ማኅደርነ ፡ ዘበምድር ፡ (ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬¤)
የነፍሳችን ፡ ማደሪያ ፡ የሚኾን ፡ ሥጋችን ፡ ቢፈርስ ፡ ቢበስብስ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋ ¤
ቤት ፡ ያለውን ፡ ተረጕመ ፡ ይኸውም ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ወሰመየ ፡ ሥጋቲነ ፡ እብያተ ፡ ዘጽቡር ፡ እስመ ፡
ነፍሳቲነ ፡ ኅዱራት ፡ ውስቴቱ ፡ እንዲል ¤ (ኢዮ) ፡ ብነ ፡ ሕንጸ ፡ በኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ዘኢ

፪ ፡ ንብሮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ¤)
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በልዕልና ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ያልፈጠረው ፡ ሌላ ፡ ሥጋ ፡ እንዳለን ፡(እሰ) ፡
ሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ፡ (ሐተታ) ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ፈጥሮታልና ፡ እንዲህ ፡
እሰ ፡ ቢሉ ፡ ይህ ፡ በምክንያተ ፡ ዘርዕ ፡ ተገኝቷል ፡ የኋላው ፡ ግን ፡ ምክንያት ፡ የለውምና ¤

፫ ፡ ወኪያሁ ፡ ንሴር ፡ ንልበሰ ፡ ቤተነ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማያት ¤ (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፡)
ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ በልዕልና ፡ ያለ ፡ ያነን ፡ ሥጋ ፡ እንድንዋሐድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ (እሰ) ፡ በነፍስ ፡
መደብ ፡ ቆሞ ¤

ዘበእንቲአሁ ፡ ንሰርሕ ¤
ዛሬ ፡ መከራ ፡ የምንቀበልሰት ፤ በመከራው ፡ የምንደክምበት ¤

፬ ፡ ወእምኪመ ፡ ሰበስናሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘንትረከብ ፡ ዕራቃቲነ ¤
ከተወሐድነውም ፡ በኋላ ፡ ከክብር ፡ ባዷችንን ፡ እንገኝም ¤

፭ ፡ እስመ ፡ እንዘኒ ፡ ሀለውነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ነኃዝን ፡ ፈድፋደ ፡ እምከበደ ፡ ዚአሁ ¤ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፫)
በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ሳለን ፡ ጠቀረ ፡ እናቅላው ፤ ከሳ ፡ እናወፍረው ፡ በማለት ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ¤
እንድም ፡ ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ መቸ ፡ በተለየነው ፡ እያልን ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ¤

ወኢንፈቅድ ፡ ንስለብ ¤
ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያነን ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ከተዋሐድነው ፡ በኋላ ፡ ልንለየው ፡ እንሻም ¤

ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንልበስ ፡ ካልእ ፡ መልዕልቱሁ ¤
በተዋሐዶው ፡ ጸንተን ፡ ልንኖር ፡ እንወዳለን ፡ እንጂ ¤ (እንድም ፡ መልስ) ፡

ወነእምር ፡ ከመ ፡ ለእመኒ ፡ ተነሥተ ፡ ቤተ ፡ ማኅደርነ ፡ ዘበምድር ¤
የነፍሳችን ፡ ማደሪያ ፡ የሥጋችን ፡ መኖሪያ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ቢያልፍ ፡

ዘውእቱ ፡ ሥጋ ¤
ማኅደር ፡ ያለውን ፡ ተረጕመው ፡ ይኸውም ፡ ሥጋ ፡ ነው ¤

ብነ ፡ ሕንጸ ፡ በኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ዘኢንብሮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ¤
በልዕልና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ያልፈጠረው ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ፡
(ሐተታ) ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ፈጥሮታልና ፡ እንዲህ ፡ እሰ ፡ ቢሉ ፡ ይህ ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡
እጅ ፡ ይናኛል ፤ ያ ፡ ግን ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እጅ ፡ አይናኝምና ¤

ወኪያሁ ፡ ንሴር ፤ ንልበስ ፡ ቤተነ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማያት ¤ ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ በልዕልና ፡
ያለ ፡ ያነን ፡ ዓለም ፡ እንድንወርስ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ¤

ዘበእንቲአሁ ፡ ንሠርሕ ¤
ዛሬ ፡ መከራ ፡ የምንቀበልለት ፡ (በመከራው ፡ የምንደክምለት ¤)

ወእምኪመ ፡ ለበስናሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘንትረከብ ፡ ዕራቃቲነ ¤
ያን ፡ ዓለም ፡ ከወረስነው ፡ በኋላ ፡ ከክብር ፡ ባዷዋችንን ፡ እንገኝም ¤

እስመ ፡ እንዘኒ ፡ ሀለውነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ነኃዝን ፡ ፈድፋደ ፡ እምከበደ ፡ ዚአሁ ¤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለን ፡ ላላ ፡ እናጽናው ፡ ጠበበ ፡ እናስፋው ፡ በማለት ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ፡ እንድም ፡
ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ መቸ ፡ በተለየነው ፡ እያልን ፡ እናዝናለን ፡ እኮን ¤

ወኢንፈቅድ ፡ ንሰለብ ¤
ዘበእንቲአሁ ፡ ንሠርሕ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያነን ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ከወረስነው ፡ በኋላ ፡ ለዚህ ፡ ብለን ፡
መከራ ፡ ተቀበልን ፡ እንልም ¤

www.zeyeneta.com

ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንልበሰ ፡ ካልእ ፡ መልዕልቱሁ ።

ምነው ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ በጨመርንበት ፡ እንላሰን ፡ እንጂ ፡ (ሐተታ) ፡ ገበሬ ፡ ሲያርስ ፡ ከርሞ አምሾውን ፡ ሲያሀድ ፡ ፡ ብለን ፡ መከራ ፡ ተቀበልን ፡ አንልም ፤ ምነው ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ በጨመርንበት ፡ እንላለን ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ይሰጠም ፡ መዋቲ ፡ በሕይወት ።

ይህ ፡ መዋቲ ፡ ሰውነታችን ፡ በሕይወት ፡ ባሕር ፡ ይሰጠም ፡ ዘንድ ።

ፍ ፡ ወውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድእነ ፡ በዝንቱ ።

በዚህም ፡ የሚረዳን ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳናል ።

ዘወሀበነ ፡ አረቦን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ (ም፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ሮሚ፡ ፭ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ፡ ኤፌ ፡ ፩፡ ፲፫ ፡ ፲፬)

የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፈለማ ፡ በልቡናችን ፡ ያሳደረብን ።

ኬ ፡ ተአመኑ ፡ እንከ ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ጽኑ ።

ወእጥብዑ ፡ ዐዚሉ ፡ ጊዜ ፡ (ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ።)

ኹልጊዜ ፡ መከራውን ፡ ሰመቃበል ፡ ጨክኑ ።

ወተአምሩ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ እንግዳ ፡ እንትሙ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋ ፡

በዚህ ፡ በሥጋችሁ ፡ እድሮ ፡ ሕያጅ ፡ እንደኾናችሁ ፡ ታውቃላችሁና ።

ወትነግዱ ፡ እምነፍስትክሙ ፡ ወተሐውሩ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ።

ከዚህ ፡ ከሥጋችሁ ፡ ተለይታችሁ ፡ ወደጌታችን ፡ ትሔዳላችሁና ።

ፏ ፡ እስመ ፡ በእሚን ፡ ነሐውር ።

በውነት ፡ እንሔዳለንና ።

ወእኩ ፡ በአድልዎ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ።)

ለሞት ፡ ወራኛ ፡ የለውምና ፡ በሐሰት ፡ ያይደለ ፡ ባዎንታ ፡ እንሄዳለንና ።

ፎ ፡ ወፈድፋዶ ፡ ንትአመን ፡ ወንትፌሣሕ ።

ይልቁንም ፡ እምነን ፡ ደስ ፡ ይለናል ፤ ደስ ፡ ይበለን ።

እስ መ ፡ ወሢእነ ፡ እምነፍስትነ ፡ ነሐውር ፡ ኀቤሁ (ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ።)

ከሥጋችን ፡ ተለይተን ፡ ወደርሱ ፡ እንሔዳለንና ።

ወናሠምሮ ፡ ለእግዚእነ ።

ጸንተን ፡ ብንገኝ ፡ ጌታችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኘዋለንና ።

ፐ ፡ ወይእዜኒ ፡ ናእኩቶ ፡ እመኒ ፡ ነባድነ ፡ ወእመኒ ፡ ሀሎነ ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ብንሔድም ፡ ብንኖርም ፡ እናመሰግነው ፡ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ማንሺ ።

ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ናድሉ ፡ በምግባሪነ ፡ (መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፲፫ ።)

ብንሔድም ፡ እናመሰግነው ፡ ብንኖርም ፡ በሥራችን ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ደሰ ፡ እናሰኘው ። አንድም ፡ ብንሔድም ፡ ብንኖርም ፡ በሥራችን ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ እናሰኘው ።

ፒ ፡ እስመ ፡ ሀለወነ ፡ ኵልነ ፡ ንቁም ፡ ቅድመ ፡ መንበረ ፡ ምዙናኒ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፴፩ ።) (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ።)

ኹላችንም ፡ ከርስቶስ ፡ በሚፈርድበት ፡ ወደባባይ ፡ እንቆም ፡ ዘንድ ፡ አለንና ።

ከመ ፡ ንትፈደይ ፡ በከመ ፡ ገበርነ ፡ በሥጋነ ።

በሥጋችን ፡ እንደሠራነው ፡ እንደሠራነው ፡ ዋጋችንን ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ።

እመኒ ፡ ሠናየ ፡ ወእመኒ ፡ እኩየ ።

በጐም ፡ ቢኾን ፡ ክፉም ፡ ቢኾን ፡ (አለ) ፡ በጐ ፡ ብንሠራ ፡ ዋጋችንን ፡ ክፉ ፡ ብንሠራ ፡ ፍዳችንን ፡ እንቀበል ዘንድ ።

ክ ፍ ል ፡ ፭ ።

፲፭ ፡ ወእንበይነ ፡ ዘንአምር ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈሪሆቶ ፡ (ኢዮ ፡ ፴፭ ፡ ፳፫ ።)

(ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር) ፡ ምስትንቱን ፡ (ፈሪሆቶ) ፡ እንድነቱን ፤ ጽድቀ ፡ (እግዚአብሔር ፡) ሰብክተ ፡ ሐዋርያትን ። (ፈሪሆቶ ፡) ትንቢተ ፡ ነቢያትን ፡ ስላወቅነ ።

www.zeyeneta.com

ትእምን ፡ ሰብአ ።
ሰው ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፤ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ናድሉ ፡ በምግባሪነ ፡ ላለው ፡ እንድም ፡ ሰው ፡ መኾንን ፡ እምነን ፡ (ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፤) ዘእምን ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ያሰውን ፡ (ወፈሪሆቶ ፡) ዘኢእምን ፡ ወዘኢተጠምቀ ፡ ይደየን ፡ ያለውን ። አንድም ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፤ ለጸድቁ ፡ ፈርዶ ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋጋ ፡ (ወፈሪሆቶ ።) በኃጥኡ ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣውን ፡ ፍዳ ፡ ስላወቅነ ፡ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ በምግባሪነ ፡ ላለው ። ለእግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ፡ ማንሻ ።

ለእግዚአብሔርሰ ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ።
ወአኮ ፡ ለርእስነ ፡ ዘንሰብክ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ (ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፡ ዘነግአክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በክንቱ ፡ ዘነግአክሙ ፡ በክንቱ ፡ ሀቡ ፡ ያለውን ፡ (ግቴ፡ ፲ ፡ ፱፡) (ወፈሪሆቶ ፡ ገብር ፡ ሐካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያግባዕከ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ ለዝንቱ ፡ ገብር እስሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ያለውን፡ (ግቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳፭-፴፡) ስላወቅነ ፡ ናአምን ፡ ሰብአ) ፡ ዙረን ፡ ዙረን ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ስናስተምር ።

(ለእግዚአብሔርሰ ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ።)
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ባለመቀበል ፡ የታወቅን ፡ ነን ።

ወንትአመን ፡ ከመኒ ፡ ንትከሠት ፡ በልብክሙ ።
በናንተም ፡ በልቡናችሁ ፡ ታውቅን ፡ እንዳለ ፡ እናምናለን ።

፲፪ ፡ ወአኮ ፡ ዘንዌድስ ፡ ካዕበ ፡ ርእሰነ ፡ በዝንቱ ፡ በጎቤክሙ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፩ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ በናንት ፡ ዘንድ ፡ ራሳችንን ፡ በዚህ ፡ የምናመሰግን ፡ አይደለም ፡

ወዳዕሙ ፡ ንሁበክሙ ፡ ምክንያተ ፡ ትጽንዑ ፡ በዘትትሜክሑ ፡ ብነ ፡ አንትሙኒ ፡ ከማነ ።
እናንተም ፡ እንደኛ ፡ በምትመኩ ፡ ገንዘብ ፡ ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የምትመኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እንነግራችኋለን ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ይኩንክሙ ፡ ለጎበ ፡ አለ ይትሜክሑ ፡ ለገጽ ፡ ወአኮ ፡ ለልብ ።
ለልቡና ፡ ያይደለ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ በሚመኩ ፡ በቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ፊት ፡ መመኪያ ፡ ሊኾናችሁ።

፲፫ ፡ አስመ ፡ ንሕነሰ ፡ ለአመኒ ፡ ኮነ ፡ አብዳነ ፡ አበድነ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ስንፍናህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አስተምረህ ፡ ዋጋ ፡ አትብላ ፡ ያለህን ፡ አለ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ አኖስ ፡ ሰነፎችም ፡ ብንኾን ፡ ስንፍናችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወአመኒ ፡ ኮነ ፡ ጠቢባነ ፡ ጠበብነ ፡ ለክሙ ።
ይኸውም ፡ እንጂ ፡ ልባምነትህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ልባሞችም ፡ ብንኾን ፡ ልባምነታችን ፡ ለናንተ፡ ብለን ፡ ነው ።

አንድም ፡ (አመኒ ፡ አበድነ ፡ አበድን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአመኒ ፡ ጠበብነ ፡ ለክሙ ፡ ይላል፡)
ብንሰንፍ ም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለን ፡ ሰንፈናል ፡ ብንለብምም ፡ ለእናንት ፡ ብለን ፡ ለብመናል ።

፲፬ ፡ አስመ ፡ ፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ ያጌብረነ ፡ ናጥብዕ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሕሊና ።
ክርስቶስን ፡ መውደድ ፡ በዚህ ፡ በመመካቱ ፡ እንድንጸና ፡ ያደርገናልና ፡ ወዳዕሙ ፡ ንሁበክሙ ፡ ምክንያተ ፡ ላለው ።
አንድም ፡ ክርስቶስን ፡ መውደድ ፡ ዋጋ ፡ ባለማብላቱ ፡ እንድንጸና ፡ ያደርገናልና ፡ አመኒ ፡ አበድን ፡ አበድን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላለው ።

አስመ ፡ አሐዱ ፡ ሞተ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉ ፡ (ዕብ ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
እንዱ ፡ እሱ ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ ስለሞተ ።

በዘወድአ ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ።
ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሞትን ፡ በፈጸመ ፡ ገንዘብ ፡ (አለ) ፡ ፈጽሞ ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሲል ፡ ነው ።

አንድም ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ፡ የኹሉን ፡ ሞት ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ ተፈልጦው ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ እግኤል ፡ ሞተ ፡ ክመ ፡ ሞተ ፡ ዚአነ ፡ ዘውእቱ ፡ ተፈልጦተ ፡ ነፍስ ፡ እምሥጋ ፡ እንዲል ፡ (ሳዊሮ) ።
አንድም ፡ ሞት ፡ ኵሉ ፡ ሞት ፡ ሁሉን ፡ በፈጸመ ፡ ገንዘብ ።
አንድም ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ፡ ለኹሉ ፡ የሚገባውን ፡ ሞት ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ ሞተሰ ፡ አምደለዎ ፡ ሰአዳም ፡ ስቁለ ፡ በመስቀል ፡ ዘበጎጣር ፡ እንዲል ፡ መቅ ፡ ወን ።
አንድም ፡ የኹሉን ፡ ሞት ፡ ድል ፡ በነሣበት ፡ በመስ ቀል ፡ እንዱ ፡ እሱ ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ ሙታልና ያጌብረነ ፡ ናጥብዕ ።

፲፭ ፡ ውእቱ ፡ ሞተ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፮ ።)
ውእቱ ፡ ሞተ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉና ፡ ሞተ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እንድም ፡ በየራሱ ፡ ስማውጣት፡ እንድ ፡ እሱ ፡ የኹሉ ፡ ቤዛ ፡ የሚኾን ፡ ሞትን ፡ ስለኹሉ ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ በል ።

www.zeyeneta.com

ከመ ፡ እለሂ ፡ የሐይዉ ፡ እኩ ፡ ለርእሶሙ ፡ ዘየሐይዉ ፡ (ሮሚ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ፡ ፰ ።)
ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ የሚነሡ ፡ ራሳቸውን ፡ ለማስገገል ፡ እንዳይደለ ፡ መጠን ።

ዘእንበለ ፡ ለዝኩ ፡ ዘበእንቲአሆሙ ፡ ሞተ፤ ፡ ወሐይወ፤ ።
ስለሳቸው ፡ ሞቶ ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፯ ፡ ወይእዜሰ ፡ አልቦ ፡ ዘነአምር ፡ በሥጋ ።
ዛሬስ ፡ በማዘፍ ፡ የምናውቀው ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ አእመርናሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋ ።
ክርስቶስንም ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በማዘፍ ፡ ብናውቀው ።

እምይእዜሰ ፡ አልቦ ፡ ዘነአምሮ ፡ እንክ ።
ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ በማዘፍ ፡ የምናውቀው ፡ አይደለም ።

፲፯ ፡ ወይእዜሰ ፡ በክርስቶስ ፡ ተሐደሰ ፡ ኵሉ ፡ ዘኮነ ። (ሮሚ ፡ ፮ ፡ ፩-፲ ።)
ዛሬስ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ታድሷል ።

ወኀለፈ ፡ ዘትካት ። (ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፲፱ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፩ ።)
ብሉይ ፡ ግብር ፡ አልፏል ።

፲፰ ፡ ወናሁ ፡ ኮነ ፡ ኵሉ ፡ ሐዲሰ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ። (ሮሚ ፡ ፭ ፡ ፲ ።)
እነሆ ፡ ሹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታደሰ ፡ ኾኗል ።

ዘእቅረበነ ፡ ኀቤሁ ፡ በክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ ወዳሉ ፡ ባቀረበን ፡ በእግዚአብሔር ።

ወወህበነ ፡ መልእክተ ፡ ሥምረቱ ።
ፈቃዱን ፡ የምንፈጽምበት ፡ ልጅነትን ፡ በሰጠን ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ ተዋሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለመ ፡ በክርስቶስ ።
እግዚአብሔር ፡ ዓለሙን ፡ ዘክርስቶስ ፡ ዋጅቶታልና ፡ ዘእቅረበነ ፡ ኀቤሁ ፡ በክርስቶስ ።

እናሕሰዮ ፡ ኃጢአቶሙ ። (ሮሚ ፡ ፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ።)
ኃጢአታቸውን ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ።

ወኢነጺሮ ።
ዕዳ ፡ አልልም ፡ ብሎ ።

ወረሰየ ፡ ላዕሌነ ፡ ቃለ ፡ ሥምረቱ ።
ወዶ ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ እንድናስተምር ፡ አድርጎናልና ፡ ዘእቅረበነ ።

ወወህበነ ፡ መልእክተ ፡ ማዘሉ ። (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)
ይቅርታውን ፡ የምናገኝበት ፡ ሐዋርያነትን ፡ ሰጥቶናልና ። የላይኛውን ፡ ሐዋርያነት ፡ ያሉ ፡ እንደ ኾነ ፡ ይህን ፡ ልጅነት ፡ የላይኛውን ፡ ልጅነት ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ ሐዋርያነት ።

፳ ፡ ወንሕነሰ ፡ ንተነብል ፡ በእምላሰ ፡ ክርስቶስ ። (ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፯ ።)
እንግዲህስ ፡ ክርስቶስን ፡ መስለን ፡ በክርስቶስ ፡ አምላል ፡ እንጸልያለን ፡ እናስተምራለን ።

ወይሁበክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሥሓ ፡ በላዕሌነ ።
በኛ ፡ ጸሎት ፡ በኛ ፡ ትምህርት ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅነትን ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣችኋል ።

ወንስአለክሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ታሥምርዎ ፡ በእግዚአብሔር ።
ንስእለክሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ታሥምርዎ ፡ በክርስቶስ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ በክርስቶስ ፡ አሥምሮት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታሠምሩት ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ማላጅ ፡ አድርገን ፡ እንማልዳችኋለን ።

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ጎበ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በአቴና ፡
ወተፈነወ ፡ ምስለ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ መስልዋናስ ።

በአቴና ፡ የተጻፈ ፡ በጢሞቴዎስና ፡ በስልዋናስ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ በተሰሎንቄ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ የተ
ላከ ፡ ክታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
መልክሔት ፡ ለእግዚአብሔር ።
አንሣሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምር ፡ ላሰጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.zeyeneta.com

ምክንያት ፡ ጽሑፎቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ዳግመ ።

እስመ ፡ ሰብእ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ሶበ ፡ ሰምዕዎ ለሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ እመ ፡ ምጽአተ እግዚእነ ፡ ይመሥጡን ፡ በደመና ፡ ከመ ፡ ንትቀበሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ አየር ፡ መስሎሙ ፡ ከመ ይከውን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ በዘመኑ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ።

ወአጠየቆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይከውን ፡ እሜሃ ፡ ዘእንበሰ ፡ ይቅድምዎ ፡ ትእምርታት ፡ አለ ፡ ይከ ውን ፡ በእስተርእዮቱ ፡ ለሐሳዊ ፡ መሢሕ ።

ወይቤሎሙ ፡ ንነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ምጽአት ፡

ወእንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዐቂ ፡ ኢያ ደንግፁክሙ ፡ ፍጡነ ።

ኢትትህወኩ ፡ እምአእምሮ ፡ ኢበመንፈስ፡ ወኢበነገር ፡ ወኢበመጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ዘእምኀቤነ፡ ለእመ ፡ ትመጽአ ፡ ዕለት ፡ እግዚእነ ፡ አልቦ፡ ዘያ ስሕቱክሙ ፡ ወኢበምንትኒ ።

ጳውሎስ ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ኵለተኛ ፡ የጸፈበት ምክንያት ።

የተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ፡ በመጀመሪያው፡ ከታቡ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ የምንኖር እኛ ፡ ጌታችን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በልዕልና ፡ እንቀበ ሰው ፡ ዘንድ ፡ በደመና ፡ ነጥቀው ፡ ይወስዱናል፡ ሲል ፡ ቢሰሙት ፡ ምጽአቱ ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉት ምልክቶች ፡ አሰቀድመው ፡ ሳይደረጉ ፡ ምጽአት፡ እንዳይደረግ ፡ ሲያሰረዳ ፡ ጸፈላቸው ።

ወንድሞቻችን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ክር ስቶስ ፡ መምጣት ፡ ገና ፡ እንደኾነ ፡ እንነግራችኋ ለን ።

ባንድነቱ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ ምጽአት ፡፡ ፈጥኖ ፡ ይደረጋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳያሸብሯ ችሁ ፡ ዕወቁ ።

(ኢበመንፈስ ፡) በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገለ ጠልኝ ፡ ብለው ፡ (ወኢበነገር ፡) ከሐዋርያት ፡ ታል ሰማን፡ ብለው ፡ (ወኢበጳጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ዘእም ኀቤነ ፡) ከኛ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳገኙት ፡ አድርገው ምጽአት ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረጋል ፡ ቢሏችሁ ፡ ምጽአት ገና ፡ እንደኾነ ፡ ከማወቅ ፡ ወጥታችሁ ፡ እንዳትታ ወኩ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ የሚያስታችሁ ፡ አይኑር እያለ ፡ ጸፈላቸው ።

ይህን ፡ ከታቡ ፡ በሎዶቅያ ፡ ላለ ፡ ጽፍ ፡ከዚ ያው ፡ አኖረው ፡ እንጂ ፡ ያንጊዜ ፡ ወደተሰሎንቄ፡ አላከውም ፡

ያንጊዜ ፡ እሰመላኩንም ፡ በምን ፡ ታስር ፡ ሳለ ፡ ለቄላሰይስ ፡ ሰዎች ፡ ከታቡ ፡ ከላክ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከታችሁ በተባሌ ፡ያነ ቡት ፡ ዘንድ ፡ ወደሎዶቅያ ፡ ላኩት ፡

እናንተም ፡ የጻፍኩትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሎዶ ቅያ ፡ ወስዳችሁ ፡ ተመልከታችሁ ፡ ቀዳ ፡ ተሰሎ ንቄ ፡ ላኩት ፡ በግለቱ ፡ አስረዳ ።

ይህን ፡ ከታቡ ፡ ሰተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ያደ ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢኪቆስን ፡ አዘ ዘው ።

www.zeyeneta.com

ቀዳማዊ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ካልአት ፡ አለ ፡ ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ አመ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ፡ ኢንበጽሖሙ ፡ ለምውታን፡ (፩፡ተሰ፡ ፬ ፡ ፲፫)፡ ሲል ፡ ሰምተው ፡ ምጽአት ፡ በጳውሎስ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡ ብለ ዋል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ገና ፡ እንደኾነ ፡ ስመንገር ፡ ይጽፋል ፡ ንነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ ምጽአተ ፡ እግ ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዐቂ ፡ ኢያደንግፀክሙ ፡ ፍጡነ ፡ ወኢትትሐ ወኩ ፡ እምአእምሮ ፡ ኢበመንፈስ ፡ ወኢበነገር ፡ ወኢበመጽሐፍ ፡(ም ፡ ፪ ቊ ፡፩)ኢትዘከሩኑ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ ህሎኩ ኅቤክሙ ፡ አቅደምኩ ፡ መንገርኩክሙ ፡ ዘንተ ፡ ቊ ፭ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ቊሙ ፡ ወዕቀቡ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘመሐ ሩክሙ ፡ ወሠርዐክሙ ፡ ዘበቃልነ ፡ ወዘበመጽሐፍነ ፡ ቊ ፲፭ ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀንይ ፡ ኢይሴሰይ ፡ ፲፤፩፡ ወለእመቦ ፡ ዘኢይትኤዘዝ ፡ ለቃልክሙ ፡ ወለመጽሐፍክሙ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወኢትትሐወልዎ ፡ ከመ ፡ ይትኀፈር ፡ ወከመሰ ፡ ጸላኤ፡ኢትረስይዎ ፡ አላ ፡ ገሥጽዎ ፡ ከመ ፡ እኁክሙ ። ፫ ፡ ፲፬ ፡ ወዝንቱ ፡ ትምህርትየ ፡ ውስተ ፡ ዙሉ፡ መጻሕፍትየ ፡ ከመዝ ፡ እጽሕፍ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ይላል ፡ ፲፰ ፡ የጸፈበት ፡ ሀገር ፡ ሎዶቅያ ፡ ከታብ ፡ ወሳጅ ፡ ጢኪቆስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፡ አምጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ።
ክኔ ፡ ከጳውሎስና ፡ ከስልዋኖስ ፡ ከጢሞቴዎስም ፡ የተላከ ፡ ከታብ ።
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተሰሎንቄ ፡ ምእመናን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።
በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ አምነው ፡ በተሰሎንቄ ሳሉ ፡ ምእመናን ፡ ትድረስ።
፪ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ።
ቸር ፡ አላችሁን ።
ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።(፩ቆሮ ፡፩፡፫ ቈላ፡ ፩፡፪ ፡)
የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ፡ ይደረግላችሁ ።
፫ ፡ ርቱዕ ፡ ናእኩቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሁሉ ፡ ጊዜ ፡ በአንቲአከሙ ፡ አኃዊነ ።
ሰለናንት ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኹልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባል ።
በከመ ፡ ይደልዎ ።
ለሱ ፡ እንደሚገባው ፡ ባንድነቱ ፡ ምንታዌ ፡ በሥስትነቱ ፡ ርባዔ ፡ ሳንቀላቅል ። አንድም ፡ ስውን ፡ ጸድቅ ፡ ቢሉት ፡ ሐሰት ፤ ባዕል ፡ ቢሉት ፡ ንዴት ፡ ኃያል ፡ ቢሉት ፡ ድካም ፡ ይሰማማዋል፡እርሱ ፡ ግን፡ ባዕል ዘአልቦ ፡ ንዴት ፡ ኃያል ፡ ዘአልቦ ፡ ድካም ፡ ጸድቅ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐሰት ፡ ነውና ።
አንድም ፡ ለስው ፡ ማመስገን ፡ እንደሚገባው ። ስውና ፡ መላእክትን፡ መፍጠሩ፡ ሊያመሰግኑት ፡ ነውና ወበእንተዝ ፡ ፈጠሮ ፡ ለስብእ ፡ ከመ ፡ ይትለእኮ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ፡ እንዲል ፡ (ሃይ ፡ አበ አትና)።
አስመ ፡ ዐብየት ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወፈድፋደት ፡ ተፋቅሮትክሙ ፡ ምስለ ፡ ዙሉ ፡ ቢጽክሙ ።(ም ፡፪ ፡፲፫ ፡፩ ተሰ ፡ ፩ ፡፪ ፡)
በሃይማኖት ፡ ከመሰሏችሁ ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ፍቅራችሁ ፡ በዝታለች ፡ ሃይማኖታችሁ ጸንታለችና ።
፬ ፡ ከመ ፡ ንሕነኒ ፡ ንትመካሕ ፡ ብክሙ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በምእመናን ፡ ፊት ፡ እንመካባችሁ ፡ ዘንድ ፡ አስከንመካባችሁ ፡ ድረስ ፡ ደርሰን ።
በአንተ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወትዕግሥትክሙ ፡ በሕማምክሙ ፡ ወምንዳቤክሙ ፡ ዘትትዔገሡ ፡ ወትትዌከፉ ።
(፪ ቆሮ ፡፯ ፡፲፪)፡ ስለሃይማኖታችሁ ፡ ታግሣችሁ ፡ ስለምትቀበሉት ፡ መከራ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ሃይ ማኖታችሁ ፡ጸንታለች ፡ ፍቅራችሁ ፡ በዝታለችና ፡ ርቱዕ ፡ ናእኩቶ ።
፭ ፡ ከመ ፡ ታርአዩ ፡ ኩነኔ ፡ ጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ። (ፊልጵ ፡፩ ፡፳፰ ፡)
የእግዚአብሔርን ፡ እውነተኛ ፡ ፍርዱን ፡ ትገልጹ ፡ ዘንድ ፡ አስከትገልጹ ፡ ዘትትዔገሡ ፡ ወትትዌከፉ

www.zeyeneta.com

ከመ ፡ ይክፍልክሙ ፡ መንግሥቶ ፡ ዘበእንቲኣሁ ፡ ተሐምሙ ።(ሉቃ ፡፳፩ ፡፴፪ ፡)
አግዚኣብሔር ፡ ስለሱ ፡ መከራ ፡ የምትቀበሉላት ፡ መንግሥተ ፡ ስማይን ፡ ያወርሳችሁ ፡ ዘንድ ። እን
ድም ፡ መከራ ፡ ለምትቀበሉላት ፡ ለመንግሥተ ፡ ስማይ ፡ ያበቃችሁ ፡ ዘንድ ፡ ታርእዩ ፡ ዘነኔ ፡ ጽድቁ፡
ላለው ።

፮ ፡ ወርቱዕሰ ፡ ይትፈደዩ ፡ በኀበ ፡ እግዚኣብሔር ፡ ሕማመ ፡ እለ ፡ የሐምሙክሙ ።(ራእ ፡ዮሐ ፡፲፭ ፡፮ ፡፯ ፡)
(ይትፈደዩ ፡ ሕማመ ፡ እለ ፡ የሐምሙክሙ ፡ ሕማመ ፡) እገባብስ ፡መከራ ፡ የሚያጸኑባችሁ ፡ ሰዎች፡
ከእግዚኣብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፍዳቸውን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ስለእሳቸው ፡ እናመሰግናቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፯ ፡ ወለክሙ ፡ ለእለ ፡ ተሐምሙ ፡ ዕረፍት ፡ ምስሌን ።
(ተሐምሙ ፡ ምስሌን ፡ ዕረፍት ፡ ምስሌን ፡) ክኖ ፡ ጋራ ፡ እንደኖ ፡ መከራ ፡ ለምትቀበሉ ፡ ለናንተ ፡ ግን
ዕረፍት ፡ ስለእሳችሁ ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባል ።
በምጽኣቱ ፡ ለእግዚእን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምስማያት ፡ ምስለ ፡ መላእክተ ፡ ኃይሉ ።(ማቴ ፡፳፭ ፡፴፩ ፡)
ክሃሊነቱ ፡ የሚገለጥባቸው ፡ መላእክትን ፡ አስክትሎ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይትፈደዩ ። እንድም ፡ ዕረፍት
ምስሌን ።

፰ ፡ ከመ ፡ ይትበቀሎሙ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ ለነ ፡ ኢያአምርዎ ፡ ለእግዚኣብሔር ፡ ወእሰ ፡ ኢይሰምዑ ፡ ትምህርተ
ወንጌሉ ፡ ለእግዚእን ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ።(ሮሜ ፪፡፰)
ወንጌልን ፡ በማይቀበሉ ፡ እግዚኣብሔርን ፡ በማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ነደ ፡ እሳትን ፡ ይፈርድባቸው ፡
ዘንድ ፡ እንድም ፡ በምጽኣቱ ፡ ይትቀበሎሙ ፡ ወንጌልን ፡ የማይቀበሉትን ፡ እግዚኣብሔርን ፡ የማያው
ቁትን ፡ ሰዎች ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ በመኾን ፡ በነደ ፡ እሳትነት ፡ ይገጥማቸው ፡ ዘንድ ፡ ይመጽኣ ።

፱ ፡ ወይረክቡ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ኩነኔ ፡ ኃጕል ።
ኃጕለ ፡ ኩነኔ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ ፍዳቸውንም ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣባቸውን ፡ ጥፋት ፡ ይቀበላሉ ።
ወተሠርዎ ፡ ዘለዓለም ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚኣብሔር ።(ኢሳ ፡፪፡፲ ፡፲፱ ፡)
ከእግዚኣብሔር ፡ ባለሚልኑት ፡ የዘለዓለም ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ።
ወእምስብሐተ ፡ ኃይሉ ።
በክሐሊነቱ ፡ ከሚያወርሰው ፡ ክብር ፡ የዘለዓለም ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ፤ መተከልን ፡ መጽብ፡
እድርጎላቸው ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ፡ አሰ ።

፲ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ ይሴባሕ ፡ በቅዱሳኒሁ ።
በመላእክት ፡ ቃል ፡ እየተመሰገነ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወይትአኰት፡ በእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡ (ቈላ ፡፫ ፡፬ ፡)
በሚያምኑት ፡ በምእመናንም ፡ ቃል ፡ እየተመሰገነ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ።
እስመ ፡ ይትአመነነ ፡ ስምዕነ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ (ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
ስምዕነ ፡ በላዕሌክሙ ፤ ይትአመነነ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡) ለናንት ፡ የመሰከርነው ፡ ምስክ
ርነት ፡ በዕለተ ፡ ምጽኣት ፡ ለናንት ፡ ይረዳልና ።

፲፩ ወበእንተዝ ፡ እጼሊ ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲኣክሙ ፡ (፩ ፡ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፪ ።)
ስለዚህም ፡ ዅልጊዜ ፡ ስለናንት ፡ እጸልያለሁ ።
ከመ ፡ ይክፍልክሙ ፡ ለዘጸውዐክሙ ፡ እግዚኣብሔር ።
አግዚኣብሔር ፡ እናንተን ፡ የጠራለትን ፡ መንግሥቱ ፡ ሰማይን ፡ ያወርሳችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለጠራሳት፡ ለመ
ንግሥቱ ፡ ሰማይ ፡ ያበቃችሁ ፡ ዘንድ ።
ወይፈጽም ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ ሣህሎ ።
ይቅርታውን ።
ወሠናይቶ ።
ልጅነትን ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ሣህሉ ፡ ልጅነትን ፡ (ወሠናይቶ ፡ ልጅነትን ፡ መደብ ፡
አድርጎ ፡ ከጽጌ ፡ እስከ ፡ ክዊነ ፡ እሳት ፡ ያለውን ።
ወምግባረ ፡ ሃይማኖት ፡ በኃይሉ ።
ከሐሊነቱንም ፡ አምኖ ፡ የሚሠራውንም ፡ ሥራ ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እጼሊ ።

www.zeyeneta.com

፲፪ ፡ ከመ ፡ ይሰባሕ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በላዕሌክሙ ። የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስሙ ፡ በናንተ ፡ ይመስገን ፡ ዘንድ ።
ወአንትሙሂ ፡ ቦቱ ። እናንተም ፡ በሱ ፡ አምናችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
በከመ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእምላክነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። እንደጌታችን ፡ እንደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቸርነት ፡ መጠን
ወአንትሙሂ ፡ ተሀልዉ ፡ ቦቱ ። እናንተም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ (ውእቱኒ ፡ ሕልው ፡ ብከሙ ፡ ይላል ፡) እሱም በናንት ፡ አድሮ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፡ ንነግረክሙ ፡ እኃዊነ ፡ በእንተ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ወንድሞቻችን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የመምጣቱን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፤ ነገና ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዳይደረግ ።
፪ ፡ ወአንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዑቁ ፡ ኢያደንግፁክሙ ፡ ፍጡነ ። ባንድነቱ ፡ ያላችሁ ፡ እናንት ፡ ምጽአት ፡ በጳውሎስ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳያሸብሯችሁ ፡ ዕወቁ ።
ኢትትሐወኩ ፡ እምእአምሮ ። ነገና ፡ እንደኾነ ፡ ከማወቅ ፡ ወጥታችሁ ፡ አትናወጡ ፡ እንዳትናወጡ ፡ ዕወቁ ።
ኢበመንፈስ ። ልብ ፡ አበላን ፡ ቢሉ ።
ወኢበነገር ። እንደበት ፡ አሰላን ፡ ቢሉ ።
፫ ፡ ወኢበመጽሐፍ ። መጽሐፍ ፡ ቢጽፉ ፡ አንድም ፡ (ኢበመንፈስ ፡) ምትሐት ፡ ቢያሳዩ ፡ (ኢበነገር ፡) ወሬ ፡ ቢያወሩ ፡ (ኢበ መጽሐፍ ፡) መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ቢሉ ።
ከመ ፡ ዘእምኀቤነ ፡ ሰአመ ፡ ትመጽኢ ፡ ዕለተ ፡ እግዚእነ ። ጌታችን ፡ የሚመጣበት ፡ ዕለት ፡ ምጽአትን ፡ ከኛ ፡ እንዳገኙ ፡ አድርገው ፡ ምትሐት ፡ ቢያሳዩ ፡ ወሬ ቢያወሩ ፡ እንዳያሸብሯችሁ ፡ ዕወቁ ።
አልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፡ ወኢበምንትኒ ፡(፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
በምንም ፡ በምን ፡ የሚያስታችሁ ፡ እይኑር ፡ እንዳይኖር ፡ ዕወቁ ።
ለእመ ፡ ኢቀደመ ፡ መጽአ ፡ ዘየሐውክ ፡ ወይትከሠት ።
የሚያሸብር ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ጸሰቀድሞ ፡ ካልመጣ ።
ብእሴ ፡ ዓመፃ ። ዓመፅን ፡ የሚሠራ ።
ወልደ ፡ ሕርትምና ።
ጥፋት ፡ የሚገባው ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ አስቀድሞ ፡ ካልመጣ ።
፬ ፡ ዘሳዊ ።
ወንጀለኛ ።
ወሐሳዊ ፡ ዘያዐቢ ፡ ርእሶ ።
ሐሰተኛ ፡ ራሱን ፡ የሚያበልጥ ።
ወይብል ፡ ሰዙሉ ፡ እነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክ ።

www.zeyeneta.com

ወይንብር ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጻሪሲ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ፡ ፫ ።
ልጁሱ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ክቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብቶ ፡ ራሱን ፡ እንደ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርግ ፡ (አስ ፡) እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ እሠራለሁ ፡ የሚል ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ እስቀድም ፡ ካልመጣ ፡ ዐቁ ፡ ኢያደንግፁከሙ ፡ (ሐቁታ) ከዚህ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰ ፡ ይሐንፅ ፡ አይባልም ፡ ይላል ፡ እንደምንል ፡ አይጣለም ፡ ቤት ፡ አይመሰም ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው አይገባም ፤ ከዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለቱ ፡ ከከተማው ፡ ይገባል ፡ የካህናቱን ፡ ቤት ፡ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኩተመሪብት ፡ ብሉ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰ ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ እንደሆ ፡ ሐንስ ፡ ነው ፡ አይገባም ።

ፍ ፡ ወኢትዜከሩኑ ፡ ከመ ፡ አመ ፡ ሀሎኩ ፡ ኅቤከሙ ፡ እቅደምኩ ፡ ወነገርኩከሙ ፡ ዘንተ ።
ከናንት ፡ ዘንድ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሜ ፡ የተመሰገ ፡ በቅጠል ፤ የሐሳዊ ፡ መሢሕን ፡ በአበባ ፡ የምጽእትን ፡ በፍሬ ፡ መስዬ ፡ እንደነገርኳችሁ ፡ አታስቡምን

፯ ፡ ወይእዜኒ ፡ ተአምሩ ፡ ዘይቅልኦ ፡ እስተርእዮ ፡ እስከ ፡ ይፀጽሕ ፡ ዕድሜሁ ።
እሁንም ፡ ከመታየት ፡ የከለከለው ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።

፯ ፡ እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአት ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፭፮ ።)
የኃጢአት ፡ ተንኮል ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ በሱ ፡ ይደረጋልና ፡ የሚደረግበት ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ። ዝምከሮሙ ፡ ወዝግብሮሙ ፡ የኃልፍ ፡ ወይሠዐር ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፴፰ ።)
ወዳዕሙ ፡ ይእዜሰ ፡ እኁዝ ፡ እስከ ፡ ይትኃደግ ፡ እማእከል ።
ከማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ ተሰይቶ ፡ በመንግሥት ። እንድም ፡ (በማእከል ፡) በማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ በመንግሥት ፡ እስኪጣል ፡ ድረስ ፡ ተጎታል ፡ እንጂ ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ። (አንድም ፡ መልስ ።)
እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአተ ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ።
(እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአት ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ፡ እስከ ፡ ይትኀደግ ፡ እማእከል ፡ ዝለሀ ፡ አቅና ።)
ከማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ ተሰይቶ ፡ በገሃነም ፡ (በማእከል ፡(በማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ በገሃነም ፡ እስኪጣል ፡ ድረስ ፡ የኃጢአት ፡ ተንኮል ፡ ትምህርት ፡ በሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይደረጋልና ፡ ከመታየት ፡ የከለከለው ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።
ወዳዕሙ ፡ ይእዜሰ ፡ እኁዝ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ተገኝቷል ።

፰ ፡ ወይእቲ ፡ እሚረ ፡ ይትከሠት ፡ ወልደ ፡ ዓመፃ ።
ያንጊዜ ፡ በዓመፃ ፡ የተወለደ ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ይገለጻል ።
ኃጥእ ።
ኃጢአተኛ ።
በህለዎ ፡ ያጥፍአ ፡ መንፈሱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ።
የኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈሲ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠፋው ፡ ዘንድ ፡ ያለው ። (ሐተታ) ፡ ዮሐንስ ፡ በረቂቅ ፡ የእሳት ፡ ጦር ፡ ወግቶ ፡ ሲጥሰው ፡ እደረደና ፡ እንዲሁ ፡ አለ ።
ወይሥዕሮ ፡ በእስተርእዮት ፡ ምጽአቱ ። (ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ፡ ፭ ።
መጥቶ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ያጠፋዋል ።
፱ ፡ ወምጽኡቱሰ ፡ ለዝንቱ ፡ በኃይል ፡ ሰይጣን ፡ ወኩሉ ፡ ግብረ ፡ ሐሰት ።
የዚህ ፡ የሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ አመጣጡ ፡ ሰይጣን ፡ የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ እያደረገለት ፡ ነው ።
በሠሉ ፡ ኃይል ።
ምውት ፡ በማንሣት ።
ወትእምርት ።
ድውይ ፡ በመፈወስ ።
ወመንክር ፡ ዘሐሰት ። (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፬ ።)
ጋኔን ፡ በማውጣት ።

www.zeyeneta.com

፩ ፡ ጠበሰሉ ፡ አስሕቶ ፡ ዘንጢአት ፡ ዕሕርቱግን ። (፪ቆሮ ፡ ፲፫፡ ፩ ፡ ፫ ።)
ሕርቱግንን ፡ በግሳት ፡ ያምትሐት ፡ ተአምራት ፡ እያደረገለት ፡ ነው ፡ (ዘንጢአት ፡ አሰ ፡) አስሐተ ፡ ዝ ፡ ጴውሎስ ፡ ካለው ፡ ሲለይ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፮ ።)
እስመ ፡ ኢተወክፉ ፡ ፍቅረ ፡ ቃሰ ፡ ጻድቅ ፡ በዘየሐይዉ ።
በሚያምኑ ፡ በሚድኑ ፡ ገንዘብ ፡ ወዶ ፡ በሠራት ፡ በወንጌል ፡ ፀቱኬ ፡ ኢያስሕክሙ ፡ ያለውን ፡ አልተቀበሉምና ።
፲፩ ፡ ወበእንተዝ ፡ ይፈኑ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይለ ፡ መስሕተ ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ፡)
(ስለዚህ ፡ (ኃይለ ፡ መስሕተ ፡) የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ያዝዝባቸዋል ፡ ኃይለ ፡ መስሕት ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚያመጣውን ፡ የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ያዝዝባቸዋል ።
ከመ ፡ ይእመኑ ፡ በሐሰት ።
በሐሰተኛው ፡ መሢሕ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ።
፲፪ ፡ ከመ ፡ ይትኰንኑ ፡ ዅሎሙ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ በጽድቅ ። (ሕዝ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ።)
በውነተኛው ፡ መሢሕ ፡ የማያምኑት ፡ ኹሉ ፡ ይፈረድባቸው ፡ ዘንድ ።
ወየኀብሩ ፡ በዓመፃ ።
በክህደት ፡ አንድ ፡ የሚኾኑት ፡ ኹሉ ፡ ይፈረድባቸው ፡ ዘንድ ።
፲፫ ፡ ወንሕነሰ ፡ አኃዊነ ፡ ርቱዕ ፡ ናእኩቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲአከሙ ፡ እለ ፡ አፍቀረክሙ ፡ እግዚአብሔር ። (ም ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
ወንድሞቻችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለወደዳችሁ ፡ ስለናንተ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እኛ ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባል ።
እስመ ፡ ኀረየከሙ ፡ ወተሣሃለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርእሰ ፡ ሕይወት ፡ ወተቀድሶ ፡ መንፈስ ፡ ወበሃይማኖተ ፡ ጽድቅ ። (፪ጴ ፡ ፩ ፡ ፩ ።)
የሕይወት ፡ መገኛ ፡ የልጅነት ፡ ባሰቤት ፡ እግዘአብሔር ፡ (ኀረየከሙ ፡ ወተሣሃለክሙ ፡ በሃይማኖተ ጽድቅ ፡) በሃይማኖት ፡ መርጧችኋል ፡ ይቅር ፡ ብሏችኋልና ። አንድም ፡ የሕይወት ፡ ባለቤት ፡ የሕይወት መገኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ኀረየከሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ተሣሃለክሙ ፡ በተቀድሶ ፡ መንፈስ ፡) በሃይማኖት ፡ መርጧችኋል ፡ በልጅነት ፡ ይቅር ፡ ብሏችኋልና ።
፲፬ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ጸውዐክሙ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌሉ ።
በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ አናንተን ፡ በጠራበት ፡ በሃይማኖት ፡ መርጧችኋልና ።
ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ በሰብሐቲሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌትነቱን ፡ መርሳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ (ክብሩንም ፡ ብትል ፡) እንድም ፡ (ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ በሰብሐቲሁ ። ዘበእንቲአሁ ፡ ጸውዐክሙ ፡) በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ እናንተን፡ የጠራለትን ፡ ክብሩን ፡ ጌትነቱን ፡ መርሳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ መርጧችኋልና ።
፲፭ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ቁሙ ።
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጽኑ ።
ወዕቀቡ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘመሀሩክሙ ፡ ወሠርውክሙ ፡ ዘበቃልነ ።
ኪቃላችን ፡ እግኝተው ፡ ያስተማሯችሁን ፡ ትምህርት ።
ወዘበመጽሐፍነ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፮) ።
ከመጽሐፋችን ፡ እግኝተው ፡ የሠሩላችሁን ፡ ሥርዓት ፡ ጠብቁ ። አንድም ፡ ዘበቃሉሙ ፡ መዘበመጽሐፎሙ ፡ ይላል ፡ ኪቃላችን ፡ አግኝተው ፡ በቃላቸው ፡ ያስተማሯችሁን ፡ ትምህርት፡ ከመጽሐፋችን ፡ አግኝተው ፡ በመጽሐፋቸው ፡ የሠሩላችሁን ፡ ሥርዓት ፡ ጠብቁ ።
፲፮ ፡ ወውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
እሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ወእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ዘአፍቀረነ ።
የወደደን ፡ አግዚአብሔር ፡ አብ ።
ወወሀበነ ፡ ፍሥሓ ፡ ዘለዓለም ።
ልጅነትን ፡ የሰጠን ።

www.zeyeneta.com

ወተስፋ ፡ ሠናየ ።
በጎውን ፡ ሃይማኖት ፡ የዕጠን ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፯ ፡ ጸጋሁ ፡ ውእቱ ፡ ያስተፍሥሕከሙ ፡ ልበክሙ ።
ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ። አንድም ፡ (በጸጋሁ ፡) በጸጋው ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ። እንድም ፡ (ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡) የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋው ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ።
ወያጽንዕክሙ ፡ በሁሉ ፡ ምግባር ፡ ወበሁሉ ፡ ቃል ፡ ሠናይ ። (፩ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡)
በበጎው ፡ ሥራ ፡ በበጎው ፡ አንጋገር ፡ እንድትጸኑ ፡ ያድርጋችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ጸልዩ ፡ ለነ ፡ (ቈላ ፡ ፬ ፡ ፫ ።)
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጸልዩልን ።
ከመ ፡ ይሩጽ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሰባሕ ፡ በከመ ፡ በኀቤክሙ ።
ወንጌል ፡ ክናንት ፡ ዘንድ ፡ እንደተገለጠ ፡ ክሹሉ ፡ ደርሶ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ።

፪ ፡ ወከመ ፡ ንድኃን ፡ እምሰብአ ፡ እኩያን ፡ ወዓላውያን ።
ክክፉ ፡ ሰዎች ፡ ከዓላውያን ፡ እጅ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ።
እስመ ፡ አኮ ፡ ኩሉ ፡ ዘየአምን ።
ኹሉ ፡ የሚያምን ፡ አይደለምና ፡ ንድነን ፡ አምሰብአ ፡ እኩያን ፡ አንድም ፡ ኹሉ ፡ ያመነ ፡ አይደለ ምና ፡ ይሩጽ ፡ ወይሰባሕ ።

፫ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ሣእምን ፡ ወጸድቅ ፡ ዘያጸንዓክሙ ፡ ወያቅበበክሙ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፱ናን ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።)
በሃይማኖት ፡ የሚያጸናችሁ ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የሚጠብቃችሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የታመነ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፬ ፡ ንትአመነክሙ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክሙ ፡ ትግበሩ ፡ ዘእዘዝናክሙ ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፮ ። ገላትያ ፡ ፭፡፲ ዘእዘዝናክሙ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትግበሩ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዘን፡ እግዚአብሔር ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ ያዘዝናችሁን ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ትፈጽሙት ዘንድ ፡ እንማልዳችኋለን ።
ወገበርክሙሂ ።
እንደገና ፡ ትሉኝ ፡ አንደኾነ ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ሠርታችሁታል ።

፭ ፡ ወእግዚእነ ፡ ያርትዕ ፡ ልበክሙ ፡ ውስተ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውስተ ፡ ተስፋሁ ፡ ለክርስቶስ ።
ጌታችን ፡ ልቡናችሁን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደመውደድ ፡ በክርስቶስ ፡ ወደሚገኝ ፡ አለኝታ ፡ ያቅናው

ክፍል ፡ ፪ ።

፮ ፡ አኃዊነ ፡ ንኤዝዘክሙ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ወንድሞቻችን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ታዝዘን ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ኾነን ፡ እናዝዛችኋለን ።
ተግኅሥዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቢጽ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በትምይንት ፡ ወአኮ ፡ በሥርዐት ፡ ዘሠራዕናሆሙ ፡ ግቱ ፡ (፲፰ ፡ ፲፯ ፡ ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲ ።)
እኛ ፡ በሠራንላችሁ ፡ ሥርዓት ፡ ያይደለ ፡ በተንኰል ፡ አነዋወር ፡ የሚኖሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ተለ ያዩዋቸው ፡ ብለን ፡ እናዝዛችኋለን ።

www.zeyeneta.com

፮ ፣ ለሊከሙ ፣ ተአምሩ ፣ ከመ ፣ ርቱዕ ፣ ትትመሰሉን ።
እኛን ፣ ትመስሉ ፣ ዘንድ ፣ እንዲገባ ፣ እናንት ፣ ቅሉ ፣ ታ ውታሳችሁ ።
ከመ ፣ አሰላዕነ ፣ ላዕሌከሙ ፣ (፩ ፣ ቆሮ ፣ ፬ ፣ ፲፮ ፣ ፩ ፣ ተሰ ፣ ፪ ፣ ፮ ።)
ለክብታችሁ ፣ እንሣልላሳን ።
ፎ ፣ መኢበሳዕነ ፣ እክል ፣ ባዕድ ፣ ብከንቱ ።
አስተምረናል ፣ ብለን ፣ ሳንጽር፡ ሳንግር ፣ ከጠቃችሁት ፣ እንጻልተመጥበን ።
ዘእንበለ ፣ ዳዕሙ ፣ ዘንጸሙ ፣ ወንወርሕ ፣ መንልተ ፣ ወሌሊተ ፣ ወንትጌስር ፣ (፩ ፣ ቆሮ ፣ ፬ ፣ ፲፪ ።)
በመዓልትም ፣ በሌሊትም ፣ ተግፃረ ፣ እደ ፣ ይዘን ፣ ሌት ፣ ከሰጺት ፣ ቀን ፣ በትምህርት ፣ ደክመን ፣ እንመ
ገባለን ፣ እንጂ ።
ከመ ፣ ኢናክብድ ፣ ላዕሌክሙ ።
እናንተን ፣ እንዳናስቸግር ፣ በናንተ ፣ ሥርዓት ፣ እንዳናጸና ።
፱ ፣ ወአኮሰ ፣ ዘኢኮነ ፣ ብውሐነ ፣ (ማቴ ፣ ፲ ፣ ፲ ።)
እንዲሀም ፣ ማለታችን ፣ አስተምሮ ፣ ዋጋ ፣ መብላት ፣ የማይገባን ፣ ኾኖ ፣ አይደለም ።
ዳዕሙ ፣ እርአያ ፣ ከመ ፣ ንኩንከሙ ፣ ከመ ፣ አንትሙ ፣ ትትመሰሉን ፣(፩ ፣ ቆሮ ፣ ፬ ፣ ፲፮ ።)
እኛን ፣ እንድትመስሉን ፣ አብነት ፣ እንኾናችሁ ፣ ዘንድ ፣ ነው ፣ እንጂ ።
፲ ፣ ወአመኒ ፣ ሀለውኩ ፣ ኀቤከሙ ፣ ዘንተ ፣ አዘዝኩክሙ ።
ከናንት ፣ ዘንድ ፣ በነበርሁ ፣ ጊዜ ፣ ይህን ፣ ነግረያችኋልሁ ።
ዘኢይፈቅድ ፣ ይትቀነይ ፣ ኢይሲሰይ ፣(ዘፍጥ ፣ ፫ ፣ ፲፮ ።)
መስከ ፣ እሽ ፣ አይመገብ ፣ ብዬ ።
፲፩ ፣ ለግዕነ ፣ ከመቦ ፣ እምውስቴትከሙ ፣ እለ ፣ የሐውሩ ፣ በሠኪት ።
ምን ፣ ስምተሀብናል ፣ ትሉኝ ፣ እንደኾነ ፣ ክናንት ፣ ወገን ፣ በሀከት ፣ አናዋር ፣ የሚናሩ ፣ ሰዎች ፣ እን
ዳሉ ፣ ሰምተናል ፤ መለክ ፣ ሲያሹ ፣ ውሉ ፣ ከሰው ፣
ሰዶቃ ፣ መመራትን ፣ ውክት ፣ እላት ።
ወአልቦ ፣ ዘይትቀነዩ ፣
ቅጣሬ ፣ እድ ፣ የማይበቍ ፣ ክናንት ፣ ዘንድ ፣ እንዳሉ ፣ ሰምተናል ።
ዓዲ ፣ መስተሐውራን ።
በዚያም ፣ ላይ ፣ ነገር ፣ አዋላጅች ፣ ናቸው ፤ ሥራ ፣ ከፈቱ ፣ ይህ ፣ ይተፈልን ።
፲፪ ፣ ወእለ ፣ ከመዝ ፣ ንኤዝዞሙ ፣ ወንጌሥጾሙ ፣ በሰሙ ፣ እግዚእነ ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ።
እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ያሉትን ፣ ጌታችን ፣ ኢያሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ አዘዜችኋል ። ብለን ፣ በጌታችን ፣ በኢየ
ሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ሰም ፣ እንመክራቸዋለን ፣ እናስተምራቸዋልን ።
ከመ ፣ በየውሃት ፣ ወበጽምው ፣ ይትገበሩ ፣ ተግባሮሙ ፣ ወይሲሰዩ ፣ ሲሳዮሙ ፣ (፩ ፣ ተሰ ፣ ፬ ፣ ፲፩ ።)
በጸጥታ ፣ በዝግታ ፣ በቅንነት ፣ ኾነው ፣ ተግባረ ፣ እድ ፣ ይዘው ፣ ይመገቡ ፣ ዘንድ ።
፲፫ ፣ ወእንትሙሂ ፣ አኃዊነ ፣ ኢትትሀክፉ ፣ ገቢረ ፣ ሠናይ ፣ ዝ኉ ፣ ጊዜ ፣ (ገላት ፣ ፮ ፣ ፱ ።)
አሁንም ፣ ወንድሞቻችን ፣ ምግባር ፣ ሃይማኖት ፣ ከመሥራት ፣ ቸል ፣ አትበሉ ።
፲፬ ፣ ወእመቦ ፣ ዘኢይትኤዘዝ ፣ ሲቃልክሙ ፣ ወለመጽሐፍከሙ ፣ ይትረሰዋ ። (ማቴ ፣ ፲፰ ፣ ፲፯ ። ፩ ፣ ፩ቆሮ ፲ ፣ ፱ ፣ ፲፩ ።)
በቃላችሁ ፣ ላስተማራችሁት ፣ ትምህርት ፣ በመጽሐፋችሁ ፣ ለሠራችሁት ፣ ሥራት ፣ የማይታዘዝ ፣
ቢኖር ፣ እንድም ፣ ለቃልነ ፣ ወለመጽሐፍን ፣ ይላል ፤ ከቃላችን ፣ አግኝታችሁ ፣ በቃላችሁ ፣ ለአስተማራ
ችሁት ፣ ትምህርት ፣ በመጽሐፋችሁ ፣ ለሠራችሁት ፣ ሥርዓት ፣ የማይታዘዝ ፣ ቢኖር ፣ ይለይ ።
ወኢትትሀወልዎ ፣ እትገናኙት ።
ከመ ፣ ይትኀፈር ፣ ይገሠጽ ፣ ዘንድ ።
፲፭ ፣ ወከመሰ ፣ ጸላኢ ፣ ኢትረስይዎ ፣ እንደባዕድ ፣ ግን ፣ አታድርጉት ።
አላ ፣ ገሥጽዎ ፣ ከመ ፣ እኁከሙ ፣ (ማቴ ፣ ፲፰ ፣ ፲፭ ።)

www.zeyeneta.com

ሠላሮሚችሁ ፡ እንደሰውነቱ ፡ ልንደርግሽሃን ፡ አንድትመለሩ ፡ እንድትገሥፁ ፡ ምክሩት ፡ ጸጸተም
ሩት ፡ አንጂ ።

ጀ ፡ መውጫው ፡ አምላክ ፡ ቁጣ ፡ የፀብክሙ ፡ በላይ ።
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባልቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹልጊዜ ፡ አንድነቱን ፡ ይስማችሁ ።
መበሰሉ ፡ ኅብር ። ስሥራው ፡ ኹሉ ፡ ያኑሯን ፡ ይሰማችሁ ።
መአግሢአን ፡ የሀሉ ፡ ምላለ ፡ ዘቅሕሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፴፫ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።)
ጌታችን ፡ ዘበሰማየ ፡ ታይ ፡ አደርግችሁ ፡ ይጉር ።

፲፯ ፡ ዘንተ ፡ አምን ፡ አሐፍዙ ፡ ለክሙ ፡ በእደየ ፡ አነ ፡ ጸውሎስ ፡ (፩ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፭፩ ።)
ይህን ፡ ከታብ ፡ እኔ ፡ ጸውሎስ ፡ ዘጀ ፡ ፈናኩሳችሁ ፡ (ሐዋታ ፡ ፲) አንዳለፈው ።
ወበንቱ ፡ ትእምርትየ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መጻሕፍትየ ።
በምጽፈው ፡ ከታብ ፡ ኹሉ ፡ ምልክቴ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲፰ ፡ ዝሙዝ ፡ እጽሕፍ ፡ አጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ፡ (ደሒሞ ፮ ፡ ፳፪ ፡
አንዲህ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እያልሁ ፡ እጽፋለሁና ፡ ጸጋ ፡ ኢኃ ፡ ያለበት ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ተሞክሉት
የሌለበት ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ አትቀበሉት ፡ ለማለት ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
አሜን ፡ ፡ ፡

www.zeyeneta.com

ፍኖ ፡ ወዙሉ ፡ አመክሩ ።
ኹሉንም ፡ መርምሩ ።
ወዘሠናየ ፡ አጽንዑ ፡ (ሮሜ፡ ፪፡ ፲፫፡ ፭፡ ዮሐ፡ ፬፡ ፩ ።)
የክፉውን ፡ ትታችሁ ፡ የበጎውን ፡ ያዙ ።
ፍፁ ፡ ወተግነሙ ፡ አምዙሉ ፡ ምግባር ፡ እኩይ ።
ከክፋው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተለዩ ።
ፍፁ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሰላም ፡ ይቀድስክሙ ፡ ፍጹመ ፡ (ሮሜ ፡፲፭ ፡፴፫ ።)
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጹም ፡ ክብር ፡ ያክብራችሁ ።
ወያጥሚክሙ ፡ ነፍስክሙ ፡ ወመንፈስክሙ ፡ ወሥጋክሙ ።
በሥጋ ፡ በነፍስ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ያደርጋችሁ ።
በንጽሕ ፡ አስክ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
(ይቀድስክሙ ፡ በንጽሕ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡) ጌታችን ፡ እስኪመጣባት ፡አስክ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ በን
ጽሕና ፡ አንድትጸኑ ፡ ያድርጋችሁ ።
ፍፀ ፡ ወዘጸውዐክሙ ፡ ጸድቅ ፡ ውእቱ ፡ ይግበር ፡ ለክሙ ። (ፍ፡ ቁሮ፡ ፩፡፱ ፲ ፲፫፡ ፪፡ተሰ፡ ፫፡ ፫፡፪፡ጢሞ፡ ፪፡፲፫።)
በሃይማኖት ፡ የጠራችሁ ፡ እርሱ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ይግበር ፡ ለክሙ ፡ ይህን ፡
ያደርግላችሁ ፡ አንድም ፡ ይህን ፡ ያደርግላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።
ፍፆ ፡ አአኃዊነ ፡ ጸልዩ ፡ ለነ ።
ወንድሞቻችን ፡ ጸልዩልን ።
ፍፈ ፡ አምኑ ፡ ዙሉ ፡ አኃዊነ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ። (ሮሜ ፡፲፮ ፡፲፮ ።)
ከኤላው ፡ ከይሁዳ ፡ ከዲያብሎስ ፡ በተለየ ፡ ሰላምታ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አሳችሁን ፡ በሉ።
ፍፈ ፡ አምሕለክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ታንብብዋ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ላዕለ ፡ ዙሉ ፡ አኃዊነ ፡ ቅዱሳን ።
ይህችን ፡ ከታብ ፡ ለምእመናን ፡ በጥባኤ ፡ ታስሟት ፡ ዘንድ ፡ ሐዋርያትዓለች ።ከግዝት መሐላ
ይቀላል ፡ ብሎ ፡ አምሕለክሙ ፡ አለ ፡ ከግዝትም ፡ መሐላ ፡ እንዲቀል ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ።
ፍፍ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምኩሕሙ ።(ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፬፡ ፊል፡ ፬፡ ፳፫ ።)
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ።
አሜን ።(ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፡ ፳፬፡ ፊል፡ ፬፡ ፳፫ ።)
በውነት ።

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኅበ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በአቴና ፡
ወተፈነወ ፡ ምስለ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወስልዋኖስ ።

በአቴና ፡ የተጻፈ ፡ በጢሞቴዎስና ፡ በስልዋኖስ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ በተሰሎንቄ ፡ ላሉ ፡ ለምች ፡ የተ
ላከ ፡ ከታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
መክብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።
አንግሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.zeyeneta.com

ሠዋኢ ግቡኦ ፡ እንዘ ይሜህሮሙ ፡ ወይነግሮሙ ፡ እንዘ ይትመሐፀኖሙ ፡ እንድኅላ ፡ ኮነ ፡ ኮኑ ፡ ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ ኀበ ፡ ሐነጸ ፡ ሰሎሞን ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤል ፡ ወአምጽኡ ፡ ሀገረ ፡ ሰማርያ ፡ ወአቅመዩ

www.zeyeneta.com

ጢሞቴዎስ፡ያሉዋሪን ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ኤባቱ ፡ ኣረማዊ ፡ ነው ፡ እናቱ ፡ ኣይሁዳዊት ፡ ናት ፡ በጳውሎስ ፡ ስብከት ፡ እምናለች ፡ ወእሙሰ ፡ አይሁዳዊት ፡ ወአምነት ፡ እንዲል ። ግብ ፡ (ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ።)

በጎ ፡ ብላቴንነቱን ፡ አይቶ ፡ ሲሻው ፡ አይቶ ፡ ክፍጹምነት ፡ እንዲደርስ ፡ ወውቶ ፡ ኃይለክትሎታል ፡ ሲያ ስክትለውም ፡ ዋዘር ፡ አስክትሎታል ፡ ወገዘር ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ በእንተ ፡ አይሁድ ፡ እሉ ፡ ውስቴ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፫ ።) ኃላም ፡ ክፍጹምነት ፡ እንደ ፡ ዶሪስ ፡ ወውቶ ፡ በኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሞታል ። ኃላም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሰውን ፡ ሹም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያልውን ፡ አትሹም ፡ እያለ ፡ ሲያጸና ፡ ጽር ፡ ይሰድለታል ። እስተበቍዐከ ፡ ቀዳሚ ፡ ዙሉ ፡ ትግበር ፡ ጸሎተ ፡ ወሰኢለ ፡ ወተጋንየ ፡ ወበእን ተዝ ፡ ጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ዙሉ ፡ ሰብእ ፡ ወላዕለ ፡ ዙሉ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ ይላል ። (ም ፡ ፪ ፡ ፩ ።)

ወከማሁ ፡ አንስትኒ ፡ ይትረሰያ ፡ ለጸሎት ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበኃፍረት ፡ ወበልቡና ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፱ ።) እሙን ፡ ነገር ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ሣናየ ፡ ግብረ ፡ ፈተወ ፡ ይላል ። (ም ፫ ፡ ፩ ።ወዲያቆ ናትኒ ፡ ከማሁ ፡ ንጹሓን ፡ ወአስተርኩባን ፡ አለ ፡ (፩ ፡ ቃሉሙ ፡(ም ፫ ፡ ፱ ።)

አለ ፡ ሠናየ ፡ ይትለእኩ ፡ እንተ ፡ ቲዐቢ ፡ ሚመተ ፡ ይግበሩ ፡ ሉሙ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ዐቅ፡ርአስከ ፡ በእ ንተ ፡ አንብሮ ፡ ወዘልፈ ፡ ህሉ ፡ ባቲ ፡ ይላል ፡ ሊቃናተ ፡ ኢታመጥቀ ። ም ፡ ፭ ፡ ፩ ።)

አክብር ፡ ዕቤራተ ፡ በጽድቅ ፡ ይላል። (ም ፡ ፭ ፡ ፫ ።)
ወሰአመ ፡ ጎረይክ ፡ ዕቤረ ፡ ጎረይ ፡ እንተ ፡ ኟ ፡ ከረምታ ፡ ይላል ። (ም ፡ ፭ ፡ ፱ ።)
እለ ፡ ሠናየ ፡ ተልእኩ ፡ ቀሲሳን ፡ ምክዕቢተ ፡ ክብር ፡ ይደልዎሙ ፡ ይላል ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።)
ላዕለ ፡ ልሒቅ ፡ ኢትስግዕ ፡ ውዲተ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።)
ወኢታጽድቆ ፡ ሰሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ፍትሕ ። ወኢትግዒ ፡ ፍጡን ፡ ወኢመነሂ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፳፩ ።)
ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ፡ ጎዳጠ ፡ ወይነ ፡ ቶስሕ ፡ ይላል ፡(ም ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ፫ ።)
ከዚያም ፡ ለአብዕልተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ አዝዞሙ ፡ከመ ፡ ኢይትአበዩ ፡ ወኢይትአመንዎ ። ሰብዕሎሙ ፡ ኃላፊ ፡ ይላል ፡ (ም ፮ ፡ ፲፯ ፡) የተጻፈበት ፡ አገር ፤ አቴና ፡ ከታብ ወባጅ ፡ ቲቶ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ፡ ወኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ቀስፋኑ ። (ቆላ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።)

በመድኃኒታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ባለኝታችን ፡ በየኢሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ። አንድም ፡ (በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ ወተስፋነ) ፡ መድኃኒታችን ፡ አለኝታችን ፡ በሚኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ስውን ፡ አጸና ዘንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ።

፪ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ወልደየ ፡ ዘአፈቅር ፡ በሃይማኖት ። (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፬) ።

በሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ምግባር ፡ ሲሠራ ፡ ባገኘው ፡ ለምወደው ፡ ለልጄ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ትድረስ ። ብዙ ፡ ቢወልዱ ፡ ሞያውን ፡ ምግባሩን ፡ አይቶ ፡ አንዱን ፡ ይወዱ ፡ እንዲሉ ።

ስላም ፡ ለከ ። ቸር ፡ አለህን ።
ወሣህል ። ይቅርታ ፡ ይደረግልህ ።
ወጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርብህ ፡ ይደረግልህ ።

፫ ፡ እስመ ፡ እስተብቍዕኩከ ፡ ትንበር ፡ ኤፌሶን ፡ እመ ፡ አሐውር ፡ መቄዶንያ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፩ ።)

ወደመቄዶንያ ፡ በሐድሁ ፡ ጊዜ ፡ በኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሜሃለሁ ፡ እኮ ።
ከመ ፡ ትግሥጾሙ ።

ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ በኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሚሃለሁና ፡ እን ዲህ ፡ የሾምሁህ ፡ ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.zeyeneta.com

ከመ ፡ ኢያምጽኡ ፡ ካልእ ፡ ትምህርተ ።
እኛ ፡ ካለስተማርነው ፡ ትምህርት ፡ ሌላ ፡ እንዳያመጡ ፡ (አለ ፡) አሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ።
፬ ፡ ወኢያምጽኡ ፡ መኃድምተ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፯ ።)
ተረት ፡ አሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ። ተረት ፡ ለራት ፡ መቆያ ፡ እንደኾነ ፡ አሪትም ፡ ለመንገል ፡ መቆያ ፡ናትና ።
ወዛውዐ ፡ ነገር ፡ ዘይፈጥሩ ።
ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ የሚናገሩትን ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ነገር ፡ እንዳያመጡ ፡ (አለ ፡) አሪትን ፡ እንዳያስተምሩ
በዘያስሕቱ ። ሰውን ፡ በሚያስቱ ፡ ገንዘብ ።
ወያመጽኡ ፡ ተጎሥሞ ።
ጸብ ፡ ከርከርን ፡ በሚያመጡ ፡ ገንዘብ ፡ ዘይፈጥሩ ።
ወየኀድጉ ፡ ሕገ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ዘሃይማኖት ።
እንድነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ ትተው ፡ ኢያምጽኡ ፡ ካለአ ።
፭ ፡ ወግኅለቅቱሰ ፡ ለትእዛዝ ፡ ተፋቅሮ ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)
ወያመጽኡ ፡ ተጎሥሞ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የትእዛዝስ ፡ ፍጻሜው ፡ ከቲም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ልቡና ፡ ኾኖ ፡ ፍቅርን ፡ መያዝ ፡ ነው ።
ወበሠናይ ፡ ግእዝ ።
በበጎው ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ።
ወሃይማኖት ፡ ዘአልቦ ፡ ኑፋቄ ።
መጠርጠር ፡ በሌለበትም ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ፍቅርን ፡ መያዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፮ ፡ እስመቦ ፡ እለ ፡ አውከኩ ፡ ወገብኡ ፡ ውስተ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፳ ።)
ውስተ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ ውስተ ፡ ነገረ ፡ ከንቱ ፡ ይላል ፡ ከወንጌል ፡ ወጥተው ፡ ወደአሪት ፡ የተመለሱ ፡ አሉና ፡ ከመ ፡ ትገሥጾሙ ።
፯ ፡ ወእንዘ ፡ ይፈቅዱ ፡ መምህራነ ፡ ይኩኑ ፡ ኢያእምሩ ፡ ዘለሊሆሙ ፡ ይነብቡ ፡ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፳ ።)
መምህራን ፡ ሊኾኑ ፡ ሲወዱ ፡ የሚናገሩትን ፡ አያውቁትም ፡ (አለ) ፡ ምሥጢሩን ። አንድም ፡ ንባቡ ፡ አሪት ፤ ትርጓሜው ፡ ወንጌል ፡ እንደሆነ ፡ አያውቁትም ።
፰ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ኦሪት ፡ ለዘይገብሮ ፡ በሕጉ ፡ (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።
አሪትን ፡ እየነቀፈ ፡ መጥቶ ፡ ነበረና ፡ አሪትስ ፡ ሕጉን ፡ ለሚፈጽመው ፡ በሕጉ ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ ደግ ፡ ሕግ ፡ ነው ።
፱ ፡ ወነአምር ፡ ዘኒ ።
ይህንም ፡ እናውቃለን ፡ (አለ ፡) የሚያመጣውን ።
ከመ ፡ አኮ ፡ ለጻድቃን ፡ ዘይሠራዕ ፡ ሕግ ።
ሕግ ፡ የሚሠራው ፡ ለጻድቃን ፡ እንዳይደለ ።
ዘእንበለ ፡ ለኃጥኣን ።
ለኃጥኣን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወለጽልሕቶን ። ለከዳተኞች ።
ወለዝሉፋን ።
ኃጢኣት ፡ አዘውታሮች ፡ ደፋሮች ፡ ተሳዳቦች ፡ ሴሰኞች ።
ወለውፁዐን ፡ እምጽድቅ ።
ከጽድቅ ፡ ለወጡ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወለርኩሳን ፡ ልብ ።
ልቡናቸው ፡ ድል ፡ ለተነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወቀተልተ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወእሞሙ ።
እናት ፡ አባታቸውን ።
ወቀተልተ ፡ አዝማዲሆሙ ።
ኢያቶቻቸውን ፡ ለማይረዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አክብር ፡ አባክ ፡ ወእመክ ፡ ብሎ ።

www.zeyoneta.com

ወቀተልተ ፥ ነፍሰ ፥
ነፍቅ ፥ ለጢንሱ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢትቅትል ፥ ነፍሰ ፥ ብሎ ።

፲ ፥ ዘማውያን ።
ለሴሰኞች ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢትዘምው ፥ ብሎ ።
ወአለ ፥ የሐውሩ ፥ ብእሲተ ፥ ብእሲ ።
ከንቱልየንላ ፥ ሚስት ፥ ለሚሔዱ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢትሔው ፥ ብሎ ፥ ብእሲተ ፥ ብእሲ ፥ ተብሎ ።
ሰረቅተ ፥ ሰብአ ፥ (ዘፀአ ፥ ፳፩ ፥ ፲፮ ።)
ሰውን ፥ እያፈኑ ፥ ለሚሸጡ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ሰረቅት ፥ የሰውን ፥ ከብት ፥ ለሚሰርቁ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢት
ስርቅ ፥ ብሎ ።
ሐሳውያን ።
(ሰብአ ፥ ሐሳውያን ፥) ሐሰት ፥ ለሚናገሩ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢትኩን ፥ ስምዐ ፥ በሐሰት ፥ ብሎ ።
ወአለ ፥ ይምሕሉ ፥ በሐሰት ።
በሐሰት ፥ ለሚምሉ ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ኢትጸውዕ ፥ ስመ ፥ እግዚአብሔር ፥ ፈጣሪክ ፥ በሐሰት ፥ ብሎ ።
ወቦ ፥ ባዕድኒ ፥ ኅዲ ፥ ብዘይትቃወምዋ ፥ ለትምህርተ ፥ ሕይወት ።
ነጣላለትና ፥ ድኅነት ፥ የሚገኝባትን ፥ ትምህርት ፥ በሚቃወሙ ፥ ሰዎች ፥ የተሠራ ፥ ሴላ ፥ ትእዛዝ ፥ አለ ።
፲፩ ፥ ዘወንጌለ ፥ ስብሐቲሁ ፥ ለብዕዕ ፥ እግዚአብሔር ፥ ዘአነ ፥ ተአመንኩ ፥ ቦቱ ፥ (ም ፥ ፩ ፥ ፲፩።)
ይችውም ፥ እኔ ፥ ያመንሁበት ፥ ንውድ ፥ ክቡር ፥ የሚኾን ፥ እግዚአብሔር ፥ በጌትነት ፥ የሠራት ፥ ወን
ጌል ፥ ናት ። አንድም ፥ ንውድ ፥ ክቡር ፥ የሚኾን ፥ እኔ ፥ የአመንሁበት ፥ እግዚአብሔር ፥ በጌትነቱ ፥የሠ
ራት ፥ ድኅነት ፥ የሚገኝባት ፥ ትምህርት ፥ ወንጌልን ፥ በሚቃወሙ ፥ ሰዎች ፥ ከዚህ ፥ ሌላ ፥ የተሠራ ፥ ትእ
ዛዝ ፥ አለ ።
፲፪ ፥ አአሩቶ ፥ ለዘተአመንኒ ።
ለሐዋርያነት ፥ ትበቃለህ ፥ ያለኝ ።
ወአጽንዐኒ ፥ በክርስቶስ ፥ ኢየሱስ ፥ እግዚእነ ፥ (ግብ ፥ ሐዋ ፥ ፱ ፥ ፲፭ ፥ ኅላትም ፥ ፩ ፥ ፲፫ ።)
በጌታችን ፥ በኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ በማመን ፥ ያጸናኝ ፥ እግዚአብሔርን ፥ አመሰግነዋለሁ ።
እስመ ፥ ምእመነ ፥ ረሰየኒ ፥ ለመልእክቱ ።
ወንጌልን ፥ ለማስተማር ፥ ችሎታለሁ ፥ ብሎኛልና ።
፲፫ ፥ እንዘ ፥ ቀዲሙ ፥ ዕራፊ ፥ እኁ ፥ ወሰዳዲ ።
ምእመናንን ፥ ከዋሉበት ፥ አላሳድር ፥ ከአደሩበት ፥ አላውል ፥ የምል ፥ ስኾን ።
ወጸወሪ ።
(ጸራፊ ፥ ወጸወሪ ፥) ክርስቶስን ፥ ዕሩቅ ፥ ብእሲ ፥ መንጌልን ፥ ዬቃላ ፥ ሕግ ፥ የምል ፥ ስኾን ፥ ረሰየኒ ፥
ለመልእክቱ ።
ወባሕቱ ፥ ተማሃለኒ ።
ነገር ፥ ግን ፥ ይቅር ፥ አለኝ ፥ ይቅር ፥ አለኝ ፥ እንጂ ፥ እንዘ ፥ ጸራፊ ፥ ወጸወሪ ።
እስመ ፥ በኢያእምሮ ፥ ገበርኩ ፥ በኢአሚን ።
ሳላውቅ ፥ ባለማመን ፥ ሳላምን ፥ ባለማወቅ ፥ ኦድናጌጥዕሁና ።
፲፬ ፥ ወፈድፋደ ፥ ጸጋሁ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ በላዕሌየ ።
የእግዚአብሔር ፥ ጸጋው ፥ ለኔ ፥ ቦዝቷልኖ ።
ወሃይማኖቱ ፥ ወፍቅሩ ፥ ለኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ እግዚእነ ።
የጌታችን ፥ የኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ፍቅሩ ፥ ሃይማኖቱ ፥ በኔ ፥ ላይ ፥ ጸንቷልና ፥ ተማሃለኒ ።
፲፭ ፥ እሙን ፥ ነገሩ ።
ነገሩ ፥ እውነት ፥ ነው ።
ወርቱዕ ፥ ይትወከፍዎ ፥ በኩሉ ።
በውስጥ ፥ በእፍአ ፥ ሊያምኑት ፥ ይገባል ።
እስመ ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ መጽአ ፥ ውስተ ፥ ዓለም ፥ ከመ ፥ ያድኅኖሙ ፥ ለኃጥኣን ፥ ዘእኒ ፥ ቀዳሚሆሙ ፥
(ማቴ ፥ ፱፡፲፫ ፥ ፲፩) ።

www.zeyeneta.com

እኔ ፡ ፊታውራሪያቸው ፡ አበጋዛቸው ፡ የምኾን ፡ ኃጥአንን ፡ ለማዳን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቷልና ፡ እንደመጣ ፡ የተነገረው ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በውስጥ ፡ በእፍኣ ፡ ሊያምኑት ፡ ይገባል ።

፲፮ ፡ ወባሕቱ ፡ ተማሃለኒ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ ዘእነ ፡ ቀዳሚሆሙ ።
ከመ ፡ ያርኢ ፡ ተአምራቲሁ ፡ በላዕሌየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐኔ ፡ ተአምራቱን ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ።
ወብዝኀ ፡ ትዕግሥቲ ።
የትዕግሥቱንም ፡ ብዛት ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ።
ወእኩኖሙ ፡ እርአያ ፡ ለእለ ፡ የእምኑ ፡ በቲ ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ።
የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ ለማግኘት ፡ ለእመኑበት ፡ ሰዎች ፡ አብነት ፡ እኾናቸው ፡ ዘንድ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ ዘእነ ፡ ቀዳሚሆሙ ።

፲፯ ፡ ንጉሥ ፡ ዘለዓለም ።
የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ እንዲኾነ ፡ ለሚያምኑበት ፡ (ሐተታ) ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ሲለይ ፡ የዘይ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ አንዱ ፡ ሲያልፍ ፡ አንዱ ፡ ሲተርፍ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ማእከለ ፡ ዓለም ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ።
ዘኢይመውት ።
የማይሽር ፡ ኀልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ።
ወኢያስተርኢ ፡ አምላክ ፡ ባሕቲቱ ።
እሱ ፡ ብቻ ፡ የማይታይ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ።
ዘሎቱ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ክብር ፡ ጌትነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ኀንዘቡ ፡ የሚኾን ።
አሜን ። በውነት ።

፲፰ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ አማኅፀንኩከ ፡ እ ፡ ወልድየ ፡ ጢሞቴዎስ ።
ልጄ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ እደራ ፡ ጥብቅ ፡ እንዲሉ ፡ እደራ ፡ አልሃለው ።
በከመ ፡ ተነብዮ ፡ ዘላዕሌክ ።
ባንተ ፡ ያለ ፡ መጻአያትን ፡ እንደማወቅህ ፡ አንድም ፡ ትርጓሜን ፡ እንደማወቅህ ፡ መጠን ፡ አማኅፀንኩከ ።
ከመ ፡ ትጽናዕ ፡ በዝኩ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።)
በበጎው ፡ ገድል ፡ ትጸና ፡ ዘንድ ።

፲፱ ፡ እንዘ ፡ ብኪ ፡ ሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ ይዘህ ።
ወሠናይ ፡ ግዕዝ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፱ ።)
በበጎው ፡ ኅብር ፡ ጸንተህ ።
እስመ ፡ ህለዉ ፡ እለ ፡ አውኀኩ ፡ እምሃይማኖት ፡ ወተሰብሩ ።
ከሃይማኖት ፡ ወጥተው ፡ ደል ፡ የተነሡ ፡ እሱና ፡ ወተሰብሩ ፡ ፈቱ ፡ ነገሥት ፡ ሰዶም ፡ በቃለ ፡ ብእሲት ፡ ስብርት ፡ እንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፲፮ ፡ ፮ ፡) (ተግ ፡ አፈ ፡ ወር ።)
ፎ ፡ እለ ፡ ሄሜኔዎስ ። ፡ ፡ ፡ ናቸው ።
ወእለ ፡ እስክንድሮስ ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬፮ ።)
እሊህ ፡ ናቸው ።
እለ ፡ መጠውክዎሙ ፡ ለሰይጣን ፡ ይትኩንኑ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፭ ።)
ይቀጡ ፡ ዘንድ ፡ ለሰይጣን ፡ እሳልፈ ፡ የሰጠኋቸው ፡ ሲያወግዛቸው ፡ እድሮብኛቸው ፡ የነበረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይለያቸዋል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከተለያቸው ፡ ማንደር ፡ ያለኃጻሪ ፡ አይኖርም ፡ ሰይጣን ፡ ያድርባቸዋልና ፡ እለ ፡ መጠውክዎሙ ፡ ለሰይጣን ፡ ይትኩነኑ ፡ እለ ።
ኢይልመዱ ፡ ፀሪፈ ።
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዴታላ ፡ ሕግ ፡ እያሉ ፡ እንዳያስተምሩ ።

www.zeveneta.com

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፡ አስተበቍዐክ ፡ ቀዳሚ ፡ ሁሉ ፡ ትግበር ፡ ጸሎተ ፡ ወሰኢለ ፡ ወተጋንዮ ፡ (ፊልጵ ፡ ፬ ፡ ፮ ።)
ከሥራው ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጸሎትን ፡ ስዒልን ፡ ተጋንየን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግልደሃለሁ
እንድም ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ጸሎትን ፡ ስኢልን ፡ ተጋንየን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግልደሃለሁ ፡ አብነት፡
ነውና ። አንድም ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጸሎትን ፡ ስኢልን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግልደሃለሁ ፡
ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ነውና ። እንድም ፡ ከኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ ጸሎትን ፡ ስእልን ፡ ተጋንዮን ፡ ታደ
ርግ ፡ ዘንድ ፡ እግልደሃለሁ ። ቀዳሚሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ እግሌቅ ፡ ቀዳሚ ፡ ፍጥረትከ ፡ ብሔሞት ፡ እን
ዲል ፡ ዘኑል ፡ ፳፱ ፡ ፳ ።

፪ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ሁሉ ፡ ሰብእ ።
ሰለዚህ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ጸልዩ ።
ወላዕለ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥት ።
ለነገሥታቱም ፡ ጸልዩ ።
ወለመኳንንት ።
ለመኳንንቱም ፡ ጸልዩ ፡ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወብልጣሶር ፡ ወልዱ ፡ እንዲል ።
ከመ ፡ በህዱዕ ፡ ወበጽምው ፡ ይኩን ፡ ንብረትነ ፡ በሁሉ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጽሕ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጸንተን ፡ እነዋራችን ፡ በጸጥታ ፡ በዕረፍት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ፡ ኅሡ ፡
ሰላማ ፡ ለብሔር ፡ ከመ ፡ ሰላመ ፡ ዚአሃ ፡ ይኩን ፡ ሰላምከሙ ፡ እንዲል ።

፫ ፡ ዝኬ ፡ ሠናይ ፡ ወጎሩይ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፲) ።
በመድኃኒታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ይህ ፡ ነዋ ።
፬ ፡ እሰመ ፡ ውእቱ ፡ ይፈቅድ ፡ ሁሉ ፡ ሰብእ ፡ ይሕየው ፡ (ሕዝ ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፱ ።)
ሰው ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ በዕረፍት ፡ ሊኖር ፡ ይወዳልና ፡ ይኩን ፡ ንብረትነ ።
ወያእምርዋ ፡ ለጽድቅ ።
ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ሊያውቋት ፡ ይወዳልና ፡ በሁሉ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጽሕ ።
፭ ፡ አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ።
አግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (አለ ፡) በተለየ ፡ አካሉ ። አንድም ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ
በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አሐዱ ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ ሊያውቁ ፡ ይወዳልና ።
ወአሐዱ ፡ ጎሩይ ፡ ማእከለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከነ ፡ ሰብአ ፡ (ኢሳ ፡ ፵፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፪ ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ።)
ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስታረቀ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለ ፡ በተ
ለየ ፡ አካሉ ። አንድም ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በሕልውና ፡ ፩
፮ ፡ ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ ቤዛ ፡ ኩሉ ።
ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ራሱን ፡ እሳልፎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ የሰጠ ።
ወኮነ ፡ ስማዕተ ፡ በዕድሜሁ ፡ (ገላት ፡ ፩ ፡ ፬ና ፡ ፪ ፡ ፳ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ።
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ መክራ ፡ የተቀበለ ። እንድም ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የመሰከረ ፡ አንሰ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡
መጸእኩ ፡ ወአንበይነዝ ፡ ተወለድኩ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ስማዕተ ፡ በጽድቅ ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፴፯ ።)
፯ ፡ ዘሎቱ ፡ ተሠየምኩ ፡ ሐዋርያ ፡ ወዓዋዲ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)
ለሩቁ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለቅርቡ ፡ አስተማሪ ። አንድም ፡ ለብዙው ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለጥቂቱ ፡ አስተ
ማሪ ፡ የተሾምሁለት ።
እሙነ ፡ አብል ፡ እውሸት ፡ እናገራለሁ ።
ወኢይሔሱ ። ሐሰት ፡ አልናገርም ።
ተሠየምኩ ፡ መምህረ ፡ ለአሕዛብ ፡ በሃይማኖት ፡ ወበጽድቅ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጸንቼ ፡ አሕዛብን ፡ ለማስተማር ፡ ተሾሚያለሁና ፡ እንደተሾምሁ ፡ እውነት ፡

www.zeyeneta.com

እናገራለሁ ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ። አንድም ፡ በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብን ፡ ለማ
ስተማር ፡ ተሾሚያለሁና ፡ እውነት ፡ እናገራለሁ ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ።
፰ ፡ ወእፈቅድ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይጸልዩ ፡ በኵሉ ፡ ገጸ ፡ መካን ።
ሰው ፡ ኹሉ ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፤ በየጊዜያቱ ፤ በየመሻርጉ ፡ ሊጸልዩ ፡ እወዳለሁ ።
ወያንሥኡ ፡ እደዊሆሙ ፡ በንጹሕ ፡ እንበለ ፡ ኀጕርጓር ፡ ወኑፋቄ ።
ያለቂም ፡ ያለጥርጥር ፡ በንጽሕና ፡ ኾነው ፡ እደ ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጸሎት ፡ እደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ሰመሥዋ
ዕት ፡ ያነሡ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ።
፱ ፡ ወከማሁ ፡ አንስትኒ ፡ ይትረሰያ ፡ ለጸሎት ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ።
ወንዶችን ፡ አሁን ፡ ይጸልዩ ፡ በኵሉ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡ እንዳልሁ ፡ ሴቶችም ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኹነው ፡ ለጸሎት ፡ ይጸረሩ ።
ወበጎፍረት ። ሰውን ፡ በማፈር ፡ ኾነው ።
ወበልቡና ። በተዘከሮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኾነው ።
ወበአንጽሖ ፡ ርእሶን ፡ እምዝሙት ።
ሰውነታቸውን ፡ ከዝሙት ፡ በመሰየት ፡ ኾነው ፡ ሰጸሎት ፡ ይጸረሩ ።
አኮ ፡ በሐብላተ ፡ ወርቅ ።
ይትረሰያ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የወርቅ ፡ እንጥልጥል ፡ በማድረግ ፡ አይደለም ።
ወበባሕርይ ።
ድንቂ ፡ ከሎታ ፡ በማድረግ ፡ አይደለም ።
ወበአልባስ ፡ ቅድው ፡ ዘዕጹብ ፡ ሜጡ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ - ፭) ።
ዋጋው ፡ ብዙ ፡ የሚኾን ፡ ያማረ ፡ ልብስ ፡ በመልበስ ፡ አይደለም ።
ወአኮ ፡ በተጸፍሮ ፡ ሥዕርቶን ።
ጠጕራቸውን ፡ ወግሮ ፡ ሥሉሰ ፡ በመሠራት ፡ አይደለም ።
፲ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘይደልዎን ፡ ሰእንስት ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፲) ።
ለሴቶች ፡ በሚገባ ፡ ግብር ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ቀዲሙ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በትምህርት ፡ ጽድቅ ፡ ወበምግባረ ፡ ሠናይ ።
አስቀድሞ ፡ በውነተኛው ፡ ትምህርት ፡ በበጎው ፡ ምግባር ፡ ጸንቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፲፩ ፡ ብእሲት ፡ በጽምው ፡ ትትመሀር ፡ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፪) ።
ሴት ፡ በዝግታ ፡ በጸጥታ ፡ ኾና ፡ ትማር ።
ወትትአዘዝ ፡ በኵሉ ፡ የውሃት ።
በፍጹም ፡ ቅንነት ፡ ኾና ፡ ሰባሏ ፡ ትታዘዝ ።
፲፪ ፡ ወብእሲትሰ ፡ ትምህር ፡ ኢናበውሓ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፴፬) ።
(ትምህርስ ፡) ልታስተምር ፡ ግን ፡ እናስናብታትም ።
ወኢትመብል ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮) ።
በባሏ ፡ ላይ ፡ አንዳትሠለጥን ፡ አትሠልጥን ።
ዳዕሙ ፡ በጽምው ፡ ተህሉ ።
በጸጥታ ፡ በዝግታ ፡ ኾና ፡ በመታዘዝ ፡ ትኑር ፡ እንጂ ።
፲፫ ፡ እስመ ፡ አዳም ፡ ቀደመ ፡ ተፈጥሮ ።
አዳም ፡ አስቀድሞ ፡ ተፈጥሯልና ።
ወአምድኀረዉ ፡ ሔዋን ፡ (ዘፍጥ ፡ ፪ ፡ ፳፪) ።
ከሱ ፡ በኋላ ፡ ሔዋን ፡ ተፈጥራለችና ፡ ኢትመብል ፡ ላዕሰ ፡ ብእሲ ።
፲፬ ፡ ወአዳምሰ ፡ ኢስሕተ ፡ እላ ፡ ብእሲት ፡ ስሕተት ፡ ወዐሰወት ፡ (ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፫) ።
ሔዋን ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ ኾናለች ፡ እንጂ ፡ አዳም ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ አልኾነምና ፡ ትም
ህር ፡ ኢናበውሓ ።

www.zeyeneta.com

፲፫ ፡ ወባሕቱ ፡ ተሐፍ ፡ በአንቲ ፡ ውሱዳ ።

ስሕተት ፡ ወዐለወት ፡ ብሎ ፡ ነቢርኔ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፀልጆጅ ፡ በእመቤታችን ፡ በጌታችን ፡ ከብራለች ።

ለእመ ፡ ነበሩ ፡ በሃይማኖት ፡ ወተፋቅሮ ፡ ወበቅድሳት ።

በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ የጸኑ ፡ ስለኾኑ ።

አንድም ፡ ትምህር ፡ ኢናበውሃ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጆቿን ፡ ሠርታ ፡ ቀጥታ ፡ ብታሳድግ ፡ ትከብራለች ፡ (ለእመ ፡ ነበሩ ፡ በሃይማኖት ፡) በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ የጸኑ ፡ ቢኾኑ ።

ወበአንጽሖ ፡ ርእሶሙ ፡ በአአምሮ ።

በውቀት ፡ በፈሊጥ ፡ ኾነው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ቢኾኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፩ ፡ እሙን ፡ ነገር ።

ነገሩ ፡ ደግ ፡ ነው ።

ዘይፈቅድ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ሠናየ ፡ ግብረ ፡ ፈተወ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ቅስና ፡ ሊሾም ፡ የወደደ ፡ በጎ ፡ ኅደረጊ ፡ ቢወድ ፡ አይደለም ፡ በቅቶ ፡ ቢገኝ ፡ ነው ።

፪ ፡ ወባሕቱ ፡ ርቱዕ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ዘኢያደሉ ፡ ለገጽ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፯) ።

ነገር ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፡ በትምህርት ፡ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ፡ ሊሾም ፡ ይገባል

ዘአልቦ ፡ ምክንያት ።

ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ።

ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ።

ያልደጋመ ፤ (ድንግል ፡ አይሾም ፡ አሳስም

ብአሲ ፡ ንቁህ ።

ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ የነቃ ።

ወጠቢብ ።

ብልህ ፡ አስተዋይ ።

ወመፍቀሬ ፡ ነግድ ።

እንግዳ ፡ ተቀባይ ።

ዘአንጽሐ ፡ ርእሶ ።

ሰውነቱን ፡ ከኃጢአት ፡ የለየ ።

ወምህር ፡ ወመጣሥጽ ።

የሚመክር ፡ የሚያስተምር ። መምህር ፡ ለራሱ ፤ መጣሥጽ ፡ ለሌላው ።

፫ ፡ ዘኢያበዝኅ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፱ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

(መጠጥ ፡ የማያበዛ) ፡ እይጠጣ ፡ አላለም ።

ዘኢያፈጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ ።

ፈጥኖ ፡ የማይማታ ። አንድም ፡ ፈጥኖ ፡ የማይገዝት ።

ባቍዕ ።

መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ የሚረባ ፡ የሚጠቅም ።

ዘኢይትገዓዝ ።

በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ የማይከራከር ።

ዘኢያፈቅር ፡ ንዋየ ።

ኃላፊውን ፡ ክብት ፡ የማይወድ ።

፬ ፡ ዘሠናይ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤቱ ።

የቤቱ ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነለት ።

www.zeyeneta.com

ዘበ ፡ ውሉድ ፡ ዘይትኤዘዙ ፡ በዘሉ ፡ ንጹሕ ፡ (፩ ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)
በንጽሕና ፡ ኾነው ፡ የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ።
ወዘሰ ፡ ኢይክል ፡ ሠሪወ ፡ ቤቱ ፡ እርኑ ፡ ያስተሐምም ፡ ቤቱ ፡ እግዚአብሔር ።
ቤተ ፡ ሰብኡን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ማሳደር ፡ የማይቻለው ፡ ከኾነ ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ያሳድራል ፡ ብለው ፡ እንደምን ፡ ይሾሙታል ፤ ምንድ ፡ ቂስ ፡ ቤተሰቦች ፡ ቢበዙ ፡ ፯ ፡ ድ ፡ ይኾናሉ ፡ እነዚያን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ማሳደር ፡ የማይቻለውን ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ያሳድራል ፡ ብለው ፡ ይሾሙታልን ።
ወኢይኩን ፡ ዘአምሐዲስ ፡ ተክል ።
ከሐዲስ ፡ አማኒ ፡ ወገን ፡ እይሾም ።
ከመ ፡ ኢይትአበይ ።
እንዳይታበይ ፡ ከኔ ፡ በላይ ፡ ቢያጡ ፡ እንጂ ፡ ኾንኝ ፡ ብሎ ።
ወኢይጸለል ።
በድንቁርና ፡ እንዳይጨፍ ።
ወኢይሥዮት ፡ ውስተ ፡ መሥገርተ ፡ ሰይጣን ።
ሰይጣን ፡ በተያዘበት ፡ አሽከላ ፡ እንዳይያዝ ፡ (አለ ፡) ትዕቢት ፡ ነው ።
ኂ ፡ ወዓዲ ፡ ርቱዕ ፡ ዘስብእ ፡ እፍአ ፡ ይጌዕድም ፡ (ም ፡ ፵ ፡ ፲) ።
ጻግሙኖም ፡ ከሞግር ። ከሃይማኖት ፡ በልፍለፋ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ያመነዝሯት ፡ ሲሏት ፡ ይገባል ።
ከመ ፡ ኢይፍት ፡ ውስተ ፡ ጽዕለት ፡ (ሮ ፡ ቍጥ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰) ።
በስድብ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ማለት ፡ ተጽእር ። ምክሙንን ፡ እንዳያስቀሩት ።
ወመሥገርተ ፡ ሰይጣን ።
ሰይጣን ፡ ሰውን ፡ በሚይዝበት ፡ አሽከላ ፡ እንዳይያዝ ።
ድ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ከማሁ ፡ ንጹሓን ።
ዲያቆናቱም ፡ (ከማሁ ፡) እንደቂሱ ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ።
ወእለትርኩባን ።
በአንድ ፡ ቦታ ፡ የተወለኑ ። አንድም ፡ ሕዋሳታቸውን ፡ የሰበሰቡ ፡ ይኹኑ ።
እለ ፡ አሐዱ ፡ ቃሎሙ ።
ሳንዱ ፡ አንድ ፡ ሳንዱ ፡ አንድ ፡ ጡት ፡ አንድ ፡ ግታ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ ነገር ፡ የማይለዋወጡ ፡ ይኹኑ ።
እለ ፡ ኢያበዝኁ ፡ ሰትየ ፡ መይን ።
መጠጥ ፡ የማያበዙ ፡ ይኹኑ ፡ አይጠጡ ፡ አላለም ።
እለ ፡ ኢያፈቅሩ ፡ ረባሕ ፡ ከንቶ ፡ (ፈሊጵ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፮ ፡ ፫) ።
ኃላፊውን ፡ ኅንዙብ ፡ የማይወዱ ፡ ይኹኑ ።
፱ ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡ ምክረ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በልብ ፡ ንጹሕ ።
ከከሀደት ፡ ከኑፋቄ ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ልቡና ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ትምህርት ፡ አጽንተው ፡ የያዙ ፡ ይኹኑ ።
፲ ፡ ወሶሙኒ ፡ ይቅድሙ ፡ አመከሮተሙ ።
እለያን ፡ ቅሉ ፡ አስቀድመው ፡ ይፈተኗቸው ።
ወእምዝ ፡ ይትለአኩ ፡ እምከመ ፡ ኅሩያን ፡ እሙንቱ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በትተው ፡ ቢገኙ ፡ ይሾሙ ።
፲፩ ፡ መልእክትኒ ፡ ከማሁ ፡ እለ ፡ አንጽሑ ፡ ርእሶን ፡ (ኩፋ ፡ ፰ ፡ ፫) ።
እሁን ፡ ወንዶችን ፡ ዲያቆናት ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ፡ እንጻልሁ ። ዲያቆናውያት ፡ ሴቶችም ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ይኹኑ ።
እለ ፡ ተምህራ ፡ ሥርዓት ።
ሥርዓት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የተማሩ ።
እለ ፡ ኢያስተዳጉጹ ።
ነገር ፡ ሠርተው ፡ እንዱን ፡ ከእንዱ ፡ የማያጣሉ ፡ ይኹኑ ።
ጠባባት። ብልሆች ።

www.zeyeneta.com

ራትዓት ።
ቅኖች ፡ ይኸኑ።
ወምእመናት ፡ በሁሉ ።
በውሰጥ ፡ በአፍአ ፡ በሥራው ፡ ሹሉ ፡ የታመኑ ፡ ይኹት ።
ወይትለአካ ።
(ይትለአካ ፡) እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ይሾሙ ።
፲፪ ፡ ወብእሲኒ ፡ ዘእሑተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ
የቄሱን ፡ ተናግሮ ፡ የዲያቆኑን ፡ አልተናገረውም ፡ ንበርና ፡ ዲያቆንም ፡ ያልደጋገመ ፡ ይኾም ፡
ድንግል ፡ አይኾም ፡ አላለም ።
ዘቦ ፡ ውሉድ ።
የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ።
ዘውናይ ፡ ግዕዘ ፡ ቤቱ ፡ (ቍ ፡ ፪ ።)
የቤቱ ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነለት ።

፲፫ ፡ ወአለሰ ፡ ውናየ ፡ ይትለአኩ ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሚመተ ፡ ይግበሩ ፡ ሎሙ ፡ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳፩) ።
(ሎሙ ፡ ለአለ ፡ ይትለአኩ ፡) በጎ ፡ ማገልገልን ፡ ላገለገሉ ፡ ዲያቆናት ፡ የበለጠ ፡ ያድርጎላቸው ፡ (አለ) ፡
ከዲቁና ፡ ወደቅስና ፡ ከቅስና ፡ ወደኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ያወጧቸው ።
በብዙኅ ፡ ሞገስ ፡ በሃይማኖተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምኖ ፡ የሚሾመት ፡ ብዙ ፡ መዓርገ ፡ ዐብት ፡ አለና ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሚመተ ፡
ይግበሩ ፡ ሎሙ ። አንድም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምኖ ፡ የሚሠራት ፡ ብዙ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አለና ፡
ይቅደሙ ፡ አመክሮቶሙ ፡ እምኩሉ ፡ ኀጢያን ፡ እሙንቱ ።

፲፬ ፡ ወዘኒ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ለከ ፡ አትአመን ፡ ከመ ፡ አበጽሐክ ፡ ፍጡን ።
ይህንም ፡ ስጽፍልህ ፡ ፈጥኜ ፡ ወደአንተ ፡ አንድመጣ ፡ አምናለሁና ።

፲፭ ፡ ወአመሰ ፡ ጐንደይኩ ፡ ከመ ፡ ታአምር ፡ ዘከመ ፡ ትሠርዕ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡
(፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳ ።)
ፈጥኜ ፡ ባልመጣ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑ ፡ ምእመናንን ፡ ሠርተህ ፡ ተዋተህ ፡ እንድታሳድር ፡
የምታሳድርበትን ፡ ሥርዓት ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዐምዳ ፡ ወድዳ ፡ ለጽድቅ ።
የሃይማኖት ፡ ጽንዕ ፡ መሠረት ፡ የሚኾን ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀጠለ ፡ አንድም ፡ የሃይማኖት ፡
ጽንዕ ፡ መሠረት ፡ የምትኾን ፡ ብሎ ፡ ለምእመን ፡ ቀጠለ ፡ አንድም ፡ ለሥርዓቱ ፡ ቀጠለ ።

፲፮ ፡ አማን ፡ ዐቢይ ፡ እስመ ፡ ምክሩ ፡ ለዝንቱ ፡ ጽድቅ ፡ (ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ።)
የዚህ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገሩ ፡ (እስመ ፡ ዐቢይ ፡) ደግ ፡ እንደመኾኑ ፡ (አማን ፡ ጽድቅ ፡) እውነት ፡ ነው ።
እንድም ፡ የዚህ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገሩ ፡ (እስመ ፡ ጽድቅ ፡) እውነት ፡ እንደመኾኑ ፡ (አማን ፡ ዓቢይ ፡) ፡
ደግ ፡ ነው ፤ ደግ ፡ ነው ፡ እኮ ።
ዝኪ ፡ ዘአስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ስብእ ።
ይኸውም ፡ በሥጋ ፡ የታየው ፡ መታየት ፡ ነው ።
ወጸድቀ ፡ በመንፈስ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፬ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተረዳነው ፡ መረዳት ፡ ነው ።
ወአስተርአዮሙ ፡ ለመላእክት ።
አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ብሎ ፡ ንበርና ፡ አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ያልኸው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትሰኝ ፡ እን
ደኾነ ፡ በዕሌተ ፡ ልደት ፡ ለመላእክት ፡ ታያቸው ።
ወሰበኩዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።
ለናሎት ፡ ነገሯቸው ። አንድም ፡ ለናሎት ፡ ታያቸው ፡ ሰአይሁድ ፡ ነገሯቸው ።
አንድም ፡ ወአስተርአዮሙ ፡ ለመላእክት ።
በዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ለመላእክት ፡ ታያቸው ።
ወሰበኩዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።
ለአንስት ፡ ነገሯቸው ።

www.zoyoneta.com

አንድም ፡ ወአስተርእዮሙ ፡ መላእክት ።
ለእንስታት ፡ ታያቸው ።
ወሰበክዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።
ለሐዋርያት ፡ ነገራቸው ።
አንድም ፡ ወአስተርአዮሙ ፡ ለመላእክት ።
ለሐዋርያት ፡ ታያቸው ።
ወሰበክዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።
ለአሕዛብ ፡ አስተማሯቸው ።
ወተአምኑ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።
በዓለሙ ፡ ዘንድ ፡ ታመነ ፡ ተረዳ ።
ወዐረገ ፡ በስብሐት ፡ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ።)
በብርሃን ፡ በሥልጣን ፡ በቅዳሴ ፡ ባረገ ፡ ጊዜ ፡ ታመነ ፡ ተረዳ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ወመንፈስ ፡ ገሃደ ፡ ይነግር ፡ ከመ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ የዐልዒ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ብዙኃን ፡ (ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፭ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ይሁ ፡ ፲፰ ።)
ወተአምኑ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ብሉ ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኔ ፡ አድሮ ፡ ገልጦ ፡ ይናገራል ።
ወይተልውሙ ፡ ለአጋንንት ፡ እኩያን ፡ ወመስሕታን ፡
እኩያን ፡ መስሕታን ፡ አጋንንትን ፡ እንዲመስሏቸው ።
ወትምህርተ ፡ ሰይጣን ፡ ዘያናፍቅ ።
የሚያጠራጥር ፡ የሰይጣንን ፡ ትምህርት ፡ እንዲይዙ ፡ ይነግር ።
፪ ፡ ኅሳብየን ፡ ሐሰት ።
ሐሰትን ፡ እንዲቀባጥሩ ።
እለ ፡ ንዴን ፡ በሕሊናሆሙ ፡ እለ ፡ የኀርሙ ፡ አውሰቦ ።
ግቢ ፡ ርኩስ ፡ እያሉ ፡ በፈቲው ፡ ጸር ፡ የሚናደዱ ፡ እንዲኾኑ ፡ እንዲናደዱ ።
ወይከልኡ ፡ መባልዕተ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ፈጠረ ፡ ለምእመናን ፡ (ዘፍጥ ፡ ፱ ፡ ፫ ።)
እግዚአብሔር ፡ ለምእመናን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ ሥጋ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ፡ ርኩስ ፡ የሚሉ ።
ከመ ፡ ይቤሰዩ ፡ ወያእኩቱ ፡ እለ ፡ ያእምርዋ ፡ ለጽድቅ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ።)
ሃይማኖትን ፡ የሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ በልተው ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ።
፫ ፡ እስመ ፡ ዅሉ ፡ ተግባረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ።
እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ። ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ አንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ።)
ወአልቦ ፡ ግዱፍ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ለአመ ፡ ተወከፍዎ ፡ እንዘ ፡ ያአኩቱ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ።)
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርተው ፡ አቡን ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግመው ፡ እምኖ ፡ ቢመገቡት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚጣል ፡ የለምና ፡ (አለ ፡) ርኩስ ፡ የለምና ፡ ይቤሰዩ ፡ ወያእኩቱ ።
፭ ፡ እስመ ፡ ይትቄደስ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበጸሎት ።
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አቡን ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግሞ ፡ ቢበሉት ፡ የሚከብር ፡ ስለኾነ ።
፮ ፡ ወዘንተ ፡ መሀሮሙ ፡ ለአኃዊከ ።
ለወንድሞችህ ፡ ይህን ፡ አስተምራቸው ።
ወትከውን ፡ ጎሩየ ፡ ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።)
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግ ፡ አገልጋይ ፡ ትኾናለህ ። አንድም ፡ ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጢሞቴዎስ ፤ (ትከውን ፤ ጎሩየ) ፤ ደግ ፡ ትባላለህ ።

www.zeyeneta.com

እንዘ ፡ ትሴስዮሙ ፡ ቃለ ፡ ሃይማኖት ።
የሃይማኖትን ፡ ነገር ።
ወሠናየ ፡ ትምህርተ ፡ ዘተመህርከ ።
ከኔ ፡ የተማርኸውን ፡ ትምህርት ፡ ስታስተምራቸው ፡ ብትገኝ ፡ ትከውን ፡ ኅሩየ ።

፮ ፡ ወለመሐድምተ ፡ ዕቤራትስ ፡ ርኩስ ፡ ዕበዮ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፬ና ፡ ፮ ፡ ፳ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪፡፲፮፡፳፫፡ቲቶ፡፩፡፲፱፡፳፱።)
ርኩሳን ፡ ቢል ፡ ለዕቤራት ፤ ርኩስ ፡ ቢል ፡ ለመሐድምት ፡ ይቀጥላል ፡ የባልቴቶች ፡ ተረት ፡ ኦሪትን ፡
ግን ፡ ተወው ።
ወእግርር ፡ ርእስከ ፡ ለጽድቅ ።
ለጽድቅ ፡ ለወንጌል ፡ ቀንዛ ።

፳ ፡ አስመ ፡ ግዝረትሰ ፡ በሥጋ ፡ ለኅዳጥ ፡ ዘመን ፡ ትበቍዕ ፡ ቦ ፡ (ም ፡ ፯ ፡ ፮ ።)
ለአሪት ፡ መገዛት ፡ ለሥጋ ፡ መጥቃሙ ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፡ ዕበዮ ።
ወጽድቅሰ ፡ ታሠልጥ ፡ በዅሉ ።

ጽድቅ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ሹሉ ፡ ነውና ፡ እግርር ፡ ርእስከ ፡ እንድም ፡ ለአሪት ፡ መገዛት ፡ ለጥ
ቂት ፡ ዘመን ፡ በሥጋ ፡ ይጠቅግልና ፡ ዕበዮ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ በሥጋም ፡ በነፍስም ፡ ትጠቅግለ
ችና ፡ አግርር ፡ ርእስከ ።
ወኀቲ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወት ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽአ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፤ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የድነነት ፡ አለኝታ ፡ ይገኝባታል ።

፱ ፡ አሙን ፡ ነገሩ ፡ ወርቱዕ ፡ ይትወከፍዎ ፡ በዅሉ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)
ነገሩ ፡ ደግ ፡ ነው ፤ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ሊያምኑት ፡ ይገባል ።

፲ ፡ አስመ ፡ በእንተዝ ፡ ንሠርሕ ፡ ወንጸግል ።
ስለዚህ ፡ በመከራው ፡ አንደከማለንና ፤ አንዋረዳለንና ።
አስመ ፡ ተወከልነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ውእቱዋ ፡ ለዅሉ ፡ ሰብኢ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ።)
ሕያው ፡ ማሕየዊ ፡ በሚኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስለአመነ ።(ሐተታ) ፡ ሕያው ፡ ለራሱ ፡ ማሕየዊ ፡ ሌሎችም ።
ወፈድፈደሰ ፡ ለመሃይምናን ፡ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፫) ።

ይልቁንም ፡ ማሕየዊነቱ ፡ ለምእመናን ፡ ነው ፡ ብሥራ ፡ ያስፋፋታልና ።
ከመገ ፡ መሀር ፡ ወገሥጾ ።
አንዲህ ፡ ምክር ፡ አስተምር ።

፲፪ ፡ ወአልቦ ፡ ዘያስተአብዳ ፡ ለውርዙትከ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።
የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ሕግንትህን ፡ የሚነቅፋት ፡ አይኑር ፡ ሕግን ፡ እንጂ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ ብሎ ፤
አንድም ፡ ሕግን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካንተ ፡ በፊት ፡ የሚጸልይ ፡ አይኑር ።
ወኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለምእመናን ፡ በቃልከ ፡ ወበምግባርከ ፡ በፍቅር ፡ ወበሃይማኖት ፡ ወበንጽሕ ።
በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ ጸንተህ ፡ በምትናገረው ፡ ነገር ፡ በምትሠራው ፡ ሥራ ፡ ለምእመናን ፡
አብነት ፡ ኾናቸው ።

፲፫ ፡ ወተዐቀብ ፡ አስከ ፡ አመጽአ ፡ በአንብቦ ።
አስክመጣ ፡ ድረስ ፡ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ተወስነህ ፡ ኑር ።
ወበምሂር ፡ ወበገሥጾ ፡ ወሰጸልዮ ፡ (ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፱) ።
በምክር ፤ በማስተማር ፤ በጸሎት ፡ ተወስነህ ፡ ኑር ።

፲፬ ፡ ወኢታስትት ፡ ጸጋሁ ፡ ዘሳዕሌከ ፡ ዘተውህበከ ፡ ምስለ ፡ ተንብዮ ።
ትርጓሜን ፡ መጻእያትን ፡ ከማወቅ ፡ ጋራ ፡ የተሰጠህን ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።
ወምስለ ፡ ሚመተ ፡ አዲሆሙ ፡ ለጸጸሳት ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፳፪ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፮ ፡ ፯ና ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።)
ቀሳውስትን ፡ በአንብሮተ ፡ አድ ፡ ከመሾም ፡ ጋራ ፡ የተሰጠህን ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል። አንድም፡
ቀሳውስት ፡ በአንብሮተ ፡ አድ ፡ ከሚሾሙት ፡ ሹመት ፡ ጋራ ፡ የሰጠህ ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።

፲፭ ፡ ዘንተ ፡ አንብብ ።
ይህን ፡ አስተውል ።

www.zeyeneta.com

ወበዝ ፡ ሀሉ ። ብዚህ ፡ እንተህ ፡ ኑር ።
ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሥላጤክ ፡ በሁለሄ ።
ፍጹምንትህ ፡ በሁሉ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ።
፲፮ ፡ ውቅ ፡ እንከ ፡ ርእሰከ ፡ በእንተ ፡ እንብቦ ።
መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ተወሰነህ ፡ እንድትኖር ፡ ዕወቅ ።
ወዘልፈ ፡ ሀሉ ፡ ባቲ ።
በዚያው ፡ እንተህ ፡ እንድትኖር ፡ ዕወቅ ።
ወእመሰ ፡ ዘንተ ፡ ገበርከ ፡ ርእሰከሂ ፡ ታድነን ።
ይህን ፡ ያደረግህ ፡ እንደኾነ ፡ ራስህን ፡ ታድናለህ ።
ወዘሂ ፡ ይሰምዐከ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬) ።
የሚሰማህንም ፡ ታድናለህ ። እንድም ፡ የምታሰተምረውን ፡ ብትሠራው ፡ ራስህንም ፡ ሌላውንም ፡ ታድ
ናለህ ፡ ለእመሂ ፡ ሰምዐከ ፡ አድኃንከ ፡ ሕዝበከ ፡ ወለእመሂ ፡ ኢሰምዐከ ፡ አድኃንከ ፡ ርእሰከ ፡ ያለውን ፡
ሕዝቅኤል ፡ እንዲህ ፡ ለውጦ ፡ አነበበው ። (ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፰) ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ ሊቃናተ ፡ ኢታመጕጽ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፴፪)
ሽማግሌችን ፡ አትንጠብ ፡ (አለ ፡) አታዋርድ ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።
ተአዘዝ ፡ ከመ ፡ ዘለአቡከ ።
ለአባትህ ፡ እንድምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለንኡሳን ፡ ከመ ፡ ዘለእኃዊከ ።
ለሕፃናቱም ፡ ወንዶች ፡ ለወንድሞችህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለልሂቃትሂ ፡ ከመ ፡ ዘለእምከ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯) ።
ለባልቴቶችም ፡ ለናትህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለንኡሳትሂ ፡ ከመ ፡ ዘለእኃቲከ ፡ በኵሉ ፡ ንጹሐ ።
ለሕፃናቱም ፡ ሴቶች ፡ ለእኅቶችህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዛቸው ፡ (በኵሉ ፡ ንጽሕ ፡) በንጽሕና ፡ ኾነህ ፡
ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ዝሙት ፡ ይቀዋወማቸዋልና ፡ ንጽሕን ፡ ያቆራኛል ።
፫ ፡ ወእከብር ፡ ዕቤራተ ፡ በጽድቅ ፡ (ቊ ፡ ፭) ።
(እከብር ፡ በጽድቅ ፤ ዕቤራተ ፡ በጽድቅ ፡) በውነት ፡ እረጅ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸው ፡ ባልቴቶችንም ፡ በእው
ነት ፡ እርዳ ።
፬ ፡ ወእመቦ ፡ ዝምኔሆሙ ፡ ዕቤር ፡ አንተ ፡ ባቲ ፡ ውሉድ ።
ከምእመናን ፡ ወሢን ፡ ልጆች ፡ ያሏት ፡ ድኃ ፡ ባልቴት ፡ ብትኖር ።
አሙ ፡ ደቂቀ ፡ ውሉድ ።
የልጅ ፡ ልጅ ፡ ያላት ፡ ብትኖር ።
ይትመሀሩ ፡ ቅድመ ፡ አሠንዮ ፡ ለቤቶሙ ።
ውሉድ ፤ ጸናቅ ፡ አባቃቸውን ፡ ሞፎዱ ።
ወይሴስዩ ፡ አዝማዲሆሙ ።
ደቂቀ ፡ ውሉድ ፤ እያቶቻቸውን ፡ ይርዱ ።
እስመ ፡ ከማሁ ፡ ሠናይ ፡ ወሥሙር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር
ይህ ፡ እናት ፡ አባትን ፡ መርዳት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።
፭ ፡ ወእንተሰ ፡ ዕቤር ፡ በአማን ፡ ንጽሕት ፡ እንተ ፡ ሣሕቲታ ፡ ትኩብር ፡ በውነት፡ እረጅ፡ ልጅ ፡ የሌላት ፡ ብቻ
ዋን ፡ በንጽሕና ፡ ዋዕዊኖር ፡ ባልቴቲቱን ፡ ማን ።
እስመ ፡ ትውከልታ ፡ እግዚአብሔር ።
ተስፋዋ ፡ አግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነውና ።

www.zeyeneta.com

ወትፀመድ ፡ ጸሎተ ፡ ወትሰእል ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ (ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፯ ፡ ፲፰ ፡ ፩) ።
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በጸሎት ፡ ፅሙድ ፡ ኾና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትለምነዋለችና ፡ ርዳት ።

፭ ፡ ወእንተሰ ፡ ትፈግፅ ፡ ምሰለ ፡ ተውኔት ፡ ምውት ፡ ይእቲ ፡ እንዘ ፡ ሕያዋ ፡ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ።)
በዘፈን ፡ በጨዋታ ፡ እየኖረች ፡ተድላ ፡ ደስታ ፡ የምታደርገውን ፡ ግን ፡ በወዲሁ ፡ አለው ፡ አለው ፡
ለትል ፡ በወዲያው ፡ ምውት ፡ ናትና ፡ አትርዳት ።
ወከመዝ ፡ ገሥጽ ።
እንዲህ ፡ ምክር ፡ አሰተምር ።
ክሙ ፡ ኢያድልዉ ፡ ወኢያመክንዩ ፡ (ም ፡ ፱ ፡ ፲፩) ።
ዘፈናን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ እንዳያዳሉላት ።

፮ ፡ ወዘሰ ፡ ኢይሔሊ ፡ ለቤቱ ፡ (ገላትያ ፡ ፮ ፡ ፲) ።
እናት ፡ አባቱን ፡ የማይረዳ ።
ወይገድፍ ፡ አዘማዲሁ ።
እያቶቹን ፡ የማይረዳ ።
ወፈድፋደሰ ፡ ለአመ ፡ ኮኑ ፡ እምሰብአ ፡ ሃይማኖት ።
ይልቁንም ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ቢኾኑ ።
ውእቱ ፡ ከሀደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ (ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፭) ።
እሱ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ካደ ።
ወየእኪ ፡ እምዘ ፡ ኢያአምን ።
ከኢአማኒም ፡ ይከፋል ።

፱ ፡ ወለአመ ፡ ጎረይክ ፡ ዕቤረ ፡ ጎረይ ፡ እንተ ፡ ሰሳ ፡ ክረምታ ።
ዲያቆናዊት ፡ ልትሾም ፡ ብትወድ ፡ ፷ ፡ ዘመን ፡ የመላትን ፡ ደም ፡ የቆረጠችውን ፡ መርጠህ ፡ ሹም ።
እንተ ፡ ፭ደ ፡ ብእሴ ፡ አውሰበት ።
ያልደጋገመችውን ።

፲ ፡ እንተ ፡ ይንዕድዋ ፡ በሱሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የሚያመሰግኗትን ።
ለአመ ፡ ኢልህቀት ፡ ውሉዳ ።
ልጆቿን ፡ ሠርታ ፡ ቀጥታ ፡ ብታሳድግ ።
ወለአመ ፡ ነግደ ፡ ተወክፈት ፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፱) ።
እንግዳ ፡ ብትቀበል ።
ወለአመ ፡ እግረ ፡ ጸድቃን ፡ ኀፀበት ።
የድሆችን ፡ እግር ፡ ብታጥብ ፡ የሚያመሰግኗትን ። ዝራፅ ፡ እክለከ ፡ ላዕለ ፡ መቃብረ ፡ ጸድቃን ፡ ጠቢት ፡
(፱ ፡ ፲፯) ፡ እደው ፡ ጸድቃን ፡ የሀልዉ ፡ ውሰተ ፡ ምሳሕክ ፡ እንዲል ፡ (ሲራ ፡ ፱ ፡ ፳፫) ፡
ወአመ ፡ ርኁበ ፡ አጽገበት ።
የተራበ ፡ ብታበላ ፡ የሚያመሰግኗትን ።
ወሱሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ለአመ ፡ ተለወት ።
ነጣጣለትና ፡ በጎውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አጽንታ ፡ ብትይዝ ፡ የሚያመሰግኗትን ፡ መርጠህ ፡ ሹም ።

፲፩ ፡ ወለንኡሳትሰ ፡ መበለታት ፡ ተግኃሥ ።
ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ግን ፡ ተለያቸው ።
ወኢትሥሚሞን ።
እትሹማቸው ።
ክሙ ፡ ኢይትፈግዓ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይፈቅዳ ፡ ይግብአ ፡ ለአውስቦ ።
ተመልሰው ፡ ባል ፡ ሊያገቡ ፡ ወደው ፡ በክርስቶስ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳያደርጉበት ።

፲፪ ፡ ወጽኑሕ ፡ ደይኖን ።
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እን ደኾነ ፡ ፍዳቸው ፡ ይቆያቸዋል ።

www.zeyeneta.com

ለእመ ፡ ክህዳ ፡ ሃይማኖቶን ፡ ቀዳሚተ ።
የቀደመ ፡ ብዕዓታቸውን ፡ ቢያፈርሱ ፡ ጽኑሕ ፡ ይይኖን ።

፲፫ ፡ ወዓዲ ፡ አጽርዕተ ፡ ወሐኬተ ፡ ይትሜሐራ ፡ እንዘ ፡ የዓውዳ ፡ አብያተ ፡ (ምሳ ፡ ፯ ፡ ፲፭) ።
በዚህም ፡ ላይ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ እየዞሩ ፡ አጽርዕትን ፡ ሐኬትን ፡ ይማራሉ ፡ (አጽርዕት) ፡ እግር ፡
ዝርጊት ፡ (ሐኬት ፡) በወር ፡ ጥልቅ ፡ በዓመት ፡ ቀሚስ ፡ ጥልቅ ።
ወአኮ ፡ አጽርዕተ ፡ ባሕቲቶ ።
መንደር ፡ ለመንደር ፡ መዞራቸውም ፡ አጽርዕትን ፡ ሐኬትን ፡ ለመማር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ያብዝኃ ፡ ነቢበ ።
አብዝተው ፡ ለመቀባጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወምግባረ ፡ ከንቱ ።
ከንቱ ፡ ሥራንም ፡ ለመሥራት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ይፈጥራ ፡ ነገረ ፡ ዘኢሀልዉ ።
ቀዋሚ ፡ ያይደለ ፡ ነገር ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ።

፲፬ ፡ እፈቅድ ፡ እንከ ፡ ለንኡሳት ፡ ያውስባ ፡ ወይትዋለዳ ፡ ወይኩና ፡ በዓልታተ ፡ ቤት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፱) ።
እኔስ ፡ ሕፃናቱ ፡ ሴቶች ፡ ባል ፡ አግብተው ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገዝተው ፡ ሊኖሩ ፡ እመዳለሁ።
መኢይርከብ ፡ ምክንያተ ፡ ወእሐተኒ ፡ በዘይጸብኦን ፡ ጸላዒ ።
ጸላዒ ፡ ዲያብሎስ ፡ ድል ፡ በሚነሣቸው ፡ ገንዘብ ፡ ድል ፡ የሚነሣበት ፡ ምክንያት ፡ እንዲያገኝ ።
ከመ ፡ ኢያጽዕላ ፡ ርእሶን ።
ራሳቸውን ፡ እንዳያስነቅፉ ፡ አንድም ፡ ራሳቸውን ፡ ከርስቶስን ፡ እንዳያስነቅፉ ፡ ንሕነ ፡ አላል ፡ ወውእቱ ፡
ርእሰ ፡ አንዲል ።

፲፭ ፡ እስመሰ ፡ እለ ፡ ተመይጡ ፡ ወተለውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፯) ።
ተመልሰው ፡ የሰይጣንን ፡ ግብር ፡ የያዙ ፡ አሱና ፡ ኢያጽዕላ ።

፲፮ ፡ ወለእመ ፡ ቦ ፡ አምእመናን ፡ ዘቦ ፡ ዕቤር ፡ ይዕቀባ ።
ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ደኃ ፡ አናት ፡ ያለችው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይርዳት ።
ወኢያከብድ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።
ምእመናንን ፡ እንዳያስቸግር ፡ እንዳታስቸግር ።
ከመ ፡ ትከሀል ፡ ለእለ ፡ በአማን ፡ ዕቤራት ።
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ ረጅ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸውን ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ እለ ፡ ሠናየ ፡ ተልእኩ ፡ ቀሲሳን ፡ ምክዕቢት ፡ ይደልዎሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፰ና ፡ ፲፫ ፡ ፭፯) ።
በጎ ፡ ማገልገልን ፡ ላገለገሉ ፡ ቀሳውስት ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ።
ወፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ ይሰርሑ ፡ በቃል ፡ ወበምህሮ ።
ይልቁንም ፡ (በቃል) ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ የሰሙትን ፡ (ወበምህሮ) ፡ ከመጽሐፍ ፡ ያገኙትን ፡ በማስተማር ፡
ለሚያከሙ ፡ መምህራን ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ።

፲፰ ፡ ወይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ኢትፍጸሞ ፡ አፉሁ ፡ ለላህም ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ አከለከ ፡ (ዘዳግ ፡ ፳፭ ፡ ፬ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፱)
እህልህን ፡ በምታሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የላምህን ፡ አፉን ፡ እትሰረው ፡ ብሏልና ።
ወይደልዎ ፡ እስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፯) ።
ይደልዎ ፡አስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ብሏልና ፡ (ምክዕቢተ ፡ ክብር ፡ ይደልዎሙ ፡) (ሐተታ) ከአባቄ ፡ ኖኅት
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሽቅብ ፡ እየሰጠ ፡ ይሔዳል ፡ በኹለተኛው ፡ ከዲያቆን ፡ ጀምሮ ፡ ይሰጣል፤
በሦስተኛው ፡ ከቂስ ፡ ይጀምራል ፤ ባራተኛው ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ሰጥቶ ፡ ይመለሳል ፡ እንድም ፡ ከኤጲስ
ቆጶሱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እባቄ ፡ ኖኅት ፡ እየሰጠ ፡ ይወርዳል ፡ በኹለተኛው ፡ ለዲያቆን ፡ ሰጥቶ ፡ ይመለሳል
በሦስተኛው ፡ ለቂስ ፡ በአራተኛው ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ሰጥቶ ፡ ይመለሳል ፡ አንድም ፡ እራቱን ፡ ከአንድ
ላይ ፡ ሦስቱን ፡ ከአንድ ፡ ላይ ፡ ኹለቱን ፡ ከአንድ ፡ ላይ ፡ አንዳንዱን ፡ በየራሱ ፡ አድርጎ ፡ በየጎንዘባችሁ፡
አንሡ ፡ ይላቸዋል ፡ ያንሣሉ ።

፲፱ ፡ ላዕለ ፡ ልሂቅ ፡ ኢትሰማዕ ፡ ውዴተ ።
በቂሱ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡ አትስማበት ።

www.zoyeneta.com

ዘእንበለ ፡ ይዝልፍዎ ፡ ከልኤቱ ፡ ወሠለስቱ ፡ ሰማዕት ፡(ዮሐ ፡፭ ፡፲፭ ።)
ኹለት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ሳይመስክሩበት ።

፳ ፡ ወለእለሂ ፡ ስሕቱ ፡ በቅድመ ፡ ዙሉ ፡ ገሥጾሙ ፡(ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።)
ስሕቱ ፡ በቅድመ ፡ ዙሉ ፡ ገሥጾሙ ፡ በቅድመ ፡ ዙሉ ፡) በጉባኤ ፡ የበደሉትንም ፡ በጉባኤ ፡ ገሥጻቸው
ከመ ፡ ባዕደኒ ፡ ይፍራህ ።
ሌላው ፡ ፈርቶ ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ፡ ዝሉፍ ፡ እንዘ ፡ ይትጌሠጽ ፡ አብድ ፡ ይከውን ፡ ማፅምረ ፡ እንዲል ።

፳፩ ፡ እሰምዕ ፡ ለከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እዳኝብሃለሁ ።

ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ።

ወበመላእክቲሁ ፡ ኅሩያን ።
በመላእክትም ፡ ፊት ፡ እዳኝብሃለሁ ።

ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ኢታደሉ ።
በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፡ በትምህርት ፡ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይተህ ፡ ሳታደላ ፡ ይህን ፡ ትጠብቅ ፡
ዘንድ ፡ እዳኝብሃለሁ ።
ወኢታጽድቆ ፡ ለሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ፍትህ
ሳይመሰክርበት ፡ እንዳያደርግ ፡ ፀውቃለሁ ፡ አትበል ።

ወኢትግበር ፡ ምንተኒ ፡ በዘትትሐመይ ።
በምትነቀፍ ፡ ገንዘብ ፡ የምትነቀፍበትን ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡እንጂ ፡ ሰምቶ ፡ ቃል ፡ ለቃል
ተጨዋውቶ ፡ ይሉታልና ።
ወኢታጽድቆ ፡ ለሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ፍትሕ ።
(አንድም) ፡ሳይመሰክርለት ፡ እንዳያደርግ ፡ ፀውቃለሁ ፡ አትበል ።
ወኢትግበር ፡ ምንተኒ ፡ በዘትትሐመይ ።
በምትነቀፍ ፡ ገንዘብ ፡ የምትነቀፍበትን ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፡ መግለጫ ፡ በልቶ ፡ ተዘምዶ ፡ ሥጋ ፡ጉሮት
አድልቶ ፡ ይሉታልና ።
፳፪ ፡ ወኢትሚም ፡ ፍጡነ ፡ ወኢመነሂ ፡(ግብ ፡ሐዋ ፡ ፮ ፡ ፮ ።)
ማንንም ፡ ግን ፡ ሳትመረምር ፡ ፈጥነህ ፡ እትሹም ።
ወኢትሳተፍ ፡ በዝ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአተ ፡ ባዕድ ።
በዚህ ፡ ሌላው ፡ በሠራው ፡ ኃጢአት ፡ አንት ፡ በፍዳ ፡ እንዳትያዝ ፡ አኮ ፡ ዘገብረ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘይትኬነን
እላ ፡ ዘሂ ፡ ሠምረ ፡ በኃጢአቱ ፡ ዝኩ ፡ እንዲል ።
ወአንጽሕ ፡ አንከ ፡ ርእስከ ።
ዕውነትህን ፡ ከኃጢአት ፡ ዕይ ።
፳፫ ፡ ወኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ።
ጥሩ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ እትጠጣ ።
ጎዳጠ ፡ ወይነ ፡ ቶስሕ ፡ (መዝ ፡፻፬ ፡፲፭) ።
ጥቂት ፡ ወይን ፡ ጨምርበት ፡ እንጂ ።
በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ከብድከ ።
ስለልብህ ፡ ደዌ ።
ወበእንተ ፡ ደዊከ ፡ ዘዘልፍ ።
ሰለጀርባህ ፡ ደዌ ፡ አንድም ፡ (በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ከብደከ ፡) ስለጀርባህ ፡ ደዌ ፡ (ወበእንተ ፡ ደዊከ ፡ዘዘ
ልፍ ፡) በማስተማር ፡ ጣፊያው ፡ ደርቆ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ።

፳፬ ፤ ቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትዐወቆ ፡ ኃጢአቱ ።
ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በትሕርምት ፡ ኑሮ ፡ ትሕርምቱን ፡ አፈረሰ ፡ ቢሉ
ኘስ ፡ ትሰኝ ፡ እንደኾነ ፡ በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ኃጢአቱ ፡ የሚታወቅበት ፡ ስው ፡ አለ ፡ (አለ ፡) እንዲህ
ያደርጋል ፡ ተብሎ ።

www.zeyeneta.com

ወይትባደሮ ፣ ውስተ ፣ ደይን ።
በሞተም ፣ ጊዜ ፣ የሚታወቅበት ፣ ሰው ፣ አለ ፣ (አለ ፣) ዕለቱን ፣ እግዚህ ፣ እንጂ ፣ ያደርግ ፣ ክር ፣ ተብሎ

ወቦ ፣ ዘይተልዎ ፣ ኃጢአቱ ።
ከሞተ ፣ በኋላ ፣ የሚታወቅበት ፣ አለ ፣ (አለ ፣) ፍሮ ፣ ፍሮ ፣ እንዲህ ፣ እንጂ ፣ ያደርግ ፣ ነፀር ፣ ተብሎ ።

ቦ ፣ ሰብእ ፣ ዘይትዐወቆ ፣ ኃጢአቱ ።
እንድም ፣ ኢትሚም ፣ ፍጡን ፣ ብሎ ፣ ነበርና ፣ የበታውንና ፣ ያልበታውን ፣ በምን ፣ አውቂዋለሁ ፣ ትሰኝ እንደኾነ ፣ ከመሾሙ ፣ እስቀድሞ ፣ ኃጢአቱ ፣ የሚታወቅበት ፣ ሰው ፣ አለ ።

ወይትባደሮ ፣ ውስተ ፣ ደይን ።
በተሾመም ፣ ጊዜ ፣ የሚታወቅበት ፣ አለ ፣ እንዲህ ፣ ያደርጋል ፣ ተብሎ ።

ወቦ ፣ ዘይተልዎ ፣ ኃጢአቱ ።
ከተሾመ ፣ በኋላ ፣ ኃጢአቱ ፣ የሚታወቅበት ፣ አለ ፣ እንዲህ ፣ እንጂ ፣ ያደርጋል ፣ ተብሎ ።

ጽፍ ፣ ወከማሁ ፣ ዘሂ ፣ ይገብር ፣ ሠናየ ፣ ይትዐወቅ ፣ ወዘሂ ፣ ካልእ ፣ ምግባሩ ፣ ኢይትከበት ፣ (ገለ ፣ ፮ ፣ ፯፱) ።
በነም ፣ የሚሠራ ፣ ክፉም ፣ የሚሠራ ፣ እንደዚህ ፣ ነው ፣ አይሰወርም ።

ምዕራፍ ፣ ፮ ።

፩ ፣ ወሰሉ ፣ ነባሪ ፣ ወቅኑይ ፣ አከብሩ ፣ አጋእዝቲከሙ ፣ በሰሉ ፣ (ኤፌ ፣ ፮ ፣ ፫ ፣ ቲቶ ፣ ፪ ፣ ፱) ።
ውሉድ ፣ እናት ፣ አባታቸውን ፣ ይርዱ ፣ ብሎ ፣ መሪዐ ፣ ቤት ፣ ጀምሮ ፣ በመካከል ፣ ሌላ ፣ አግብቶበት ነበርና ፣ ከቀደመ ፣ ነገሩ ፣ ተመለሰ ፣ ቤተ ፣ ሰብእችም ፣ በሥራው ፣ ኹሉ ፣ ጌቶቻቸሁን ፣ እርዱ ።

ከመ ፣ ኢይፅርፉ ፣ ላዕለ ፣ ስመ ፣ እግዚአብሔር ።
ስመ ፣ እግዚአብሔርን ፣ እንዳይነቅፉ ፣ በእግዚአብሔር ፣ ማመን ፣ ቤተሰብእ ፣ ለጌታው ፣ ላይገዛ ፣ ነው ብሎው ።

ወላዕለ ፣ ትምህርቱ ።
ወንጌልን ፣ እንዳይነቅፉ ። በወንጌል ፣ ማመን ፣ ቤተ ፣ ሰብእ ፣ ለጌታው ፣ ላይገዛ ፣ ነው ፣ ብለው ።

፪ ፣ ወእለሰ ፣ ቦሙ ፣ አጋእዝት ፣ መሃይምናን ፣ ኢያስተሐቅሩ ።
ምእመናን ፣ ጌቶች ፣ ያሏቸው ፣ ቤተ ፣ ሰብእችም ፣ ጌቶቻቸውን ፣ አይናቁ ፣ አያቃሉ ።

እስመ ፣ አኃዊሆሙ ፣ እሙንቱ ፣ በሃይማኖት ።
በሃይማኖት ፣ እንድ ፣ ስለኾኑ ።

ዓዲ ፣ ፈድፋደ ፣ ይትቀነዩ ፣ ሎሙ ።
ይልቁንም ፣ አብልጠው ፣ ይገዙላቸው ፣ እንጂ ።

እስመ ፣ ምእመናን ፣ ወፍቁራን ፣ እሙንቱ ።
በሃይማኖት ፣ ስለመሰሏቸው ።

ወለአሉ ፣ ይትዌከፉ ፣ ወይትለአኩ ፣ በፍሥሐ ፣ ሎሙ ።
ትእዛዛቸውን ፣ እየቀቀበሉ ፣ ደስ ፣ ብሏቸው ፣ ደስ ፣ አሰኝተው ፣ ይርዷቸው ።

ከመዝ ፣ መሀር ፣ ወገሥጽ ፣ (ም ፣ ፬ ፣ ፲፮ ፣ ቲቶ ፣ ፪ ፣ ፭) ።
እንዲህ ፣ ምከር ፣ አስተምር ።

ወአስተብቍዖሙ ።
አለዝበህ ፣ ማልዳቸው ።

፫ ፣ ወእመሰበ ፣ ዘይሜህር ፣ ካልአ ፣ (ገላ ፣ ፩ ፣ ፮ ፣ ፱ ።)
እኛ ፣ ከአስተማርነው ፣ ትምህርት ፣ ሌላ ፣ የሚያስተምር ፣ ሰው ፣ ቢኖር ።

ወኢይገብእ ፣ ኀበ ፣ ትምህርተ ፣ ነገረ ፣ ሕይወት ፣ (፪ ፣ ጢሞ ፣ ፩ ፣ ፲፫) ።
ድኅነት ፣ የሚገኝበትን ፣ ትምህርት ፣ ወደመማር ፣ የማይመለስ ።

ዘውእቱ ፣ ቃለ ፣ እግዚእነ ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ።
ይኸውም ፣ ወንጌል ፣ ነው ።

www.zeyneta.com

ወኅበ ፡ ትምህርተ ፡ ጽድቅ ።
አንድነቱን ፡ ሥሉስነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ ወደመግር ፡ የማይመለስ ።

፩ ፡ ውእቱኬ ፡ ዘይትዔበይ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያአምር ።
የሚያውቀው ፡ ሳይኖር ፡ የሚታበይ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ነዋ ።
ዘእንበለ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዘየኀሥሥ ።
መቅሠፍትን ፡ ይሻል ፡ እንጂ ።
ወነገረ ፡ ጋእዝ ።
የጸብእ ፡ የክርክርን ፡ ነገር ፡ ይሻል ፡ እንጂ ።
ዘእምኔሁ ፡ ይመጽእ ፡ ተሐምሞ ።
ምቀኝነት ፡ የሚመጣበት ።
ወተቃንየ ።
መቃኖት ።
ፀሪፍ ። ሰው ፡ ሎሳይብ ።
ምክር ፡ እኩይ ።
ክፉ ፡ ትምህርት ፡ ጠማማ ፡ ምክር ።

፭ ፡ እስተዳጉጾ ፡ ሰብአ ፡ ሙሱናን ።
ሰውን ፡ ከሰው ፡ ማጣላት ፡ የሚመጣበት ፡ እንድም ፡ (እስተዳጉጾ ፡)ሰውን ፡ ከሰው ፡ ማጣላት ፡(ሰብአ ሙሱናን ፡) ድል ፡ የተነሡ ።
ወውዑአን ፡ እምጽድቅ ።
ከጽድቅ ፡ የወጡ ።
ወይሬስይዎ ፡ ለጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተግባረ ።
ወንጌልን ፡ መበያ ፡ የሚያደርጉትን ።
ተገንሥሙ ፡ ለእሉ ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ተለያቸው ።

፮ ፡ እስመ ፡ ለንስ ፡ ተግባረነ ፡ ዓቢይ ፡ ውእቱ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡(ም ፡፬ ፡፭)፡ፈል ፡፬ ፡፲፩ ፡፲፪)።
የኛስ ፡ እኮ ፡ ደገኛ ፡ ሥራችን ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንድም ፡ የኛ ፡ ደገኛ ፡ ሥራችን ፡ፈሪሀ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ተገንሥሙ ፡ ለእሉ ።

፯ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘአምጻእነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።
ስንወለድ ፡ ይዘነው ፡ የተወለድነው ፡ የለምና ።
ወአልቦ ፡ ዘንክል ፡ ነሢአ ፡ እምኔሁ ፡ (መክ ፡ ፭ ፡ ፲፭)
በሞት ፡ ጊዜም ፡ ይዘነው ፡ የምንሔድ ፡ የለምና ።

፰ ፡ እምከመ ፡ ረከብነ ፡ ሲሳየነ ፡ ወአራዘነ ፡ የአከለነ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ምሳ ፡ ፴ ፡ ፳ ።)
የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ የዓመት ፡ ልብሳችንን ፡ ከአገኘን ፡ ይበቃናል ፡ ኢዮብ ፡ ዕራቅየ ፡ ወፃእኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፡ ወዕራቅየ ፡ እገብእ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ እንዲህ ፡ ለውጦ ፡ እነበበው ፡ በዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ተባብረውበታል ፡ ያዕቆብ ፡ በአሪቱ ፡ እምከመ ፡ ረከብኩ ፡ እክለ ፡ ዘእበልዕ ፡ ወልብስ ፡ ዘእትኤረዝ ፡ ይከውነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ብሏል ፡ ባሰቢቱም ፡ በወንጌል ፡ ሲሳየነ ፡ ዘለዕለትነ ፡ ብሏል (ማቴ፡ ፮፡ ፲፩፡ ፫ቱሂም) በሕንጻ ፡ መኮሳት ፡ ኢትኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ፡ አላ ፡ ሥራዕ ፡በዐቅም ፡ ዘየእክል ፡ ለሲሳይከ ፡ ወለአራዝከ ፡ ለሕይወትከ ፡ ብለዋል ፡ ማሪ ፡ ይስሐቅም ፡ ወለእመ ፡ ተርፈከ እመፍቅደከ ፡ ዕለትከ ፡ ሀቦ ፡ ለነዳይ ፡ ወለማዩር ፡ ብሏል ፡ ከዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡አለ ፡ሰመ ነኮሳት ፡ በቁሙ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ የሰብእ ፡ ዓለም ፡ የዕለት ፡ ያለው ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ የዓመት ፡ ምግብ ፡ የዓመት ፡ ልብስ ።

፱ ፡ ወእለሰ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይብዐሉ ፡ ይወድቁ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ፡(ምሳ ፡፳፫ ፡፭ና ፡፳፰ ፡፳፱)።
ከዚህ ፡ ወጥተው ፡ ሥጋዊ ፡ ከብር ፡ ሊከብሩ ፡ የሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በፍዳ ፡ ይያዛሉ ።
ወብዙኅ ፡ መሣግረ ፡ ፍትወት ፡ ዘዕበድ ፡ ዘይብእሶሙ ፡ ወዘያስጥሞሙ ፡ ለሰብእ ፡ ውስተ ፡ ተሠርዎ ፡ ወሞት ።
ሰዎችን ፡ በመነቀል ፡ ባሕር ፡ የሚያስጥማቸው ፡ ስንፍና ፡ ባመጣው ፡ በፈቲው ፡ ጦር ፡ ይያዛሉ ።

www.zeyeneta.com

፲ ፡ እስመ ፡ ሥርዉ ፡ ለዝሉ ፡ እኩይ ፡ አፍቅሮ ፡ ንዋይ ።
የኃጢአት ፡ ነቁዕ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ነውና ፡ ይወድቁ ።
እስመ ፡ ብዙኃን ፡ በዛቲ ፡ ስሕቱ ።
በዚች ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ከሕግ ፡ የወጡ ።
ወፀለዉ ፡ ሃይማኖቶሙ ።

ሃይማኖታቸውን ፡ የለወጡ ፡ አሉና ፡ (አለ ፡) እለ ፡ ግያዝ ፡ እለ ፡ ይሁዳ ፡ (ነገ ፡ ካልዕ ፡ ፭ ፡ ፭ኛ ፡ ማቴ፡ ፭፮ ፡ ፲፰ ፡ -፲፯ ፡ ማር ፡ ፲፭ ፡ ፲ ፡ ሉቃ ፡ ፭፪ ፡ ፫-፯) ።
ወኃሠሡ ፡ ለርእሶሙ ፡ ብዙኀ ፡ መቅሠፍተ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭-፭፩ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፭) ፡
በራሳቸው ፡ መቅሠፍትን ፡ የሚያመጡ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ (ለርእሶሙ) ራሳቸውን ፡ ለመጉዳት ።

፲፪ ፡ ወአንተሰ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጉየይ ፡ እምዝ ።
ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጢሞቴዎስ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ራቅ ።
ወዴግን ፡ ጽድቀ ፡ (፪ኛ ጢሞ ፡ ፪ ፭፪ ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩) ፡
ጽድቅን ፡ ተከተል ፡(አለ) አጽንተህ ፡ያዝ ።

ወምሂረ ፡	ማስተማርን ።
ወሃይማኖተ ፡	ሃይማኖትን ።
ወተፋቅሮ ፡	ፍቅርን ፡
ወትዕግሥተ ፡	ትዕግሥትን ።
ወትሕትና ።	ትሕትናን ፡ አጽንተህ ፡ ያዝ ።

፲፫ ፡ ተጋደል ፡ ሠናየ ፡ ገድለ ፡ በሃይማኖት ፡(፩ ቆሮ ፡፱ ፡፭፭ ፡፭፯) ።
በሃይማኖት ፡ ጸንተህ ፡ በጎ ፡ ገድልን ፡ ተጋደል ።
ለተመጥዎ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘሎቱ ፡ ተጸዋዕከ ።(፩ል ፡፫ ፲፪ ፡፲፩) ፡
በሃይማኖት ፡ የተጠራህላት ፡ የማታልፍ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይን ፡ ለመውረስ ፡
ወአመንከ ፡ ሠናየ ፡ እሚነ ፡ በቅድመ ፡ ብዙኃን ፡ ሰማዕት ።

በብዙ ፡ ምስክር ፡ ፊት ፡ በጎ ፡ እምነት ፡ ያመንህለት ፡ ወገዘሮ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ በእንተ ፡ አይሁድ ፡እለ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ እንዲል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡(፲፯ ፡፫) ።

፲፫ ፡ ከመዝ ፡ እኤዝዘከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ሙታን ፡ ያሐዩ ፡ (ዘዳግ ፡፴፪ ፡፴፱) ፡
ሙታን ፡ ሕሊናን ፡ ትንሣኤ ፡ ሕሊና ፡ ሙታን ፡ ሥጋን ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋ፡በሚያሥነሣቸው፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ አዳኝብሃለሁ ።
ወኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ።
በኢየሱስ ፡ ከርስቶስም ፡ ፊት ፡ አዳኝብሃለሁ ።
ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በቅድመ ፡ ጲላጦስ ፡ ጳንጤናዊ ፡ (ዮሐ ፡፲፰ ፡፴፯ ፡፲፱ ፡፲፩ ።)
በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ።አንድም ፡ አንሰ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መጸእኩ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ
ተወለድኩ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ሰማዕተ ፡ በጽድቅ ፡ ብሎ ፡ የመስከረ ፡ (ዮሐ ፡፲፰ ፡፴፯ ።)

፲፬ ፡ በሠናይ ፡ አሚን ፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ በንጽሕ ።
እኤዝዘከ ፡ በሠናይ ፡ አሚን ፡ ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በሠናይ ፡ አሚን፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ በሠናይ ፡ አሚን፡)
በበ ጕው ፡ ጸንተህ ፡ ብንጽሕና ፡ ኾነህ ፡ ይህን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ አዳኝብሃለሁ ።
እንዘ ፡ ኢታደሉ ።
በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፤ በትምህርት ፤ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይተህ ፡ ሳታዳላ ።
እስከ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ።
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ከርስቶስ ፡ እስከሚመጣበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ።

፲፭ ፡ ዘያስተርኢ ፡ በዕድሜሁ ፡
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የሚገለጽ ።
ዘባሕቲቱ ፡ ብፁዕ ፡(ም ፭ ፡፲፩ ።)
እሱ ፡ ብቻ ፡ ንዑድ ፡ ከቡር ፡ የሚኾን ።

www.zeyeneta.com

ወኃያል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት አግዚአ ፡ አጋዕዝት ፡ (ራሕ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ዘዳግ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።)
ኃያል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አግዚአ ፡ አጋእዝት ፡ የሚኾን ።

፲፯ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ።
እሱ ፡ ብቻ የማይሻር ።
ዘአይመውት ።
ዓልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ፡
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘአይጠፍእ ፡ አምቅድመ ፡ ዓለም ።
ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የማይጠፋ ፡ ብርሃን ፡ ያለው ፡ ዓልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለው ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ፡(ዮሐ ፡፩ ፡፲፰ ።)
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ያየው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ሊያየው ፡ የሚችል ፡ የሌለ ።
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘአይጠፍዕ ፡ አምቅድመ ፡ ዓለም ።
አንድም ፡ የማይለይ ፡ ዕውቀት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚቻለው ፡ የሌለ ።
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘአይጠፍዕ ፡ አምቅድመ ፡ ዓለም ።
አንድም ፡ የማይመረመር ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የመረመረው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ሊመረምረው ፡ የሚቻለው ፡ የሌለ ።
ዘሰቱ ፡ ክብር ፡ መስብሐት ፡ ወኃይል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ከብር ፡ ጌትነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።
አሜን ። በእውነት ።

፲፮ ፡ ለአብዕልተ ፡ ዝንቱኒ ፡ ዓለም ፡ አዝዞሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትአበዩ ።
የዚህን ፡ ዓለም ፡ ባለጸጎች ፡ እንዳይታበዩ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወኢይትአመንዎ ፡ ለብዕሎሙ ፡ ኃላፌ ፡ ዘአንበለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡(መዝ ፡፷፪ ፡፲፩ ፡ሉቃ ፡፲፪ ፡፳።)
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፡ ኃላፊውን ፡ ከብት ፡ እንዳይተማመኑ ፡ አንድም ፡ በሕያው ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ በኃላፊው ፡ ከብት ፡ እንዳይመኩ ።
ዘውእቱ ፡ ይሁበነ ፡ በብዝኀ ፡ ብዕሉ ፡ ኵሎ ።
በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ኹሉን ፡ የሚሰጠን ።
ከመ ፡ ንትፌሣሕ ።
ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ።
፲፰ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ግብረ ፡ ሠናየ ።
(አዝዞሙ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ሠናየ ፡) በጎውን ፡ ሥራ ፡ ይሥሩ ፡ ዘንድ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወይብዐሉ ፡ በገቢረ ፡ ጽድቅ ።
በትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ይከብሩ ፡ ዘንድ ።
ወይኩኑ ፡ ራትዓነ ።
ቅኖች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።
ወጸጋውያነ ።
ለጋሶች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።
ወሱቱፋነ ።
እነዚያ ፡ በመስጠት ፡ ነዳያን ፡ በመቀበል ፡ ለጸሎት ፡ ቆሞ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

www.zeyeneta.com

፲፱ ፡ ወይሣርሩ ፡ ለርእሶሙ ፡ መሠረተ ፡ ሠናየ ፡ ለዘይመጽእ ፡ ዓለም ።
ለሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ለራሳቸው ፡ በጎ ፡ ቢጋርን ፡ ይበግሩ ፡ ዘንድ ፡ (አሰ ፡)በጎ ፡ ተስፋን፡ ይይዙ፡ዘንድ
ከሙ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘበእግን ፡(ግቱ ፡፮ ፡፹ ።)
የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ለመውረስ ።
፳ ፡ እ ጢሞቴዎስ ፡ ዕቀብ ፡ ግኀኒትከ ፡ (፪፡ ጢሞ ፡፩ ፡፲፬ ።)
ጢሞቴዎስ ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ። እንድም ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ።
ተንኣሙ ፡ ለርኩሳን ፡ አለ ፡ ያመጽኡ ፡ ኅጣሬ ፡ ከንቶ ፡ (፪፡ ጢሞ ፡፪ ፡፲፮ ።)
ክንቱ ፡ ኑሮን ፡ የሚያመጡ ፡ ድል ፡ የቀኑሙ ፡ ሰዎችን ፡ ተለያቸው ።
ወያሰስልዎ ፡ ለጽድቅ ፡ ቤሐሰት ።
ጽድቅን ፡ ብኃጢአት ፡ እውነትን ፡ በሐሰት፡ እምልኮትን ፡ በክህደት ፡ ወንጌልን ፡ በአሪት ፡ የሚለውጡ
ትን ፡ ተለያቸው ።
፳፩ ፡ እስሙ ፡ እሉ ፡ ስሕቱ ፡ እምተስፋ ፡ ሃይማኖት ።
እለሃ ፡ ሔምና ፡ ከሚኀኘው ፡ ተስፋ ፡ ወተተዋልና ።
፳፪ ፡ ምስሌከ ፡(ም ፡፮ ፡፯ ፡፪ ጢሞ ፡፪ ፡፲፪ ።)
ጸጋ ፡ እድሮብህ ፡ ይኑር ።
አሜን ። በእውነት ።
ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳሚ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በአቴና ፡ ወተፈነወ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ።
በአቴና ፡ የተጻፈ ፡ በቲቶ ፡ እጅ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ የተሳከ ፡ መጀመሪያ ፡ ክታብ ፡ ዶረስ ፡ ተፈጸመ ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

ኦነሢሶቶ ፡ ላኅጅመሬን ፡ ኦስጀምሮ ፡ ላቴመረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

ምክንያት ፡ ጽሒፎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ መልእክተ ፡ ዳግሚተ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ረድእ፡ በእንተ ፡ መከራ ፡ ወምንዳቤ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሁ፡ወላዕለ፡ ሕዝቡ ፡ እምእሕዛብ ።

እስመ ፡ ተንሥኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ ሕዝቡ፡

በመዓት ፡ ብዙኀ ፡ ወያሕምምዎሙ ፡ ወይሣቅይዎሙ

ቦ ፡ ዘይሞትሕም ፡ ወቦ ፡ ዘይበረብሩ ፡ ንዋየ፡ ቦ ፡ ዘይቀትልዎ ፡ ወቦ ፡ ዘይሰድድዎ ፡ እምሀገር ፡ ለሀገር ። ።

ወእዘዞ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ከሙ ፡ ይትጋደል፡ ሠናየ ፡ ገድለ ፡ ወኢይፍራህ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለመከይድናን ።

ወይገሥጾሙ ፡ ከመ ፡ ኢይፍርሁ ፡ ወያጽንዖሙ

በተበሉ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

ወዓዲ ፡ እዘዞ ፡ ከመ ፡ ይብጻሕ ፡ ኀቤሁ ፡ ፍጡነ ወያመጽኦ ፡ ምስሌሁ ፡ ለማርቆስ ፡ እምቅድመ ፡ ይሙት ።

ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ህሎ ፡ ሙቁሐ፡በሮሜ እመ ፡ ሙቃሔሁ ፡ ደኃራዊ ፡ በምክንያተ ፡ አጥምቆተ ፡ ብእሲተ ፡ ኔሮን ፡ ወእዝማዲሁ ፡ወፈነዎ ፡ በእደ ፡ አንክሮሎስ ።

ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ ለደቅ ፡ መዝሙሩ ፡ለጢሞቴዎስ ፡ ኹለተኛ ፡ ክታብ ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት፡በሱና በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ እሕዛብ ፡ መከራና ፡ ችግር ፡ ስላመጡባቸው ፡ ለማጽናናት ፡ ነው ።

በሱና ፡ በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሥተው ፡ መከራ ፡ ያደርሳቸው ፡ ይሣቅይዋቸው ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ከነሱም ፡ ወገን ፡ የሚያስሩት ፡ ገንዘቡን ፡ የሚዘርፉት ፡ የሚገሉት ፡ ካንጹ ፡ ሀገር ፡ መጻጉ፡ ሀገር ፡ የሚያሳድዱትም ፡ ነበረ ።

ለራሱ ፡ በጎ ፡ ተጋድሎ ፡ እንዲጋደል ፡ ምእመናንንም ፡ ሳይፈራ ፡ እንዲያስተምራቸው ።

እነዚያንም ፡ እንዳይፈሩ ፡ እንዲመክራቸው ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚገኝባት ፡ ተቤሩ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እየነገረ ፡ እንዲያጸናቸው ፡ አዝዞታል ።

ዳግመኛም ፡ ከመሞቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይሞት፡ ማርቆስን ፡ ይዞ ፡ ፈጥኖ ፡ ወደሱ ፡ እንዲመጣ ፡ አዘዘው ።

የኔሮንን ፡ ሚስቱንና ፡ ዘመዶቹን ፡ በማጥመቁ ምክንያት ፡ ኹለተኛ ፡ በሮም ፡ በታሠረ ፡ ጊዜ ፡ በሮም ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ ጻፈለት ።

በእንከሮሎስ ፡ እጅ ፡ ላክለት ።

www.zeyeneta.com

መልእክት ፥ ካልእት ፥ ጎበ ፥ ጢሞቴዎስ ።

ቀዳማዊ ፥ ብሎ ፥ ነበርና ፥ ካልእት ፥ (አለ ፥) ጢሞቴዎስ ፥ ኀፍተኛ ፥ ቢያስተምር ፥ ዓላውያን ፥ መከራ ፥ አጽንተውበታል ፥ መከራውን ፥ ታግሦ ፥ ቢያስተምር ፥ የምእመናን ፥ እአምሯቸው ፥ ፈዞ ፥ ጀራቸው ፥ ደን ዝዞ ፥ ትምህርቱን ፥ የማይቀበሉት ፥ ኾነዋል ፥ ይቀበሉኛል ፥ ብዬ ፥ ነበር ፥ እንጂ ፥ የማይቀበሉኝማ ፥ ከኾነ ። እስመ ፥ ውስተ ፥ ቤተ ፥ እቡየ ፥ ብዙኀ ፥ ማኅደር ፥ ወምዕራፍ ፥ ቤቱ ፥ እንዲል ፥ (ዮሐ ፲፬ ፥ ፪) መንግሥተ ፥ ሰማይ ፥ በብዙ ፥ ወገን ፥ ትወረስ ፥ እንጂ ፥ የለን ፥ ተባሕትዎስ ፥ ብይዝ ፥ ምን ፥ ፅዳየ ፥ ብሎ ፥ ተባሕትዎ ፥ ተመ ኝቷል ፥ ይህን ፥ ሰምቶ ፥ ለዚህ ፥ ይጽፋል ። መለተጋድሌኒ ፥ ለእመ ፥ በሕጉ ፥ ኢተጋደለ ፥ ኢይከውፍ ፡ ሞዝ ጋና ፥ ይላል ። (ም ፥ ፪ ፥ ፭ ፥) ወዘንተኒ ፥ ተአምር ፥ ከመ ፥ ዐለጢኖ ፥ ሱሎሙ ፥ እለ ፥ በእስያ ፥ አለ ፥ ፈሉ ንስ ፥ ወኢርዋኔስ ፥ የሀቦ ፥ እግዚአብሔር ፥ ማህለ ፥ ለቤተ ፥ ሄኔሴፎሩ ፥ ይላል ፥ (ም ፥ ፩ ፥ ፲፮ ፥) ተዘከር ፥ ለኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ዘተንሥአ ፥ እሙታን ፥ (፪ ፥ ፰ ፥) ዴማስ ፥ ኀደገኒ ፥ ወአፍቀሮ ፥ ለዝንቱ ፥ ዓለም ፥ ዘይእዜ ፥ ወሖረ ፥ ተሰሎንቄ ፥ (፬ ፥ ፱ ፥) ወአምጽእ ፥ ምስሌከ ፥ ለማርቆስ ፥ እስመ ፥ ይበቍዓኒ ፥ ለመልእ ክት ፥ (፬ ፥ ፲፩ ፥) ወፈሉንኒ ፥ ዘመጽሐፈ ፥ ዘኀደጉ ፥ በጢሮአስ ፥ ኀበ ፥ አክርጳ ፥ ተግሣፅ ፥ ምስሌከ ፥ አለ አስክንድሮስ ፥ ነሀቢ ፥ ብዙኃ ፥ ሚቀየኒ ፥ ይፍድዮ ፥ እግዚአብሔር ፥ በከመ ፥ ምግባሩ ፥ አስተሩጥን ፥ ትምጻእ ፥ ኀቤየ ፥ እምቅድመ ፥ ክረምት ፥ ይላል ፥ የጸፈበት ፥ ሀገር ፥ ሮም ፥ በዳግማይ ፥ እስራቱ ፥ ከታብ ፥ ወሳጅ ፥ አንከሮሉስ ፥ ነው ።

፩ ፥ እምጳውሎስ ፥ ሐዋርያሁ ፥ ለእግዚእነ ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ በፈቃደ ፥ እግዚአብሔር ።

በፈቃደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ጸንቸ ፥ ብኀኝ ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ከሾመኝ ፥ አንድም ፥ ሰውን ፥ በፈቃደ ፥ እግዚአብሔር ፥ አጸና ፥ ዘንድ ፥ የኢየሱስ ፥ ክርስቶስን ፥ ነገር ፥ ከማስተምር ፥ ከኔ ፥ ከጳውሎስ ፥ የመጣች ፥ ክታብ ። ወበተስፋ ፥ ሕይወት ፥ በኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ (ዮሐ ፥ ፩ ፥ ፬ ፥ ዮሐ ፥ ፫ ፥ ፲፩-፲፫ ።)

በኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ በሚገኝ ፥ በሕይወት ፥ እለኝታ ፥ ጸንቸ ፥ ብኀኝ ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ከሾመኝ ፥ ከኔ ፥ ከጳውሎስ ።

፪ ፥ ለጢሞቴዎስ ፥ ወልድየ ፥ ዘአፈቅር ፥ (፩ ፥ ጢሞ ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ ቲቶ ፥ ፩ ፥ ፬) ።

በሃይማኖት ፥ ጸንቶ ፥ ምግባር ፥ ሲሠራ ፥ ባገኘው ፥ ለምወደው ፥ ለልጄ ፥ ለጢሞቴዎስ ፥ ትድረስ ።

ሰላም ፥ ለከ ።

ቸር ፥ አለህኝ ።

ወሣህል ።

ሐዋርያነት ፥ ይጽናልህ ።

መጽጋ ፥ እግዚአብሔር ፥ አቡነ ፥ ወእግዚእነ ፥ ኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ።

የእግዚአብሔር ፥ አብ ፤ የጌታችን ፥ የኢየሱስ ፥ ክርስቶስ ፥ ጸጋው ፥ ይደረግልህ ።

፫ ፥ አእኩቶ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ዘኪያሁ ፥ አመልክ ፥ በልብ ፥ ንጹሕ ፥ እምፍጥረትየ ።

እምልደትየ ፥ ሲል ፥ ነው ፥ ከቂም ፥ ከበቀል ፥ ንጹሕ ፥ በኾነ ፥ ልቡና ፥ ከአብርሃም ፥ ከይስሐቅ ፥ ከያዕቆብ ጀምሮ ፥ በአሪት ፥ ጣያትን ፥ ሳልቀላቅል ፥ የማመልከው ። አንድም ፥ ከሐዲስ ፥ ተፈጥሮ ፥ ጀምሮ ፥ በወንጌል አሪትን ፥ ሳልቀላቅል ፥ የማመልከው ፥ እግዚአብሔርን ፥ አመሰግነዋለሁ ።

ወዘልፈ ፥ እዜክረከ ፥ በጸሎትየ ፥ መዓልተ ፥ ወሌሊተ ፥ (ግብ ፥ ሐዋ ፥ ፳፫ ፥ ፩ ፥ ፳፬ ፥ ፲፯ ፥ ሮሜ ፥ ፩ ፥ ፯ ፥ ፱ ።)

በመዓልትም ፥ በሌሊትም ፥ በምጸልየው ፥ ጸሎት ፥ አስብሃለሁ ።

፬ ፥ ወእፈቱ ፥ እርአይከ ፥ ወእዜክር ፥ አንብዐከ ።

እንባህን ፥ አስቤ ፥ ላይህ ፥ አወጻለሁ ፥ ሲለየው ፥ እያለቀስ ፥ ተለይቶታል ።

፭ ፥ ወአትፈግሕ ፥ ተዘኪርየ ፥ ሃይማኖተከ ፥ ዘእልቦ ፥ ኑፋቄ ፥(ግብ ፥ሐዋ ፥፲፯ ፥፩ ።)

መጠርጠር ፥ የሌለበትን ፥ ሃይማኖትህን ፥ አስቤ ፥ ደስ ፥ ይለኛል ።

እንተ ፥ ጎደረት ፥ ላዕለ ፥ እምከ ፥ ኤውኒቄ ፥ ወእምሐውትከ ፥ ሎይድ ።

በናትህ ፥ በኤውንቄ ፥ በእያትህ ፥ በሎይድ ፥ ጸንታ ፥ ያለች ።እንድም ፥ በጉባኤ ፥ አሪት ፤ በጉባኤ ፥ ወን ጌል ፤ በጉባኤ ፥ ነቢያት ፤ በጉባኤ ፥ ሐዋርያት ፥ ጸንታ ፥ ያለች ። እንድም ፥ በጉባኤ ፥ ሎዶቅያ ፤ በጉባኤ ፥ ተሰሎንቄ ፥ ጸንታ ፥ ያለች ።

ወእፈጽም ፥ ፍሥሐየ ።

ፈጽሞ ፥ ደስ ፥ ይለኛል ።

www.zeyeneta.com
ምዕራፍ ፲፫ ፪ ፪ ፫ ፫ ፫

www.zeyeneta.com

እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ያስጠበቀኝን ፡ ምእመንን ፡ ሊጠብቅልኝ ፡እንዲቻለው አምናለሁና ።

ወኢይትገፈር ፡ እምዝ ፡ አፋ ፡ ዑቈ ።

እንድም ፡ ካለሁበት ፡ ሐዋርያነት ፡ ወጥቼ ፡ ከብር ፡ እንዳጣ ፡ አልኾንም ፡ እስሙ ፡ አእምር ፡ ዘተአመንኩ ።

ያመንሁበትን ፡ ዐውቀዋለሁና ፡ (አለ) ፡ ባለተምር ፡ ገብር ፡ ሐካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያግባዕከ ፡ ወርትየ። ለዝንቱ ፡ ገብር ፡ አስሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ብሎ ፡ እንዲፈርድብኝ ።

ወእትአመንሂ ፡ ከመ ፡ ይክል ፡ ዐቂበ ፡ ሊተ ፡ ዘአዋህነኒ ፡ እስከ ፡ ይእቲ ፡ ዕስት ።

ባስተምር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ያስጠበቀልኝን ፡ ቀኃፁን ፡ ሊሰጠኝ፡ እንዲቻለው ፡ ዐውቃለሁና ፡ ኢይትኃፈር ።

፲፫ ፡ ወይኩን ፡ ለከ ፡ አርአያ ፡ ውእቱ ፡ ቃለ ፡ ሕይወት ፡ ዘሰማዕከ ፡ በኀቤየ ፡ በሃይማኖት ፡ ወፍቅረ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፫ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡)

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በመውደድ ፡ ጸንተህ ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ የሰማኸው ሕይወት ፡ የሚገኝበት ፡ የወንጌል ፡ ትምህርት ፡ አብነት ፡ ይሁንህ ፡ (አለ) ፡ (ኩኖ ፡ አርግኦ ፡ መአምነለ ብዩ ፡ የነገርኩህ ።

፲፬ ፡ ዕቀብ ፡ ግነፀንተከ ፡ ሠናየ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘነዳር ፡ በላዕሌከ ።(ቍ፡ ፲፪ ፡፩ ጢሞ ፡፮ ፡ ፳ ።)

ግነፀንተከ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ዕቀብ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ) ፡ እድሮብህ ፡ ባለ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በፅ አደራህን ፡ ጠብቅ ።

ወዘንተኒ ፡ ተአምር ፡ ከመ ፡ ዐለውኒ ፡ ዘሱሙ ፡ አለ ፡ በእስያ ።

ይህንም ፡ ታውቀዋለህ ፡ በእስያ ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ጥለውኝ፡ እንደሔዱ ፡ ፈተነህ ፡ ና ፡ ለማስት ፡ እንድም፡ በእስያ ፡ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ትምህርቴን ፡ አንቀበልም ፡ እንዳሉ ፡ ታውቃለህ ፡(ያስ) እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲኾን ፡ ማስ ተግርን ፡ እንዳልተውኩ ፡ እንተም ፡ አትተው ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

እለ ፡ ፈሉጎስ ፡ ወሔርሞጌኔስ ፤ ናቸው ።

፲፯ ፡ ወየሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማህለ ፡ ለቤተ ፡ ሄኔሴፎሩ ።

ለሄኔሴፎሩ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታውን ፡ ይስጠው ።

ከመሰ ፡ ብዙኅ ፡ አፅፈዱኒ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ ብሎኛልና ።

መኢኃፍረ ፡ በእግዘ ፡ መጥቅሕቱ ።

ከሰራቢም ፡ ጊዜ ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘኛል ፡ አላልምና ፡ የሀቦ ።

፲፰ ፡ ወበጲሖ ፡ ኀበ ፡ ሮሜ ፡ ፍጡነ ፡ ጎሙኒ ፡ ወረከቦ ፡ ሙትሕየ ፡(ግብ ፡ሐዋ ፡፳፰ ፡፲፮ ።)

ሮም ፡ ደርሶ ፡ ታስሬ ፡ አግኝተኝ ጠየቀኝ ፡ እንጂ ፡ ኢኀፈፈ ፤ ጠይቆኛልና ፡ የሀቦ ።

፲፱ ፡ የሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርከብ ፡ ማህለ ፡ በኀበ ፡ እግዚእን ፡ በዕለቲ ፡ ፀለት ።

በጌታችን ፡ ፈት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ይቅርታን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ማማኞን ፡ ይስጠው ።

ወመጠነ ፡ ተልእከኒ ፡ በኤፌሶን ፡ ለቢከ ፡ ተአምር ።

በኤፌሶን ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ሲሣር ፡ እንዳገለገልኝ ፡ ታውቃለህ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ወእንተኒ ፡ ወልድየ ፡ ጽናዕ ፡ በጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

አንተኒ ፡ ቢል ፡ ለሄኔሴፎሩ ፡ ዋዊ ፤ አንተሰ ፡ ቢል ፡ ፡አለውኒ ፡ ላለው ፡ አፍራሽ ፤ ልጂ ፡ አንተም ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሾመህ ፡ ሐዋርያነት ፡ ጸንተህ ፡ ኑር ።

፪ ፡ ወዘሰማዕከ ፡ በላዕሌየ ፡ በኀበ ፡ ብዙኃን ፡ ሰማዕት ፡ ከያሁ ፡ መዐርፉ ፡ ለመሃይምናን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ።(፩ ፡ ጢሞ ፡፫ ፡፪ ።)

በብዙ ፡ ምስክር ፡ ፊት ፡ ከኔ ፡ የተማርኸውን ፡ ትምህርት ፡ ለሌላው ፡ ማስተማር ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎች፡ አስተምራቸው ፤ እንድም ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ አስተምራቸው ።

www.zeyeneta.com

ከመ ፡ ይምሀሩ ፡ ለባዕዳን ።
ያው ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ ወጸሙ ፡ ከመ ፡ ጌር ፡ መስተጋድል ፡ ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ም ፭ ፡ ፮ና ፯ ፡ ፭) ።
ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጢሞቴዎስ ፤ እንደበገ፡ ሥጋዊ ፡ እርበኛ ፡ ጸር ፡ ድከም ፡ እንድም ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያገለግል ፡ መንፈሳዊ ፡ እርበኛ ፡ እንደመኾንህ ፡ እንድም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሚ ያገለግል ፡ መንፈሳዊ ፡ እርበኛ ፡ ጸር ፡ ድከም ።

፬ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘይትቃተል ፡ ወይሔሊ ፡ ንብረተ ፡ ዝ ፡ ዓለም ።
ወደሰልፍ የሚገባ ፡ ገብቶም ፡ ላም ፡ እረዱ ፡ ጠጅ ፡ አውርዱ ፡ የሚል ፡ የለምና ።
ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ያድሉ ፡ ለዘሜሞ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፭፩ ።)
ገሎ ፡ ለልቦ ፡ ሲያገር ፡ ጌታውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ መስተጋድልኒ ፡ አይከውኖ ፡ ምዝጋና ፡ ለአመ ፡ በሕጉ ፡ ኢተጋደለ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
እርበኛም ፡ ባለበት ፡ ጸንቶ ፡ ካልተዋጋ ፡ አይመስገንም ፡ ደጀን ፡ ኹን ፡ ቢሉት ፡ ፊታውራሪ ፡ ልኹን ፡ ፊታውራሪ ፡ ኹን ፡ ቢሉት ፡ ደጀን ፡ ልኹን ፡ ቢል ። አንድም ፡ በቀኝ ፡ እስፍ ፡ ሲሉት ፡ በግራ ፡ እስፍ ፡ ሲሉት በቀኝ ፡ ልኹን ፡ ቢል ።

፮ ፡ ወዘኒ ፡ ይጸሙ ፡ ሐረሳዊ ፡ ግብር ፡ ይቀድም ፡ ለረኪበ ፡ ፍሬሁ ።
(ይጸሙ ፡ ግብረ) ፡ የሚጽር ፡ ገበሬ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥራ ፡ ይደክማል ፡ (ለረኪበ ፡ ፍሬሁ) ፡ ፍሬ ውን ፡ ለማግኘት ። አንድም ፡ በሥራ ፡ ያሚደክም ፡ ገበሬ ፡ (ያቀድም ፡ ረኪበ ፡ ፍሬሁ) ፡ ወፍ ፡ መጠጠው ፡ አይጥ ፡ ቆረጠው ፡ ሳይል ፡ አስቀድሞ ፡ እሹቱን ፡ ይቀምሳል ፡ እንደዚህም ። ኹሉ ፡ አስተምርና ፡ እሸት ፡ ትምህርትን ፡ ልቅመሳት ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ወለቡ ፡ ዘእቤለክ ።
የዎ ነግርህን ፡ ነገር ፡ አስተውል ።

፯ ፡ የህብክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበበ ፡ በዙሉ ።
በውስጥ ፡ በእፍአ ፡ በሥራ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕውቀቱን ፡ ይግለጥልህ ።

፰ ፡ ተዘከር ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙታን ፡(፩ቆሮ ፡፲፭ ፡፬ ፡፳ ።)
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አስበው ፡(አስ)አብነት ፡ አድርገው ።
ዘእምዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ዘመሀርኩ ፡ በስሙ ፡ (፪ ሳሙ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።)
ከዳዊት ፡ ባሕርይ ፡ የተወለደ ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደኾነ ፡ የማስተምርለት ።

፱ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ እሠርሕ ።
በመከራ ፡ የምደከምለት ።

ወአትሞታሕ ፡ ከመ ፡ ጉ ሕልያ ፡ (ቮ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፊል ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።)
እንደሌባ ፡ እንደቀጣፊ ፡ የምታስርለት ።
ወባሕቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ኢይትአሰር ፡ (ፊል ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ብታሰር ፡ ትምህርት ፡ አይፈታም ።

፲ ፡ ወበእንተዝ ፡ እትኤገሥ ፡ በዙሉ ፡ በእንተ ፡ ኅሩያኒሁ ፡ (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።)
ስለዚህ ፡ ምእመናንን ፡ ስለማስተምር ፡ በውስጥ ፡ በእፍአ ፡ መከራውን ፡ ታግሼ ፡ አቀበላለሁ ።
ከመ ፡ እሙንቱኒ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘበኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ዋቄው ፡ ለሐዋርያት ፡ ነው ። እነሱም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕይወት ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ (አስ ይወርሱ ፡ ዘንድ ።
ወስብሐተ ፡ ዘለዓለም ፡ ዘበሰማያት ።
በልዕልና ፡ ያለ ፡ የዘለዓለም ፡ ክብርን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ እሙን ፡ ነገር ።
ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።
እምከመ ፡ ወደየኒ ፡ ዘመዊቶ ፡ ንዒሪ ፡ ሕይወተ ፡(፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ጴጥ ፪ ፡ ፲፫ ።)
በሞት ፡ ያለመለየት ፡ ዘላዊ ፡ ሕይወት ፡ እንመለስለታለን ።

www.zeyeneta.com

፲፪ ፡ ወእምከመ ፡ ዐረይነ ፡ ትዕግሥተ ፡ ንዒረ ፡ ነጊሥ፡ (ማቴ፡ ፲፡ ፴፫ ።)
በመከራም ፡ ከመስልነው ፡ በከብር ፡ እንመስለዋለን ፡ እንድንመስለው ፡ እሙን ።
ወእመስ ፡ ከሀድናሁ ፡ ውእቱ ፡ ይከሀደነ ፡(ሮሚ ፡፫ ፡፬ ።)
እሱ ፡ ብንለው ፡ ግን ፡ እሱም ፡ አሱ ፡ ይለናል ።

፲፫ ፡ ወእመኒ ፡ ኢአመናሁ ።
ባናምነውም ፡ ለኛ ፡ ይባሰን እንጂ ፡ እሱስ ፡ የታመነ ፡ የባሕርይ ፡ እምላክ ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ።
ወኢይክል ፡ ከሂደ ፡ ርእሶ፡ (ሮሚ፡ ፫፡ ፫፡ ዘጎል፡ ፭፫፡ ፲፱ ።)
ከሂዱ ፡ ርእሱ ፡ ከሂዱ ፡ ርእሶ ፡ ይላል ፡ ራሱን ፡ አሱ ፡ አይልም ።

፲፬ ፡ ከመዝ ፡ ዘከርሙ ።
እንዲህ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወአስምዕ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር፡ (፩፡ ጢሞ፡ ፭፡ ፬ ፡ ቲቶ፡ ፫፡ ፱ ።)
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አዳኝባቸው ።
ኢትትላኩይ ፡ በግብር ፡ ዘኢይበቍዕ ።
በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ አትከራከር ።
በዘይትገፈትው ፡ እለ ፡ ይስምው ።

የሚሰሙ ፡ ሰዎች ፡ ድል ፡ በሚነሡ ፡ ገንዘብ ።

፲፭ ፡ አስተሩጥን ፡ ከመ ፡ ትረሲ ፡ ርእሰከ ፡ ኅሩየ ፡ ለኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡(፩ ጢሞ ፡፬ ፡፯ ፡ቲቶ ፡፪ ፡፫ ።
አስተምረህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ደግ ፡ ለመባል ፡ ለማስተማር ፡ ቸኩል ።
ከመ ፡ ገባራዊ ፡ ዘኢይትኀፈር ፡ ዘርቱዓ ፡ ይመትር ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ።
(አስተሩጥን ፡ በጽድቅ ፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡) ገበሬ ፡ ቀን ፡ ለቀን ፡ ሳያፍር ፡ ሳይፈር ፡ እሸ
ትን ፡ እታንቶ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲቆርጥ ፡ እንተም ፡ ሳታፍር ፡ ሳትፈር ፡ ወንጌልን ፡ እታንተህ ፡ ለማስተማር፡
ቸኩል ። እንድም ፡ እንደ ፡ ነገር ፡ ገበሬ ፤ የነገር ፡ ገበሬ ፡ ባጸባበይ ። ገብቶ ፡ ሳያፍር ። ሳይፈር ፡ ነገሩን ፡
እታንቶ ፡ እንዲቆርጥ ፡ ወንጌልን ፡ እታንተህ ፡ ሳትፈር ፡ ሳታፍር ፡ ለማስተማር ፡ ቸኩል ።

፲፮ ፡ ወለነገረ ፡ ርኩሳንሰ ፡ ዘአልቦ ፡ ባቍዕ ፡ ዕበዮ ፡
ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ድል ፡ የተነሡ ፡ ሰዎች ፡ የሚያስተምሩት ፡ አሪትን ፡ ግን ፡ ተወው ።
እስመ ፡ ያዐብይዋ ፡ ለኃጢአቶሙ ፡ (፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፮ ።)
ኃጢአታቸውን ፡ ያስፋፏታልና ፡ ርኩሳን ።

፲፯ ፡ ወነገሮሙኒ ፡ ከንቱ ።
ነገራቸውም ፡ ከንቱ ፡ አሪት ፡ ነውና ፡ ዕበዮ ።
ከመ ፡ ዘይትረዐይ ፡ ወይልህቅ ፡ በብዙኃን ።
የዓብይዋ ፡ ከመ ፡ ዘይትረዓይ ፡) በብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚሰፋ ፡ ቍስል ፡ ያስፋፏታልና ፡ ዋጣ ፡ ቂጥኝ፡
ቍስለ ፡ ሥጋ ፡ ችፌ ፡ ጕርምጥ ፡ ናቸው ።
እለ ፡ ሄሜኔዎስ ፡ ወፊሎጦስ ። (፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፳) ናቸው ።

፲፰ ፡ እለ ፡ እውከኩ ፡ እምጽድቅ ።
ከጽድቅ ፡ የወጡ ።
ወይብሉ ፡ ወድአ ፡ ኮነ ፡ ትንሣኤ ፡ ምውታን ፡ ወይገፈትው ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ለብዙኃን ።
ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ይሏችኋል ፡ ሌላን ፡ አለ ፡ ታሞ ፡ መነሣት ፡ አጥቶ ፡ ማግኘት ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ እያሉ፡
የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚለዋውጡ ።

፲፱ ፡ ወዘሰ ፡ ጽኑዕ ፡ በመሠረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀውም ።
ወይብሉ ፡ ወድአ ፡ ኮነ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ እምጻኤ ፡ ዓለማትነቱን ፡ በማመን ፡
የጸና ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ በማመን ፡ ይጸናል ።
እንዘ ፡ ቦ ፡ ዝንቱ ፡ ማዕተብ ።

እምጻኤ ፡ ዓለማትነቱ ፡ አብነት ፡ ኾኖት ። እንድም ፡ ተዘክሮ ፡ ስኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙ
ታን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የጌታን ፡ ትንሣኤ ፡ በማመን ፡ የጸና ፡ የራሱን ፡ ትንሣኤ ፡ በማመን ፡ ይጸናል ።

www.zeyeneta.com

የጌታ ፡ ትምህርት ፡ አብነት ፡ ኾኖት ። አንድም ፡ እምከመ ፡ ዐረይነ ፡ ትዕግሥት ፡ ንዒሪ ፡ ነጊሥ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የጌታን ፡ መከራ ፡ በማመን ፡ የጸና ፡ በትዕግሥት ፡ ይጸናል ።
(እንዘ ፡ ቦ ፡ ዝንቱ ፡ ማዕተብ) ።
የጌታ ፡ መከራ ፡ አብነት ፡ ኾኖት ። አንድም ፡ ወለነገረ ፡ ርኩሳንሰ ፡ ዘአልቦ ፡ ባቍዕ ፡ ዕበዮ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የጌታን ፡ ትምህርት ፡ በማመን ፡ የጸና ፡ በሃይማኖት ፡ ይጸናል ።
(እንዘ ፡ ቦ ፡ ዝንቱ ፡ ማዕተብ) ።
የጌታ ፡ ትምህርት ፡ አብነት ፡ ኾኖት ።
ወየአምሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእሊአሁ ። (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፫ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ።)
እግዚአብሔር ፡ ያመኑበት ፡ ወገኖቹን ፡ ይወዳቸዋል ።
ወይርነቅ ፡ እምዓመፃ ፡ ዙሉ ፡ ዘይሰሚ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ።
ስመ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፡ ከከሀዲት ፡ ክፍዳ ፡ ይርቃል ።
ውስተ ፡ ቤትኒ ፡ ዓቢይ ፡ አኮ ፡ ባሕቲቱ ፡ ንዋየ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ።
በቤተ ፡ መንግሥት ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ዕቃ ፡ ብቻ ፡ አይኖርም ።
ዓዲ ፡ ቦ ፡ ዘዕፅኒ ፡ ወዘልሕኩትኒ ።
የዕንጨትም ፡ የሸክላም ፡ አለ ፡ እንጂ ።
ቦ ፡ ዘለክብርኒ ፡ ወቦ ፡ ዘለጎሳርኒ ።
ለክብርም ፡ ለጎሣርም ፡ የሚኾን ፡ እለ ፡ (ሐተታ) ፡ ለክብር ፡ የሚለው ፡ እንጀራ ፡ የሚጣልበት ፡ ወጥ ፡ የሚቀዳበት ፡ ገበታው ፡ ነው ፡ ለጎሣር ፡ የሚለው ፡ የሚነደው ፡ ዕንጨቱ ፡ ነው ።
(እንድም) ፡ ውስተ ፡ ቤትኒ ፡ ዐቢይ ፡ አኮ ፡ ባሕቲቱ ፡ ንዋየ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ።
በቤተ ፡ ወንጌል ፡ ጻድቃን ፡ ብቻ ፡ አምነው ፡ አይኖሩም ።
ዓዲ ፡ ቦ ፡ ዘዕፅኒ ፡ ወዘልሕኩትኒ ።
ኃጥአንም ፡ አምነው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ።
ቦ ፡ ዘለክብርኒ ፡ ወቦ ፡ ዘለጎሣርኒ ።
ለክብር ፡ የሚላቸው ፡ እምነው ፡ ተጠምቀው ፡ የክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ናቸው ፡ ለጎሣር ፡ የሚላቸው ፡ እምነው ፡ ተጠምቀው ፡ የንስሐ ፡ ሥራ ፡ ያልሠሩ ፡ ናቸው ። እንድም ፡ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ የክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ። አንድም ፡ ውስተ ፡ ቤትኒ ፡ ዐቢይ ፡ አኮ ፡ ባሕቲቱ ፡ ንዋየ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ።
በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ጻድቃን ፡ ብቻ ፡ አይነሡም ።
ዓዲ ፡ ዘዕፅኒ ፡ ወዘልሕኩትኒ ።
ኃጥአንም ፡ ይነሣሉ ፡ እንጂ ።
ቦ ፡ ዘለክብርኒ ፡ ወቦ ፡ ዘለጎሣር ።
ለክብርም ፡ ለጎሣርም ፡ የሚኾን ፡ አለ ፡ (ሐተታ) ፡ ለክብር ፡ የሚላቸው ፡ እለሰ ፡ ሠናየ ፡ ገብሩ ፡ ይወፅኡ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለሕይወት ፡ ባለው ፡ የሚነሡ ፡ ናቸው ፡ ለጎሣር ፡ የሚላቸው ፡ እለሰ ፡ እኩየ ፡ ገብሩ ፡ ይወፅኡ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለደይን ፡ ባለው ፡ የሚነሡ ፡ ናቸው ።
ጽፎ ፡ ወእመሰ ፡ ዘአንጽሐ ፡ ርእሶ ፡ አምዝ ፡ እኩይ ፡ ይከውን ፡ ንዋየ ፡ ክብር ፡ ቅዱስ ።
ወለነገረ ፡ ርኩሳንሰ ፡ ዘአልቦ ፡ ባቍዕ ፡ እያለ ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፡ ከዚህ ፡ ከከፉ ፡ ነገር ፡ ሰውነቱን ፡ የለየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ ክቡር ፡ ዕቃ ፡ ይኾናል ።
ወባቍዐ ፡ ለመልእክተ ፡ እግዚኡ ።
ጌታውን ፡ ለማገልገል ፡ የጠቀመ ፡ ይኾናል ።
ወድልወ ፡ ለዙሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።
ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የበቃ ፡ ይዘጋጃል ።
ጽፎ ፡ ጕየያ ፡ ለፍትወተ ፡ ውርዙት ፡ ወዴግና ፡ ለጽድቅ ፡ (ፊጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፩ ።)
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ የሕግንነትን ፡ ሥራ ፡ ትተህ ፡ ጽድቅን ፡ ተከታተላት ፡ (አለ) ፡ አጽንተህ ፡ ያዛት ።
ወለሃይማኖት ፡ ሃይማኖትን ።
ወተፋቅሮ ።
ፍቅርን ፡ አጽንተህ ፡ ያዝ ።
ወሰላም ፡ ምስለ ፡ ዙሎሙ ፡ እለ ፡ ይጼውዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በልብ ፡ ንጹሕ ።
ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ልቡና ፡ ኾነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚለምኑ ። አንድም ፡ ከከሀዲት ፡

www.zeyeneta.com

ከኑፋቄ ፣ ንጹሕ ፣ በኾነ ፣ ልቡና ፣ ኾነው ፣ እግዚአብሔርን ፣ ከሚያምኑ ፣ ሰዎች ፣ ጋራ ፣ ፍቅር ፣ እንድነትን ፣ ወደመያዝ ፣ ገሥግሥ ።

፳፪ ፡ ዕበየ ፡ ለነገረ ፡ ዕበድ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯ ።)
የስንፍናን ፡ ነገር ።
መስላቅ ።

የዋዛ ፡ የፈዛዛ ።
ወተነሥሥ ፡ ከንቱ ።
የጸብዕ ፡ የከርከርን ፡ ነገር ፡ ተወው ። አንድም ፡ (ነገረ ፡ ዕበድ ፡) ሥርዓተ ፡ ፈሪሳውያን ፡ (ነገረ ፡ ስላቅ ፡) ሥርዓተ ፡ ሰዱቃውያን ፡ (ተንሥሥ) ፡ ከንቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ረበናትን ፡ ተወው ።
ተአምር ፡ ከመ ፡ መንሙት ፡ ያመጽእ ።
ይህ ፡ ኹሉ ፡ ጸብዕ ፡ ከርከርን ፡ እንዲአመጣ ፡ ታውቃለህና ።

፳፬ ፡ ወገብረ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ኢይትገአዝ ፡ (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፯ ።)
ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምእመን ፡ ግን ፡ በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ አይከራከርም ።
አላ ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ ይከውን ፡ ምሰለ ፡ ኵሉ ።
ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ እንደየዋህ ፡ ሕፃን ፡ ይኾናል ፡ አንጂ ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ ከኹሉ ፡ ታው ፡ እንዳሕፃን ፡ የዋህ ፡ ይኾናል ፡ አንጂ ።
መመምህረ ፡ ወመሥተጋሥ ፡ እምኵሉ ።
ከፉውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታግሦ ፡ የሚመክር ፡ የሚያስተምር ፡ ይኾናል ፡ አንጂ ።

፳፭ ፡ ወይጌሥጽ ፡ በየውህት ፡ ለእለ ፡ ይትቃረኑ ።
የሚከራከሩትን ፡ ባለመቃወም ፡ ኾኖ ፡ ይረታል ፡ አንጂ ።
እመቦ ፡ ከመ ፡ የህቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነስሑ ።
ምናልባት ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ መመለሱን ፡ ይሰጣቸው ፡ እንደኾነ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መለጠት ፡ እንዳለ ፡ ብሎ ፡ ይጌሥጽ ፡ ላለው ፡ አሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መለጠት ፡ መጠራጠር ፡ አይደለም ፡ የእሱን ፡ መመለስ ፡ መጠራጠር ፡ ነው ፡ አንጂ ።
ወያእምርዋ ፡ ለጽድቅ ።
ጽድቅን ፡ ሃይማኖትን ፡ ያውቁት ፡ ዘንድ ።

፳፮ ፡ ወያንቅሁ ፡ ነፍሶሙ ፡ እመሥገርተ ፡ ሰይጣን ።
ለውነታቸውን ፡ ከለይጣን ፡ እሽክላ ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ።
እስመ ፡ ወድእ ፡ አሥገሮሙ ፡ ለተሊወ ፡ ፈቃዱ ።
ፈቃዱንም ፡ ለማሠራት ፡ ፈጽሞ ፡ እጅ ፡ አድርጎቸዋልና ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወዘንተ ፡ ባሕቱ ፡ እእምር ።
ይህን ፡ ብቻ ፡ ዕወቅ ።
ከመ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ይመጽእ ፡ ዓመታት ፡ አኩያት ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
ወደኋላ ፡ ከፉ ፡ ዘመን ፡ እንዲመጣ ።

፪ ፡ ወይከውኑ ፡ ሰብእ ፡ መፍቀርያነ ፡ ርእሶሙ ።
ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ራሳቸውን ፡ የሚወዱ ፡ የሚኾኑበት ።
መፍቀርያነ ፡ ፈጊዕ ፡ ወንዋይ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፱-፴፩ ።)
ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማድረግን ፡ ገንዘብን ፡ የሚወዱ ።
ነባብያን ።
ቀባጣሮች ፡ የሚኾኑበት ።

www.zoyeneta.com

በላውያን ፡ ወንጀለኞች ፡
ዝኑራን ፡ ትዕቢተኞች ፡
ጽሩፋን ፡ ተሳዳቦች ፡
ዓላውያን ፡ እዝማዲሆሙ ፡
እናት ፡ አባታቸውን ፡ የማይረዱ ፡ የሚኾኑበት ፡
አለ ፡ አልበሙ ፡ እኩቴት ፡
እግዚአብሔርን ፡ የማያመሰግኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማያመሰግናቸው ፡
ፎ ፡ ውፁእነ ፡ ጽድቅ ፡ ከጽድቅ ፡ የወጡ ፡
እሰ ፡ እልበሙ ፡ ምሕረት ፡
ለሰው ፡ የማያዝኑ ፡ የማይራሩ ፡ ኃጢአትን ፡ ሽልገው ፡ የማይሠሩ ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ የማያዝኑላቸው ፡ የማይራሩላቸው ፡
ሥሑጻን ፡
ጠለቅላቆች ፡ ተገዳዳሮች ፡ ተቀጣጣቦች ፡
ጸላዕያነ ፡ ሠናይ ፡
በጎውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሚጠሉ ፡
፩ ፡ ዝሉፋን ፡
ኃጢአት ፡ አዘውታሮች ፡ ደፋሮች ፡ ሴሰኞች ፡ ተሳዳቦች ፡ የሚኾኑበት ፡
ጽሉዓን ፡
እግዚአብሔርን ፡ የሚጠሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጠላቸው ፡
አለ ፡ ያበድሩ ፡ ሐውዘ ፡ እምፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ፊል ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፡)
ከመከራ ፡ ተድላ ፡ ሥጋን ፡ ከመንፈል ፤ አሪትን ፡ የወደዱ ፡
ፌ ፡ ይትሜሰሉ ፡ ጸድቃነ ፡
ጸድቃንን ፡ የሚመስሉ ፡ የሚኾኑበት ፡
ወይከህድዎ ፡ ለኃይለ ፡ ጽድቅ ፡
የወንጌልን ፡ ምሥጢር ፡ የሚክዱ ፡ የሚኾኑበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲመጣ ፡ ይህን ፡ ብሎ ፡ ዕወቅ ፡
ወለእሰ ፡ ከመዝ ፡ ተገኅስኩሙ ፡ (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ፡ ጽ፳ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ፡)
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ተለያቸው
ፏ ፡ እሰመ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይትባሐኡ ፡ አብያተ ፡ ሰብእ ፡
እሊህ ፡ ወደሰው ፡ ቤት ፡ ጥልቅ ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡
ወይጼውዕዎን ፡ ለአንስት ፡ እለ ፡ ፅፉራት ፡ በኃጢአት ፡ (ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፬ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡)
በኃጢአት ፡ የጸኑ ፡ ሴቶችን ፡ ማርከው ፡ ይመስጿቸዋልና ፡
ወያወርዳ ፡ ውስተ ፡ ብዙኀ ፡ ፍትወት ፡
(እለ ፡ ፅፉራት ፡ ወእለ ፡ ያወርዳ ፡) ወደፈቲው ፡ ጸር ፡ የሚያዳርሱ ፡ ሴቶችን ፡ ማርከው ፡ ይመስጿቸዋልና ፡
ፃ ፡ ወዘልፈ ፡ ይትጌሠጹ ፡
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹልጊዜ ፡ ይማራሉ ፡
ወኢያእምርዋ ፡ ግሙራ ፡ ለጽድቅ ፡
ክቶ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልን ፡ እያውቋትም ፡
ፆ ፡ ከመ ፡ ኢያኔስ ፡ ወኢያንበሪስ ፡ (ዘጸአ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡
እንደ ፡ ኢያኔስ ፡ እንደ ፡ ኢያንበሪስ ፡ ኢያኔስ ፡ ኢያንበሪስ ፡ ሙሴን ፡ እንደተቃወሙት ፡
እንደዚህም ፡ ኹሉ ፡ እሊህም ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልን ፡ ተቃወሚት ፡ (ሐተታ ፡) ኢያኔስ ፡ ኢያንበሪስ ፤ ስማቸው ፡ በአሪቱ ፡ አልተጻፈም ፡ እሱ ፡ ባወቀ ፡ ተናግሯቸዋል ፡
ሰብእ ፡ ሙስናን ፡ ልብ ፡
ልቡናቸው ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡
ወንፉቃነ ፡ ሃይማኖት ፡
ሃይማኖት ፡ የሌላቸው ፡

www.zeyeneta.com

፱ ፡ ወኢይትሌዓሉ ።
ልዕልና ፡ ነፍስ ፡ የማያገኙ ።
እስመ ፡ ፈድፋዶት ፡ ዕበዶሙ ።
ስንፍናቸው ፡ በዝታለች ፡ ጸንታለችና ።
ወተዐውቀት ፡ ለዙሉ ።
ለኹሉ ፡ ታውቃለች ፡ ተረድታለችና ።
ከመ ፡ እበዶሙ ፡ ለእልክቱ ፡ ዓዲ ።
የኢያኔስ ፡ የኢያንበሬስ ፡ ስንፍናቸው ፡ ከኹሉ ፡ ደርሳ ፡ እንደታወቀች ፡ (ዓዲ ፡ እበዶሙ ፡ ለእልክቱ ፡
የሊህም ፡ ስንፍና ፡ ለኹሉ ፡ ታውቃለች ፡ ተረድታለችና ።

፲ ፡ ወአንተሰ ፡ ተለውከ ፡ ትምህርትየ ።
እንተ ፡ ግን ፡ ትምህርቴን ፡ አጽንተሃል ።
ወተመሰልከ ፡ በግእዝየ ።
ግብሬንም ፡ ይዘሃል ።
በዘመህርኩክ ፡ በሃይማኖት ፡
ባስተማርሁህ ፡ ሃይማኖት ፡ጸንተህ
ወበተፋቅሮ ፡ ወበትዕግሥት ።
በፍቅር ፡ በትዕግሥት ፡ ጸንተህ ።
ወበጎድዐት ።
በገፃታ ፡ በጸጥታ ፡ ኾነህ ፡ ግብሬን ፡ ይዘሃል ።

፲፩ ፡ ወበተሰዶ ።
ሀገር ፡ ጥሎ ፡ በመሰደድ ።
ወበሕማም ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ፡ መዝ ፡ ፴፬ ፡ ፳ ።)
በመከራ ፡ እኔን ፡ መስለሃል ።

ተአምር ፡ መጠነ ፡ ረክበኒ ፡ በአንጾኪያ ፡ ወበኢቆንያ ፡ ወበልስጥራን ፡ መጠነ ፡ ተወገሥኩ ፡ ተሰዶ ።
ሀገር ፡ ጥሎ ፡ ስመሰደድ ፡ በአንጾኪያ ፡ በኢቆንያ ፡ በልስጥራን ፡ ያገኘኝን ፡ መከራ ፡ ታውቀዋለህና ።
ወእምኵሉ ፡ አድኀነኒ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ከኹሉ ፡ እንዳዳነኝ ፡ ታውቃለህና ፡ ተሰውከ ።

፲፪ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይሕየዉ ፡ በጽድቀ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሐምሙ ፡ (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፬
ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትሩፋት ፡ ሊከብሩ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ መከራ ፡ ይቀበላሉ ።

፲፫ ፡ ወሰብእስ ፡ እኩያን ፡ ይትሌዓሉ ፡ ውስተ ፡ እንተ ፡ ተአኪ ።
ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ክክፋት ፡ ወደክፉት ፡ ይሔዳሉ ።
ወይስሕቱ ፡ ወያስሕቱ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
ለራሳቸው ፡ ስተው ፡ ሌላውን ፡ ያስታሉ ።

፲፬ ፡ ወአንተሰ ፡ ሀሉ ፡ በዘተምህርከ ፡ ወተአመንከ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፪ ፡)
አንተ ፡ ግን ፡ ባመንኸው ፡ እምነት ፡ በተማርኸው ፡ ትምህርት ፡ ጸንተህ ፡ ኑር ፡

፲፭ ፡ ተአምር ፡ በጎበ ፡ መኑ ፡ ተምህርከ ፡ እምንእስከ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱሰ ፡ በሃይማኖተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
(ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፱ ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ብትጸና ፡ ሊያድንህ ፡ የሚቻለው ፡ ከቡር ፡ ወንጌልን ፡ ከሕግንትህ ፡
ጀምሮ ፡ ዘግን ፡ እንደተማርህ ፡ ታውቃለህና ። (አሰ ፡) ከኔ ፡ እንደተማርህ ።

፲፮ ፡ ወኵሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘበመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጽሕፈ ፡ ይበቍዕ ፡ በኵሉ ፡ ትምህርት ። (፪ ጴጥ ፡ ፩፲፱-፳፩
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ትምህርት ፡ በመኾን ፡ ይጠቅማል ።

ወተግሣጽ ፤ ምክር ፡ እዝናት ፡ በመኾን ።
ወአርትዖ ፤ ልቡናን ፡ ለማቅናት ።

www.zeyeneta.com

ወአጥብዖ ፤ ዕውቀትን ፣ በመግለጽ ።
ወጽድቅ ፤ ትሩፋት ፣ በማሠራት ፣ ይረባል ፣ ይጠቅማል ።

፲፯ ፣ ከመ ፣ ይትገሠጽ ፣ ብእሴ ፣ እግዚአብሔር ፣ ውስተ ፡ ዅሉ ፣ ምግባረ ፣ ሠናይ ፣ (፭ ፣ ጢሞ ፣ ፮ ፣ ፲፮። ም ፪፡ ፭፭።
ብእሴ ፣ እግዚአብሔር ፣ ምእመን ፣ በጕውን ፣ ሥራ ፣ ዅሉ ፣ ይማር ፣ ዘንድ ፣ አርትዖ ፣ ጥበብ ፤ ሳለው ።
አንድም ፣ ብእሴ ፣ እግዚአብሔር ፣ ምእመን ፣ በበጎው ፣ ሥራ ፣ ፍጹም ፣ ይኾን ፣ ዘንድ ፣ (ዘበመንፈስ ፣ እግዚ
አብሔር ፣ ተጽሕፈ ፣ ይበቍዕ ፣ ሳለው ።)

ም ዕ ራ ፍ ፣ ፬ ።

፩ ፣ ወእኤዝዘከ ፣ በቅድመ ፣ እግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር ፣ ፊት ፣ አዳኝብሃለሁ ።
ወእግዚእነ ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ዘሀለዎ ፣ ይኩንን ፣ ሕያዋን ፣ ወሙታን ፣ አመ ፣ ይመጽእ ፣ በመንግሥቱ ።
(ግብ ፣ ሐዋ ፣ ፲፡፵፪ ። ፪ ተሰ ፣ ፩ ፡ ፭፡፳ ። ፩ ጴጥ ፣ ፬ ፣ ፭ ።
በጌትነቱ ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ በሙታንም ፣ በሕያዋንም ፣ ይፈርድ ፣ ዘንድ ፣ ባለው ፣ በጌታችን ፣ በኢየሱስ ፣
ክርስቶስም ፣ ፊት ፣ አዳኝብሃለሁ ።

፪ ፣ ከመ ፣ ትሰብክ ፣ ቃሎ ።
(እኤዝዘከ ፣ ከመ ፣ ትስብክ ፣ ቃሎ) ፣ ወንጌልን ፣ ታስተምር ፣ ዘንድ ፣ አዳኝብሃለሁ ።
ቀዊመክ ፣ በድቡት ። (ኢሳ ፣ ፶፰ ፣ ፩ ።
በሐዋርያነት ፣ ጸንተህ ፣ (በድቡት) ፣ በዝግታ ፣ በጸጥታ ፣ ኾነህ ፣ ታስተምር ፣ ዘንድ ፣ አዳኝብሃለሁ ።
በጊዜሁ ። ዓላውያን ፣ መከራ ፣ በማያጸንብህ ፣ ጊዜ ።
ወዘእንበለ ፣ ጊዜሁ ።
ዓላውያን ፣ መከራ ፣ በሚያጸንብህ ፣ ጊዜ ። አንድም ፣ (በጊዜሁ) ፣ የምእመናን ፣ ጆሯቸው ፣ ተከፍቶ ፣
ልቡናቸው ፣ ነቅቶ ፣ ትምህርቱን ፣ በሚቀበሉበት ፣ ጊዜ ፣ (ወዘእንበለ ፣ ጊዜሁ) ፣ አእምሯቸው ፣ ፈዞ ፣ ጆሯቸው ፣
ደንዝዞ ፣ ትምርቱን ፣ በማይቀበሉበት ፣ ጊዜ ፤ ፀሐይ ፣ የሚሞቀኝ ፣ የለም ፣ ብሎ ፣ መውጣቱን ፣ ወኃ ፣ የሚ
ጠጣኝ ፣ የለም ፣ ብሎ ፣ መፍሰሱን ፣ ይተዋልን ።
ገሥጽ ፤ ገሥጽ ።
ወተዛለፍ ፣ (ቲቶ ፩፡፱፡፲ ። ዝለፍ ።
ናዝዝ ፤ ገሥጽ ፣ ብሎ ፣ ነበርና ፣ ናዝዝ ።
ወየውህ ፣ እንዘ ፣ ትትዔገሥ ፣ በኵሉ ፣ ወትሚህር ። (ም ፣ ፱፡፭፬ ፫፡፲፡፲፮ ።)
ተዛለፍ ፣ ብሎ ፣ ነበርና ፣ የውህ ፣ አለ ፣ ዅሉን ፣ ታግሠህ ፣ ስታስተምር ፣ ናዝዝ ፣ የውህ ።

፫ ፣ እስመ ፣ ይበጽሕ ፣ ጊዜሁ ፣ አመ ፣ የዓበይዎ ፣ ለትምህርተ ፣ ሕይወት ፣ (፩ ጢሞ ፣ ፩፡፲፫ ፣ ፱፡፩ ።)
ሕይወት ፣ የሚገኝባት ፣ ትምህርት ፣ ወንጌልን ፣ አንቀበልም ፣ የሚሉበት ፣ ጊዜ ፣ ይመጣልና ።
ወየሐውሩ ፣ በፍትወቶሙ ።
ልቡናቸው ፣ በሚወደው ፣ ሥራ ፣ ጸንተው ፣ የሚኖሩበት ፣ ጊዜ ፣ ይመጣልና ።
ወያመጽኡ ፣ መምህራነ ፣ ለርእሶሙ ፣ በሐኮተ ፣ አዘኢሆሙ ።
በጆሯቸው ፣ ቀበዞነት ፣ ለራሳቸው ፣ መምህራንን ፣ የሚያመጡበት ፤ የሀገራችን ፣ ሰዎች ፣ ከአፍርንጅ ፣
ተጨዋውተው ፣ አፎንሱን ፣ አምጥተው ፣ እንደነበረ ።
አንድም ፣ ለራሳችን ፣ መምህራን ፣ ነን ፣ የሚሉበት ፣ ጊዜ ፣ ይመጣልና ።
ወይመይጡ ፣ እዘኢሆሙ ፣ አምጽድቅ ።
ዕዝነ ፣ ልቡናቸውን ፣ ከጽድቅ ፣ ከወንጌል ፣ የሚመልሱበት ።
፬ ፣ ወያመጽኡ ፣ ካልአ ፣ ትምህርተ ።
እኛ ፣ ካስተማርነው ፣ ትምህርት ፣ ሌላ ፣ የሚያስተምሩ ።
ወይትመየጡ ፣ ኀበ ፣ መኃድምት ። (፩ ጢሞ ፣ ፩ ፣ ፮ ። ፪ ተሰ ፣ ፪፡ ፲፩ ።
ወደተረት ፣ ወደአረት ፣ የሚመለሱበት ፣ ጊዜ ፣ ይመጣልና ።

www.zeyeneta.com

ኟ ፡ አንተስ ፡ ንቃህ ፡ አንተ ግን ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ንቃ ።
ወጥበብ ፡ በሁሉ ።
በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ተራቀቅ ።
ወጸሙ ። ጸር ፡ ድከም ።
ወግበር ፡ ምግባረ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወኩን ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፩ ፡ ፳ ።)
የወንጌልን ፡ ሥራ ፡ ሥራ ፡ (ወኩን) ፡ ብቃ ። አንድም ፡ (ወግበር ፡ ምግባረ) ፡ ሥራ ፡ ሥራ ፡ (ወንጌላዊ ፡ ኩን) ፡ ወንጌላዊም ፡ ኹን ።
ወፈጽም ፡ መልእክተክ ።
ተልእኮህንም ፡ ፈጽም ።

፮ ፡ ወአንሰ ፡ ወዓአኩ ፡ ወሠለጥኩ ።
እኔ ፡ ተልእኮየን ፡ ፈጽሜአለሁ ።
ወበጽሐኒ ፡ ዕድሜየ ፡ ለአዕርፎ ። (ፈል ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።)
የማርፍበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ።

፯ ፡ ሠናየ ፡ ገድለ ፡ ተጋደልኩ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳፭ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።
በጎ ፡ ገድልን ፡ ተጋደልሁ ።
በድርየኒ ፡ ፈጽምኩ ። (ፈል ፡ ፫ ፡ ፲፬ ።
ቅድድሚንም ፡ ጨረስሁ ።
ወሃይማኖትየኒ ፡ ዐቀብኩ ።
ሃይማኖቴንም ፡ ጠበቅሁ ።

፰ ፡ አንከሰ ፡ ጽኑሕ ፡ ሊተ ፡ አከሊለ ፡ ጽድቅ ፡ ዘየዓሥየኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይእተ ፡ ዕለተ ፡ መኩንኑ ፡ ጽድቅ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ፡ ራእ ፡ ፪ ፡ ፲ ።
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኩናኒ ፡ በርትዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕለተ ፡ ሞት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የሚለጠኝ ፡ ዋጋዬ ፡ ይቆየኛል ።
ወአኮ ፡ ለባሕቲትየ ።
መስጠቱም ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ምጽአተ ፡ ዚአሁ ።
የሱን ፡ መምጣት ፡ ለሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፱ ፡ አስተፋጥን ፡ ትምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ ፍጡነ ። (ቍ ፡ ፳፭ ።
ፈጥነህ ፡ ወደኔ ፡ ና ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፡ ዲማስ ፡ ጎደገኒ ፡ ወአፍቀሮ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘይአዜ ፡ ወሐረ ፡ ተሰሎንቄ ። (ቈላስ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ፡ ም ፡ ፩ ፲፫ ።)
ዲማስ ፡ ሆዴ ፡ ይምላ ፡ ደረቴ ፡ ይቅላ ፡ ብሎ ፡ ትቶኝ ፡ ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ሔደ ።
ወቆሬቂስኒ ፡ ገላትያ ።
ቆሬቂስም ፡ ወደገላትያ ፡ ሔደ ።
ወቲቶ ፡ ዳልማጥያ ።
ቲቶም ፡ ዳልማጥያ ፡ ሔደ ።

፪ ፡ ወሉቃስ ፡ ባሕቲቱ ፡ ምስሌየ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፴፮ ፡ ቈላስ ፡ ፬ ፡ ፲ ።)
ሉቃስ ፡ ብቻ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አለ ።
ወአምጽእ ፡ ምስሌክ ፡ ለማርቆስ ።
ማርቆስን ፡ ይዘኸው ፡ ና ።
እስመ ፡ ይበቍዐኒ ፡ ለመልእክት ።
ቢጣሉ ፡ ለማስታረቅ ፡ ክታብ ፡ ወስዶ ፡ ለመስጠት ፡ ይቢቃኛልና ።
ወፈነውክም ፡ ለጢኪቆስ ፡ ኤፌሶን ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፬ ፡ ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፳፩ ፡ ቈላ ፡ ፬ ፡ ፯ ።)
ጢኪቆስ ፡ የለምን ፡ ትለኝ ፡ አንደኾነ ፡ ጢኪቆስንስ ፡ ኤፌሶን ፡ ለደርሁት ።

www.zeyeneta.com

፲፫ ፡ ወፈሎንኒ ፡ ዘመጽሐፍ ፡ ዘጎደጉ ፡ በጢሮአስ ፡ ጎበ ፡ አክርጳ ፡ ተግላፅ ፡ ምስሌከ ።
በጢሮአስ ፡ ከአክርጳ ፡ ዘንድ ፡ የተውኹትን ፡ የመጽሐፉን ፡ መጠቅለያ ፡ ጀባውን ፡ ይዘኽው ፡ ና ።
ወዓዲ ፡ መጻሕፍተ ። ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከታብ ።
ወረቀ ፡ ዕብራውያን ፡ የሚጸፍበትን ፡ ብራና ።
ወፈሎንኒ ፡ ዘመጽሐፍ ፡ ዘጎደጉ ፡ ስጢሮአስ ፡ ጎበ ፡ አክርጳ ፡ ተግላፅ ፡ ምስሌከ ።
እንድም ፡ ከአክርጳ ፡ ዘንድ ፡ በጢሮአስ ፡ የተውሁትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከነመጠቅለያው ፡ ይዘኽው ፡ ና ።
ወእዲ ፡ መጻሕፍተ ።

መጻሕፍተ ፡ ነቢያትን ፡ (ወረቀ) ፡ ዕብራውያን ፡ የሚጸፍበትን ፡ ብራና ።

፲፬ ፡ እስ ፡ እስክንድሮስ ፡ ነሀቢ ፡ ብዙኀ ፡ ግቀየኒ ። (፩ ጢሞ ፡ ፩ ፳ ።
እንጥረኛ ፡ አስእስክንድሮስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ አጸናብኝ ።
ይፍድዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኪመ ፡ ምግባሩ ። (፪ሳሙ ፡ ፫ ፩፱ ፡ መዝ ፡ ፷፪ ፡ ፩ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሥራው ፡ ፍዳውን ፡ ይክፈለው ፡ (ሐተታ ፡) እንደበጎ ፡ ሽማግሌ ፡ ተናገረ ፤ በጎ ፡ ሽማግሌ ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ የሚመርቀውን ፡ መርቆ ፤ የሚታረቀውን ፡ ታርቆ ፤ የሚረግመውን ፡ ረገሞ ፡ ይሞታል ፤ የሚመርቀውን ፡ እንዲመርቅ ፡ የሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሣህሰ ፡ ለቤተ ፡ ሄኔሴፍሩ ። የሚታረቀውን ፡ እንደመታረቅ ፡ ወአምጽአ ፡ ምስሌከ ፡ ሰግርቆስ ፤ የሚረግመውን ፡ እንዲራገም ፡ እስ ፡ እስክንድሮስ ፡ ነሀቢ ፡ ብዙኀ ፡ ግቀየኒ ፡ ይፍድዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኪመ ፡ ምግባሩ ፡ ብሏል ፤ ይሽውም ፡ አልቀረ ፡ ከራስጌው ፡ ተስቅሎ ፡ የነበረ ፡ መዶሻ ፡ ወርዶ ፡ አናቱን ፡ በጥብጦ ፡ ገሎታል ።
ወአንተኒ ፡ ወልድየ ፡ ተዐቀቦ ።
አንተም ፡ ልጄ ፡ እወቅበት ።
እስመ ፡ ፈድፋደ ፡ ተቃወሞ ፡ ለነገርነ ።
ፈጽሞ ፡ ትምህርታችንን ፡ ተቃውሞታልና ።

፲፭ ፡ ወበቀዳሚ ፡ ነገርየ ፡ አልቦ ፡ ዘጎብረ ፡ ምስሌየ ።
በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ የለም ።
ዳዕሙ ፡ ሁሎሙ ፡ ጎደጉኒ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፴፪ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።
ኹሉም ፡ ጥለውኝ ፡ ሔዱ ፡ እንጂ ።
ወይስረይ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ።
ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበላቸው ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቆመ ፡ ሊተ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፫ ፡ ፲፩ና ፡ ፳፯ ፡ ፳፫ ።)
እግዚአብሔር ፡ አግዞኛልና ።
ወአጽንዐኒ ።
በረድኤት ፡ አጽንቶኛልና ።
ከመ ፡ ይእመኑ ፡ በስብከተ ፡ ዚአየ ፡ ወይስምዑ ፡ ሁሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ከመ ፡ ድኅንኩ ፡ አምአፈ ፡ አንበሳ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ።)
ከአፈ ፡ አንበሳ ፡ እንደዳንሁ ፡ (አለ) ፡ በቁሙ ፡ ስለንበሳ ፡ ሰጥተውታልና ።
አንድም ፡ ከአለእስክንድሮስ ፡ እንደዳንሁ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ስምተው ፡ በኔ ፡ ስብከት ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ።

፲፰ ፡ ወያድኅነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኵሉ ፡ ግብር ፡ እኩይ ።
ከመከራው ፡ ኹሉ ፡ እንዲያድነኝ ፡ ስምተው ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ።
ወያሐይወኒ ፡ ውስተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዘበሰማያት ።
በልዕልና ፡ ባለች ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ እንዲያኖረኝ ።
ውእቱ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ። ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፳ገላት ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።
ክብር ፡ ጌትነት ፡ ያለው ።
ለዓለመ ፡ ዓለም ። ለዘለዓለሙ ።
አሜን ። በውነት ።

፲፱ ፡ አምኅ ፡ ጽርሰቅላ ፡ ወአቂላ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፪ ። ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፫ ።
ጵርሰቅላን ፡ አቂላን ፡ ቸር ፡ አላችሁ ፡ በል ።

www.zeyeneta.com

ወቤተ ፡ ሄኔሴፎሩ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።
የሄኔሴፎሩን ፡ ወገን ፡ ቸር ፡ አላችሁ ፡ በል ።

፳ ፡ ኤርስጦስ ፡ ነበረ ፡ ቆሮንቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ።
ኤርስጦስ ፡ የለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደኾነ ፡ ኤርስጦስስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ቀረ ፡ ነበረና ፡ ተርፈ ፡ ይመራሉሱ ፡ ትርፍ ፡ ውስተ ፡ ልማድክ ፡ እንዲል ።

ወለጥሮፊሞስ ፡ ኀደግዎ ፡ በሀገረ ፡ መሊጡ ፡ ይደዊ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፬ና ፡ ፳፩ ፡ ፳፱ ፡)
ጥሮፊሞስንም ፡ በመሊጡ ፡ ታሞ ፡ ተውሁት ።

፳፩ ፡ አስተፋጥን ፡ ትምጻእ ፡ ኀቢየ ፡ አምቅድመ ፡ ክረምት ።
ክረምት ፡ ሳይገባ ፡ ፈጥነህ ፡ ና ፡ ክረምት ፡ ላዩ ፡ ውኀ ፡ ታቹ ፡ ውኀ ፡ ነው ፡ አያስተላልፍምና ። አንድም ፡ ሳልሞት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ (ሐተታ ፡) ክረምት ፡ አለው ፡ ሞትን ፡ ክረምት ፡ ክቡድ ፡ ነው ፡ የመምህርም ፡ ሞት ፡ ክቡድ ፡ ነውና ፡ ክረምት ፡ አያስተያይም ፡ ሞትም ፡ አያስተያይምና ።

ይኤዎቡስ ፡ ኤውግሎስ ፡ ወጴዲስ ፡ ወሊናስ ፡ ወቀላውድያ ።
ኤውቡሎስ ፡ ጴዴስ ፡ ሊናስ ፡ ቀላውድያም ፡ ቸር ፡ አለህ ? ይሉሃል ። ወሰሎሙ ፡ አጋዊን ።
ወንድሞቻችን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አለህ ? ይሉሃል ።

፳፪ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የህሉ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አድሮብህ ፡ ይኑር ።
ወጸጋሁ ፡ ምስሌክሙ ፡ (ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡)
ጸጋው ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ።

አሜን ። በውነት ።

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ካልኣት ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በሮሜ ፡ ወተፈነወት ፡ በእደ ፡ አንክሮሎስ።

በሮም ፡ የተጻፈች ፡ በአንክሮሎስ ፡ እጅ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ሁለተኛ ፡ የተላከች ፡ ክታብ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።

ወስብሓት ፡ ለእግዚአብሔር ።

አነግሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.zeyeneta.com

ምክንያተ ፡ ጽሑፍቱ ፡ ለሐዋርያ ፡ ጎበ ፡ ቲቶ ።

እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰበከ ፡ ቀዳሚ ፡ በሀገረ ፡ ቀርጤስ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአብአሙ ፡ ጎበ፡ ሃይማኖት ።

ወእምድኅረ ፡ ንስቲት ፡ መዋዕል ፡ አንዘ፡ የሐ ውር ፡ ጎበ ፡ ካልእ ፡ ብሔር ፡ ጎደን ፡ ሀየ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ክመ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ኢያ ምጽኡ ፡ ካልአ፡ ትምህርተ ፡ ወዛውጓ ፡ ነገር ፡ ወመሐድምተ ፡ዕቤ ራት ፡ ዘይፈጥሩ ።

ወአዘከሮ ፡ ዙሉ ፡ እከያቲሆሙ ፡ ለሰብአ ፡ ቀርጤስ ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ።

ወአዘዞ ፡ ክመ ፡ ይዛለፎሙ ።

ወሓዲ ፡ አዘዞ ፡ ክመ ፡ ይሚጮ ፡ ጳጳሳተ ፡ወቀ ሲሳነ ፡ ለለአህጉር ።

ወእርአዮ ፡ ዘክመ ፡ ይደልዎሙ ።

ወኵሉ ፡ ነገሩ ፡ ወትእዛዙ ፡ ለዝንቱ ፡ መል እክት ፡ ይመስል ፡ ክመ ፡ መልእክተ ፡ ጢሞቴዎስ፡ ቀዳሚዊ ።

ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ አንዘ፡ ሀሎ ፡ ብሔረ ፡ ናቆድል ።

ወፈነዎ ፡ በእደ ፡ አርጣማ ፡ ረድኡ ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቲቶ ፡ ክታብ ፡ የጸፈበት ምክንያት ።

ጳውሎስ ፡ አስቀድሞ ፡ ቀርጤስ ፡ በምትባል፡ ሀገር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ አስተምሮ ፡ ወደሃይማኖት ፡ መልሷቸው ፡ ነበረ ።

ከዮቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደሌላ ፡ ሀገር ፡ሲሔድ የባልቴቶችን ፡ ተረት ፡ አሪትን ፡ ወይም ፡ ከልባቸው ፈጥረው ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ አንዳያመጡ ፡ ይገሥ ጻቸው ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ ቲቶን ፡ ከዚያ፡ ትቶት ፡ ሔዶ ፡ ነበረ ።

የቀርጤስ ፡ ሰዎች ፡ የሚሠሩትን ፡ ክፋታቸ ውን ፡ ኹሉ ፡ እያስታወሰ ፡ ጻፈለት ፡

በቁርጥ ፡ እንዲዘልፋቸው ፡ እዘዘው ።

ዳግመኛም ፡ ጳጳሳቱንና ፡ ቀሳውስቱን ፡ በየሀገሩ ፡ እንዲሾም ፡ አዘዘው ።

ጳጳሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገ ባቸውንም ፡ ገለጸለት ።

የዚህ ፡ ክታብ ፡ ነገሩም ፡ ትእዛዙም ፡ ኹሉ፡ የጢሞቴዎስን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ክታብ ፡ ይመስ ላል ።

ይህን ፡ ክታብ ፡ ናቆድል ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ ሳለ ፡ ጸፈለት ።

በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ በአርጣማ ፡ አድ ፡ ላከለት።

www.zeyeneta.com

ቲቶ ፡ የቀርጤስ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እናቱም ፡ አባቱም ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፡ በጎ ፡ ብላቴናነቱን ፡ እይቶ ፤ ክፍጹምነት ፡ እንዲያርስ ፡ ዐውቆ ፡ አስከትሎታል ፡ ሲያስከትለውም ፡ ሳይገዝር ፡ አስከትሎታል ፡ ወቲቶስ ፡ ዘምስሌየ ፡ እንዘ ፡ አረማዊ ፡ ውእቱ ፡ ኢያገበርከዎ ፡ ይትገዘር ፡ እንዲል ። ኀላም ፡ ከፍጹምነት ፡ እንደደረሰ ፡ ዐውቆ ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሞታል ፡ ኀላም ፡ አንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሹም ፡ አንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አትሹም ፡ እያለ ፡ ሲያጸና ፡ ጽፎ ፡ ይሰድለታል ፡ ምክንያቱ ፡ አንደ ፡ ቅዳሜዊ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ነው ። ለመስተካህድ ፡ ብእሲ ፡ እምከመ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፤ ገሠጾት ፡ ወእበየ ፡ ጎድጎ ፡ ወእምሮ ፡ ከመ ፡ ዓላዊ ፡ ውእቱ ፡ ዘከማሁ ፡ ያስሕት ፡ ወያጌጊ ። ወአምከመ ፡ ፈነውከዎ ፡ ለአርጢሞን ፡ ኀቤከ ፡ አው ፡ ጢኪቆስ ፡ ፍጡን ፡ ነዓ ፡ ኀቤየ ፡ ሀገረ ፡ ናቆጵል ፡ እስመ ፡ አጥባዕኩ ፡ አከርም ፡ ሀየ ፡ ሰዘማስ ፡ ጸሐፌ ፡ ሀገር ፡ ወስአጵሎስ ፡ ጽሑቀ ፡ አከብሮሙ ፡ ከመ ፡ ኢይጸንሱ ፡ ምንተኒ ፡ ወአሊአነሂ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ፡ በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ፡ እምኀ ፡ ዙሎ ፡ ዘያፈቅረነ ፡ በሃይማኖት ፡ ይላል ፡ የጸፈበት ፡ ሀገር ፡ ናቆጵል ፡ ከታብ ፡ ወሳጅ ፡ አርማግ ፡ ረድኡ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ገብሩ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዩ ፡ ከምኾን ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ። ወሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። በሃይማኖቶሙ ፡ ሰኀሩያኒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ፡ ሰውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ።
ወበእአምሮ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ባንድነት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ምስትነትን ፡ በምስትነት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ እንድነትን ፡ በማመን ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ። አንድም ፡ (በሃይማኖቶሙ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡) በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ።
ወበእአምሮ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በትንቢተ ፡ ነቢያት ፡ ጸንቶ ፡ ያለ ፡ ሥጋዌውንም ፡ በማመን ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ፡ ፡

፪ ፡ ወበተስፋ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘአሰፈወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢይሔሱ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ።
(ዘአሰፈወ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡) ተናግሮ ፡ የማያስቀር ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ባናገረው ፡ የዘለዓለም ፡ በሚኾን ፡ በሕይወት ፡ አለኝታ ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ። አንድም ፡ ስውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ከሾመኝ ።
ወእርአየ ፡ ቃሎ ፡ በዕድሜሁ ፡ በስብከተ ፡ ዚአነ ፡ ኪያሁ ፡ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።
አኛ ፡ እሱን ፡ በማስተማራችን ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ የገለጠ ። አንድም ፡ ወንጌልን ፡ የገለጠ ።
ወተአመንኒ ፡ ሊተ ፡ ላዕሌሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፩-፲፩ ።

ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ለሐዋርያነት ፡ ትበቃለህ ፡ ያለኝ ፡ አግዚአብሔር ፡ ባናገረው ፡ ተስፋ ፡ ጸንቼ ፡ ብኀኝ ። አንድም ፡ ስውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ።

ለቲቶ ፡ ወልድየ ፡ ዘእፈቅር ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበሃይማኖት ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፪ ።)
በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ ጸንቶ ፡ ምግባር ፡ ሲሠራ ፡ ባገኘው ፡ ለምወደው ፡ ለልጄ ፡ ለቲቶ ፡ ትድረስለት ።
ሰላም ፡ ለከ ። ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ቸር ፡ አስሀን ።
ወጸጋ ። ሐዋርያነት ፡ ይጽናልህ ።
ወሣህል ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ።
ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታ ፡ ይደረግልህ ።

፭ ፡ እስመ ፡ እንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ኀደጉከ ፡ ውስተ ፡ ቀርጤስ ፡ ከመ ፡ ታስተራትዕ ፡ ዘተርፈ ።
ከኔ ፡ የቀረውን ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሜሃለሁ ፡ አኮን ።
እንድም ፡ በቀርጤስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሜሃለሁና ፡ እንዲህ ፡ የሾምህ ፤ ከኔ ፡ የቀረውን ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.zeyeneta.com

እንድም ፡ አእምር ፡ ይላል ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ እንደኾነ ፡ ዕወቅ ፡፡
ወትሚም ፡ ቀሲላን ፡ ለለአህጉር ፡፡
በየሀገሩ ፡ ቀሳውስትን ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ እንደኾነ ፡ ዕወቅ ፡ (ሐተታ ፡) ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ሳንድ ፡ እውራጃ ፡ እንድ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሳንድ ፡ እውራጃ ፡ እንድ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ይሾማል ፡ እንደ ፡ ጎጃም ፡ እንደትግሬ ፡ እንደ ፡ ጐንደር ፡ ባለው ፡፡ ቂስ ፡ ግን ፡ በየሀገሩ ፡ ካልኾነ ፡ አይኾንምና ፡ ለለአህጉር ፡ አለ ፡፡
በከመ ፡ አዘዝኩከ ፡፡
በቀዳሚ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እንደአዘዝሁህ ፡ (ሐተታ ፡) ያንዱንስ ፡ ሳንዱ ፡ አያመጣም ፡ ብሎ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ እንዳዘዝሁህ ፡፡
ኗ ፡ ብእሴ ፡ ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ፡፡
ያልደጋገመ ፡ ይሾም ፡፡
ጎራይ ፡፡ ደግ ፡፡
ዘኢየሐምይዎ ፡ በእኩይ ፡፡
በከፉ ፡ ነገር ፡ የማያነሡት ፡፡
ዘቦ ፡ ውሉድ ፡ መሃይምናን ፡፡
የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ ይሾም ፡፡
ዘኢያስተዋድይዎሙ ፡ በምርዓት ፡፡
በድርዓት ፡ የማይከሷቸው ፡ የማያጣሏቸው ፡፡
አለ ፡ ኢኮኑ ፡ ዝሉፋን ፡፡
ኃጢአት ፡ አዘውታሮች ፡ ሴሰኞች ፡ ደፋሮች ፡ ተሳዳቦች ፡ ያልኾኑ ፡፡
እለ ፡ ይትኤዘዙ ፡ (ፈ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡፡ ፭ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ፡ ፫ ፡፡
የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡፡
ኗ ፡ ወርቱዕ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐሜት ፡፡
ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ቅስና ፡ ሊሾም ፡ ይገባል ፡፡
ዘኢያደሉ ፡፡
በፍርድ ፤ በብያኔ ፡ በትምህርት ፤ በጸሎት ፤ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ፡፡
ከመ ፡ መጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ፈ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፈ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭፬ ፡፡)
መጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደመኾኑ ፡ እንደመጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደፀሐይ ፡ እንደሙሴ ፤ እንደ ፡ ጌታ ፤ እንደቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፤ እንደእስጢፋኖስ ፤ እንደራሱ ፡፡
ዘኢኮነ ፡ መዓትመ ፡፡
ቁጡ ፡ ያይደለ ፡፡
ዘልቡብ ፡፡
ገራም ፡፡ እንድም ፡ (ዘልቡብ) ፡ ዐዋቂ ፡፡
ዘኢያበዝኀ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ፡፡
አብዝቶ ፡ የማይጠጣ ፡ አይጠጣ ፡ አላለም ፡፡
ወኢያፈጥን ፡ እደሁ ፡ ለዘቢጥ ፡፡
ፈጥኖ ፡ የማይማታ ፡ ፈጥኖ ፡ የማይገዝት ፡፡
ወዘኢያፈቅር ፡ ንዋየ ፡ ክንቶ ፡፡
ኃላፊውን ፡ ከብት ፡ የማይወድ ፡፡
ፀ ፡ መፍቀሬ ፡ ነግድ ፡፡
እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡፡
ዘሠናይ ፡ ምግባሩ ፡፡
ግብሩ ፡ ያማረ ፡ የበጀ ፡፡
ዘአንጽሐ ፡ ርእሶ ፡፡
ስውነቱን ፡ ከኃጢአት ፡ የለየ ፡፡
ጻድቅ ፡፡ እውነተኛ ፡፡
ወጌር ፡፡ ቸር ፡፡

www.zeyeneta.com

ወየዋህ ፡ ቅን ፡፡
ወመሥተጓግሥ ፡፡
ትዕግሥት ፡ ያለው ፡፡
፱ ፡ ዘያንሐሲ ፡፡
ነገር ፡ አላፊ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡፡
ዘምሁር ፡ ቃለ ፡ ሃይማኖት ፡፡
የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ የተማረ ፡፡
ዘይከል ፡ ገሥጾ ፡ በትምህርተ ፡ ሕይወት ፡፡ (፱ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፩) ፡፡
ሕይወት ፡ በሚገኝበት ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ መምከር ፡ ማስተማር ፡ የሚቻለው ፡፡
ወይዘልፎሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዋሥኡ ፡፡
የሚከራከሩትንም ፡ የሚረታ ፡ ይኹን ፡፡ ተከራከሮ ፡ የማይረታ ፡ አለና ፡፡
፲ ፡ አስመ ፡ ብዙኃን ፡ አለ ፡ ኢይትኤዘዙ ፡፡
ለወንጌል ፡ የማይታዘዙ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡፡
ወነገሮሙኒ ፡ ከንቱ ፡፡
ነገራቸው ፡ ከንቱ ፡ አሪት ፡ የሚኾን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡፡
ወያስሕትዎሙ ፡ ለጽሉላን ፡ ልብ ፡፡
ልበ ፡ ደነቋርት ፡ የኾኑትን ፡ ያስታቸዋልና ፡፡
፲፩ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለአለ ፡ እምአይሁድ ፡ እለ ፡ ርቱዕ ፡ ይፍጽምዎሙ ፡ አፋሆሙ ፡፡ (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ፡፡)
ይልቁንም ፡ ምላሽ ፡ ሊያሰጣቸው ፡ ከሚገባ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የሚኾኑትን ፡የሚረታ ፡ሊኾን ፡ይገባል ፡፡
እስመ ፡ እሉ ፡ ይገፈትዑ ፡ አብያተ ፡ ኵሉ ፡፡ (፱ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡)
እሊህ ፡ የሰውን ፡ ኹሉ ፡ ልቡና ፡ ይለዋውጣሉና ፡፡
ወይሜህሩ ፡ በዘኢይደሉ ፡፡
በማይገባ ፡ ያስተምራሉና ፡፡
በዘይረብሑሙ ፡ ጎሳር ፡፡
ጥቅማቸው ፡ ኃሳር ፡ በሚኾንባቸው ፡ ግንዘብ ፡፡
፲፪ ፡ ወናሁ ፡ ይቤ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ነቢዮሙ ፡ በአንቲአሆሙ ፡፡
የነሱንም ፡ ነገር ፡ ከሳቸው ፡ አንዱ ፡ መምህራቸው ፡ ተናግሯል ፡፡
አስመ ፡ ሰብአ ፡ ቀርጤስ ፡ መደልዋን ፡ ሐሳውያን ፡ ዘልፈ ፡፡
የቀርጤስ ፡ ሰዎችማ ፡ እንጂ ፡ ግብዞች ፡ ዘወትር ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ፡ አኩ ፡ ብሎ ፡፡
አራዊት ፡ እኩያን ፡ ከርሠ ፡ መካን ፡፡
አራዊት ፡ አኩያን ፡ ናቸው ፡ እኩ ፡ (ከርሠ ፡ መካን) ፡ ዕዕድ ፡ ስቁርት ፡ ይላታል ፡ ሰሎሞን ፡ ያች ፡ ውኃ ፡
እንዳትቋጥር ፡ ዘር ፡ የማትቋጥር ፡ ሲል ፡ እሊህንም ፡ ምሥጢር ፡ የማያቋጥሩ ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ አለ ፡ (ሐተታ
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ተናግሮት ፡ ሳይጸፍ ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ ተናግሮ ፡ ሳይጸፍ ፡ የቀረውንም ፡
ማምጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡፡ አንድም ፡ ወተከውን ፡ ቀርጤስ ፡ ዒላት ፡ መራዕይ ፡ ያለውን ፡ ሶርንያስ ፡ እን
ዲህ ፡ ስውጦ ፡ አነበበው ፡፡ እንድም ፡ ዜውስ ፡ በግብሩ ፤ ጴዮናሰዩስ ፡ በነገሩ ፡ ተናግሮታል ፤ ስዲ ፡ ጳው
ሎስ ፡ ግን ፡ ወደናንት ፡ ያልመጣ ፡ ኢዩጴዶስ ፡ የሚባል ፡ ነቢይ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሏል ፡፡
፲፫ ፡ ወዝንቱ ፡ ስምዕ ፡ እሙን ፡ ላዕሌሆሙ ፡፡ (፱ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ፯ ፡፡)
ይህ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የታመነ ፡ ምስክር ፡ ነው ፡፡
በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኮንስፎሙ ፡ ምቱረ ፡፡
ስለዚህ ፡ ቁርጥ ፡ አድርገህ ፡ ተከራከራቸው ፡፡
ከመ ፡ ይጠይቁ ፡ በሃይማኖት ፡፡
ሃይማኖትን ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡፡
፲፬ ፡ ወኢያምጽኡ ፡ መኃድምተ ፡፡
ተረት ፡ አሪትን ፡ እንዳያመጡ ፡፡

www.zoyeneta.com

ወሥርዓተ ፡ ስብእ ።
ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ትምህርት ፡ ኦሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ።
ዘይመይጣ ፡ ለጽድቅ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፮ ።)
ወንጌልን ፡ የሚለውጣት ፡ ብሎ ፡ ለኦሪት ፡ ቀጠለ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ ዙሉ ፡ ዘኮነ ፡ ንጹሕ ፡ ለንጹሓን ፡ (ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ፡ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፍ ።
የተፈጠረ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ለንጹሓን ፡ ንጹሕ ፡ እንጂ ፡ ነው ።
ወለርኩሳንስ ፡ እለ ፡ ኢያእምኑ ፡ አልቦሙ ፡ ንጽሕ ፡ ምንትኒ ።
ድል ፡ ለተነሡ ፡ ሳለመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ንጽሕ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ የላቸውም ።
እስመ ፡ ርኩስ ፡ ሕሊናሆሙ ።
ልቡናቸው ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ነውና ።

፲፯ ፡ ወበልቦሙ ፡ የእምኑ ፡ ከሙ ፡ ዘያእምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በልቡናቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያውቁት ፡ አድርገው ፡ አናምናለን ፡ ይላሉ ።
ወይከህድዎ ፡ በምግባሮሙ ።
በሥራቸው ፡ ግን ፡ ይክዱታል ።
ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ ወከሃድያን ።
ድል ፡ የተነሡ ፡ ከሃድያን ፡ ናቸው ።
ወምኑናን ፡ በውስተ ፡ ዙሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (፪ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፯ ።)
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተርቃዎች ፡ ናቸው ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፮ ።

፩ ፡ ወእንተሰ ፡ ንግር ፡ ዘይደሉ ፡ ለትምህርተ ፡ ሕይወት ፡ (፩ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፫ ፡ ፪ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።
አንተ ፡ ግን ፡ ተርታ ፡ እንዳትባል ፡ ልታስተምረው ፡ የሚገባህ ፡ ሕይወት ፡ የሚገኝበትን ፡ ትምህርት ፡
ሥራውን ፡ እየሠራህ ፡ አስተምር ።

፪ ፡ ሊቃውንትኒ ፡ ይኩኑ ፡ ንጹሓነ ፡ እምዝሙት ።
ሽማግሌችም ፡ ከዝሙት ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አስተምር ፡ (ሐተታ ፡) ከዚህ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡ ሲራከም ፡ ፫ተ ፡ ግብራተ ፡ አስቆረረት ፡ ነፍስየ ፡ እንዘ ፡ አረጋዊ ፡ ዘማዊ ፡ ወእንዘ ፡ ባዕል ፡ ደንጻዊ ፡
ወእንዘ ፡ ነዳይ ፡ ዕቡይ ፡ ብሂል ።

ወንቋሓነ ፡ ከንዋመ ፡ ሐኪት ፡ የነቁ ፡ ይኹኑ ።
ወጠቢባነ ። ዐዋቆች ፡ ይኹኑ ።
ወኢይናፍቁ ፡ በሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ አይጠራጠሩ ።
ይትፋቀሩ ፡ ፍቅርን ፡ ይያዙ ።
ወይለብዉ ፡ ያስተውሉ ።
ወይትግህሡ ፡ ይታገሡ ።

፫ ፡ ልሒቃትኒ ፡ ከማሁ ፡ ይትቀደሳ ።
ባልቴቶችም ፡ ሴቶች ፡ ሊቃውንትኒ ፡ ይኩኑ ፡ ንጹሓነ ፡ እንዳልሁ ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ።
ወያሠንያ ፡ ግእዘን ።
ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ።
ኢያስተሐውራ ፡ ነገረ ።
ነገር ፡ እያዋሰዱ ።
ወኢይትቀነያ ፡ ለስቴ ፡
ለመጠጥ ፡ አይገዙ ።

www.zeyeneta.com

ወኢይሰጠያ ፡ ውሰተ ፡ ስካር ።
ስክረው ፡ ወድቀው ፡ ተዘርረው ፡ አይደሩ ፡ (ሐተታ ፡) ስካር ፡ ሲዘፍኑ ፡ ሲያጨበጭቡ ፡ ማደር ፡ ነው ፡
ሰጥየት ፡ ነዊምሰ ፡ ዘይመስል ፡ መዊተ ፡ እንዲል ፡ (ተግ ፡ ዮሐ ፡ አፈ ፡) ከነዚያው ፡ አጥቶት ፡ ወድቆ ፡
ተዘርሮ ፡ ማደር ፡ ነው ። ዳዕሙ ፡ ይገሥጻ ፡ ወይምሐራ ፡ ሠናየ ፡ ትምህርተ ፡ ለአንስት ።

በጎውን ፡ ትምህርት ፡ ለሕፃናቱ ፡ ለሴቶች ፡ ያስተምሩ ፡ ይምከሩ ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ያንጽሑ ፡ ርእሶን ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።)
ስውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ።

፬ ፡ ወንኡሳትኒ ፡ ያፍቅራ ፡ አምታቲሆን ፡ ወውሉዶን ።
ሕፃናቱም ፡ ሴቶች ፡ ባሎቻቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይውደዱ ።
አይዘምዋ ።
መውደዱም ፡ ይፀ ፡ ነው ፡ ክሴላ ፡ አይሕዱባቸው ።
ወይግበራ ፡ ሠናየ ።
በጎውን ፡ ሥራ ፡ ይሥሩ ።
ወያውንያ ፡ ግእዞን ፡
ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡
ወሥርዓተ ፡ ቤቶን ።
የቤታቸውን ፡ ሥራ ፡ ያከናውኑ ፡ (አለ) ፡ ቤተ ፡ ለቦቻቸውን ፡ ሠርተው ፡ ቀጥተው ፡ ያሳድሩ ።
ወይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ፡ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፪ ።)
ለባሎቻቸው ፡ ይገዙ ።
ከመ ፡ ኢይፅርፍ ፡ አሐዱኒ ፡ ላዕለ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ወንጌልን ፡ አንዳይነቅፍ ፡ በወንጌል ፡ ማመን ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ሳትገዛ ፡ ነው ፡ ብሎ ።

፭ ፡ ወለወራዙትኒ ፡ ገሥጾሙ ፡ ያንጽሑ ፡ ርእሶሙ ።
ሕፃናቱም ፡ ወንዶች ፡ ስውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወይኩኑ ፡ ጠቢባን ።
ዐዋቆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ወኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለኵሎሙ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ።
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አብነት ፡ ኾናቸው ።
ወይኩን ፡ ነገርከ ፡ ወትምህርትከ ፡ በንጽሕ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፫ ።
የምትናገረው ፡ ነገር ፡ የምታስተምረው ፡ ትምህርት ፡ በንጽሕና ፡ ይኹን ።

፯ ፡ ወበሥሩዕ ፡ ነገር ።
በተከናወነ ፡ ነገር ፡ ይኹን ።
ዘአልቦ ፡ ነውር ።

ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ ይኹን ።
ዘአይሜንኖ ፡ አሐዱኒ ።
አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ቸል ፡ የማይለው ፡ ይኹን ።
ከመ ፡ ይትኀፈር ፡ ጸላኒ ።
ጸላዒ ፡ ዲያብሎስ ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ።
ወይኅጣዕ ፡ ዘይነብብ ፡ ላዕሌነ ፡ ሕሡመ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።
በኛ ፡ ላይ ፡ የሚናገረው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አንዳያገኝ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፱ ፡ ነባሪኒ ፡ ይትአዘዙ ፡ ለአጋእዝቲሆሙ ።
ቤተ ፡ ሰብአችም ፡ ለጌቶቻቸው ፡ ይገዙ ።

www.zayeneta.com

ወያሥምርዎሙ ፡ በሰሉ ። (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፭ ፡ ፭ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፭ ፭ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።
በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ያሰኝዋቸው ። ወኢይቅስጡ
ከብት ፡ እያንሣሡ ።
ወኢይትዋሥኡ ፡ በሰሉ ።
ወሰደው ፡ አልወሰድንም ፡ አይበሉ ።
፲ ፡ አላ ፡ ያሠንዩ ፡ በንጹሕ ፡ ሃይማኖቶሙ ።
በንጽሕና ፡ ኾነው ፡ በመታመን ። በመታመን ፡ ኾነው ፡ በንጽሕና ፡ ግብራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ይንዓድዋ ፡ በሰለሄ ፡ ለትምህርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲ ።
መድኃኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስተማራት ፡ ወንጌልን ፡ ሕዝቡም ፡ አሕዛቡም ፡ ያከብሯት ፡ ዘንድ
፲፩ ፡ እስመ ፡ ተዐውቀት ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቡኀበ ፡ ኩሉ ፡ ሰብእ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፭ ። ፩ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፱ ።
ጸጋው ፡ ወንጌል ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ታውቃለች ፡ ተረድታለችና ።
፲፪ ፡ ወትሜህረነ ፡ ከመ ፡ ንትናከራ ፡ ለኃጢአት ።
ኃጢአትን ፡ እንለያት ፡ ዘንድ ፡ ታስተምረናልችና ።
ወለፍትወት ፡ ዓለም ።
ፈቲውንም ፡ እንለያት ፡ ዘንድ ።
ወንሕየው ፡ በጽድቅ ፡ ወበንጽሕ ፡ ወበተሩቅሮ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፬ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ በጽድቅ ፡ ጸንተን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ትሜህረን ።
፲፫ ፡ እንዘ ፡ ንሴር ፡ አብዕያ ። (፩ ቆሮ ፡ ፭፮ ፡ ፊል ፡ ፫ ፡ ፳ ።)
ብፅዓን ፡ መስጠቱን ፡ ተስፋ ፡ እድርገን ።
ወምጽኡተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለእምላክነ ፡ ዓቢይ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢያሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በጌትነት ፡ መምጣቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ። እንድም ፡ አብዕያ ፡ ምጽኡተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ይላል ፡) በጌትነት ፡
መጥቶ ፡ ብፅዓን ፡ መስጠቱን ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ፡ ንሕየው ፡ በጽድቅ ።
፲፬ ፡ ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአነ ፡ (ገላ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፮ ።)
ራሱን ፡ ስለኛ ፡ አሳልፎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ የሰጠ ።
ከመ ፤ ይቤዝወነ ፡ እምኃጢአት ።
ከኃጢአት ፡ ይለየን ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ከፍዳ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ዘመጣው ።
ወያንጽሐ ፡ ሎቱ ፡ ሕዝበ ፡ ሐዲሰ ።
ወገኖቹን ፡ ለሱ ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ የበቁ ፡ ሐዲስ ፡ ልጆች ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ።
ወይትቀነዉ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ። (ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡)
በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ የሚፈካከሩ ።
፲፭ ፡ ከመዝ ፡ ንግር ፡ ወገሥጽ ።
እንዲህ ፡ ምክር ፡ አስተምር ።
ወተዛለፍ ። ዝለፍ ።
እንዘ ፡ ታቴሕት ፡ ርእስክ ፡ ለኵሉ ።
ትሕትናን ፡ ይዘህ ።
ወእልቦ ፡ ዘያስሕተክ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ፡)
የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ስሑት ፡ ነው ፡ የሚልህ ፡ ሰው ፡ አያኑር ፡ አንድም ፡ ስሑት ፡ የምትባልባትን ፡
ሥራ ፡ አትሥራ ።
፩ ፡ ተዘከሮሙ ፡ ለቀደምት ፡ ወለመኳንንት ።
ቀሳውስት ፡ ዲያቆናትን ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ በሰሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።
በበጎ ፡ ምግባር ፡ ኹሉ ፡ ጸንተው ፡ ይታዘዙ ፡ ዘንድ ፡ ዘከሮሙ ።
ወይኩኑ ፡ ጥቡዓን ፡ ቦቱ ።
በዚያው ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ዘከሮሙ ።

www.zeyeneta.com

፮ ፡ ወኢይትቆጥኡ ።
እንዳይበሳጩ ።
ወኢይትግእዙ ።
እንዳይጣሉ ፡ እንዳይከራከሩ ።
አላ ፡ መሐርያን ፡ ወየዋሃን ፡ ይኩኑ ፡ ምስለ ፡ ዅሉ ፡ ሰብእ ። (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ፡)
ከሰው ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ መሀርያን ፡ ይኹኑ ፡ እንጂ ፡ አይትቆጥኡ ፤ የዋሃን ፡ ይኹኑ ፡ እንጂ ፡ አይትግእዙ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ንሕነሂ ፡ ትካት ፡ አብድነ ፡ ዘእንበለ ፡ እአምሮ ።
እኛም ፡ እኮ ፡ ከዚህ ፡ እስቀድሞ ፡ ባለማወቅ ፡ ስንፈን ፡ ነበር
ወከህድነ ። ከደን ፡ ነበር ።
ወስሕትነ ። ከሕግ ፡ ወጥተን ፡ ነበር ።
ወተቀንይነ ፡ ለፍትወት ።
ለፈቲው ፡ ተገዝተን ፡ ነበር ።
ወለሐውዝ ፡ ዘዘዚአሁ ።
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሚኾን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ተገዝተን ፡ ነበር ።
ወተለዉነ ፡ እኩየ ።
በከፉ ፡ ግብር ፡ ጸንተን ፡ ነበር ።
ወተቃንያ ።
መቃናትን ፡ ይዘን ፡ ነበር ።
ወእሕሰምነ ፡ ወጸላዕነ ፡ ቢጸነ ፡ (ፅ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ። ኤፌ ፡ ፪፡ ፱፡ ፬፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።)
ወንድሞቻችንን ፡ እናሳዝን ፡ እንጠላ ፡ ነበር ።

፬ ፡ ወአመ ፡ አስተርአየ ፡ ምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ መድኃኒነ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።)
ቸር ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ የሚኾን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማን ፡ ቸርነቱ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ።

፭ ፡ አኮ ፡ በምግባረ ፡ ጽድቅነ (ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፰ ፱ ።
በሥራችን ፡ በጉልበታችን ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ በምሕረቱ ።
በቸርነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቸርነቱ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ።
አድኅነነ ፡ በጥምቀተ ፡ ዳግም ፡ ልደት ፡ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ።)
ዳግም ፡ ልደት ፡ በሚባል ፡ ጥምቀት ፡ ዳግም ፡ ልደትን ፡ በሚያስከትል ፡ ጥምቀት ፡ ከዚህ ፡ ዅሉ ፡ አዳነን ።
ወተሐድሶ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመታደስ ፡ አዳነን ። እንድም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ተሐድሶን ፡ በሚያስከትል ፡ ጥምቀት ፡ አዳነን ።

፮ ፡ ዘሞጸ ፡ ላዕሌነ ፡ በብዕሉ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ። (ኢዮ ፡ ፫፡፭ ፡ ሕዝ ፡ ፴፯ ፡ ፴፭ ።)
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለካሰልን ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ሁበቱን ፡ አብዝቶ ፡ ባሳደረው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፯ ፡ ከመ ፡ ንጽደቅ ፡ በጸጋሁ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፭ ።)
በቸርነቱ ፡ እንከብር ፡ ዘንድ ።
ወንረስ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ። (ሮሜ ፡ ፰ ፲፭ ።)
የማታልፍ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንወርስ ፡ ዘንድ ።

፰ ፡ እሙን ፡ ነገር ።
ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።
ወበእንተዝ ፡ እፈቅድ ፡ ታጽንዖሙ ።
ስለዚህ ፡ ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ። እንድም ፡ (አጽንዕከ) ፡ በሐዋርያነት ፡ ላጸናህ ፡ እወዳለሁ ።

ከመ ፡ የሐልዩ ፡ ተራድኦ ፡ በሥሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ እለ ፡ ተአመኑ ፡ በእግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር ፡ ያመኑት ፡ ምእመናን ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ መራዳትን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ እፈቅድ ፡ ታጽንዖሙ ።

www.zeyeneta.com

ዝኬ ፡ ሠናይ ፡ ዘይበቍዖ ፡ ለስብእ ። (ቍ. ፲፬ ።)
ለሰው ፡ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ነዋ ።

፲፬ ፡ ነገረ ፡ ጋዕዝ ።
የጸብዕ ፡ የከርከርን ፡ ነገር ።
መዕበድ ። የስንፍናን ፡ ነገር ።
ዘይፈጥሩ ። ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ የሚናነሩትን ።
መመጎድምት ።
የተረትን ፡ ነገር ።
መመከሕ ።
የዋዛ ፡ የፈዛዛን ፡ ነገር ፡ የሚናነሩትን ።
ተግሐሥሙ ።
(ተግሐሥሙ) ፡ ተለያቸው ።
አስሙ ፡ ከንቱ ፡ ውኑቱ ።
ከንቱ ፡ ነውና ።
ወኢይበቍዕ ። ፭ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯ ።
አይረባም ፡ አይጠቅምምና ።

፲ ፡ ለመስተካህድ ፡ ብእሲ ፡ እምከመ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ ጌሠድኩ ፡ ወኣበየ ፡ ጎድጎ ። (፪ዮሐ ፡ ፲ ማቴ ፡ ፲፰ ፡፲፭ ።
ተከራካሪን ፡ ስው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ከረታኸው ፡ በኋላ ፡ አልመለስም ፡ ቢል ፡ ተወው ።
፲፭ ፡ ወእምሮ ፡ ከመ ፡ ዓላዊ ፡ ውኑቱ ።
ገብቶ ፡ ወጥ ፡ እንደኾነ ፡ አስታውቅበት ።
ዘከማሁ ፡ ያሰሕት ፡ ወያጌጊ ።
እንደሱ ፡ ያለውን ፡ የሚያስት ፡ እንደኾነ ።
ወይረክብ ፡ ኵነኔ ። (፭ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፭ ።)
ፍዳውን ፡ እንዲቀበል ፡ አስታውቅበት ።

፲፮ ፡ ወእምከመ ፡ ፈነውከዎ ፡ ለአርጢሞን ፡ ኀቤከ ።
አርጢሞንን ፡ ወዳንት ፡ በሰደድሁት ፡ ጊዜ ።
አው ፡ ጢኪቆስ ።
ጢኪቆስንም ፡ ቢኾን ፡ በሰደድሁት ፡ ጊዜ ።
ፍጡን ፡ ነዓ ፡ ኀቤየ ፡ ሀገረ ፡ ናቆጶል ። (፪ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።
እኔ ፡ ካለሁበት ፡ ዘንድ ፡ ናቆጶል ፡ ፈጥነህ ፡ ና ።
አስሙ ፡ አጥባዕኩ ፡ አክርም ፡ ሀየ ።
ከዚያ ፡ ልከርም ፡ ወድኀለሁና ።

፲፯ ፡ ለዜማስ ፡ ጸሐፌ ፡ ሀገር ፡ ወለአጵሎስ ፡ ጽሑቀ ፡ አከብሮሙ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰፡ ፳፬፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፮ ።)
ሀገር ፡ አሳዳሪ ፡ ዜማስንና ፡ አጵሎስን ፡ ተግተህ ፡ አርዳቸው ።
አይጸነሱ ፡ ምንተኒ ።
በምንም ፡ በምን ፡ እንዳይቸገሩ ።

፲፰ ፡ ወአሊአነሂ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ፡ (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፰ ።)
(እሊአነ ፡) ምእመናን ፡ በጎውን ፡ ትምህርት ፡ ይማሩ ።
በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ።
መምህራን ፡ በማስተማር ፡ ጸንተው ፡ በሚኖሩ ፡ ገንዘብ ።
ከመ ፡ አይኀጥኡ ፡ (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ፡)
ምእመናን ፡ ፍሬ ፡ ትምህርትን ፡ እንዳያጡ ።
አንድም ፡ ወአሊአነሂ ፡ ይትመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ ሠናየ ።
መምህራን ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡ ይማሩ ፡ (አለ ፡) ሠርተው ፡ ሥሩ ፡ ይበሏቸው ።

www.zeyeneta.com

በዘይቀውሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ግብር ።
ምእመናን ፡ በበጎው ፡ ግብር ፡ ጸንትው ፡ ብሚናኑ ፡ ንጎዘብ ፡ ከመ ፡ ኢይኅጥኡ ።
ምእመናን ፡ ፍሬ ፡ ትሩፋትን ፡ እንዳያጡ ።

፲፩ ፡ አምኑከ ፡ ዙሎሙ ፡ እሰ ፡ ምስሌየ ።
ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ዅሉ ፡ ቸር ፡ አሰሀን ፡ ይሉሃል ።
አምኅ ፡ ዙሉ ፡ ዘያፈቅረን ፡ በሃይማኖት ።
በሃይማኖት ፡ የሚመስሰንን ፡ ዅሉ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በል ።
ጸጋሁ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ዙልከሙ ። (ገላ ፡ ፩ ፡ ፮ ።
እድሮባችሁ ፡ ይኑር ።

አሜን ፡ በውነት ።

ተፈጸመት ፡ መልእክተ ፡ ጎበ ፡ ቲቶ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በሀገረ ፡ ናቆጵል ፡ ወተፈነወት ፡ ምስለ ፡ አርማግ ፡ ረድኡ ።
በናቆጵል ፡ የተጻፈች ፡ በአርማግ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ ለቲቶ ፡ የተላከች ፡ ከታብ ፡ ደረሰች ፡ ቀፈጸመች ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

አንግሥቶ ፡ ሳስጀመረን ፡ እስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

ምክንያተ ፡ ጽሒፍቱ ፡ መልእክተ ፡ ለሐዋርያ ጳውሎስ ፡ ጎበ ፡ ፊልሞና ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ አናሲሞስ ፡ ንብረ ፡ ዚአሁ ።

እስመ ፡ አናሲሞስ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ይትቀነይ ፡ ሎቱ ፡ ለፊልሞና ፡ እምብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ እንዘ ፡ አረማዊ ፡ ውእቱ ፡ ወኢአምነ ፡ በእግዚአነ ።

ወፊልሞናስ ፡ ብእሲ ፡ ምእመን ፡ ወጸድቅ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ አብፍምያ ፡ ወወልዱ ፡ አከርጶስ ፡ ዘኮነ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ።

ወአናሲሞስኒ ፡ ገብሩ ፡ ኮነ ፡ ዐቃቤ ፡ ንዋዩ ።

ወአጥፍአ ፡ ወርቀ ፡ እግዚኡ ፡ ወጎጥአ ፡ ዘይፈድየ ።

ወሖረ ፡ ጎበ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ሙቁሐ በሮሜ ፡ እመ ፡ ቁጻሚ ፡ ሙቃሔሁ ፡ ወተማኅፀነ ፡ ቦቱ ።

ወአጥመቆ ፡ ሐዋርያ ፡ ወመሀሮ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ እንዘ ፡ ያስተ በቍዖ ፡ ከመ ፡ ይስረይ ፡ ሎቱ ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለፊልሞና ፡ ክታብ ፡ የጸ ፈበት ፡ ምክንያት ፡ ስለአኒሲሞስ ፡ ዕል ፡ አናሲሞስ ፡ ነው ።

አናሲሞስ ፡ ዌጌታችን ፡ ባያምን ፡ አረማዊ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ለፊልሞና ፡ ይገዛለት ፡ ነበረ ።

ፊሊሞና ፡ ግን ፡ ከሚስቱ ፡ ከአብፍምያና ፡ በዚች ፡ ሀገር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ከተሾመ ፡ ከልጁ ፡ ከአከርጶስ ፡ ጋራ ፡ ያመነ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

አገልጋዩ ፡ አናሲሞስም ፡ ዕቃቤት ፡ ጠባቂው ፡ ነበረና ፡ የጌታውን ፡ ወርቅ ፡ አጥፍቶ ፡ የሚከፍለው ስላጣ ፡ ማርልኝ ፡ ሲል ፡ ይጽፍለታል ።

በመጀመሪያ ፡ እስራቱ ፡ በሮም ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ ሔዶ ፡ (ያመለበት ፡) ተማፀነበት ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ሃይማኖት ፡ ወንጌልን ፡ እስተምሮ ፡ አጥምቆ ፡ ዕዳውን ፡ ይቅር ፡ እንዲለው ፡ ሲማልድ ፡ ይህን ፡ ከታብ ፡ ጸፈለት ።

www.zeyeneta.com

መልእክት ፡ ኀበ ፡ ፊልሞና ።

ፊልሞና ፡ የቆላስይስ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በጳውሎስ ፡ ስብከት ፡ አምኑዋል ፡ አናሲሞስ ፡ የሚባል ፡ ባሪያ ፡ ሸሽረው ፡ እሱ ፡ ሲያምን ፡ አላመነም ፡ የእምነት ፡ ነገር ፡ አንዴ ፡ ጊዜ ፡ ቅይይጥምና ፡ ለተልእኮ ፡ ወጥቶ ፡ የጌታው ፡ ዘብት ፡ ጠፍቶበት ፡ ማን ፡ ባስታረቀኝ ፡ እያሉ ፡ ሰደዝን ፡ ከጳውሎስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያስታርቅህ ፡ የለም ፡ ብለውት ፡ ሮም ፡ ወርደ ፡ አስተምሮ ፡ አሳምኖ ፡ አጥምቆ ፡ ሲያስታርቅ ፡ ይህን ፡ ጽፎ ፡ ሰዶታል ፡ እስተበቍዓከ ፡ አስተብቍዖተ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ እሙ ፡ ልሒቅ ፡ አነ ፡ ዘከመ ፡ ተአምር ፡ ወይእዜኒ ፡ ሂ ፡ ሙቁሔ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አነ ፡ አስተበቍዓከ ፡ በእንተ ፡ ወልድየ ፡ ዘወለድክዎ ፡ በመዋቅሕተ ፡ ዘውእቱ ፡ አናሲሞስ ፡ ዘቀዲሙሰ ፡ ኢበቍዐከ ፡ ወይእዜኒ ፡ ሶሂ ፡ ጣለ ፡ ተሂ ፡ ባቍዐ ፡ ከነ ፡ ጥቀ ፡ ሳፍሁ ፡ ፈነውክዎ ፡ ኀቤከ ፡ ተወክፎ ፡ ከመ ፡ ወልድየ ፡ ዐፈቀድኩሰ ፡ አንብሮ ፡ ገቢ ፡ ይትልአከኒ ፡ ህየንቴከ ፡ በመዋቅሕተየ ፡ ዘበወንጌል ፡ ወኢፈቀድኩ ፡ ምንተኒ ፡ እግበር ፡ ዘአንበለ ፡ ታእምር ፡ አንተ ፡ ክመ ፡ ኢይኩን ፡ ሠናይቲከ ፡ በአገብሮ ፡ ይላል ።

ወእመሂ ፡ ዘአሰሰ ፡ ለከ ፡ አው ፡ እመዐ ፡ ዘይፈድየክ ፡ ላዕሌየ ፡ ረሲ ፡ ይላል ፦አኮ ፡ እኔ ፡ ከመ ፡ ኀብር ፡ እላ ፡ ዘይጌይስ ፡ እምኀብር ፡ ወእመሰ ፡ እጎየ ፡ እንተ ፡ ትወክፎ ፡ ክሣየ ፡ ይላል ፡ ወምስለዝኒ ፡ አስተዳሉ ፡ ሊተ ፡ ማኅደረ ፡ ይላል ። የጸፈበት ፡ ሀገር ፡ ሮም ፡ በቀዳማዊ ፡ እሸራቴ ፡ ከታብ ፡ ወላጅ ፡ አናሲሞስ ። እሱስ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ይሰጠዋል ፡ ቢሉ ፡ ወስዶ ፡ በባጠገብ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣል ፡ ከጳውሎስ ፡ ክታብ ፡ መጥቶለሃል ፡ ብለው ፡ ይሰጡታል ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከመጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ተመልክቶ ፡ ይታረቀዋል ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎሰ ፡ ሠቂሑ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፩ ።)

የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እሳሩ ፡ ከምኾን ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ ክታብ ።

ወጢሞቴዎስ ፡ እኁነ ።

ከወንድማችን ፡ ከጢሞቴዎስም ፡ የተላከች ፡ ክታብ ፡ (ሐተታ ፡) እንዳለፈው ።

ለፊልሞና ፡ ዘናፈቅር ፡ ዘየኀብር ፡ ግብረ ፡ ምስሌነ ።

ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚኾን ፡ ሰምንወደው ፡ ለፊልሞና ፡ ትድረስ ።

ወለእብኵምያ ፡ እኅትነ ።

ለኅታችን ፡ ለአብፍምያም ፡ ትድረስ ፡ (ሐተታ ፡) ባልና ፡ ሚስት ፡ ልጣ ፡ ከጕስት ፡ እያለች ፡ ታዳከማለችና ፡ እንዳታዳክም ። እነድም ፡ እቂም ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በምትኾን ፡ ግብር ፡ ትግልድ ፡ ታስታርቅ ፡ ለማለት ።

፪ ፡ ወለአከርጳ ፡ ወልዱ ፡ ዘይገብር ፡ ምስሌነ ።

ከኛ ፡ ጋራ ፡ ወንጌልን ፡ ለሚያስተዋር ፡ (ዘየኀብር ፡) በጣኦትማር ፡ አንድ ፡ ለሚኾን ፡ ለልጁ ፡ ለአከርጳም ፡ ትድረስ ፤ (ሐተታ ፡) ያባቴ ፡ ቍም ፡ ወራሹ ፡ የሙት ፡ እልፅር ፡ እያለ ፡ ያዳክማልና ፡ እንዴያዳክም ።

አንድም ፡ እሱም ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በሚኾንበት ፡ ግብር ፡ ይማልዱ ፡ ዐስታርቅ ፡ ለማለት ።

ወለአለ ፡ ምስሌሆሙ ፡ አለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። (ቆላ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)

ከሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ላሉ ፡ ለቤተ ፡ ሰብእቻቸውም ፡ ትድረስ ፡ (ሐተታ ፡) ፡ ሥጋችን ፡ ወርቁ ፡ ለዝና ፡ እኹሉ ፡ ለቀጠና ፡ ልብሱ ፡ ለርዝና ፡ እያሉ ፡ ያደክማሉና ፡ እንዳያዳክሙ ። አንድም ፡ ሉሱም ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በሚኾንበት ፡ ግብር ፡ ይማልዱ ፡ ያስተታርቁ ፡ ለማለት ።

፫ ፡ ሰላም ፡ ለከሙ ።

ቸር ፡ አላችሁን ።

ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡)

የእግዚአብሔር ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ።

፩ ፡ አአኩቶ ፡ ለአምላኪየ ፡ ዘልፈ ።

ፑ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ዘሠራዕኩ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ አመ ፡ አውፃእኩሙ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ (ዘጸ ፡ ፲፱ ፡ ፭)
ሕጉም ፡ ከግብጽ ፡ ባወጣኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እንደሠራሁላቸው ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ አይደለም ።
እስመ ፡ እሙንቱኒ ፡ ኢነበሩ ፡ በሥርዓትየ ።
እነሱ ፡ በሕጌ ፡ ጸንተው ፡ አልኖሩምና ።
ወእነኒ ፡ ተሀየይክሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ። (ኤር ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡)
እኔም ፡ ቸል ፡ አልኋቸው ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏልና ። (ሐተታ ፡) ዘመኑን ፡ በዘመን ፡ ስለአደሰው ፡
እሠርዕ ፡ ሕገ ፡ ሐዲስ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሕጉስ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፤ እሠርዕ ፡ ለሕግ ፡ እንጂ ፤ ለዘመን ፡
አይመችም ። ይህስ ፡ ነእምር ፡ ከመ ፡ ተሠርዓ ፡ እዝግን ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ ብሎ ፤ ሕጉን ፡
በዘመን ፡ ስለአደሰው ፡ እሠርዕ ፡ ሕገ ፡ ሐዲስ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሕጉስ ፡ ሕጉ ፡ ነው ፤ እንዳይሉት ፡ ወአኮ ፡
ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ዘሠራዕኩ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ አለ ።
ዘሠራዕኩ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ያለውንም ፡ ይዘው ፡ ኪዳነ ፡ ናኅን ፡ ግዘፈተ ፡ አብርሃምን ፡ ክዘነተ ፡ መልከ ፡
ጼዴቅን ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ አመ ፡ አውፃእኩሙ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ አለ ።

ፒ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሥርዓት ፡ እንተ ፡ እሠርዕ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ፡ እምድኅረ ፡ እማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡
እግዚአብሔር ፡ እወዲ ፡ ሕግየ ፡ ውስተ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ወእጽሕፎ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፫ ፡)
ካዎስት ፡ ሽህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ለኩሉቱም ፡ ነገድ ፡ ለዐሥሩም ፡ ነገድ ፡ የምሠራት ፡
ሥርዓት ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ እጽፈዋለሁ ፡ በሕሊናቸው ፡ እቀርጸዋለሁ ።

ወእከውኖሙ ፡ አምላክሙ ።
እኔ ፡ አባት ፡ እኾናቸዋለሁ ።
ወእመንቱኒ ፡ ይከውኑኒ ፡ ሕዝብየ ።
እነሱም ፡ ልጆቼ ፡ ይሆኑኛል ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ እንጂ ። (ሐተታ ፡) ሕግ ፡ ሕግ ፡ በማለት ፡ አለ
የውም ፡ የቀደመውን ፡ ስርየተ ፡ ሥጋ ፤ የዛሬውን ፡ ስርየተ ፡ ነፍስ ፡ በማለት ፡ ለይቶታል ። እጽሕፎ ፡
እጽሕፎ ፡ በማለት ፡ አለየውም ፡ የቀደመውን ፡ በብራና ፤ የዛሬውን ፡ በልቡና ፤ በማለት ፡ ለይቶታል ።

www.zeyeneta.com

፲፩ ፡ ወኢይምህር ፡ እንከ ፡ እት ፡ እኅዋሁ ፡ እንበለ ፡ ይክል ፡ ቅኣምነቡ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እንግዲህ ፡ መጻህ ። እግዚአብሔርን ፡ ይመክት ፡ ማለት ፡ ወንጌሎን ፡ ወንድሙን ፡ አያስተምርም ።
እስመ ፡ ዘሉሙ ፡ የአምሩኒ ፡ ንኡሶሙ ፡ ወዓቢዮሙ ፡ (ኤር ፡ ፴ ፡ ፴፬ ።)
ታናሹም ። ታላቁም ። ያውቁኛልና ።

፲፪ ፡ ከመ ፡ እግሀሎሙ ፡ ወእሰሪይ ፡ ሉሙ ፡ ኃጢአትሙ ።
ይቅር ፡ እላቸው ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እስተሰርይላቸው ፡ ዘንድ ። ወኢይዜከር ፡ ሉሙ ፡ አበሳሆሙ ።
በደላቸውን ፡ አላስብባቸውም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሂልና ፡ የቀደመችውስ ፡ ኪዳን ፡ ሕግ ፡ ትና ፡ ቢኾን ፡
ሌላ ፡ ሕግ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ባልወደደም ፡ ንበር ።

፲፫ ፡ ወብሂለ ፡ ታሉስ ፡ በአንተ ፡ ሐዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ ፈቂዶ ።
እሠርዕ ፡ ሕገ ፡ ሐዲስ ፡ ግለቱ ፡ እንግዳ ፡ ሥርዓት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ዕለወደደ ፡ ነው ።
እስመ ፡ ቀዳሚት ፡ በሌት ።
የቀደመችው ፡ ብልየት ፡ ነበረባትና ። እንድም ፡ እንግዳ ፡ ሥርዓት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ እሠርዕ ፡ ሕገ ፡
ሐዲስ ፡ ግለቱ ፡ የቀደመችው ፡ ብልየት ፡ ስለነበረባት ፡ ነው ፡ እንድሁን ፡ ታወቅ ፡ ትረዳ ።
ወዘሰ ፡ ይበጽ ፡ ወይረሥእ ፡ ቅሩብ ፡ ውእቱ ፡ ጸሙሰና ።
እንኪያስ ፡ ጽሙ ፡ ያስፈው ፡ ሕግ ፡ ሃንትንም ፡ ጸኅልፈት ፡ ተሬስ ፡ ትርኢ ፡ ጽሙ ፡ ቢት ፡ ያሣሪ ፡ ያጌጠ ፡
ንበረ ፡ ሊደርስ ፡ ቀርቧል ፡ ጽሙ ፡ ልክስ ፡ የተሞ ፡ ዋጽሙ ፡ ንበረ ፡ ሥዕልቅ ፡ ቀርቧል ፡ እንደ ፡ ጠፋ ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፱ ።

ክፍል ፡ ፭ ።

፩ ፡ ወለቀዳሚትኒ ፡ ደብተራ ፡ ሥርዓተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ኅቲ ።
ዕቀደመች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ በጎን ፡ የሚያርጹበት ፡ መቅለምት ፡ ደመን ፡ የሚዋበሱበት ፡ ብርቱ ፡ ሥጋ
ውን ፡ የሚቀቅሉበት ፡ ድስት ፡ ንበራት ፡ ነበረባት ።
ወመቅደሰ ።
መቅደስም ፡ ንበረባት ፡ መቅደስ ፡ ዕሥራት ፡ ክንድ ፡ ደብተራ ፡ ፻ያይቱ ፡ ክንድ ፡ ኢንድም ፡ (መቅደስ ፡
በመላዋ ፡ ሠላሳዋ ፡ ክንድ ፡ ደብተራ ፡ ልብስት ፡ ።

፪ ፡ ወቀዳሚት ፡ ደብተራ ፡ እንተ ፡ ተሠርዐ ፡ ትርሚታ ፡ ባቲ ፡ ተቅዋመ ፡ መረዳት (ዘጸአ ፡ ፳፮ ፡ ፳፫ ፡ ወዘ ።
ጌጣ ፡ ሰብኪናወት ፡ ዕቀደመች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ መብራት ፡ የሚያበሩበት ፡ መቅረዝ ፡ ንበራት ፡ መና
ራት ፡መናራት ፡ ቢል ፡ ይቀኖል ፡ ደተዘዋመረ ፡ ነው ። ኑር ፡ እምኑር ፡ እንዲል ፡ በዓረብ ፡ ዝርያን ፡
ዘእምብርሃን ፡ ሲል ፡ ናር ፡ እንዲል ፡ አሳት ፡ ሲል ።
ወማዕድ ።
ሰደቃም ፡ ንበራት ፡ ንቨረባት ። ጉለት ፡ ክንድ ፡ ኑዞ ፡ ክንድ ፡ ከሰንዝር ፡ ወሮክ ፡ ክንድ ፡ ቁመት ።
ወኅብስት ፡ ዘይመርዑ ።
(ኅብስተ ፡ ዘይመርዑ ፡) ኅብስት ፡ የሚያቀርበትን ፡ ሰዶቃ ፡ ንበራት ። (መኳስት ፡ ዘይመርዑ ፡) ማለት ፡
ማኅ ፡ የሚያቀርቡትም ፡ ኅብስት ፡ ንበራት ፡ ንበረባት ፡ ከኢት ፡ በመሥዋዕታ ፡ ዕሥራትኑ ፡ ንዘርቱ ፡
ይዝው ፡ ኅብተቱ ፡ ከድሽቱን ፡ በልተው ፡ ከድሉን ፡ ትተው ፡ መኅተቱ ፡ ማኅ ፡ ዘድከት ፡ ያዝው ፡
ኅብተው ፡ የቀለሙን ፡ በልተው ፡ ትከሰን ፡ ተከተው ፡ መኅተቱ ፡ ጽንዲዘ ፡ እንዘኝ ፡ ሸድኅ ፡ ዘሚን ፡
ሙላ ፡ ኤድራ ፡ እንመትም ፡ ንበር ። ምሳሌ ፡ ንው ፡ ግዕድ ፡ የምድሪ ፡ ርስት ፡ ኅብስቱ ፡ ያለርሱለቱ ፡
ነገር ፡ እስጀሌል ። እንድም ፡ ማዕጽ ፡ የመባየኒ ፡ ንዘዘት ፡ የጌታ ፡ አሥራሰሉት ፡ መኾን ፡ ለኅዘው ፡ የሚ
ቅበሉት ፡ ፲፱ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸውና ።
ወይብልዋ ፡ ቅድስት ፡ (ዘጸ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ።)
ሃያይቱን ፡ ክንድ ፡ ቅድስት ፡ ይሏት ፡ ንበር
፫ ፡ ወለውላጢትሰ ፡ ደብተራ ፡ እንተ ፡ እምድኅረ ፡ ካልኢ ፡ መንጦላዕት ፡ ይብልዋ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ (ዘዕእ ፡
፳፮ ፡ ፴፫ ።)
ከኩሉቱኒው ፡ መጋርያ ፡ ውጻይ ፡ ያለችውን ፡ ወሥፍንን ፡ ከንድ ፡ ማን ፡ ቅድስቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ይሏት ፡ ነበር ።
ቅድስት ፡ የአሪት ፡ ቅድሱ ፡ ቅዱሳን ፡ የወንጌል ። እንድም ፡ ቅድስት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፤ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡
የመንግሥተ ፡ ሰማይ ። እንድም ፡ ቅድስት ፡ የሥጋ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ የነፍስ ።

www.zeyeneta.com

፪ ፡ ወውስቴታ ፡ ግልጠንት ፡ ዘወርት ፡ (ዘፀአ ፡ ፴ ፡ ፴፪ ፡ ፴፯ ፡፡)
ውስቴታ ፡ ለቅድስት ፡ ነው ፤ በውስጢም ፡ የወርቅ ፡ ማዕጠንት ፡ ነበረባት ፤ ነበራት ፡፡
ወታቦትኒ ፡ እንቶ ፡ ውስቴታ ፡ ኦሪት ፡፡
ጽላት ፡ ያለባት ፡ ታቦት ፡ በውስጢ ፡ ነበረባት ፡ ነበራት ፡ በጽሕፈቱ ፡ መጻፈያውን ፡ ተናገረ ፡፡
እንተ ፡ ይኪድንዋ ፡ በወርቅ ፡ ውቱረ ፡ (ዘፀአ ፡ ፳፭ ፡ ፲ ፡፡)
ቅፉለ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በውስዋ ፡ በአፍአ ፡ በወርቅ ፡ የተለበጠ ፡ ታቦት ፡ በውስጢ ፡ ያለባት ፡፡
ወወስቴታ ፡ መሶበ ፡ ወርቅ ፡ ዘመና ፡ (ዘፀአ ፡ ፲፮ ፡ ፴፫ ፡፡)
በውስጢ ፡ መና ፡ ያለበት ፡ መሶበ ፡ ወርቅ ፡ ነበረባት ፡ ነበራት ፡፡ መሶበወርቅ ፡ የእመቤታችን ፡ መና ፡ የጌታችን ፡፡
ወበትረ ፡ አሮን ፡ አንተ ፡ ሠረጸት ፡ (ዘኁል ፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡፡)
ሳይተክሏት ፡ ውኃ ፡ ሳያጠጧት ፡ የለመለሙች ፡ ያበበች ፡ ያፈራች ፡ የአሮን ፡ በትር ፡ ነበረች ፡፡
ወጽላትኒ ፡ ዘአራት ፡፡
ጽሕፈቱን ፡ ተናገር ፡ መጻፈያውን ፡ አልተናገረም ፡ ነበርና ፡ ሕግ ፡ የተጻፈባት ፡ ጽላትም ፡ በውስጢ ፡ ነበረባት ፡፡
፭ ፡ ወመልዕልታ ፡ ኪሩቤል ፡ ዘሰብሐት ፡ ይጸልሉ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋል ፡ (ዘፀ ፡ ፭ ፡ ፳፭ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ፡ ፴፯ ፡፡)
መልዕልታ ፡ ለታቦት ፡ ነው ፡ ከወደላይ ፡ ባንበሩ ፡ ኪሩቤል ፡ ተሥለውባት ፡ ነበር ፡ (ዘዕብራውያት ፡) ዘብር ሃን ፤ ዘክብር ፤ ሲል ፡ ነው ፡፡ (ታሪክ ፡) አንተ ፡ ተሠርዐ ፡ ትርሲታ ፡ ያስውን ፡ ይዘው ፡ ይተርካሉ ፡፡ መለደ ብተራ ፡ ግበር ፡ ላቲ ፡ ዐሠርተ ፡ አዕጸደ ፡ እምቢሶስ ፡ ፍቱል ፡ እንዲል ፤ አራት ፡ ጎብር ፡ አምስተኛው ፡ ወርቁ ፡ ዘቦ ፡ የተሠራ ፡ ግምጃ ፤ ቀሙቱ ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፤ ወርዱ ፡ አራት ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፡ ፈርጅ ፡ አምጥተህ ፤ አምስቱን ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ አምስቱን ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ አድርገህ ፡ በሰፍ ፡ አያይዘው፤ መቶ ፡ መግስጥ ፡ አምሳ ፡ ሆጻጻት ፡ አብጅለት ፤ ኹሉቱንም ፡ አንስት ፡ አያደረግህ ፡ በቀለበት ፡ ያዘው ፡ ብሉታል ፤ አንደ ፡ ደበሉ ፡ ቁልፍ ፡ አንድም ፡ ኹለቱንም ፡ ተባት ፡ አያደረግህ ፡ በቀለበት ፡ ያዘው ፡ ብሉታል ፤ አንድም ፡ ኹሉንም ፡ እንስትና ፡ ተባዕት ፡ አያደረግህ ፡ ቆልፈው ፡ ብሉታል ፡ እንደተሚስ ፡ ቁልፍ ፡፡ የዚህ ፡ መግስጡም ፡ ሆጻጻቱም ፡ የወርቅ ፡ ነው ፤ ብስጥን ፡ ቁመቱ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱ ፡ አራት ፡ አራት ክንድ ፡ አሥረአንድ ፡ ፈርጅ ፡ አምጥተህ ፡ አምስቱን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አምስቱን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አድርገህ ፡ በሰፍ ፡ አያይዘው ፤ መቶ ፡ መግስጥ ፡ አምሳ ፡ ሆጻጻት ፡ አብጅለት ፡ ብሉታል ፤ የዚህ ፡ መግስጡም ፡ ሆጻጻቱም ፡ የብርት ፡ ነው ፤ ቁልፉ ፡ እንደደበሉ ፡ ነው ፤ ልብሰ ፡ በግዕ ፡ ሕሱየ ፡ ይላል ፡ ዓሊምነቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ማዕሰ ፡ መጻጺት ፡ ሰፍተህ ፡ አኑር ፡ ብሉታል ፡፡
በስተቀኝ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ውፍረህ ፡ ባርባ ፡ ምዕግድ ፡ ሃያ ፡ አዕግድ ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፤ ቁመቱ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ወርዱ ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡፡ በስተግራም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረህ ፡ ባርባ ፡ ምዕግድ ፡ ሃያ ፡ አዕግድ ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፡፡ በስተክበር ፡ ቤት ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ሰፍረህ ፡ ባሥራ ኹለት ፡ ምዕግድ ፡ ዐሥር ፡ አዕግድ ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፡፡

ዘጠኝን ፡ ክንድ ፡ ይደዙታል ፤ ክንድ ፡ ይቀራል ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ አይቀርም ፤ ስንዝር ፡ በስቱግራ ፡ ስንዝር ፡ በስተቀኝ ፡ ይቀራል ፡፡ ኹለት ፡ አዕግድ ፡ አምጥተህ ፡ አንዱን ፡ በስተቀኝ ፡ ከወዲህ ፡ ስንዝር ፤ ከወዲህ ፡ ስንዝር ፡ ፈልፍለህ ፡ ከመካከል ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፡፡
አንዱን ፡ በስተግራ ፡ ከወዲዘ ፡ ስንዝር ፤ ከወዲህ ፡ ስንዝር ፡ ፈልፍለህ ፡ ከመካከል ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፡ ስንዝር ፡ ስንዝር ፡ ይታያል ፡ ቀረፈ ፡ ደብተራ ፡ ይላል ፡ የመዓዝን ፡ መግቻ ፤ በስተመግቢያም ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ሰፍረህ ፡ በስተቀኝ ፡ ኹለት ፡ አዕግድ ፡ አቁም ፤ በስተግራም ፡ ኹለት ፡ አዕግድ ፡ አምጥተህ ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፤ ስድስቱን ፡ ክንድ ፡ ይይዙታል ፡ አንድ ፡ ፀምድ ፡ አምጥተህ ፡ ከመካከል ፡ አቁም ፡ ብሉታል ፡ ሰባት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ይኾናል ፡፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ይቀራል ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አይቀርም ፡ በስተቀኝ ፡ ክንድ ፡ ኪጋት ፡ በስተግራ ፡ ክንድ ፡ ኪጋት ፡ ይቀራል ፡፡ ደብተራ ፡ አሬት ፡ ጠባብ ፡ ነበረች ፡ ለመፍራም ፤ ሰው ፡ በሰያፍ ፡ ካልኾነ ፡ ፊት ፡ ሰፊት ፡ አታስገባም ፡ ነበር ፡፡ የዚህ ፡ ከባሱ ፡ የወርቅ ፡ ምዕግዱ ፡ የብርት ፡ ነው ፤ ካህናት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚገቡበት ፡ ነውና ፡ እንዲችል ፡፡ ሃያ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረህ ፡ ወደውስጥ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ሲቀር ፡ ባምስት ፡ አዕግድ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ንጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሉታል ፤ የዚህ ፡ ከባሱም ፡ ምዕግዱም ፡ የወርቅ ፡ ነው ፡ ሲቀ ፡ ካህናቱ ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነውና ፤ የሚገባ ፡፡ ዙሪያውን ፡ በአምስት ፡ ሜጋር ፡ ያዘው ፡ ብሉታል ፡፡ ኹለቱን ፡ ወደላይ ፡ ኹለቱን

www.zeyeneta.com

ወደታች ፡ እንዳይታወቅ ፡ እየመረመርሀ ፡ በችንካር ፡ ያዘው ፡ ብሎታል ፡ ወዘግአከልሰ ፡ ይዕዱ ፡ በጥ በብ ፡ ይላል ፡ እምስተኛውን ፡ ግን ፡ በመካከል ፡ አሳልፈው ፡ ብሎታል፤ እንደሱሪ ፡ መሸቀቅ ፤ እንደሳንቃ ፡ መወርወሪያ ፤ እንደ ፡ ሽግጌ ፡ መወርወሪያ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ለብጠው ፡ ብሎታል ፤ ወርቅ ፡ እንዲተበል ። የግምጃን ፡ ቁመት ፡ ለደብተራ ፡ አሪት ፡ ወርድ ፤ የግምጃን ፡ ወርድ ፡ ለደብተራ ፡ አሪት ፡ ቁመት ፡ ሰጥተህ ፡ አልብስ ፡ ብሎታል ።

ቁመቱ ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ዐሥሩን ፡ መካከሉ ፡ ይይዘዋል ፡ ዘጠኙ ፡ በስተቀኝ ፡ ዘጠኙ ፡ በስተግራ ፡ ይወርዳል ፤ ወርዱ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ሠላሳውን ፡ መካከሉ ፡ ይይዘዋል ፤ ዘጠኙ ፡ በስተ ከበር ፡ ቤት ፡ ይወርዳል ፤ አንዲቱ ፡ በስተመጓጀያ ፡ ትወርዳለች ፤ ዙሪያውን ፡ ክንድ ፡ ክንድ ፡ ክፍት ፡ ይቀራል ፤ ይህንም ፡ በካስማ ፡ ያዘው ፡ ብሎታል ።

ካስማውም ፡ ቋሊማውም ፡ የወርቅ ፡ ነው ፤ የብስጥን ፡ ወርድ ፡ ለደብተራ ፡ አሪት ፡ ቁመት ፤ የብስጥን ፡ ቁመት ፡ ለደብተራ ፡ አሪት ፡ ወርድ ፡ ሰጥተህ ፡ አልብስ ፡ ብሎታል ፤ ቁመቱ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ዐሥሩን ፡ መካከሉ ፡ ይይዘዋል ፡ ዐሥሩ ፡ በስተቀኝ ፡ ዐሥሩ ፡ በስተግራ ፡ ይወርዳል ፡ ወርዱ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ሠላሳውን ፡ መካከሉ ፡ ይይዘዋል ፡ ዐሥሩ ፡ በስተከበር ፡ ቤት ፡ ይወርዳል ፤ ዙሪያው ፡ ክንድ ፡ ክንድ ፡ ክፍት ፡ የነበረው ፡ ይለብሳል ፤ አራቱ ፡ በስተመግቢያ ፡ ይወርዳሉ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ክፍት ፡ ይቀራል ፤ አራት ፡ ጎብር ፡ እምስተኛ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ።

ይህንም ፡ በካስማ ፡ ያዘው ፡ ብሎታል ፤ ካስማውም ፡ ቋሊማውም ፡ የብርቸ ፡ ነው ፡ ብረት ፡ ኃያል ፡ ነውና ፡ ነፍስ ፡ እንዳይነጥለው ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ያን ፡ ስፍር ፡ ቅጥር ፡ የሌለው ፡ ማዕሰ ፡ መጸዲት ፡ አልብስ ፡ ብሎታል ። ዙሪያውን ፡ ቅጥር ፡ አብጅለት ፡ ብሎታል ፤ በስተቀኝ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ በሃያ ፡ አዕማድ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ፤ ቁመቱ ፡ አምስት ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ወርዱ ፡ ክንድ ፡ ከሰን ዝር ፡ አምስት ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ እያለፍሀ ፡ ትከለው ፡ ብሎታል ።

በስተግራም ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ በሃያ ፡ አዕማድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ። በስተከበር ፡ ቤት ፡ አምሳ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ ባሥር ፡ አዕማድ ፡ አምሳ ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ፤ መጋረጃውንም ፡ በዘንግ ፡ በኩላብ ፡ ያዘው ፡ ብሎታል ።

አንድም ፡ እንደሐመረ ፡ ኖኅ ፡ መጋረጃ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲሰቢት ፡ ያምትሰበሰብ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲሰቢት ፡ የምትዘረጋ ፡ ናት ።

በስተመግቢያም ፡ አምሳ ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ በስተቀኝ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ በምስት ፡ አዕማድ ፡ ዐሥራ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ።

በስተግራም ፡ ዐሥራምስት ፡ ክንድ ፡ ሰፍረሀ ፡ በሦስት ፡ አዕማድ ፡ ዐሥራምስት ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ፡ ብሎታል ፤ ሃያ ፡ ክንድ ፡ ክፍት ፡ ይቀራል ፤ ሕቀ ፡ ተዓቲቶ ፡ ይላል ፤ ደብተራ ፡ አሪት ፡ እንደገ በያ ፡ እንደበረት ፡ እንዳትኾን ፡ ቍቲት ፡ እልፍ ፡ ብለሀ ፡ ባራት ፡ አዕማድ ፡ ሃያ ፡ ክንድ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ጋርድ ብሎታል ። ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዳትታይ ።

ቅጥር ፡ ዝቅ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ብቅ ፡ ብሳ ፡ አሻግሮ ፡ ሲያይዋት ፡ የታጠቀ ፡ ጎልማሳ ፡ መስላ ፡ እምራ ፡ አጊጣ ፡ ትታይ ፡ ነበር ። ምሳሌ ፡ ነው ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ የቤተ ፡ እሥራኤል ፡ ሠላሳው ፡ የሠላሳው ፡ በረክት ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፤ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፤ ያዕቆብ ፡ ዐሥራኹለቱን ፤ ሙሴ ፡ ዐሥራኹለቱን ፡ ባርኳቸዋል ፤ በተለየ ፡ ሌዊን ፡ ለክህነት ፡ ይሁዳን ፡ ለምስፍና ፡ ባርኳቸዋል ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ይሆናል ።

ርብቃን ፡ ወንድሞቿ ፡ አጎትነ ፡ ኩኒ ፡ እልፈ ፡ ወአእላፈ ፡ ብለው ፡ ባርከዋታል ፤ አርን ፡ ዕለት ፡ ዕለት እግዚአብሔር ፡ ይባርክሙ ፡ እያለ ፡ ይባርካቸው ፡ ነበር ፡ ሠላሳ ፡ ይሆናል ። ዐሥሩ ፡ የዐሥሩ ፡ ቃላት ፡ ዘጠኙ ፡ የዘጠኙ ፡ በረከት ፡ ሰድስት ፡ በረከተ ፡ ገሪዛን ፡ ምስት ፡ በረከተ ፡ በለዓም ፡ አምስቱ ፡ የአምስቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሙሴ ፤ አራቱ ፡ ያራቱ ፡ ደቂቀ ፡ አሮን ፡ አልዓዛር ፤ ይታምር ፤ አብዩድ ፤ ናዳብ ። ኹለቱ ፡ የፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ የፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ። አንዲቱ ፡ የበረከተ ፡ ዲቦራ ፡ ምሳሌ ። አንድም ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፤ የደብተራ ፡ ርእሱ ። ዐሥሩ ፡ የዐሥሩ ፡ ሕዋሳት ፤ ዘጠኙ ፡ የዘጠኙ ፡ ማዕርጋት ፡ ስድስቱ ፡ የስድስቱ ፡ ቃላት ፡ አምስቱ ፡ የጎምስ ፡ ጠባባት ፡ አራቱ ፡ የአራቱ ፡ ወንጌላውያን ፤ ኹለቱ ፡ የፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ የፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ። አንድም ፡ የሥጋው ፡ የደሙ ፡ ምሳሌ ፤ አንዲቱ ፡ የግእዝ ፡ ርትዕት ፡ ምሳሌ ። አንድም ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ዐሥሩ ፡ እንደመጀመሪያው ፡ የዐሥሩ ፡ ቃላት ፤ ዘጠኙ ፡ እንደኹለተኛው ፡ የዘጠኙ ፡ ማዕርጋት ፤ አምስቱ ፡ የአምስቱ ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፤ አራቱ ፡ ያራቱ ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት ፡ ኹለቱ ፡ የፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ የፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ። አንድም ፡ የሥጋው ፡ የደሙ ፡ ምሳሌ ፤ አንዲቱ ፡ የግእዝ ፡ ርትዕት ፡ ምሳሌ ፡ በስተግራ ፡ ያሉት ፡ የካህናት ፡ ብሊት ፤ ግራ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ ሀብት ፡

www.zeyeneta.com

ስርየት ፡ ኢያሳውያር ፡ በስተቀኙ ፡ ያሉት ፡ የከዘሄል ፡ ሐዲስ ፡ ቀኙ ፡ ኃያል ፡ ነው ፡ ዛብት ። ስርየት ፡ ያሳሄስ ፡ በስተጥግ ፡ ያሉት ፡ የሰማይ ፡ ብሳኒ ፡ ሞከረ ፡ አንፈባኝዋል ። በስተሰሜን ፡ ቤት ፡ ያሉት ፡ የሰማዕታት ፡ ሐዲስ ፡ መከፈ ፡ አሰጸናርባቸውና ። ዙሪያው ፡ ዳያርያት ፡ ጸዳኖት ፡ አራቱ ፡ ጎብር ፡ ያፈቱ ፡ ዓለርያት ፡ ብሳያ ፡ የቁጣ ፡ ነፍስ ፡ ማዕሰ ፡ መጸሪት ፡ የነበቢሐ ፡ ነዳስ ፡ ዐዜል ፡ ሳዩ ፡ ብሄሃን ፡ ሰፍር ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ ብርሃን ፡ የመለኮት ፤ መለኮት ፡ አራቱኩ ፡ ዓለርያት ፡ ደጉ ፡ ነጭነን ፡ ነበቢት ፤ ነፍሳን ፡ የጻዲቁ ፡ ምሳሌ ። አንድም ፡ አራቱ ፡ ጎብር ፡ ያፈቱ ፡ ጸጋ ፡ ምእመናን ፡ ቁዩ ፡ ይማኸሙን ፡ ያፈሳሰና ፡ ጥሩ ፡ መከረኝው ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፡ ቢጫው ፡ ባሉተስፋ ፡ ፍጠሮና ፡ ጭ ፡ የንጹሐን ፡ ያሰጣል ይህን ፡ ለማን ፡ ደኛዋል ፡ ቤሉ ፡ ነቢረኝ ፡ አለረች ፡ ለማለት ።

፮ ፡ መኢኮን ፡ ይእዜ ፡ ጊዜሁ ፡ ከመ ፡ ንንግር ፡ በበገጹ ፡ መዘከመ ፡ ሥርዓት ፡ ውትርሲቱ ።
የሥርዓቱን ፡ የጌጡን ፡ ነገር ፡ በየልዕሉ ፡ በየፋደጅ ፡ በየክባቡ ፡ እዐናገር ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ጊዜው ፡ አይደለም ። (ለተታ ፡) ምነው ፡ ሐዋርያ ፡ ደመዪ ፡ ጠቅሶ ፡ ካሰበው ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ አስተምሮ ፡ አዕምሮ ፡ ይሙሉ ፡ አንጄ ፡ የለ ፡ ሰዳደንን ፡ እገዴሃ ፡ አሉ ፡ ቤሉ ፡ አሪትን ፡ የምናስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ አልኈል ፡ ወን ጌሉን ፡ የምናስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ሰበል ።
ወውእቱ ፡ እናፈጥሰ ፡ ደዕይኩ ፡ ዘኢፈ ፡ ይቈውኡ ፡ ኅሠናት ፡ ይግበሩ ፡ ምሥጥኒሆሙ ፡ ዅሉ ፡ ጊዜ ።
(ዘጉል ፡ ፲፰ ፡ ፫ ፡)
(ይበውኡ ፡ ዅሉ ፡ ጊዜ ፡ ይግበሩ ፡ ምሥጥኒሆሙ ፡ ዘኢፈ ፡ ጊዜ ፡) ከሚያደርጉ ፡ ከንዮ ፡ ከሰናቱ ፡ ዕዳቸው ፡ ዕለት ። መሥዋዕት ፡ ያቋርቡ ፡ ዘንድ ፡ ጣት ፡ ግታ ፡ ይጠቡ ፡ ነበር ።

፯ ፡ ወውስተ ፡ ውሳጤትሰ ፡ ምዕረ ፡ በበዓመት ፡ ይበውኡ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ባሕቲቱ ።
ከአሥራቱ ፡ ኮንድ ፡ ሞን ፡ (በበዓመት ፡ ባሕቲቱ ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ባሕቲቱ) ። ባመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ብቻ ፡ ይገባ ፡ ነበር ።
ምክለ ፡ ደም ፡ ዘያበውኡ ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ወበእንተ ፡ ሕዝቡ ፡ በበይነ ፡ ኃጢአቶሙ ። (ዘመኡ ፡ ፴ ፡ ፲ ።)
አስቀድሞ ፡ የራሱን ፤ ኋላ ፡ የሕዝቡን ፡ ኃጢአት ፡ ለማስተሰረይ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ደሙ ፡ ለሕም ፡ ደመጠሊ ፡ ይዞ ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

፰ ፡ ወከመዝ ፡ አዘዘ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ ።
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲህ ፡ አዝዞ ፡ ነበርና ፡ (አሰ) በዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ይኸን ፡ ብሎ ፤ሊቀ ካህናቱ ፡ ብቻ ፡ ይግባ ፡ ብሎ ፡ በደሙ ፡ ላሕም ፡ በደሙ ፡ ጣሊ ፡ ይኸን ፡ ብሎ ።
አስመ ፡ ዓዲሃ ፡ ኢተዐውቀት ፡ ፍኖተ ፡ ለቅዱሳን ፡ በቀደሚት ፡ ደብተራ ።
በቀደሙች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ የቅዱሳን ፡ ሕጋቸው ፡ ወንጌል ፡ ገና ፡ ስላልታወቀች ።

፱ ፡ ወባሕቲቱ ፡ አምሳሌ ፡ ለካ ፡ ዝክቱ ፡ ሊዝንቱ ፡ ሰዋዕል ፡ ዘዩቱ ፡ ያበውኡ ፡ ተጠሪኖሙ ፡ መሰዋዕተ ፡ ዘእ ይክል ፡ ፈጽሞ ፡ ለዘያቀርቦ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ገዳጅ ፡ መፈጸም ፡ የማይቻለውን ፡ ሙ ርብን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርቢበት ፡ ያ ዘመን፡ አሪት ፡ (ለዝንቱ ፡) ለዘሂ ፡ ለዘመን ፡ ወንጌል ፡ አምሳል ፡ ኸኑ ፡ አምሳል ፡ ኸኑ ፡ እንጂ ፡ እስመ ፡ ዓዲ፡ ኢተዐውቀት ። አንድም ፡ (ዝክቱ ፡ ዘእይክል ፡ ፈጽሞ ፡) ስሚያቀርበው ፡ ሰውነ ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸም ፡ የማይቻለው ፡ ያ ዘመኑ ፡ አሪት ፡ (ለዝንቱ ፡ ዘዩቱ ፡ ያበውኡ ፡ ቍርባኑ ፡)ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ለሚያቀርቡበት፡ ለዚህ ፡ ለዘመን ፡ ወንጌል ፡ አምሳል ፡ ኸነ ፡ አምሳል ፡ ኸኑ ፡ እንጂ ።

፲ ፡ ወኀዕኑ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባልዕት ፡ መብዘይበልቆ ። (ዘሴዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ፡)
ይህን ፡ ብሉ ፡ ይዘን ፡ አትብሉ ፡ ይህን ፡ ጠጡ ፡ ይዘን ፡ አትጠጡ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ማዳን ፡ ፤ ስርየት ፡ ማሰጠት ፡ ስላልተቻላቸው ። (ሐተታ ፡) ይህን ፡ ብሉ ፡ ይህን ፡ አትብሉ፡ ይኸን ፡ አሪት ፡ አትብልው፡ ዘከልኤ ፡ ጥሬሌሁ ፡ መዘጽሩቅ ፡ ስኮናሁ ፡ ትላለች ፡ ይህን ፡ ጠጡ ፡ ይህን ፡ አትጠጡ ፡ የሚል ፡ ወይት፡ አሲ ፡ ቢሉ ፡ ውሃቸው ፡ የኩሬ ፡ ወኃ ፡ ነው ፡ ጎድፍ ፡ የወደቀበት ፡ እንደኾነ ፡ ጠርጣው ፡ ጥለው ፡ ርኩስ፡ እስከ ፡ ዶርክ ፡ ይሉ ፡ ነበረና ።

ወጥምቀታት ፡ ዘዘዚአሁ ። (ዘመአ ፡ ፭፱ ፡ ፫)
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከሚኾን ፡ ጥምቀት ፡ በቀር ።

እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሕግ ፡ ዘሥጋ ።
ይችውም ፡ ሥጋዊት ፡ ሥራት ፡ ናት ።

www.zeyeneta.com

እስከ ፡ አመ ፡ ይትራታዕ ፡ ተሠርዐ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡)
ወንጌል ፡ አስኪሥራ ፡ አሪት ፡ ተሠራ ፡ (ዘተሠርዐ ፡) የተሠራው ፡ ሕግ ፡ ወንጌል ፡ አስኪሥራ ፡ አም ሳለ ፡ ኮነ ።

ክፍል ፡ ፯ ።

፲፩ ፡ ወከርስቶስሰ ፡ ዘመጽአ ፡ ከዊኖ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ለእንተ ፡ ትመጽእ ፡ ሠናይት ፡ በውስተ ፡ እንተ ፡ ተግቢ ፡ ወትኄይስ ፡ ደብተራ ፡ እንተ ፡ ኢገብራ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ወኢኮነት ፡ በውስተ ፡ ዝ ዓለም ።(ም፡ ፮፡፳፡ ፲፩፡ ም፡፰፡፪)
ሰምትመጣው ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኾኖ ፡ የመጣው ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በምከንያተ ፡ ዘርዕ ፡ ያይደለ ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ወደተገኘች ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ርእሱ ፤ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ ያይደለ ፡ በሱ፡ ፈቃድ ፡' ወደተተከለች ፡ ደብተራ ፡ መስቀል ።

፲፪ ፡ እኮ ፡ በደመ ፡ ላሕም ፡ ወጠሊ ፡ ዘቦአ ፡ (ዘሌዋ፡ ፲፮፡ ፫፡ ፲፬ ።)
ደመ ፡ ላሕም ፡ ደመ ፡ ጠሊን ፡ ይዞ ፡ የገባ ፡ አያደለም ።
አላ ፡ በደመ ፡ ዚአሁ ፡ ቦአ ፡ በምዕር ፡ ውስተ ፡ ቅድስት ፡ ዘለዓለም ፡ (ም፡ ፲፫፡ ፳፡ ግብ ፡ ሐዋ፡ ፳፡ ፳፰ ።)
ደሙን ፡ ይዞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደእዝነ ፡ እብ ፡ ወደ ፡ ገጸ ፡ አብ ፡ ገባ ፡እንጂ ።
ወረከበ ፡ መድኃኒተ ፡ (ኢሳ ፡ ፵፮፡ ፲፯ ።)
ድኅነተ ፡ ምእመናን ፡ አገኘ ።

፲፫ ፡ ሶበ ፡ ደመ ፡ ላሕም ፡ ወጠሊ ፡ ወካዕሰ ፡ ዕጕልት ፡ ያነጽሕ ፡ እምኃጢአት ፡ (ዘኍል፡ ፲፱፡ ፱ ።)
ደመ ፡ ላሕም ፡ ደመ ፡ ጠሊ ፤ ሐመደ ፡ ዕጕልት ፤ ሥጋዊ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያስተሰርይ ፡ ከኾነ ።
ወይቄድሶሙ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለእለ ፡ ረከሱ ።
በኃጢአት ፡ ያደፉትን ፡ የሚያከብራቸው ፡ ከኾነ ።

፲፬ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፈደ ፡ ደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘሶበ ፡ ርእሶ ፡ በመንፈስ ፡ ዘለዓለም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ዘአልቦ ፡ ነውር ፡ (ዘሌዋ ፡ ፭፡ ፲፱ ። ፭ ፡ ፩፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳትነት ፡ ራሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ የዘለዓለም፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ያቀረበ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደምማ ።
ያነጽሕ ፡ ሕሊናነ ፡ እምግብር ፡ ምውት ፡ (ም፡ ፩፡ ፪፡ ፳፱ ።)
ከአሪት ፡ ከኃጢአት ፡ ከፍዳ ፡ ከፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ልቡናችንን ፡ እንደምን ፡ ያህል ፡ ያነጻ ፡ ይኾን ።
ከመ ፡ ናምልኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ (፩፡ ተሰ፡ ፩፡ ፱ ። ፩፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፯ ።)
(ንትልእኮ ፡) ብሎ ። ሊቁ ፡ ወሰዶታል ፡ ሕያው ፡ የሚኾን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናገለግለው ፡ ዘንድ።

፲፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ ለሐዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ኢየሱስ ፡ ጎሩየ ፡ ኮነ ፡ (ም፡ ፲፪፡ ፳፱ ፡ ፭፡ ጢሞ ፡ ፪፡ ፭ ።)
ስለዚህ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ መምህር ፤ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አስታራቂ ፡ ኾነ ።
ከመ ፡ ጥዒሞ ፡ ሞተ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለእለ ፡ ስሕቱ ፡ በቀዳሚ ፡ ሥርዓት ፡ (ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፭ ።)
በቀደመች ፡ ሕግ ፡ በአሪት ፡ የበደሉትን ።
እለ ፡ ሎሙ ፡ አሰፈወ ።
ተስፋውን ፡ ያናገረላቸውን ።
ወጸውያሙ ፡ ውስተ ፡ ፀድቱ ፡ ዘለዓለም ፡ (ግብ፡ ሐዋ፡ ፳፮፡ ፲፰ ።)
ወደማታልፍ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ወደመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የጠራቸውን ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቶ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ አስታራቂ ፡ ኾነ ።

፲፮ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ሥርዓት ፡ ግብር ፡ ይመጽኤ ፡ ሞት ፡ ላዕለ ፡ ዘሠርዓ ።
ትእዛዝ ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ በእዛዚ ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ ይመጣል ፡ አዝዘሃልና ፡ ግድ ፡ ሙትስ ፡ አይሉትም ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ቁርጥ ፡ ሥርዓት ፡ ሠርቶ ፡ የሚሞት ፡ ስለኾነ ።

፲፯ ፡ ሥርዓቱሰ ፡ ለዘይመውት ፡ ጽንዕት ፡ ይእቲ ።
የመዋቲ ፡ ሰው ፡ ሥርዓቱ ፡ የጸናች ፡ ናት ።
እስመ ፡ ኢትበቍዕ ፡ አመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ዘሠርዓ ።
(አመ ፡ ሕያው ፡ ዘሠርዓ ፡) ኢትበቍዕ ፡ አመ ፡ ሕያው ፡) በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ የሠራት ፡ ሥራ፡ ካልሞተ ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምምና ።

www.zeyeneta.com

እንድም ፡ ኅበ ፡ ሀሎ ፡ ሥርዓት ፡ ግብር ፡ ይመጽእ ፡ ሞት ፡ ላዕለ ፡ ዘሠርዓ ።
ርስት ፡ ጉልት ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ በባለርስት ፡ በባለጉልት ፡ ግድ ፡ ሞት ፡ ይመጣቢታል ።
ሥርዓቱስ ፡ ለዘይመውት ፡ ጽንዕት ፡ ይእቲ ።
የመዋቲ ፡ ስው ፡ ርስቱ ፡ ጉልቱ ፡ ለሚሞትላት ፡ ለልጆቹ ፤ ልሙትላት ፡ ለሚል ፡ ለሱ ፡ የጸናች ፡ ናት ፡ (ማለት ፡) ቢሞትላት ፡ ለልጆቹ ፤ ልሙትላት ፡ ቢል ፡ ለሱ ፡ የጸናች ፡ ናት ።
እስመ ፡ ኢትበቍዕ ፡ አመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ዘሠርዓ ።
በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ላለ ፡ የሠራት ፡ ሥራት ፡ ካልሞተላት ፡ ለልጆቹ ፤ ልሙትላት ፡ ካለለ ፡ ለሱ ፡ አት ረባም ፡ አትጠቅምምና ።
(እንድም ፡) ኅበ ፡ ሀሎ ፡ ሥርዓት ፡ ግብር ፡ ይመጽእ ፡ ሞት ፡ ላዕለ ፡ ዘሠርዓ ።መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ካለች ፡ ዘንድ ፡ በሰማዕታት ፡ ግድ ፡ ሞት ፡ ይመጣል ።
ሥርዓቱስ ፡ ለዘይመውት ፡ ጽንዕት ፡ ይእቲ ።
የሰማዕታት ፡ ርስታቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የጸናች ፡ ናት ፡
እስመ ፡ ኢትበቍዕ ፡ አመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ዘሠርዓ ።
ካልሞቱላት ፤ እንሙትላት ፡ ካላሉ ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምምና ።

፲፮ ፡ ከማሁ ፡ ቀዳሚኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ደምስ ፡ ኢተሐደሰት ፡ ሥርዓት ።
እንደዚህም ፡ ዅሉ ፡ የቀደመችው ፡ ሕግ ፡ አሪት ፡ ያለደም ፡ አልጸናችም ።

፲፱ ፡ ወነጊሮ ፡ ሙሴ ፡ ዅሉ ፡ ትእዛዘ ፡ አሪት ፡ ለዅሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይነሥእ ፡ ደመ ፡ ላሕም ፡ ወጡሊ ፡ ምስለ ፡ ማይ ፤ ሙሴ ፡ የአሪትን ፡ ትእዛዝ ፡ ለሕዝቡ ፡ ነግሮ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ውኃ ፡ በብርት ፡ ይዞ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ደመ ፡ ላሕም ፡ ደመ ፡ ጠሲን ፡ ተቀብሎ ፡
ወጥጢረለይ ፡
ጽሕመ ፡ ጠሲ ፡ የሐር ፡ ጉንጉን ፡ ይዞ ።
ወቆጽለ ፡ ሁሰጹ ፡ ወይነዝኅ ፡ መጽሐፈ ፡ አሪትኒ ።
እንዶድ ፡ እምባን ፡ ቅጠል ፡ ስሚዛ ፤ ጨምሮ ፡ በዚያ ፡ እየነከረ ፡ መጽሐፈ ፡ አሪቱን ፡ ይረጨው ፡ ነበር ። (ሐተታ) ምነው ፡ እይጠፋም ፡ ቢሉ ፡ በተአምራት ፡ እንድም ፡ እጥፎ ።
ወኵሉ ፡ ሕዝበ ።
ሕዝቡንም ፡ ዅሉ ፡ ይረጭ ፡ ነበር ።

፳ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ዝውእቱ ፡ ደመ ፡ ሕግ ፡ ዘአዘዘክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡(ዘፀአ ፡ ፳፬ ፡፮-፰)
እግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ይዅን ፡ ብሎ ፡ ያዘዘላችሁ ፤ ዳግም ፡ ሕግ ፡ የተነበበበት ፡ ሕግ ፡ የሚጸናበት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አያለ ፡ ይረጭ ፡ ነበር ።

፳፩ ፡ ወይነዝኅ ፡ ደብተራሂ ።
ደብተራ ፡ አሪትንም ፡ ይረጭ ፡ ነበር ።
ወኵሉ ፡ ንዋየ ፡ ግበሪሆሙ ። (ዘሌዋ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።)
ንዋየ ፡ ቅድሳቱንም ፡ ዅሉ ፡ ደረጭ ፡ ነበር ።

፳፪ ፡ ወዓዲ ፡ ይሬሲ ፡ ክመዝ ፡ በቅሩብ ።
በቀሊል ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ፡ እንዲህ ፡ በተርታ ፡ ነገር ፡ ያነጸ ፡ ነበር ።
እንድም ፡ (በቅሩብ ፡) በዓመት ፡ በዓመት ፡ ያነጻ ፡ ነበር ።
ወበደም ፡ ይነጽሕ ፡ ዅሉ ፡ በሕገ ፡ አሪት ፡ (ዘሌዋ ፡፲፮ ፡፲፯ ።)
በአሪቱ ፡ ሥርዓት ፡ ሥጋዊ ፡ አፍአዊ ፡ ኃጢአት ፡ ዅሉ ፡ በደመ ፡ ላሕም ፡ በደመ ፡ ጠሲ ፡ ይሰረይ ፡ ነበር ።
ወዘእንበለ ፡ ይትነዛኅሰ ፡ ደም ፡ ኢይሰረይ ፡ (ኤፌ ፡፩ ፡፯ ።)
ደም ፡ ሳይረጭ ፡ ግን ፡ አፍአዊ ፡ ሥጋዊ ፡ ኃጢአት ፡ አይሰረይም ፡ ነበር ።

፳፫ ፡ ወእመሰ ፡ ዝኩ ፡ ግብር ፡ ዘበአምሳለ ፡ ሰማያት ፡ በዝንቱ ፡ ደም ፡ ይነጽሕ ፡ ውእቱሰ ፡ ዘበሰማያት ፡ መሥዋዕት ፡ ይጌይስ ፡ ወየዓቢ ፡ እምዝ ፡(ም ፡፭ ፡፩ ።)
በሰማያዊት ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ እምሳል ፡ የተሠራች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፤ በደመ ፡ ላሕም ፡ በደመ ፡ ጠሲ ፡ የምትከብር ፡ ከኾነ ፡ ሰማያዊ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾን ፡ የከርስቶስ ፡ ደምማ ፡ ከዚህ ፡ እንደምን ፡ አይበልጥ ፡ (አለ ፡) እንደምን ፡ አያኸብር ፡ አያነጸ ።

www.zeyeneta.com

፩፬ ፡ ወአኮ ፡ ውስተ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ዘበአ ፡ ኢየሱስ ፡ ኀበ ፡ ቅድስት ፡ አንተ ፡ ተገብረት ፡ በአርአያ፡ ጽድቅ ።
ውስተ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ያለውና ፡ ኀበ ፡ ቅድስት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኢየሱስ ፡ በሰማያዊት ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ እምሳል ፡ ወደ ፡ ተሠራች ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ የገባ ፡ አይደለም ።
አንድም ፡ ውስተ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ያለውንና ፡ ኀበ ፡ ቅድስት ፡ ያለውን ፡ በየራሱ ፡ ለማውጣት ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ልግባ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በሰማያዊት ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ እምሳል ፡ ወደተሠራች ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ የገባ ፡ አይደለም ።

፳፭ ፡ በእንበለ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ከመ ፡ ያስተርኢ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአነ ፡ (ቍ፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፭፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩ ።)
ሰለኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ርእሱ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መስቀል፡ ገባ ፡ አንጂ ። አንድም ፡ ሰለኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በባለሟልነት ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደእዝነ ፡አብ ወደ ፡ ገጸ ፡ አብ ፡ ገባ ፡ አንጂ ።

፳፮ ፡ ወአኮ ፡ ዘልፈ ፡ ዘይሠውዕ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ዘይገብር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወይበውዑ ፡ ውስተ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ በበዓመት ፡ በደመ ፡ ባዕድ ፡ (ዘፀአ ፡፴ ፡፲ ።)
የቀደመው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በዓመት ፡ በዓመት ፡ ደመ ፡ ላህምን ፤ ደመ ፡ ጠሊን ፡ ይዞ ፡ ወደቅድስተ፡ ቅዱሳን ፡ ይገባ ፡ እንደነበረ ፤ እሱም ፡ ዅልጊዜ ፡ ራሱን ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ርእሱ ፡ ወደ ደብተራ ፡ መስቀል ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።

፳፯ ፡ ወአመ ፡ አኮሰ ፡ ብዙኀ ፡ እምተቀትለ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ።
አንዲህስ ፡ ባይኾን ፡ (እለ) አንድ ፡ ጊዜስ ፡ ባይኾን ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሞተ፡ ነበር ። አንድም ፡ መሥዋዕቱስ ፡ እሱ ፡ ባይኾን ፡ ብዙ ፡ እልሕምት ፡ ብዙ ፡ አባግዕ ፡ ሲሠዉ ፡ በኖሩ ፡ ነበር ። አንድም ፡ ብዙ ፡ ምእመናን ፡ ባልዳኑም ፡ ነበር ፡ (እለ ፡)እንደተጐዱ ፡ በቀሩ ፡ ነበር ።
አሳ ፡ ይእዜ ፡ ምዕረ ፡ በጎልቀተ ፡ ዓለም ፡ ሦዐ ፡ ርእሶ ፡ (ም፡ ፩፡ ፱፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፡ ፲፭ ።)
ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ሠዋ ፡ እንጂ። ከመ ፡ ይሥዐራ ፡ ለኃጢአት ፡ በመሥዋዕቱ ።
በሱ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ኃጢአትን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ።

፳፰ ፡ ወበከመ ፡ ጽኑሕ ፡ ለሰብእ ፡ ምዕረ ፡ መዊት ።(ዘፍ ፡ ፫ ፡፲፱ ።)
ውሎ ፡ ውሎ ፡ ከቤት ፡ ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ ከመሬት ፡ እንዲሉ ፡ ለሰው ፡ ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ ሞት ፡ እንዲቆየው ።
ወአምድኅረሁ ፡ ዳይን ።
ኋላም ፡ መቃብር ፡ እንዲከተለው ።

፳፱ ፡ ከማሁ ፡ ክርስቶስኒ ፡ ምዕረ ፡ ሦዐ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለብዙኃን ። (ም ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡)
ከርስቶስም ፡ የብዙዎችን ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአት ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ሠዋ ።
ወዳግመሰ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ያስተርእዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይሴፈውዎ ፡ ያሕይዎሙ ፡ (ኢሳ፡ ፶፫፡ ፲፪፡ ፩ኀተሰ፡፩፡፲)
እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት፡ ኾኖ፡ ይታይላቸዋል ፡ (ሐተታ ፡) ምነው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ኃጢአት ፡ ያለበት ፡ ኾኖ ፡ ታይቷልና ፡ እንዲህ፡አለ ቢሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሰው ፡ ኃጢአት ፡ ሊሞት ፡ እንደመጣ ፡ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ በሰው ፡ ኃጢአት ሊሞት ፡ አይመጣምና ። አንድም ፡ ኃጢአት ፡ የሌለባቸው ፡ አድርጎ ፡ ያከበረክቻቸዋል ፡ ርኢ ፡ አባ ፡ እሱንተ ፡ ደናግለ ፡ ንጹሐተ ፡ ብሎ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ፡ እስመ ፡ ጽላሎታ ፡ ይእቲ ፡ ኦሪት ፡ ለእንተ ፡ ትመጽኢ ፡ ሠናይት ።
ለምትመጣው ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ነበረችና ።
እስመ ፡ ኢኮነት ፡ ለሊሃ ።(ቈላስ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ፡)
ቀዋሚተ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ቀዋሚት ፡ ስላልኾነች ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ ነበረችና ።
ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አመ ፡ ያበውዑ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘለፈ ፡ ዘዘልፉ ፡ ዓመት ፡ ኢይክል ፡ ለሊሁ ፡ ግሙራ ፡ ፈጽሞ፡ ሸእለ ፡ ያበውዕዎ ። (ም ፡ ፱ ፡ ፳፭ ፡)

www.zeyeneta.com

ስለዚህ ፡ በዓመት ፡ በዓመት ፡ መሥዋዕት ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ለሚያቀርቡት ፡ ሰዎች ፡ ማዳጅ ፡ መፈጸም አይቻለውም ፡ ነበር ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ እምአዕረፉ ፡ እምዘ ፡ ይሠውዑ ።

ግዳጅ ፡ መፈጸምስ ፡ የሚቻለው ፡ ቢኾን ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ከሚሠውት ፡ መሥዋዕት ፡ ወርፈው ፡ ቢኖሩ ፡ ነበር ፤ ባመት ፡ ባመት ፡ ባልሠውም ፡ ነበር ።

፪ ፡ እስመ ፡ ይሰሪ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለእሰ ፡ ይሠውዑ ።

ለሚያቀርቡት ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ባስተሰረየላቸው ፡ ነበር ።

ወያነጽሕ ፡ በምዕር ።

እንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንጻቸው ፡ ነበርና ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ባልሠውም ፡ ነበር ።

፫ ፡ እላ ፡ ጻዕሙ ፡ ቦሙ ፡ ዘይገብሩ ፡ ተዝካረ ፡ ኃጢአት ፡ በበዓመት ።(ዘሌዋ ፡ ፲፮ ፡ ፴፬ ፡ ኢያ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ።)

እንድ ፡ ጊዜ ፡ ማንጻት ፡ ባይቻለው ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ የኃጢአት ፡ መታሰቢያ ፡ የሚቀርቡት ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ ነበራቸው ፡ እንጂ ።

በውእቱ ፡ መሥዋዕት ።

(አምአዕረፉ ፡ በውእቱ ፡ መሥዋዕት ፡) (ተዝካረ ፡ ኃጢአት ፡ በውእቱ ፡ መሥዋዕት ።)

፬ ፡ እስመ ፡ አይከል ፡ ደመ ፡ ላሕም ፡ ወጠሊ ፡ ይኅድግ ፡ ኃጢአተ ። (መዝ ፡ ፶፩ ።)

ደመ ፡ ላሕም ፤ ደመ ፡ ጠሊ ፡ አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ኃጢአትን ፡ ማስተሰረይ ፡ አይቻለውም ፡ ነበርና፡ የኃጢአት ፡ መታሰቢያ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ ነበራቸው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ አመ ፡ ይመጽእ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ይቤ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ኢፈቀድከ ።

ስለዚህ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መሥዋዕተ ፡ አሪቱን ፡ ቍርባን ፡ አሪቱን ፡ አልወደድህም ፡ አላ ፡ አልበሰከኒ ፡ ሥጋ ።

ሥጋ ፡ ልበሰ ፡ አልከኝ ፡ እንጂ ፡ አለ ። እንድም ፡ (ኢፈቀድኩ ፡)

ሥጋ ፡ ልበሰ፡ አልከኝ፡ እንጂ፡ መሥዋዕተ፡ አሪቱን ፡ ቍርባን ፡ አሪቱን ፡ አልወደድሁም ፡ አልሀ ፡ አለ።

፮ ፡ መሥዋዕተ ፡ ዘበእንተ ፡ ኃጢአት ፡ ኢሠመርከ ።(ሚክ ፡ ፮ ፡፮ ፡)

ኃጢአት ፡ ስለማስተሰረይ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ መሥዋዕት ፡ አልወደድህም ፡ አለ ።

ውእተ ፡ ጊዜ ፡ እቤ ፡ ነየ ፡ መጻእኩ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡ ብዬ ፡ ሰው ፡ ኾንሁ ፡ አለ ።

ውስተ ፡ ርእሰ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንቲአየ ።

የኔም ፡ ነገር ፡ ከኾለቱ ፡ መሥመር ፡ በላይ ፡ ተጽፏል ፡ (አለ ፡)

አልበሰከኒ ፡ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ርእሰ ፡ ይላል ፡ በዳዊት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ፡ (አለ ፡)

ሥጋከ ፡ እንጽሕ ፡ ተብሎ ። ውስተ ፡ ርእሰ ፡ መጽሐፍ ፡ ይላል ፡ በአሪት ፡ ተጽፏል፡ ስቅለተ ፡ ትፌአያ፡ እስራኤል ፡ ለሕይወትከ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲከ ፡ ወኢትትአመኖ ፡ ተብሎ ።

ከመ ፡ እግበር ፡ ፈቃደከ ፡ መኮርኩ ፡ አምላኪየ ።

ፈቃድህ ፡ መስቀልን ፡ ልፈጽም ፡ ወደድሁ ። ነቢይ ፡ እንግር ፡ ያለውን፡ ሐዋርያ ፡ እግበር፡ ብሎታል ። ሐዋርያ ፡ እግበር ፡ ያለውንም ፡ ሊቁ ፡ እመጡ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

፰ ፡ መልዕልቶ ፡ ይቤ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ኢፈቀድከ ፡ ዘበእንተ ፡ ኃጢአት ፡ ኢሠመርከ ፡ ዘይሠውዑ በሕገ ፡ አሪት ፡ ብሂሎ ።

ኢፈቀድኩና ፡ ኢሠመርኩ ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ በአሪት ፡ ሥርዓት ፡ ኃጢአት ፡ ስለማስተሰረይ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ቍርባን ፡ አሪቱን ፡ መሥዋዕተ ፡ አሪቱን ፡ አልወደድሁም ፡ ብሎ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ወዋጅ ፡ ነገረበት ።

፱ ፡ ወእምዝ ፡ ይቤ ፡ ነየ ፡ መጻእኩ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ፈቃደከ ፡ አምላኪየ ።

ወዋጅ ፡ ከነገረበትም ፡ በኋላ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡ ብዬ ፡ ሰው ፡ ኾንሁ ፡ አለ ።

እንድም ፡ በአሪቱ ፡ ሥርዓት ፡ ኃጢአት ፡ ስለማስተሰረይ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ መሥዋዕተ ፡ አሪቱን ፡ አልወደድሁም ፡ ብሎ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ወዋጅ ፡ ከነገረበት ፡ በኋላ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡ ብዬ ፡ ሰው ፡ ኾንሁ ፡ አለ ። አሆ ፡ ብሂሎ ፡ ተአዛዚ ፡ ከዊኖ ፡ መጽአ ፡ ለእድኅኖ ፡ እንዲል ።

ወዝቃል ፡ ይነሥት ፡ ቀዳሚየ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ደኃራዩ ።

ይኸውም ፡ ቃል ፡ በኋላ ፡ የተሠራ ፡ ወንጌልን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ በፊት ፡ የተሠራች ፡ አሪትን ፡ ያፈር ሳል ፡ የኋላው ፡ ቃሉ ፡ ዓዬ ፡ የፊቱን ፡ ያወጣዋል ፡ እንዲሉ ።

www.zeyeneta.com

፲ ፡ ከመ ፡ ንትቀደስ ፡ በሥምረቱ ፡ በቅርባነ ፡ ሥጋሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከነ ፡ በምዕር ። (ም ፡ ፱ ፡ ፲፪፡ ፳፰ ። ቈላስ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።)

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ ወዶ ፡ ባቀረበው ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ እንከብር ፡ ዘንደ ። እንድም ፡ (ሥምረቱ ፡ ለአብ ፡) የአብ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደመኾኑ ።

፲፩ ፡ ወሰሉ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይቀውም ፡ ዙሉ ፡ አሚረ ።

ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኹሉ ፡ ኹልጊዜ ፡ ቁሞ ፡ ያገለግል ፡ ነበር ።

ወይሠውዑ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ መሥዋዕተ ፡ እንተ ፡ ሰግሙራ ፡ ኢትከል ፡ እንጽሖ ፡ ኃጢአት ። (ቊ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፲፩።)

ፈጽሞ ፡ ኃጢአት ፡ ማስተስረይ ፡ የማይቻላትን ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርብ ፡ ነበር ።

፲፪ ፡ ወውእቱሰ ፡ ምዕረ ፡ ሥዐ ፡ ርእሶ ፡ መሥዋዕተ ፡ እንተ ፡ ለዝሉፋ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትን ፡ (ቊ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።)

እሱ ፡ ግን ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡ ስለማስተስረይ ፡ የዘለዓለም ፡ መሥዋዕት ፡ ራሱን ፡ እንድ ፡ ጊዜ፡ ሠዋ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ።

ያንን ፡ ይቀውም ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፡ ሠውቶ ፡ በአብ ፡ ዕሪና ፡ ተቀመጠ ።

፲፫ ፡ ወይጸንሕ ፡ እንከ ፡ እስከ ፡ ይገብኡ ፡ ጸላእቱ ፡ ታሕተ ፡ መከየዶ ፡ እገሪሁ ፡ (መዝ ፡ ፻፱ ፡ ፩ ።)

እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ጠላቶቹ ፡ በእግሩ ፡ እርግጥ ፡ በእጁ ፡ ጭብጥ ፡ ብሰው ፡ እስኪገዙለት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ይጠብቃል ፡ አገር ፤ ሥልጣነ ፡ መለኮት ፤ ረድኤት ፤ ሐዋርያት ፡ መስቀል ፤ ናቸው ። ጸላዕት ፡ አይሁድ ፤ መናፍቃን ፤ አጋንንት ፡ ናቸው ።

፲፬ ፡ አሐተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ገብረ ፡ እንተ ፡ ሰግሙራ ፡ ለአለ ፡ ይትቄደሱ ። (ቊ ፡ ፲፪ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፳፯ ፡)

አምነው ፡ ስሚከብሩ ፡ ሰዎች ፡ የማታዳግም ፡ መሥዋዕት ፡ ራሱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሠዋ ፡

፲፭ ፡ ወሰማዕትነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ምስክራችንም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

፲፮ ፡ እምድኅረ ፡ ይቤ ፡ ዛቲ ፡ ሥርዓት ፡ እንተ ፡ እሠርዕ ፡ ሎሙ ፡ እምድኅረ ፡ እማንቱ ፡ መዋዕል ።

ካምስት ፡ ሽህ ፡ አምስት ፡ ሙቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የምሠራት ፡ ሥርዓት ፡ ይሆች ፡ ናት ፡ ካለ ፡ በኋላ ።

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እወዲ ፡ ሕግየ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ወእጽሕፎ ፡ ውስተ ፡ ሕሊናሆሙ ።

(ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ።)

ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ እጽፈዋለሁ ፡ በሕሊናቸው ፡ እቀርጸዋለሁ ።

፲፯ ፡ ወኢይዜኮር ፡ እንከ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወኢበሳሆሙ ።

እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ኃጢአት ፤ ሆዶላቸውን ፡ በደል ፡ አልልባቸውም ፡ አለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ብሏልና ፤ ምስክራችን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። እንድም ፡ ምስክራችን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ካምስት ፡ ሽህ ፡ ፭፻ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የምሠራት ፡ ሕግ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ሕጌን ፡ በልቡና ቸው ፡ እጽፈዋለሁ ፡ በሕሊናቸው ፡ እቀርጸዋለሁ ፡ እንግዲህ ፡ ወዳህ ፡ ዕዳቸውን ፡ ዕዳ ፡ አልልባቸውም፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏልና ፡ የማታዳግም ፡ መሥዋዕት ፡ ራሱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሠውቶ ፡ (ነበር ።)

፲፰ ፡ ወእምከመሰ ፡ ይትኀደግ ፡ ከመዝ ፡ አልቦ ፡ እንከ ፡ መሥዋዕት ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ፡ (ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፭፭።)

አንድ ፡ ጊዜ ፡ በተሠዋውስ ፡ መሥዋዕት ፡ ኃጢአት ፡ የሚሰረይ ፡ ከኾነ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ኃጢ አት ፡ ስለማስተሰረይ ፡ ኹለተኛ ፡ መሥዋዕት ፡ የለም ።

ክፍል ፡ ፱ ።

፲፱ ፡ ብነ ፡ አኀዊነ ፡ ሞገሰ ፡ ውስተ ፡ በአትነ ፡ ቤቱ ፡ መቅደስ ፡ በደሙ ፡ ለኢየሱስ ፡

(ፍ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ። ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲፰ና ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)

እምከመሰ ፡ ይትዔደግ ፡ ከመዝ ፡ አልቦ ፡ እንከ ፡ መሥዋዕት ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ወንድሞቻችን ፡ ደሙን ፡ ይዘን ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ በጣን ፡ ጊዜ ፡ ባለሚልነት ፡ መወደድ ፤ መታ ፈር ፡ አሰን ። ባለሚልነት ፡ በሥላሴ ፡ ዘንድ ፡ መወደድ ፡ በምእመናን ፤ መታፈር ፡ በአይሁድ ፡ በአጋን ንት ፡ በመናፍቃን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.zeyeneta.com

፩ ፡ እስመ ፡ ሐደሰ ፡ ለነ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወሕይወት ፡ ግብተ ፡ በመንጦላዕቱ ፡ ሥጋሁ ፡ (ም ፡ ፱ ፡ ፭ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፭ ።)

ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግ ፡ እገልጋይ ፡ እሱ ፤ ሥጋውን ፡ መጋረጃ ፡ አድርጎ ፡ ሕግ ፡ ተስፋን ፡ ልደትን ፡ አድሶልናልና ።

ካህን ፡ ዐቢይ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።)

የብሉዩ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መጋረጃውን ፡ ዋሎ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ እንደነበረ ። አንድም ፡ የብሉዩ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መጋረጃውን ፡ ገልጦ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ እንደነበረ ፡ በሥጋ ፡ ተገልጦ ፡ ሕገ ፡ ተስፋን ፡ ልደትን ፡ አድሶልናልና ።

ጽጌ ፡ ንቅረብ ፡ እንከ ፡ በልበ ፡ ጽድቅ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ እንድናትን ፡ ሥስትነትን ፡ በተረዳ ፡ ልቡና ፡ ኾነን ፡ እንቅረብ ።

ወበሃይማኖት ፡ ፍጹም ፡ ምእመን ።

በታመነ ፡ ፍጹም ፡ ሃይማኖትም ፡ ኾነን ፡ እንቅረብ ፡ (ሐተታ ፡) አንዱ ፡ ከጐደለ ፡ ፍጹም ፡ አይባልምና ፡ እንድነት ፡ ሥስትነት ፡ ጥምቀት ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ እንዳለ ፡ አምኖ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ እንዳለ ፡ ካለ መኑ ፡ ፍጹም ፡ አይባሉምና ፡ በታመነ ፡ ፍጹም ፡ ሃይማኖት ፡ ኾነን ፡ አለ ።

እንዘ ፡ ንጹሕ ፡ ልብነ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)

ልቡናችንን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ አድርገን ።

ወንጹሓን ፡ ንሕነ ፡ እምግባረ ፡ እኪይ ።

ከከፉም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ንጹሓን ፡ ኾነን ። (ሐተታ ፡) ንጽሕ ፡ ኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ከኛ ፡ የሚገኝ ፡ አንዱ ፡ ከሱ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ፡ ከኛ ፡ የሚገኝ ፡ ቀራብ ፡ በሃይማኖት ፤ ከሱ ፡ የሚገኝ ፡ ማንጻት ፡ ነው ።

ወሕጹብ ፡ ሥጋነ ፡ በማይ ፡ ንጹሕ ፡ (ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭ ፡ ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

በማየ ፡ ገቦ ፡ ተጠምቀን ፡ (ሐተታ ፡) ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ አልተቀላቀለበትምና ፡ ማይ ፡ ንጹሕ ፡ አለ ።

ጽቮ ፡ ናጽንዕ ፡ እንከ ፡ እሚነ ፡ ወተስፋነ ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ።

ዘእንበለ ፡ ጸረን ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ፤ እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ተስፋችንን ፡ አጽንተን ፡ እንያዝ ። (እሚነ ፡ በተስፋነ ፡) በተስፋው ፡ ማመንን ፡ አጽንተን ፡ እንያዝ ።

አስመ ፡ ጸድቀ ፡ ዘአሰፈወነ ። (ም ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። ፲፩ ፡ ፲፩ ።

እምከመ ፡ ሐርኩ ፡ ወእስተዳሉኩ ፡ ለከሙ ፡ መካነ ፡ እመጽእ ፡ ካዕበ ፡ ወእነሥአከሙ ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ የነገረን ፡ አሱ ፡ የተናገረውን ፡ የማያስቀር ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ እምላክ ፡ ነውና ።

ጽፀ ፡ ወንትቀነው ፡ ምስለ ፡ ቢጽነ ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበምግባረ ፡ ሠናይ ፡ (ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬)

በሃይማኖት ፡ የመሰለንን ፡ ወንድማችንን ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ እንምሰለው ፡ እምከመ ፡ ርኢከሙ ፡ ብእሴ ፡ ለባሴ ፡ ምግባር ፡ ኪያሁ ፡ ተመሰሉ ፡ ቦቱ ፡ እንዲል ፡ (እፈ ፡ ወ ።)

ጽፎ ፡ ወኢንኅድግ ፡ ማኅበረነ ።

ጉባኤያችንንም ፡ አንፍታ ።

ዘከመ ፡ ይለምዱ ፡ ካልኣን ።

ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ጉባኤ ፡ መፍታትን ፡ እንደለመዱ ፡ (ኢይለምዱ ፡) ሐዋርያት ፡ ጉባኤ ፡ መፍታትን ፡ እንዳለመዱ ።

ዳዕሙ ፡ ንትገሠጽ ፡ (ቍ ፡ ፴፯ ።)

ጉባኤ ፡ ከመፍታት ፡ እንከልከል ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ንሬኢ ፡ ዘከመ ፡ ትቀርብ ፡ ዕለት ፡ (ፎ ፡ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ፬ ።)

ዕለት ፡ የሚባለው ፡ ዕድሜያችን ፡ እንደቀረበ ፡ እናውቃለንና ።

ጽፏ ፡ ወለእመ ፡ በግብር ፡ ንኤብስ ፡ እምድኅረ ፡ አእመርናሃ ፡ ለጽድቅ ፡ አልቦ ፡ እንከ ፡ መሥዋዕት ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፮ ፡ ዘኁል ፡ ፲፭ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ።)

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካመነ ፡ ከተጠመቅን ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ አጉበሮን ፡ ተጋፍተን ፡ በነቢር ፡ ብንበድል ፤ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ኃጢአት ፡ ስለማስተስረይ ፡ ኹለተኛ ፡ ጥምቀት ፤ ኹለተኛ ፡ መሥዋዕት ፡ የለም ።

www.zeyeneta.com

ሕግ ፡ አላ ፡ ጽኑሕ ፡ ግሩም ፡ ደይን ፡ ወአሳት ፡ ዘቅንዓት ፡ ዘይበልዖ ፡ ለከሃድያን ፡
(ም ፡ ፱ ፡ ሕግ ፡ ፤ ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ሕፃ ፡ ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፲፩ ፤ ሶር ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፡ ፫ ፡ ፰ ።)
ከሃድያንን ፡ እንደእሳት ፡ የሚያቃጥላቸው ፡ ለእምልኮቱ ፡ ቀንቶ ፡ የሚያመጣው ፡ ግሩም ፡ ዴይን ፡ ይቆየናል ፡ እንጂ ። (ሐተታ ፡) ዘይበልዖ ፡ ለከሃድያን ፡ አለ ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ዘንዶ ፡ አለ ፡ ይበላሃል ፤ አንበሳ ፡ አለ ፡ ይሰብርሃል ፤ ወንበዴ ፡ አለ ፡ ይቀጠቅጥሃል ፡ እንደማለት ።

ሕጽ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘስሕተ ፡ እምአሪተ ፡ ሙሴ ።
ከሙሴ ፡ ሕግ ፡ ከአሪት ፡ ወጥቶ ፡ የበደለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።

እምከመ ፡ ከልኤቱ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰማዕት ፡ ዘለፍዎ ፡ ይመውት ፡
(ዘጎል ፡ ፲፭ ፡ ፴ ፡ ፤ ዘዳግ ፡ ፲፯ ፡ ፮ ።)
ኹለት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ መስክረውበት ፡ የሚሞት ፡ ከኾነ ።
ወኢይምሕርዎ ፡ የማይምሩት ፡ ከኾነ ።

ሕፀ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ይደልዎ ፡ ይትኰነን ፡ ዘተካየዶ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡
(ም ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።)
ወልደ ፡ እግዚአብሔርንማ ፡ ምሉ ፡ የከዳው ፡ ሊፈረድበት ፡ እንደምን ፡ እይገባም ።

ወአርኩሰ ፡ ደመ ፡ ሥርዓት ፡ ዘቦቱ ፡ ተቀደሰ ። (ዕፁ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ፡ ፳፱ ።)
የከሰረበትን ፡ ደሙን ፡ ያሳደፈ ፡ (ሐተታ ፡) እሱስ ፡ አያድፍም ። ሳይበቃ ፡ የተቀበለ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ከመ ፡ ደመ ፡ ዝሉ ፡ ሰብእ ።
ረሰዮ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ እንደዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ደም ፡ አድርጎት ። (ከመ ፡ ግብር ፡ ዘይት ከየድ ፡) ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ፡ ባዳራሽ ፡ እንደተነጠፈ ፡ ዳውጅ ፡ አድርጎት ።

ወዘጸወለ ፡ መንፈሰ ፡ ጸጋሁ ፡ (ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ፡)
መንፈሰ ፡ ቅዱስንም ፡ የሰደበ ፡ (ሐተታ ፡) ያዋሐደ ፡ የከፈለ ፡ የፈጠረ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ በኃጢአት ፡ ኾኖ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እልከፈለም ፡ እላዋሐደም ፡ አልፈጠረም ፡ ግለት ፡ ነውና ። አንድም ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ የሚያከብር ፡ የሚለውጥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በኃጢአት ፡ ኾና ፡ መቀበል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አያከብርም ፡ አይለውጥም፡ ጎብስቱም ፡ ጎብስት ፡ ነው ፤ ወይኑም ፡ ወይን ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነውና ።

ወ ፡ ነእምሮ ፡ ለዘይቤ ፡ እነ ፡ እትቤቀል ፡ ወእነ ፡ እትፈደይ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
(ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ፡ መዝ ፡ ፻ ፡ ፬ ።)
እኔ ፡ እበቀላለሁ ፡ ፍዳ ፡ ኃጢአትንም ፡ እኔ ፡ እከ ፈላለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እናውቃለን ።

መካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ይኴንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቦ ።
ዳግመኛም ፡ በወገኖቹ ፡ ይፈርዳል ፡ ያለውን ፡ እናውቃለን ፡ (አለ) ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ ብሎ ፡ በእስራኤል ፤ ለእስራኤል ፡ ብሎ ፡ በእሕዛብ ፡ ይፈርዳል ፡ ያልውን ፡ እናውቃለን ።

ወኀበ ፡ ጥቀ ፡ ግሩም ፡ ወዲቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ።
በሕያው ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መያዝ ፡ እጅግ ፡ ጭንቅ ፡ ነው ፤ እጅ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ። አንድም በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መያዝ ፡ እጅግ ፡ ጭንቅ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ እናውቃለንና፡ እፎ ፡ ይደልዎ፡ (ሐተታ ፡) ከዚህ ፡ ጥቂ ፡ ግሩም ፡ ወዲቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰ ፤ ዳዊት ፡ ይጌይስኒ ፡ እደቅ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምእደቅ ፡ ውስተ ፡ እጹ ፡ ሰብእ ፡ ይላል ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ከዚያ፡ ዳዊት ፡ የሥጋውን ፡ ተናገረ ፡ ከዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የነፍሱን ፡ ተናገረ ።

ወኀደ ፡ ወተዘከሩ ፡ መዋዕለ ፡ ዘቀዲሙ ፡ ዘእመ ፡ አጥመቁክሙ ።
በዚያውም ፡ ላይ ፡ በተጠመቃችሁ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ የነበራችሁበትን ፡ ዘመን ፡ አስቡ ።

ዘከመ ፡ ተዐገሥክሙ ፡ ብዙኀ ፡ ሕማመ ። (ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ፡
ብዙ ፡ መከራ ፡ ታግሣችሁ ፡ ተቀብላችሁ ፡ እንደነበረ ።

ወኢፈ ፡ ወተጽዕልክሙ ።
ተዋርዳችሁ ፡ እንደነበረ ።

www.zeyeneta.com

ፀሣቀዩክሙ ።
ሥቃይ ፡ እጽንተውባችሁ ፡ እንደነበረ ፡ እስቡ ፡ ዘይሳቀይሰ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ሰብዙኅ ፡ ውዳሴ ፡ እንዲል ።
ወተሣለቁ ፡ ሳዕሌክሙ ።
ዘብተውባችሁ ፡ እንደነበረ ፡ እስመ ፡ ሥላቅ ፡ ያመነሥዋ ፡ ለነፍስ ፡ እንዲል ።
ወበዘተሳተፍዎሙ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ከመዝ ፡ ኮኑ ።
ተሳተፍክዎሙ ፡ ካለ ፡ ለእለ ፡ ከመዝ ፡ ፤ ምስለ ፡ እለ ፡ ከመዝ ፡ ካለ ፡ ተሳተፍክሙ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ። በዚህ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሐዋርያትን ፡ መስላችኋቸው ፡ እንደነበረ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ካሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ እንድ ፡ ኾናችሁ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ተዘከሩ ።

ወፀፀ ፡ ወኅበርክሙ ፡ ሐሚመ ፡ ምስሌየ ፡ በመዋቅሕትየ ።
በእሰራት ፡ ሳለሁ ፡ በተቀበልሁት ፡ መከራ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንድ ፡ ኾናችሁ ፡ እንደነበረ ፤ እኔን ፡ መስላችሁ ፡ እንደ ፡ ነበረ ።
ወበተበርብሮ ፡ ንዋይክሙ ፡ በትፍሥሕት ፡ ዘተወኪፍክሙ ።
ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ በተቀበላችሁት ፡ በክብታችሁ ፡ መዘረፍ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንድ ፡ ኾናችሁ ፡ እንደነበረ ፤ እንድም ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ የተቀበላችሁትን ፡ የክብታችሁን ፡ መዘረፍ ፡ አስቡ ።
እስመ ፡ ተአምሩ ፡ ክመ ፡ ብክሙ ፡ ንዋይ ፡ ዘይጌይሰ ፡ ዘይነብር ፡ ለዓለም ፡ በሰማያት ።
(ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ።)
የበለጠ ፡ የማያልፍ ፡ ገንዘብ ፡ በልዕልና ፡ እንዳላችሁ ፡ ታውቃላችሁና ፡ (አለ ፡) የማታልፍ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ እንዳለች ፡ ታውቃላችሁና ።

ወኢ ፡ ኢትግድፉ ፡ እንክ ፡ ሞገስክሙ ።
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ሃይማኖታችሁን ፡ እትጣሉ ። ጥለውት ፡ ሳለ ፡ እንዳልጣሉት ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ፡ የጣሉትን ፡ እስኪያነሡት ፡ ይዘገያልና ።
እንተ ፡ ባቲ ፡ ትረክቡ ፡ ብዙኅ ፡ ዕሤተክሙ ፡ ወቢየ ፡ (ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ።)
ፍጹም ፡ ዋጋ ፡ የምታገኙባትን ፡ ሃይማኖት ።

ወፀፄ ፡ ወባሕቱ ፡ ትዕግሥተ ፡ ትፈቅዱ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ትዕግሥት ፡ ያሻችኋል ፡ ትዕግሥት ፡ ያሻችኋል ፡ እንጂ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ትረክቡ ።
ከመ ፡ ገቢረክሙ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትርክቡ ፡ ተስፋክሙ ። (ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱ ፡)
እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ ሠርታችሁ ፡ ተስፋችሁን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ።

ወፀፂ ፡ እስመ ፡ ዓዲ ፡ ጎዳጥ ፡ መዋዕል ።
እንግዲህ ፡ ዘመኑ ፡ ጥቂት ፡ ነውና ።
ወይበጽሕ ፡ ዘይመጽእ ።
የሚመጣውም ፡ ይደርሳልና ።
ወኢይጐንዲ ፡ (ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፳ ፡ ፪ ፡ ፫ ።
አይቀርምና ፡ ወልድየ ፡ ሞተ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጐንደየ ፡ እንዲል ። (ጦቢ ፡ ፲፡ ፬ ፡)
ወጸድቅሰ ፡ በእሚን ፡ የሐዩ ። (ዕንባ ፡ ፪ ፡ ፬ ።)
ጻድቅም ፡ እንጂ ፡ ጻድቅም ፡ እኮን ፡ በሃይማኖት ፡ ይኸብራል ።
እንድም ፡ ለነቢዩም ፡ ሰጥቶ ፡ ይክብራል ። አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለንን ፡ እናውቃለን ።

ወፀፆ ፡ ወእመሰ ፡ ተመይጠ ፡ ኢትሠምሮ ፡ ነፍስየ ።
ከወንጌል ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ ቢመለስ ፡ ልቡናዩ ፡ አትወድም ፡ (ኢተመይጠ ፡) ከአሪት ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ካልተመለሰ ፡ ልቡናዩ ፡ እትወደውም ፡ ያሉውን ፡ እናውቃለን ።

ወፀፇ ፡ ንሕነሰ ፡ ኢይደልወነ ፡ ንትመየጥ ፡ ድኅሬነ ፡ ለሕርትምና ። (ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፲፮ ።)
እኛ ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣብን ፤ ጥፋት ፡ ሊኾንብን ፡ ወደኋላ ፡ መመለስ ፡ አይገባንም ፡ (አለ) ወደአሪት ፡ መመለስ ፡ አይገባንም ።
ዘእንበለ ፡ ለሃይማኖት ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ ደኅግናል ፡ እንጂ ።
እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሕይወተ ፡ ነፍስነ ።
ይህችውም ፡ የነፍሳችን ፡ ሕይወት ፡ የምትኾን ፡ ናት ።

www.zoyeneta.com

ም ዕ ራ ፍ ፲፭ ።

፩ ፥ ሃይማኖትሰ ፥ ጥይቅት ፥ ይእቲ ፥ ለዘይሴፈዋ ። (ም ፥ ፲ ፥ ፴፫ ፥ ዮሐ ፥ ፭ ፥ ፳፱ ፥ ሮሜ ፥ ፬ ፥ ፲፭ ።)
ንሕነሰ ፥ ኢይደልወነ ፥ ንትመየጥ ፥ ድኅሬነ ፥ ለኅርትምና ፥ ዘእንበለ ፥ ለሃይማኖት ፥ እንተ ፥ ይእቲ ፥ ሕይወተ ፥ ነፍሰነ ፥ ብሎ ፥ ነበርና ፥ ሃይማኖት ፥ ሃይማኖት ፥ ትላለህ ፥ እንጂ ፥ ምን ፥ ቁም ፥ ነገር ፥ ናት ፥ ትሉኝ ፥ እንደኾነ ፥ ሃይማኖትስ ፥ ተሰፋ ፥ ለሚያደርጋት ፥ ሰው ፥ ዋጋ ፥ በማሰጠት ፥ የተረዳች ፥ ናት ። ሀልዉ ፥ እሴ ፥ ተአመኑ ፥ ተሰፈዎሙ ፥ ንዋየ ፥ ዘኢያስተርኢ ።
ከዚህም ፥ አስቀድሞ ፥ የማይታየውን ፥ የማያልፍ ፥ መንግሥተ ፥ ሰማይን ፥ ኀንዘብ ፥ በማድረግ ፥ ጸንተ ተው ፥ የሚኖሩ ፥ ነበሩ ።

፪ ፥ ዘበእንቲአሁ ፥ ሰማዕተ ፥ ኮኑ ፥ ሊቃውንት ፥ በሃይማኖት ።
(ቀደምት ፥ በሃይማኖት ፥ ሰማዕተ ፥ ኮኑ ፥ በሃይማኖት ፥) የቀደሙ ፥ ሰዎች ፥ አምነው ፥ መከራ ፥ የተቀበሉትን ።

፫ ፥ ኀአምር ፥ ከመ ፥ ተፈጥረ ፥ ዓለም ፥ በቃለ ፥ እግዚአብሔር ።
(ኀአምር ፥ በሃይማኖት ፥ ተፈጥረ ፥ በሃይማኖት ፥) ዓለም ፥ በእግዚአብሔር ፥ ቃል ፥ እንደተፈጠረ ፥ እናውቃለን ። (አለ ፥) ከሃሊነቱን ፥ አምኖ ይኩን ፥ ባለው ፥ ቃል ፥ እንደፈጠረው ፥ እናውቃለን ።
ወእስተርእየ ፥ ዘኢያስተርኢ ፥ ምንትኒ ፥ ዘከነ ፥ እምኀበ ፥ ኢሀሎ ። (ም ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ መዝ ፥ ፴፫ ፥ ፮ ።)
ባለመኖር ፥ አይታይ ፥ የነበረው ፥ ዓለም ፥ ከለመኖር ፥ ወደመኖር ፥ መጥቶ ፥ እንደታየ ፥ እናውቃለን ። (ሐተታ ፥) ፈላስፎች ፥ ግሥ ፥ ዓለም ፥ ከግሥ ፥ ዓለም ፥ ተገኘ ፥ ይሉ ፥ ነበርና ፥ እስተርእየ ፥ ዘኢያስተርኢ ፥ ምንትኒ ፥ ኮነ ፥ እምኀበ ፥ ኢሀሉ ፥ አለባቸው ።

፬ ፥ በተአምኖ ፥ ጎየሰ ፥ መሥዋዕተ ፥ አቤል ፥ እምዘ ፥ ቃየል ፥ ዘአብአ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ (ዘፍ ፥ ፬ ፥ ፬ ፥ ፭ ፥ ፲ ።)
ከዚህ ፥ በኋላ ፥ በተአምኖ ፥ በተአምኖ ፥ እያለ ፥ ከአቤል ፥ እስከሱ ፥ ያሉትን ፥ ያመጣል ፥ ቃየል ፥ ካቀረበው ፥ መሥዋዕት ፥ በተአምኖ ፥ ጎየሰ ፥ አቤል ፥ እምኖ ፥ ያቀረበው ፥ መሥዋዕት ፥ በለጠ ፥ ተሻለ ፥ (አለ ፥) ዐረገ ።
ወበእንቲአሁ ፥ ሰማዕተ ፥ ኮነ ፥ ከመ ፥ ጸድቅ ፥ ውእቱ ።
ደግ ፥ ሰው ፥ እንደኾነ ፥ ስለሱ ፥ መስክረለት ።
ወሰማዕቱ ፥ እግዚአብሔር ፥ በተወከፎ ፥ መሥዋዕቱ ።
መሥዋዕቱን ፥ በመቀበል ፥ ምስክሩም ፥ እግዚአብሔር ፥ ነው ፥ (አለ ፥) እግዚአብሔር ፥ መመስከሩ ፥ መሥዋዕቱን ፥ መቀበሉ ፥ ነው ።
ወበእንቲአሁ ፥ መሞቶ ፥ ዓዲ ፥ ተናገረ ፥ (ም ፥ ፲፪ ፥ ፳፬ ።)
ዳግመኛም ፥ ደግ ፥ ሰው ፥ ስለኾነ ፥ ከሞተ ፥ በኋላ ፥ ጌታ ፥ ስለሱ ፥ ተናገረለት ። አንድም ፥ እሱ ፥ ከሞተ ፥ በኋላ ፥ ተናገረ ። (ታሪክ ፥) አዳም ፥ ቃየልንና ፥ ቡድን ፥ አንድ ፥ ጊዜ ፥ አቤልንና ፥ አቅሌማን ፥ አንድ ፥ ጊዜ ፥ መንታ ፥ መንታ ፥ ወለደ ፤ እካለ ፥ መጠን ፥ ባደረሱ ፥ ጊዜ ፥ ያራራትሀ ፥ መስሎት ፥ የአቤልን ፥ መንትያ ፥ አቅሌማን ፤ ቃየል ፥ የቃየልን ፥ መንትያ ፥ ቡድን ፥ አቤል ፥ ያግቡ ፥ ብሎ ፥ አዘዘ ።
ሉድ ፥ ወትመስል ፥ ሔዋንሃ ፥ እማ ፥ ይላታል ፥ ይህ ፥ ቀረሽ ፥ የማትባል ፥ መልከ ፥ መልካም ፥ ናት ።
አቅሌማ ፥ ግን ፥ መልኳ ፥ ምንም ፥ አይል ፥ ዓይነ ፥ መጭማጫ ፥ ጠጉረ ፥ ላሁጫ ፥ ነበረች ።
በዚህ ፥ ቃየል ፥ አዘነ ፥ ያሉለውን ፥ ከፉ ፥ ለኔ ፤ የኔን ፥ መልካም ፥ ለሌላ ፥ ብሎ ። መሥዋዕት ፥ ሠውና መሥዋዕቱን ፥ የተቀበለለት ፥ ያግባት ፥ አላቸው ። ቃየል ፥ መቸስ ፥ እግዚአብሔር ፥ ይበላው ፥ ይመስል ፥ ብሎ ፤ ለታበቍል ፥ ባለው ፥ ቃል ፥ የሰበሰበውን ፥ ሥንዴ ፥ ከነእንክርዳዱ ፥ አምጥቶ ፥ ከደንጊያ ፥ ላይ ፥ አፈሰሰ ፤ ቁራ ፥ መጥቶ ፥ በተንበት ፥ ላዕለ ፥ ቃየልሰ ፥ ወላዕለ ፥ መሥዋዕቱ ፥ ኢነጸረ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲል ። አቤል ፥ ግን ፥ ንጹሕ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንጂ ፥ ንጹሕ ፥ ነገር ፥ ይወዳል ፥ ብሎ ፥ ጥፍሩ ፥ ያል ዘረዘረ ፤ ቀንዱ ፥ ያልከረከረ ፤ ጠጉሩ ፥ ያላረረ ፥ በግ ፥ አምጥቶ ፥ ሠዋ ። አሳት ፥ ከሰማይ ፥ ወርዶ ፥ መሥዋዕቱን ፥ አቃጠለለት ። ላዕለ ፥ አቤልሰ ፥ ወላዕለ ፥ መሥዋዕቱ ፥ ነጸረ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲል ።
በዚህም ፥ አዘነ ፥ አባቱ ፥ ቢያያለ ፥ በኔ ፤ እግዚአብሔር ፥ ቢያደላ ፥ በኔ ፥ ብሎ ፥ እያዘነ ፥ ሲሔድ ፥ ሰይጣን ፥ ተገልጦ ፥ ምንት ፥ ያቴከዘኩ እ አዛል ፥ አለው ። እኔ ፥ አላዝን ፥ ግን ፥ ይዘገ፤ አባቴ ፥ ቢያደላ ፥ በኔ ?

www.zeyeneta.com

አግዚአብሔር ፡ ቢያደላ ፡ በኔ አለው ። አትገለውም ፡ ሁለቱንስ ፡ ማን ፡ ወሰዶብህ ፡ አለው ። ይህም ፡ አለ ? ብሎ ፡ ከዚያ ፡ አብነት ፡ ነሥቶ ።

አንድም ፡ አንዱ ፡ ሰይጣን ፡ ሰው ፡ መስኖ ፤ አንዱ ፡ ሰይጣን ፡ ቁራ ፡ መስሎ ፡ ሰው ፡ የመሰለው ፡ ደን ጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ቢወረውር ፡ ቁራ ፡ የመሰለውን ፡ ሲገለው ፡ አየ ፤ ይህም ፡ አለ ? ብሎ ፡ ከዚያ ፡ አብ ነት ፡ ነሥቶ ።

አንድም ፡ ለታብቅል ፡ ባለው ፡ የሰበሰበውን ፡ ሥንዴ ፡ ከነአንከርዳዱ ፡ አምጥቶ ፡ ከደንጊያ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ። ቁራ ፡ መስሎ ፡ ጮጥቶ ፡ በተነበት ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ቢወረውር ። ገሎታል ። ይህም ፡ አለ ፤ ብሎ ፡ ከዚያ ፡ አብነት ፡ ነሥቶ ።

(ነዓ ፡ እጉየ ፡ ለሐውጸ ፡ ማዕረር) ወንድሚ ፡ አየተጫወትን ፡ ሔደን ፡ ተከሉን ፡ አይተን ፡ አሸቱን ፡ እንኩቶውን ፡ በልተን ፡ አንምጣ ፡ ብሎ ፡ ይዞት ፡ ሔደ ፡ ተክሉን ፡ አይተው ፤ አሸቱን ፡ በልተው ፡ ሲመ ለሱ ፡ ውኃ ፡ አንጠጣ ፡ ብሎ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ አየመራ ፡ ይዞት ፡ ሔዶ ፡ እንዳይጠረጥረው ፡ በፊት ፡ አሱ ተነንብሶ ፡ ጠጣ ፡ ኋላ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ፈንታህን ፡ ጠጣ ፡ አለው ። አጠጣስሁ ፡ ብሎ ፡ ሲነነበስ ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ቢመታው ፡ ገሎታል ።

ከዚያ ፡ ሲመለስ ፡ ጌታ ፡ ብደመና ፡ ተገልጠ ፡ ቃየል ፤ አይቴ ፡ አጉክ ፡ አቤል ፡ አለው ። አነኑ ፡ ዐቃ ቢሁ ፡ ለአቤል ፡ አለው ፤ ለአሙ ፡ ኢኮንክ ፡ ዐቃቢሁ ፡ ስምንት ፡ ቀተልክ ፡ ብሎታልና ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ጌታ ፡ ተናገረለት ፡ አለ ።

አንድም ፡ አዳም ፤ ቃየል ፤ አይቴ ፡ አጉክ ፡ አቤል ፡ አለው ፤ አነኑ ፡ ዐቃቢሁ ፡ ለአቤል ፡ አለው ፡ ይወደው ፡ ነበርና ፡ ጠርጥሮ ፡ አየፈለገ ፡ ቢሔድ ፡ አሠረ ፡ ደም ፡ አገኘ ፡ አሬሳውንም ፡ አገኘ ፡ ይላል ፤ አቤል ፡ ወልድየ ፡ መኑ ፡ ቀተለከ ፡ አለው ፡ ቃየል ፡ አጉየ ፡ ቀተለኒ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯልና ፤ ከሞተ በኋላ ፡ አሱ ፡ ተናገረ ፡ አለ ። መላኩም ፡ ለሄኖክ ፡ ማጎደረ ፡ ነፍሳትን ፡ እያዞረ ፡ ሲያሳየው ፡ አንዲት ፡ ነፍስ ፡ አየተንጠረጠረች ፡ በትካሰስ ፡ ስታሳጣ ፡ አይቶ ፡ ዛ ፡ መንፈስ ፡ ዘሙኑ ፡ አለው ፡ ዘአቤል ፡ ዘቀተሉ አጉኑ ፡ ትስኪ ፡ ኪያሁ ፡ አስክ ፡ አመ ፡ ይትነሥኡ ፡ ደቂቁ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ብሎታ ልና ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አሱ ፡ ተናገረ ፡ አለ ። አንድም ፡ አቤልስ ፡ ይትናገር ፡ በዜና ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወር) ነገሩ ፡ ጽንፍ ፡ አስክ ፡ ጽንፍ ፡ ስለደረስ ፡ አስክ ፡ ምጽአት ፡ ሲነገር ፡ የሚኖር ፡ ስለዘነ ። ቃየል ፡ ማለት ፡ መስተገብረ ፡ ምድር ፤ ጥሪት ፡ ማለት ፡ ነው ። አቤል ፡ ማለት ፡ በማዕ ፡ ደመና ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከኹሉም ፡ ሃይማኖት ፡ የአቤል ፡ ሃይማኖት ፡ ይበልጣል ፡ እሥረጸ ፡ ጽድቀ ፡ እምኅበ ፡ ነፍሱ ፡ እንዲል ፤ ጽጌያት ፡ ከአዕጹቃቸው ፡ እንዲፈነዱ ፡ ያስተማረው ፡ ሳይኖር ፡ ንጹሕ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ ንጹሕ ፡ ነገር ፡ ይወዳል ፡ ብሎ ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረቡ ፡ ነው ።

፭ ፡ በተአምኖ ፡ ፈለሰ ፡ ሄኖክ ፡ ከመ ፡ አይርአዮ ፡ ለሞት ፡ (ዘፍጥ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፱፭ ።)

ሄኖክም ፡ ሞትን ፡ እንዳያየው ፡ በሃይማኖት ፡ ዐረገ ።

ወኢተረክበ ፡ ለሞት ፡ አልተገኘም ።

እስመ ፡ ከበቶ ፡ አግዚአብሔር ።

አግዚአብሔር ፡ ክረዓይት ፡ ክፍዳቸው ፡ ከእጃቸው ፡ ከግብራቸው ፡ ሰውሮታልና ። ወአምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ኅብር ፡ ተከብተ ፡ ሄኖክ ፡ ወአልቦ ፡ ዘአአመረ ፤ በኅበ ፡ ተከብተ ፡ እንዲል ፡ (ሄኖክ) ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ከእግረ ፡ ገነት ፡ ወድቆ ፡ አገልግሎታል ፡ በሰባተኛው ፡ አሳርጎታል ። ይህ ፡ ከኾነ ፡ ወአልቦ ፡ ዘአአመረ ፡ በኅበ ፡ ተከብተ ፡ እንዲል ፡ ማለቱ ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ለዚያው ፡ ለገነት ፡ ምሥራቅ ፡ ምዕራብ ፡ ሰሜን ፡ ደቡብ ፡ አለውና ፡ ተለይቶ ፡ ስላልታወቀ ፡ ነው ። ሄኖክ ፡ ማለት ተሐደሰ ፡ ማለት ነው ። ጥንቱን ፡ እንጂ ፡ ብልየት ፡ ቢኖርበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሐዲስ ፡ ተሐድሶ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አዳም ፡ ዘመብል ፡ ምክ ንያት ፡ ብልየትን ፡ ቢያመጣ ፡ ከመብል ፡ ተከልክሎ ፡ ፡ ተሐድሶን ፡ አምጥቶ ፡ ነበርና ። ከአቤልም ፡ ሃይማኖት ፡ የሄኖክ ፡ ሃይማኖት ፡ ይበልጣል ። አቤል ፡ ዅሉ ፡ ቢያገለግል ፤ ምን ፡ ተጠቀመ ፡ ሞተ ፡ አንጂ ፡ ሳይል ፡ ማገልገሉ ። ሞት ፡ አንዳለ ፡ በአቤል ፤ ትንሣኤ ፡ እንዳለ ፡ በሄኖክ ፡ ታውቋል ፡ በአቤል ፡ አፍርሆ ፡ ወበሄኖክ ፡ አንቅሖ ፡ እንዲል ፡ (አፈወርቅ ፡)

ወዘአንበለ ፡ ያፈልሶ ፡ ሰማዕተ ፡ ኮኖ ፡ ከመ ፡ አሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሳያሳርገውም ፡ አግዚአብሔርን ፡ አንዳገለገለው ፡ መሰከረለት ፡ (አለ) ፡ በማሳረጉ ።

፮ ፡ ወዘአንበለ ፡ ተአምኖሰ ፡ ኢይትከሠል ፡ ያሥምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ኦር ፡ ፭ ፡ ፫ ፡ ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

ያለሃይማኖትስ ፡ አግዚአብሔርን ፡ ሊያገለግሉት ፡ አይቻልም ።

www.zeyeneta.com

ወርቱዕ ፣ ይትአመን ፣ ይቅድም ፣ ዘይበውእ ፣ ኀበ ፣ እግዚአብሔር ።

በሕግ ፣ በአምልኮት ፣ ወደእግዚአብሔር ፣ የሚቀርብ ፣ ሰው ፣ አስቀድሞ ፣ ሊያምን ፣ ይገባል ።

ወያእምር ፣ ከመ ፣ ህሎ ፣ ዘይሜኦሙ ፣ ለእለ ፣ የኀሥሥዎ ። (ዓሞ ፣ ፭ ፣ ፬ ፣ ሚልክ ፣ ፫ ፣ ፲፬ ፣ ፲፯ ።)

በሕግ ፣ በአምልኮት ፣ ለሚሹት ፣ ሰዎች ፣ እግዚአብሔር ፣ የሚሰጣቸው ፣ ዋጋ ፣ እንዳለ ፣ ዋጋቸውን ፣ የሚሰጥ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዳለ ፣ ሊያውቅ ፣ ይገባል ።

፯ ፣ በተአምኖ ፣ እመ ፣ ነገርዎ ፣ ሰናኅ ፣ በእንተ ፣ ዘኢያስተርኢ ፣ ግብር ፣ ዘኅቡዕ ፣ ፈርሀ ፣ (ዘፍጥ ፣ ፮ ፣ ፳ ።)

ኖኅ ፣ የማይታይ ፣ የማየ ፣ ሥራዊን ፣ የማየ ፣ ድምሳሴን ፣ ነገር ፣ በነገሩት ፣ ጊዜ ፣ እምኖ ፣ ፈራ ፣ (አለ፡ አይቀርም ፣ አለ ። (ሐተታ) ፣ ነገርዎ ፣ አለ ፣ ምነው ፣ አንድ ፣ ሱርያል ፣ አይደለምን ፣ ቢሉ ፤ መጽሐፍ ፣ ሰም ፣ ካልጠራ ፣ ማብዛት ፣ ልማዱ ፣ ነውና ፣ ወብዕዕት ፣ አንቲ ፣ እንተ ፣ ተአምኒ ፣ ከመ ፣ ይከውን ፣ ቃል ፣ ዘነገሩኪ ፣ እምኀበ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዳለ ፣ የነገራት ፣ እንድ ፣ ቅዱስ ፣ ገብርኤል ፣ ሲሆን ፣ ሉቃ ፣ ፩ ፣ ፴፭ ። ወፈጸሙ ፣ አፈ ፣ አናብስት ፣ እንዳለ ፣ እንድ ፣ ዳንኤል ፣ ሲሆን ፣ (ዕብ ፣ ፲፩ ፣ ፴፬ ።)

ወገብረ ፣ ንፍቀ ፣ ታቦት ።

ንፋቀ ፣ ታቦት ፣ ሲል ፣ ነው ፣ ጠፈረ ፣ ቤት ፣ ሥጠተ ፣ ልብስ ። እንዳለው ፣ ያለ ፣ ነው ።

በዘያድኅን ፣ ቤቶ ፣ አመ ፣ ተኰነነ ፣ ዓለም ።

ዓለም ፣ በማየ ፣ ሥራዊ ፣ በማየ ፣ ድምሳሴ ፣ በተቀጣ ፣ ጊዜ ፣ ቤተ ፣ ሰብኤን ፣ በሚያድን ፣ ገንዘብ ፣ ያድን ፣ ዘንድ ፣ የሚያድንበት ፣ ክፍል ፣ ክፍል ፣ ያለው ፣ መርከብ ፣ ሥራ ።

ወኮነ ፣ ወራሲሃ ፣ ለጽድቀ ፣ ሃይማኖት ። (ሮሜ ፣ ፫ ፣ ፳፪ ፣ ፭፬ ፣ ፬ ፣ ፭ ።)

አምኖ ፣ ለሚገኘው ፣ ከብር ፣ ባለቤት ፣ ኾነ ፣ ባለቤት ፣ ተባለ ።

፮ ፣ በተአምኖ ፣ ሰምዐ ፣ ዘተሰምየ ፣ አብርሃም ።

አብርሃም ፣ የተባለ ፣ አብራምም ፣ እምኖ ፣ እሽ ፣ በጂ ፣ አለ ።

ወተአዘዘ ፣ ይሑር ፣ ብሔረ ፣ ኀበ ፣ ህለዎ ፣ ይንሣእ ፣ ርስቶ ።

ርስት ፣ አድርጎ ፣ ይወርሰው ፣ ዘንድ ፣ ወዳሰው ፣ ሀገር ፣ ወደከነዓን ፣ ይሔድ ፣ ዘንድ ፣ አብርሃም ፣ አብርሃም ፣ ዓዕ ፣ እምብሔርኹ ፣ ወተፈለጥ ፣ እምአዝማዲክ ፣ ደለውን ፣ እሽ ፣ በጂ ፣ አለ ።

ወሖረ ፣ እንዘ ፣ አኮአምር ፣ ኀበ ፣ ይብጽሕ ። (ዘፍጥ ፣ ፲፪ ፣ ፩-፬ ።)

የሚደርሰበትን ፣ ሳያውቅ ፣ ሔደ ፣ ያወጣኝ ፣ እንጂ ፣ ያገባኛል ፣ ብሎ ።

፱ ፣ በተአምኖ ፣ ፈለሰ ፣ ወነበረ ፣ ብሔረ ፣ ዘአሰፈዎ ፣ ከመ ፣ ነኪር ፣ በኀይመታት ፣ ምስለ ፣ ይስሐቅ ፣ ወያዕቆብ ፣ አለ ፣ እሙንቱ ፣ ይወርስዎ ፣ ለተስፋሁ ። (ዘፍጥ ፣ ፲፪ ፣ ፯ና ፣ ፲፭፡ ፲፱ ።)

ተስፋውን ፣ ከሚወርሱ ፣ ከይስሐቅ ፣ ከያዕቆቡ ፣ ጋራ ፣ ተስፋ ፣ ባናገረልት ፣ ሀገር ፣ በከነዓን ፣ እንደመ ጻተኛ ፣ እንደስደተኛ ፣ ኾኖ ፣ በድንኳን ፣ ኖረ ። (ሐተታ ፡) ምነው ፣ ጠየርገ ፣ ይሴሐቅ ፣ ውስተ ፣ ማኅፈደ ፣ አብርሃም ፣ አውሥ ፣ ድል ፣ የለምን ፣ ቢሉ ፤ ለእንግዳ ፣ መቀበያ ፣ ብሎ ፣ አራት ፣ ደጅ ፣ ያላት ፣ ቤት ፣ ሠርቶ ፣ ነበር ፣ እንጂ ፣ እኖርበታለሁ ፣ ብሎ ፣ ስላልሠራው ።

፲ ፣ እስመ ፣ ኮኑ ፣ ይጸንሑ ፣ ሀገረ ፣ እንተ ፣ ባቲ ፣ መሠረት ፣ እንተ ፣ ኪንያሃ ፣ ወገባሪሃ ፣ እግዚአብሔር ። (ም ፣ ፲፪ ፣ ፳፪ ። ኢሳ ፣ ፴፫ ፣ ፳ ።)

ሠሪዋ ፣ ተጠባቢዋ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሚኾን ፣ ጽንዕ ፣ መሠረት ፣ ያላት ፣ ሀገር ፣ መንግሥተ ፣ ሰማይን ፣ ደጅ ፣ ይጸኑ ፣ ነበርና ።

በተአምኖ ፣ ይእቲኒ ፣ ሣራ ፣ ረከበት ፣ ኃይለ ፣ ታውዕእ ፣ ዘርዐ ፣ እንዘ ፣ መካን ፣ ይእቲ ፣ ጸዘረሥዐት ።

ሣራም ፣ እሷስ ፣ እንኳ ፣ ብእርጅና ፣ ላይ ፣ መካን ፣ ስትኾን ፣ ልጅ ፣ ትወልድ ፣ ዘንድ ፣ ሙቀት ፣ ልም ላሚ ፣ አገኘች ። (ሐተታ ፡) ምነው ፣ እሷስ ፣ ስንኳ ፣ አለ ፣ ቢሉ ፣ ከወንድ ፣ አእምሮ ፣ የሴት ፣ አእምሮ ፣ ያንሳልና ፤ ከዚያውም ፣ ዘንድ ፣ የባልቴት ፤ ብትብሱ ፣ ብትብሱ ፣ ከሷን ፣ ትብሱ ፣ ተው ፣ ተመለሱ ፤ለማለት ።

፲፩ ፣ እስመ ፣ ተአመነቶ ፣ ከመ ፣ ጻድቅ ፣ ዘአሰፈዎ ። (ዘፍጥ ፣ ፳፩ ፣ ፪ ።)

ተስፋውን ፣ የነገራት ፣ እሱ ፣ የተናገረውን ፣ የማያስቀር ፣ እውነተኛ ፣ የባሕርይ ፣ አምላክ ፣ እንደኾነ ፣ አምናዋለችና ። (ሐተታ ፡) ምነው ፣ ወሴሐተት ፣ ሣራ ፣ ይላል ፤ ዓዲያኑ ፣ እግዚእየኒ ፣ ልሕቀ ፣ ብላ ፣ ስታ ፣ የለምን ፣ መቼ ፣ አምናለች ፣ ቢሉ ፤ ሥላሴ ፣ ምንት ፣ አስሐቃ ፣ ለሣራ ፣ ባሉ ፣ ጊዜ ፣ ኢሴሐቁ ፣ ብላ ፣ ከቤተ ፣ ሃይማኖቷ ፣ ጥልቅ ፣ ብላ ፣ ገብታለች ።

www.zeyeneta.com

፲፪ ፡ እንዘ ፡ ከልኤሆሙ ፡ ከመ ፡ በድን ፡ ነፍስቶሙ ። (ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ፤)
ኹለቱም ፡ መቶት ፡ ልምሳሜ ፡ ተለይቷቸው ፡ ሳለ ።
ከመ ፡ ይኩን ፡ ብዝኆሙ ፡ ከመ ፡ ኮከበ፡ ሰማይ ፡ ወከመ ፡ ኖኅ ፡ ባሕር ፡ ዘኢይትኃሰቅ ። (ዘፍጥ ፲ ፡ ፭ ፡ ፩ና ፳፪ ፡ ፲፮ ።)
ብዛታቸው ፡ እንደማይቆጠር ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኮከብ ፡ እንደባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፤ እንድም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኮከብ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ የማይቆጠር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፤ (ሐተታ) ፡ እንደ ፡ ሮሜ ።

፲፫ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ እንዘ ፡ ይትአመኑ ፡ ሞቱ ፡ ወኢረከቡ ፡ ተስፋሆሙ ። (ቍ ፡ ፴፱ ።)
አሊህ ፡ ኹሉ ፡ አምነው ፡ ሞቱ ፡ እንጂ ፡ ተስፋቸውን ፡ አላገኙም ።
ወባሕቱ ፡ እምርሁቅሰ ፡ ርእይዎ ፡ ወተአምኅዎ ። (ዘጎ ፡ ፳፫ ፡ ፲፮ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ ርቀው ፡ አይዋት ፤ እጅ ፡ ነሷት ።
አንድም ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ እንዘ ፡ ይትአመኑ ፡ ሞቱ ።
አሊህ ፡ ኹሉ ፡ አምነው ፡ ሞቱ ።
ወኢረከቡ ፡ ተስፋሆሙ ።
ተስፋቸውን ፡ ግን ፡ አላገኙም ።
ወባሕቱ ፡ እምርኁቅሰ ፡ ርእይዎ ፡ ወተአምኅዎ ።
ርቀው ፡ አዩዋት ፡ እጅ ፡ ነሷት ፡ እንጂ ። (ሐተታ ፡) ነጋድያን ፡ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ሲሔዱ ፡ ኑረው ፡ በሀገራቸው ፡ እንጸር ፡ ሲደርሱ ፡ ሀገራቸውን ፡ አይተው ፡ ሀገራችን ፡ ነሽ ፤ እየንሽ ፡ ኢያሱ ፡ እጅ ፡ እንዲነሱ።
ወእአመሩ ፡ ከመ ፡ ነግድ ፡ ወፈላሲ ፡ እሙንቱ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። (ዘፍጥ ፡ ፳፫ ፡ ፬ ። ፵፯ ፡ ፱ ፡መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፲፫ ።)
በዚህ ፡ ዓለም ፡ መጻተኛ ፡ ስደተኛ ፡ እንደኾኑ ፡ ዐወቁ ።

፲፬ ፡ ወእለ ፡ ከመዝ ፡ ይብሉ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ያሬእዩ ፡ ነገረ ፡ ከመ ፡ ሀገሮሙ ፡ የኀሥሡ ።
ፈላሲ ፡ እነ ፡ ውስተ ፡ ምድርከሙ ። ወነግድ ፡ ከመ ፡ ሑሱ ፡ እበውየ ፡ ያሉ ፡ እለ ፡ አብርሃም ፤ እለ ፡ ዳዊት ፤ ሀገራቸውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንዲሹ ፡ ያስረዳሉ ። እንድም ፡ እሊህ ፡ ሰብአ ፡ ከነዓን ፡ ቤት ፡ ያይሠሩ ፤ ዘር ፡ ያይዘሩ ፡ ሀገራቸውን ፡ ባቢሎንን ፡ መመለስ ፡ አምሯቸዋልን ፡ የሚሉ ፡ ልብአ ፡ ከነዓን ፡ እለ ፡ አብርሃም ፡ ሀገራቸውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንዲሹ ፡ ያስረዳሉ ፡ ይህንም ፡ ሊቁ ፡ ወእአመሩ ፡ ከመ ፡ ነግድ ፡ ወፈላሲ ፡ እሙንቱ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ያሉ ፡ እለ ፡ ጳውሎስ ፡ እለ ፡ አብርሃም ፡ ሀገራቸውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንዲሹ ፡ ያስረዳሉ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

፲፭ ፡ ወሶበሰ ፡ ይፈቅዱ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ እምኔሃ ፡ ወፅኡ ፡ አምተከሀሉሙ ፡ ይግብኡ ፡ ጎቤሃ ።
ወደ ፡ ወጡባትስ ፡ ሀገር ፡ ወደባቢሎን ፡ መመለስ ፡ ኾተው ፡ ቢኾን ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ በተቻላቸው ፡ ነበር ፡ (አለ ፡) ግን ፡ በክለክላቸው ፡ ነበር ኢያቡር ፡ ኹሉ ፡ አልተመለሰምን ።

፲፮ ፡ ወይእዜሰ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ትኄይስ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ በሰማያት ፡ ኮኑ ፡ ይሴፈዉ ።
አንኪያስ ፡ በልዕልና ፡ ያለች ፤ የበለጠች ፡ ሀገር ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጉ ፡ እንደነበረ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ።
ወበእንተዝ ፡ ኢያኀፍር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይትበሀል ፡ አምላኮሙ ፡ (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፪ ፡ ፴፪ ፡)
ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኹሉ ፡ አምላክ ፡ ሲኾን ፡ አምላክ ፡ ሠለስቱ ፡ መባልን ፡ አያፍርም ።
እስመ ፡ አስተዳለወ ፡ ሎሙ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ ተሰፈዎ ። (ቍ ፡ ፲ ።)
ተስፋ ፡ ያደረጓት ፡ ሀገር ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ አዘጋጅቶላቸዋልና ፡ የኹሉ ፡ አምላክ ፡ ሲኾን ፡ አምላክ ፡ ሠለስቱ ፡ መባልን ፡ አያፍርም ።

፲፯ ፡ በተአምኖ ፡ ወሰዶ ፡ አብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ወልዱ ፡ ከመ ፡ ይሠዋ ፡ (ዘፍ ፡ ፳፪ ፡ ፪ ፡ ፲ ።)
አብርሃምም ፡ አምኖ ፡ ልጁን ፡ ይስሐቅን ፡ ይሠዋው ፡ ዘንድ ፡ ወሰደው ፡ አለ ፡ ልመሥዋዕትነት ፡ አቀረበው ፡ አሠ ፡ አመከሮ ።
አብርሃም ፡ አብርም ፡ ሠዕ ፡ ሊተ ፡ ይስሐቅሃ ፡ ወልደከ ፡ ዘታፈቅር ፡ ብሎ ፡ በተፈታተነው ፡ ጊዜ ።

፲፰ ፡ ወአብአ ፡ ዘአሐዱ ፡ ሎቱ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ አሰፈዎ ፡ ወይቤሎ ፡ እምይስሐቅ ፡ ይሰመይ ፡ ለኪ ፡ ዘርዕ ።
(ዘፍ ፡ ፳፩ ፡ ፲፪ ።)
(ወለዶ ፡ ወአብአ) ፡ እምይስሐቅ ፡ ይሰመይ ፡ ለኪ ፡ ዘርዕ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ያናገረለትን ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ለመሥዋዕትነት ፡ አቀረበው ።

www.zeyeneta.com

፲፱ ፡ ተአሚኖ ፡ ከሙ ፡ ይከል ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሥአቶ ፡ እሙታን ። (ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)

አግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ሊያሥነሣለት ፡ እንዲቻለው ፡ አውቆ ፡ ያሥነሣልኛል ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ አበአ ።

ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ተዝካረ ፡ ውእቱ ፡ ዘተውህበ ።

ስለዚህ ፡ ይስሐቅ ፡ መሥዋዕት ፡ ኾኖ ፡ የተሰጠው ፡ አብርሃም ፡ የሃይማኖት ፡ መታሰቢያ ፡ ኾነ ። እንድም ፡ መሥዋዕትነት ፡ የተሰጠው ፡ ይስሐቅ ፡ የአብርሃም ፡ መታሰቢያ ፡ ኾነ ፡ ልጁን ፡ ሠዋ ፡ ተብሎ ። እንድም ፡ ይስሐቅ ፡ መሥዋዕት ፡ ኾኖ ፡ የተሰጠው ፡ አብርሃም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ መታሰቢያ ፡ ኾነ ። እንድም ፡ መሥዋዕትነት ፡ የተሰጠው ፡ ይስሐቅ ፡ የአግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ መታሰቢያ ፡ ኾነ ፡ (ታሪክ ፡) ጌታ ፡ ብየ ፡ ዐርክ ፡ አብርሃም ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ሲያመሰግን ፡ ሰምተው ፡ መላእክት ፡ ወኮኖ ፡ ቃላት ፡ በሰማያት ፡ ይላል ፡ ብፁዕ ፡ አብርሃም ፡ ዐርክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ ፡ አመሰግነዋል ። ሰይጣን ፡ ሰምቶ ፡ ወዳጁ ፡ ትለዋለህ ፡ እንጂ ፡ ካረጀ ፡ በኋላ ፡ የወለደው ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ አለው ፤ ሠዋልኝ ፡ ብትለው ፡ አይሠዋልህም ፡ አለው ።

ጌታም ፡ የአብርሃምን ፡ ጽድቁን ፡ የሰይጣንን ፡ ሐሰቱን ፡ ለመግለጽ ፤ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ሠዕ ፡ ሊተ ፡ ይስሐቀሃ ፡ ወልደከ ፡ ዘታፈቅር ፡ አለው ፤ ለእናቱ ፡ የነገርኋት ፡ እንደኾነ ፡ ታዳክመኛለች ፡ ብሎ ፡ በዋለበት ፡ ኹለቱን ፡ ብላቴኖች ፡ አስከትሎ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ገሠገሠ ። በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ተራራ ፡ ካለበት ፡ ደረሰ ፤ ከሦስቱ ፡ ተራራ ፡ ከመካከለኛው ፡ የብርሃን ፡ አላማ ፡ ተተክሎ ፡ ሲጠቅሰው ፡ አየ ፡ ከዚህ ፡ ሠዋ ፡ እንጂ ፡ ሲለኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ (አነ ፡ ወወልድየ ፡ ሰጊደነ ፡ ንገብኢ ፡) እኔና ፡ ልጄ ፡ ስግደን ፡ እን መለሳለን ፤ እናንተ ፡ ከዚህ ፡ ቆዩ ፡ ብሎ ። ኹለቱን ፡ ብላቴኖች ፡ ከእግረ ፡ ደብር ፡ ትቶ ፡ ወአደሮ ፡ ዕፀ ፡ ለይስሐቅ ፡ ይላል ፡ ለይስሐቅ ፡ ዕንጨቱን ፡ አሸከሞ ፡ እሱ ፡ እሳቱን ፡ ወቅለምቱን ፡ ይዘው ፡ ሲሔዱ ፡ ከግእከለ ፡ ደብር ፡ ደረሱ ። (አባ ፡ እሬሬ ፡ ዕፀ ፡ ወእሳተ ፡ አይቴ ፡ በግዑ ፡ ፡) ሪንጨቱን ፡ እኔ ፡ ይጥለው ፤ እሳቱን ፡ ወቅለምቱን ፡ እንተ ፡ ይዘህል ፤ በጉ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ አለው ። በግዑሰ ፡ ጎበ ፡ ሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ፡ ወልድየ ፡ አለው ።

ከርእሰ ፡ ደብር ፡ ሲደርሱ ፡ ዕንጨቱን ፡ አረበረበ ፡ ደንጊያውን ፡ ጸፈጸፈ ፡ አባቱ ፡ ደንጊያውን ፡ ጸረጸ ፍህ ፤ ዕንጨቱን ፡ ረበረብህ ፤ በጉ ፡ የለም ፤ አኔን ፡ የምትሠዋኝ ፡ መስሎኛልና ፡ ስፈራገጥ ፡ እጅህን ፡ እግ ርህን ፡ እንዳላስቆርጥህ ፡ እጂን ፡ እግሬን ፡ አሰረኝ ፡ አለው ። እጁን ፡ እግሩን ፡ አሰረው ፤ ዓይኔን ፡ ዓይተህ ፡ ራር ተህ ፡ ትተኸኝ ፡ ከፈጣሪህ ፡ እንዳትጣላ ፡ ደፍተህ ፡ አስተኛኝ ፡ አለው ። ወአስከቦ ፡ በከብዱ ፡ ይላል ፤ ደፍቶ ፡ አስተኛው ። ሾተሉን ፡ ከአንገቱ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ አስባለሁ ፡ ሲል ፡ ከወደኋላ ፡ ተው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማ ። ዙሮ ፡ ቢያይ ፡ ነጭ ፡ በግ ፡ በዕፀ ፡ ሳቤቅ ፡ ታስር ፡ አየ ። ይህን ፡ ሠዋ ፡ ሲለኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይስሐቅን ፡ ፈቶ ፡ በጉን ፡ ሠውቷል ።

ምሳሌ ፡ ነው ፡ ይስሐቅ ፡ የዓለሙ ፤ በግዕ ፡ የወልዱ ፡ እግዚአብሔር ፤ ይስሐቅ ፡ በበጉ ፡ መሥዋዕትነት ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ዓለሙም ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕትነት ፡ ለመዳኑ ፡ ምሳሌ ። እንድም ፡ በግዕ ፡ የትስ ብእት ፤ ይስሐቅ ፡ የመለኮት ፤ ወቅለምት ፡ ከበግዕ ፡ እንጂ ፡ ከይስሐቅ ፡ እንዳልደረሰ ፤ ሕማም ፡ ሞትም ፡ በስ ውነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመለኮቱ ፡ የለበትምና ፤ ኹለቱ ፡ ብላቴኖች ፡ የኹለቱ ፡ ወንበዶች ፡ የፈያታዊ ፡ ዘየማ ንና ፡ የፈያታዊ ፡ ዘጸጋም ። አሳት ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ወቅለምት ፡ የሥልጣን ፡ እግዚአብሔር ፤ ይስሐቅ ፡ ከአ ግረ ፡ ደብር ፡ ዕንጨቱን ፡ ተሸክሞ ፡ መሔዱ ፤ ጌታ ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፡ ከሊቶስጥራ ፡ አስከ ፡ ቀራንዮ ፡ ለመሔዱ ፡ ምሳሌ ። በጉ ፡ ከአብርሃም ፡ መንጋ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤ ጌታ ፡ ከቤተ ፡ አብርሃም ፡ መወለዱን ፡ ያጠይቃል ። አልታወቀም ፡ ቢሉ ፡ ቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡ አለመመርመሩን ፡ ያጠይቃል ።

አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ በሕሊና ፡ በሠዋው ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ተነሥቷል ። ሕሊና ፡ አብርሃም ፡ የመ ታብር ፡ ይስሐቅ ፡ የጌታ ፤ ጌታ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ የመነሣቱ ፡ ምሳሌ ።

ያዕቆብ ፡ በእንቀጸ ፡ አሚን ፡ አኮኑ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ጸድቀ ፡ ዖበ ፡ እዕረገ ፤ ለይስሐቅ ፡ ወልዱ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ብሎ ፡ ምግባሩን ፡ መስክሮለታል ፤ ከዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በተአምኖ ፡ አብ ርሃም ፡ ወሰዶ ፡ ለይስሐቅ ፡ ወልዱ ፡ ብሎ ፡ ሃይማኖቱን ፡ መስክረለት ።

፳ ፡ በተአምኖ ፡ በዘይከውን ፡ ባረከሙ ፡ ይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለዔሳው ፡ በእንተ ፡ ዘህለምሙ ፡ ይርከቡ ። (ዘፍጥ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ።)

(በተአምኖ ፡ ባረከሙ ፡ ፡) ይሰሐቅ ፡ ኋላ ፡ ያገኙት ፡ ዘንድ ፡ ስላሉት ፡ የሚደረገውን ፡ ዐውቆ ፡ በሃይማኖት ፡ ያዕቆብንና ፡ ኤሳውን ፡ ባረካቸው ።

www.zeyeneta.com

(ታሪክ ፡) ወኮነ ፡ ይስሐቅ ፡ ያፈቅሮ ፡ ለዔሳው ፡ አስመ ፡ ዘውእቱ ፡ ነዐወ ፡ ይሴሰይ ፡ ወያዕቆብሰ ፡ ንጹሕ ፡ እምዝንቱ ፡ ይላል ።

ዔሳው ፡ ያውሬ ፡ ሥጋ ፡ እያደነ ፡ እያበላው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይወደው ፡ ነበር ።

ለአበው ፡ ዕለተ ፡ በረከት ፡ አላቸው ፤ ወልድየ ፡ አምቅድመ ፡ እሙት ፡ ትባርከ ፡ ነፍስየ ።

ልጄ ፡ ዛሬ ፡ በረከት ፡ የማድልባት ፡ ቀን ፡ ናትና ፡ እንደ ፡ ምወደው ፡ አድርገህ ፡ አብልተኸኝ ፡ ሳልሞት ፡ ልመርቅህ ፡ አለው ። እሽ ፡ ብሎ ፡ በችኩል ፡ አደን ፡ ሲሔድ ፡ የሚለብሳት ፡ ልብስ ፡ ነበረችው ፡ ዘንግቷት ፡ ሔደ።

ርብቃ ፡ ይህን ፡ ሰምታ ፡ ያዕቆብን ፡ ትወደው ፡ ነበርና ፡ ልጄ ፡ ዛሬ ፡ አባትህ ፡ በረከት ፡ የሚያድልባት ፡ ቀን ፡ ናትና ፡ ኹለት ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ አምጥተህ ፡ ሰጥተኸኝ ፡ እንደሚወደው ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቻህ ፡ አብልተኸው ፡ ተመረቅ ፡ አለችው ።

እናቴ ፡ መክረልት ፡ ሲሹ ፡ መቅሠፍት ፡ እንዲሉ ፡ በረከቱን ፡ ስሻ ፡ መርገሙ ፡ ቢደርስብኝሳ ፤ ወን ድሜ ፡ ዔሳው ፡ ጸጓር ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ጸጉር ፡ የለኝ ፡ በጾ ፡ ዳሶ ፡ አይቶ ፡ ዛሬስ ፡ ዓይኔ ፡ ጠፋና ፡ ዘበተብኝ ፡ ብሎ ፡ ይረግመኝ ፡ የለምን ፡ አላት ። (ወልድየ ፡ መርገምከሰ ፡ ይኩን ፡ ላዕሌየ ፡) መርገምህ ፡ በኔ ፡ ይኹን ፡ አሰችው ። አምጥቶ ፡ ሰጥታት ፡ እንደ ፤ ሚወደው ፡ አድርጋ ፡ አዘጋጅታ ፡ የበጉን ፡ ጠጉር ፡ በደም ፡ ከፊቱ ፤ ከደረቱ ፡ ከት ከሻው ፡ አጣብቃ ፡ ዔሳው ፡ አደን ፡ ሲሔድ ፡ የሚሰብላትን ፡ ልብስ ፡ አልብሳ ፡ ያነን ፡ አስይዛ ፡ ሰደደችው ። አባቴ ፡ እንደምትወደው ፡ አድርጌ ፡ አምጥቼልሃሰሁ ፡ ተነሣ ፡ በልተህ ፡ መርቀኝ ፡ አለው ። አንተ ፡ ማነህ ፡ አለው ። አነ ፡ ዔሳው ፡ ወልድከ ፡ ዘበኩርከ ፡ አለው ። ፈጠንህሳ ፡ አለው ። ፈጣሪህ ፡ እንጂ ፡ ከመነሻ ፡ ላይ ፡ ሰጠኝ ፡ አለው ።

(እስኩ ፡ ቅረበኒ ፡) እስኪ ፡ ቅረበኝ ፡ አለው ። በጾ ፡ ዳሶ ፡ አይቶ ፡ ጸጉርከሰ ፡ ዘዔሳው ፡ ወቃልከሰ ፡ ዘያዕቆብ ፡ አለው ፤ እኔ ፡ ምን ፡ እዳዬ ፡ ኹላችሁም ፡ ልጆቼ ፡ ብሎ ፡ በልቶ ፡ ይመርቀዋል ። ናሁ ፡ ጼና ፡ አል ባሲሁ ፡ ለወልድየ ፡ ጥቀ ፡ ጥንቁቀ ፡ ከመ ፡ ጼና ፡ ገዳም ፡ ዘባረከ ፡ እግዚአብሔር ። አምጠሉ ፡ ለሰማይ ፡ ወእምስፍሓ ፡ ለምድር ፡ ይኩን ፡ በረከትከ ፡ ኩኖ ፡ እግዚአ ፡ ለእጉከ ፡ ብሎታል ።

ያዕቆብ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ዔሳው ፡ መጥቶ ፡ አባቴ ፡ እንደምትወደው ፡ አድርጌ ፡ አምጥቼልሃለሁ ፡ ተነሣ ፡ በልተህ ፡ መርቀኝ ፡ አለው ። አንተ ፡ ማነህ ፡ አለው ። አነ ፡ ዔሳው ፡ ወልድከ ፡ ዘበኩርከ ፡ አለው ። አሁን ፡ እንደምወደው ፡ አድርጎ ፡ አብልቶኝ ፡ የመረቅሁት ፡ ማነው ፡ (ቡሩክ ፡ ብእሲሁ ፡) እንዲያውም ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በበረከት ፡ ላይ ፡ በረከት ፡ ይጨምርለታል ። ያዕቆብ ፡ እጉከ ፡ ነሥአ ፡ በረከተከ ፡ በጕሳሉት ፡ ብሎታል ።

በአማን ፡ ተሰምየ ፡ ያዕቆብ ፡ ክልኤ ፡ ጊዜ ፡ አዕቀጸኒ ፤ ቀዳሚ ፡ ብኵርናየ ፡ ወዳግም ፡ በረከትየ ፡ እያለ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመረ ። አሑቲኑ ፡ አባ ፡ በረከትከ ፡ ወአልቦኑ ፡ ዘአትረፍከ ፡ ሊተ ፡ አለው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጌታህ ፡ አደርጌዋለሁ ፡ ምን ፡ ይኾናል ፡ (እስኩ ፡ ቅረበኒ ፡) እስኪ ፡ ቅረበኝ ፡ ብሎ ፡ ናሁ ፡ ጼና ፡ አልባሲሁ ፡ ለወልድየ ፡ ጥቀ ፡ ጥንቁቀ ፡ ከመ ፡ ጼና ፡ ገዳም ፡ ዘባረከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምጠሉ ፡ ለሰማይ ፡ ወአምስፍሓ ፡ ለምድር ፡ ይኩን ፡ በረከትከ ፡ ሕየው ፡ በቀስትከ ፡ ወለአመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ታቅልል ፡ ጾሮ ፡ አድንን ፡ ርእስከ ፡ (ተገዛ ፡) ብሎታል ። ምሳሌ ፡ ነው ፡ ዔሳው ፡ የምእመናን ፡ አስራኤል ፤ ያዕቆብ ፡ የምእመናን ፡ አሕዛብ ፤ በአስራኤል ፡ ተሰፋ ፡ አሕዛብ ፡ ለመግባታቸው ፡ ምሳሌ ፡ እንከሰ ፡ ብኵርና ፡ ለነ ፡ ወአኮ ፡ ለአይሁድ ፡ እንዲል ፡ (ሃይ ፡ አበ) ፳፭ ፡ በተአምኖ ፡ አመ ፡ ይመውት ፡ ያዕቆብ ፡ ባረኮሙ ፡ ለደቂቀ ፡ ዮሴፍ ፡ ለለአሐዱ ፡ (ዘፍ ፡ ፵፰ ፡ ፲፭ ።)

ያዕቆብም ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ የዮሴፍን ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ ባረካቸው ።

ወሰገደ ፡ ውስተ ፡ ከተማ ፡ በትሩ ፡ (ዘፍ ፡ ፵፯ ፡ ፴፩ ።)

በበርሸሙ ፡ በመቋሚያ ፡ ሰይፉ ፤ ባውራጣቱ ፤ ባልጋው ፡ ሸንኮር ፡ ሰገደ ። ታሪክ ፡ ወደከመ ፡ ያዕቆብ ፡ አቡከ ፡ ብለው ፡ ለዮሴፍ ፡ ነገሩት ፡ ሳይሞት ፡ ልጆቼን ፡ ላስባርክ ፡ ብሎ ፡ ይዞ ፡ ሔደ ።ልጅህ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ተጽናንቶ ፡ ሰግዶ ፡ ተቀመጠ ። ምሳሌ ፡ ነው ። ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ያዕቆብ ፡ የዓለሙ ፤ ልጅህ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ተጸናንቶ ፡ ሰግዶ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ዓለሙም ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ ጽንዐ ፡ ነፍስ ፡ አግኝቶ ፡ ጸንቶ ፡ ሰመነግቷቱ ፡ ምሳሌ ። ወአቀ ፦ ለኤፍሬም ፡ በየማኑ ፡ ኀበ ፡ ጸጋሙ ፡ አስራኤል ፡ ወለምናሴ ፡ አቀሞ ፡ በጸጋሙ ፡ ኀበ ፡ የማነ ፡ አስራኤል ፡ ይላል ። ኤፍሬምን ፡ ዐሰ ፡ ቀኝ ፡ በያዕቆብ ፡ ግራ ፤ ምናሴን ፡ በሰ ፡ ግራ ፡ በያዕቆብ ፡ ቀኝ ፡ አቁሟቸዋል። ወአስተጋለፈ ፡ እዴሁ ፡ ይላል ፡ እጁን ፡ አመሳቅሎ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ከኤፍሬም ፡ ላይ ፡ ጫነ ። አባቴ ፡ በዙሩ ፡ ልጄ ፡ ምናሴ ፡ ነውና ፡ ደህና ፡ አድርገህ ፡ ባርከው ፡ አለው ። አአምር ፡ ወልድየ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ይከውን ፡ ሕዝበ ፡ ወቢየ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘይንእስ ፡ የዓብዮ ፡ ብሎታል ።

ይከውን ፡ ሕዝቤ ፡ ወቢየ ፡ ማለቱ ፡ እለ ፡ ጌዴዎን ፡ እለ ፡ የፍታሔ ፡ ከምናሴ ፡ ይወለዳሉና ። ዘይንእስ ፡ የዐብዮ ፡ ማለቱ ፡ መስፍኑ ፡ ኢያሱ ፤ ኢየርብዓም ፡ ንጉሡ ፡ ከኤፍሬም ፡ ይወለዳሉና ፤ ምሳሌ ፡ ያዕቆብ ፡

www.zeyeneta.com

የእግዚአብሔር ፡ ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ኤፍሬም ፡ የምእመናን ፡ አሕዛብ ፤ ምናሴ ፡ የምእመናን ፡ እስራኤል ፤ ማቅ ረብ ፡ የወልድ ፤ ማከበር ፡ የአብ ፡ አድሎ ፡ ሰጥቶ ፡ መናገር ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አንቺ ፡ ኹሉም በኾሉ ፡ አለ ።

፭፻፮ ፡ በተአምኖ ፡ አመ ፡ ይመውት ፡ ዮሴፍ ፡ ተዝከረ ፡ በእንተ ፡ ፀአቶሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ ወአዘዘ ፡ በእንተ ፡ አዕፅምቲሁ ፡ (ዘፍ ፡ ፶ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮)

(በተአምኖ ፡ ተዝከረ ፡) ዮሴፍም ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ፀአት ፡ እንዳላቸው ፡ ዐውቆ እግዚአብሔር ፡ በጕብኝቸው ፡ ጊዜ ፡ ዕፅሜን ፡ ይዛችሁ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡ (አመ ፡ ሐውጸ ፡ ይሔ ውጸከሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትጎድን ፡ ሥጋየ ፡ ዲበ ፡ ዛ ፡ ምድር ፡) ብሎ ። (ሐተታ ፡) አሁን ፡ ዮሴፍን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ በግብጽ ፡ ቢቀር ፡ የሚረከስ ፤ በከነዓን ፡ ቢቀበር ፡ የሚቀደስ ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ፤ ለጊዜው ፡ ፀአት ፡ እንደአላቸው ፡ ለማጠየቅ ፤ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ግብጽ ፡ የመቃብር ፤ ከነዓን ፡ የትንሣኤ ፡ ግብጽ ፡ የገሃነም ፡ ከነዓን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አምሳል ፡ ናትና ።

፭፻፯ ፡ በተአምኖ ፡ ተወሊዶ ፡ ሙሴ ፡ ጎብዕዎ ፡ ሠለስተ ፡ አውራኀ ፡ በቤተ ፡ አበዊሁ ፡

(በተአምኖ ፡ ጎብዕዎ ፡) ሙሴም ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ በናቱ ፡ ባባቱ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሰውረው ፡ እናቱ ፤ እናት ፡ አባቱ ። አንድም ፤ መወለዳት ፡ ናቸው ።

እስመ ፡ ርእይዎ ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ።

በጕ ፡ ብላቴና ፡ እንደኾነ ፡ አይተውታልና ። ለዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ይክድኖ ፡ ሞገስ ፡ እምንእሱ ። ወተሰብሐ ፡ ገጹ ፡ ለሙሴ ፡ እንዲል ፡ ዘፀአ ፡ ፪፡፪ ፡ ፍቡይ ፡ ፡በፊቱ ፡ ብርሃን ፡ ተሰሉበት ፡ ተወልዷል ።

ወኢፈርሁ ፡ ትእዛዘ ፡ ንጉሥ ፡ (ዘፀአ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ ፳፯ና ፡ ፪ ፡ ፪ ፡)

ከፍ ፡ ብሎ ፡ አንገታችንን ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ባታችንን ፡ ይቀጣናል ፡ ሳይሉ ፡ ሰውረው ፡ አኖሩት ። (ታሪክ) ፍሐ ፤ ሲፓራ ፡ የሚባሉ ፡ ኹለት ፡ ዐቀብተ ፡ መወልዳት ፡ ሹመዋል ። መልኩን ፡ አይተው ፡ ወሰሐቦን ፡ አርአያሁ ፡ መንገለ ፡ አሚን ፡ ይላል ፡ ለዝለ ፡ ዘፈጠሮ ፡ ይቅትሉ ፡ ብለው ፡ ትተውታል ።

፭፻፰ ፡ በተአምኖ ፡ ልሂቆ ፡ ሙሴ ፡ ከሕደ ፡ ከመ ፡ አይበልዎ ፡ ወልደ ፡ ወለተ ፡ ፈርዖን ፡ (ዘፀአ ፡ ፪፡ ፲-፲፪)

(በተአምኖ ፡ ከህደ ፡)ሙሴም ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ ወልደ ፡ ወለተ ፡ ፈርዖን ፡ ነህ ፡ ቢሉት ፡ የፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ኾኖ ፡ ከመደለት ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ እንዲበልጥ ፡ አምኖ ፡ አይደለኹም ፡ አለ ።

፭፻፭ ፡ ወአብደረ ፡ ይሕምም ፡ ምስለ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምይደለው ፡ ለሰዓት ፡ ወይኩኖ ፡ ኃጢአተ ።

ከግብጻውያን ፡ ጋራ ፡ ጥቂት ፡ ሰዓት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሲያደርግና ፡ ያውም ፡ ዕዳ ፡ ሲኾንበት ፤ ከሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ መቀበልን ፡ ወደደ ።

፭፻፱ ፡ እስመ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ የዐቢ ፡ ትዕይርተ ፡ መስቀሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ እምዙሉ ፡ መዛግብቲሆሙ ፡ ለግብጽ ፡ (ም ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፡ ዘፀ ፡ ፬፡ ፭፻፬ ። ም ፡ ፲ ፡ ፴፭ ።)

ከግብጻውያን ፡ ከዕንቋቸው ፡ ከወርቃቸው ፡ ይልቅ ፡ የክርስቶስን ፡ መከራ ፡ መስቀል ፡ መቀበል ፡ እንዲበልጥ ፡ ስላወቀ ፤ ዐውቆ ፡ ከሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ መቀበልን ፡ ወዷልና ።

፭፻፲ ፡ በተአምኖ ፡ ኀደረ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ኢፈርሆ ፡ መዓተ ፡ ንጉሥ ፡ (ዘፀአ ፡ ፲፡ ፲፩ ፡ ፭፻፭ ።)

እሱን ፡ ሲሻ ፡ ያላከበት ፡ ንጉሥ ፡ ያላማለው ፡ መኰንን ፡ እንደሌለ ፡ ሲያውቅ ፡ ሳይፈር ፡ ሳያፍር ፡ በግብጽ ፡ ኖረ ።

እስመ ፡ አብደረ ፡ ይፍርሆ ፡ ለዘኢያስተርኢ ፡ እምዘ ፡ ይሬኢ ። (ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፮)

ከሚያየው ፡ ከፈርዖን ፡ ይልቅ ፡ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊፈራ ፡ ወዷልና ።

ጸኒሆ ፡ ዕጌቶ ።

ዋጋዬን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፤ ዋጋዬ ፡ ይቆየኛል ፡ ብሎ ።

፭፻፲፩ ፡ በተአምኖ ፡ ግብረ ፡ ፍሥሐ ።

በሃይማኖት ፡ በጉን ፡ ሠዋ ።

ወነዝኀ ፡ ደመ ፡ ከመ ፡ አያጥፍእ ፡ ሎሙ ፡ በኵሮሙ ፡ ብድብድ ፡ (ዘፀአ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።)

የእስራኤልን ፡ በዙር ፡ በኵሩን ፡ ቸነፈር ፡ እንዳያጠፋ ፡ ደሙን ፡ ለመቃን ፡ ለመድረኩ ፡ ረጨ ፡ (ታሪክ)

www.zeyeneta.com

ጌታ ፡ ሙሴን ፡ በግብጽ ፤ ሞተ ፡ በሰር ፡ አምጥቼ ፡ ከግብጽ ፡ አወጣችኋለሁ ፡ አለው ። ይህማ ፡ ከኾነ ፡ የእስራኤልስ ፡ በሰር ፡ በሰሩ ፡ ሊያልቅ ፡ አይደለም ፡ አለው ። ይህስ ፡ እንዳይኾን ፡ ዓመት ፡ የኾነው ፡ በግ፡ ቀንዱ ፡ ያልከረከረ ፤ ጥፍሩ ፤ ያልዘረዘረ ፤ ጠጉሩ ፤ ያላረረ ፡ ከቤቱ ፡ ያለው ፡ ከመንጋው ፤ የሌለው ፡ ከገበያ፡ ገዝቶ ፡ የሚያዝያ ፡ ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ ባደረገች ፡ በአሥር ፡ አስራችሁ ፡ ባሥራአራት ፡ ሠውት ፤ ስትሠውትም ፡ ከመዓልቱ ፡ አንዱን ፡ ሰዓት ፡ ነሥታችሁ ፤ ያነን ፡ ከሦስት ፡ ከፍላችሁ ፤ በኩለት ፡ እጅ ፡ ብርሃን። ከሌቱም ፡ አንዱን ፡ ሰዓት ፡ ነሥታችሁ ፡ ያነን ፡ ከሦስት ፡ ከፍላችሁ ፡ ባንድ ፡ እጅ ፡ ጨለማ ፡ ሠውት ። ደሙን ፤ ለመቃን ፡ ለመድረኩ ፡ እርጩት ። ያንን ፡ እያየ ፡ ሞተ ፡ በሰር ፡ ይከለከልላችኋል ።

ሐምሳ ፡ብጎዕ ፡ አረፍርፉበት ፡ ብሏቸዋል ። አራት ፡ ነገር ፡ ያመጣሉ ፡ እዘ ፡ ከል ፤ ዝፍተ፡ ወይን ፤ የሥንዴ ፡ ቅርጣን ፡ የበለስ ፡ ቅርጣን ፤ ስትበሉትም ፡ እንድትፈጽት ፡ ሰባት ፡ ዐሥር ፡ እሥራኹለት ፡ እየኾናችሁ ፡ ብሉት ። ያለው ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ የሌለው ፡ ጐረቤቱን ፡ እየያዘ ፡ ይብላ ።

ብርንዶውን ፡ አትብሉ ፤ ጥብሱን ፡ ብሉ ፤ ዝግኑን ፡ ቅቅሉን ፡ አትብሉ ፡ አትርፋችሁ ፡ አታሳድሩ ፤ የተረፈውን ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉ ፤ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ አትውሰዱ ፤ አጥንቱን ፡ አትሰብሩ ።

ስትበሉትም ፡ ኮፈታ ችሁን ፡ ደፍታችሁ ፡ በሎታችሁን ፡ ይዛችሁ ፡ ዝናራችሁን ፡ ታጥቃችሁ ፤ ጫማ ችሁን ፡ አድርጋችሁ ፡ እየቸኮላችሁ ፡ ብሉት ፡ ብሏቸዋል ።

ምሳሌ ፡ ነው ፡ በግዕ ፡ የጌታ ፤ ዓመት ፡ የኾነው ፡ በግ ፡ ወርድ ፡ እንጂ ፡ ቁመት ፡ አይጨምርም ፤ ጌታም ፡ መሠዋቱ ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡ ነውና ፤ ቀንዱ ፡ ያልከረከረ ፤ ጥፍሩ ፡ ያልዘረዘረ ፡ ጠጉሩ ፡ ያላረረ ፤ አለ ፡ በሐልዮ ፡ በነቢብ ፤ በገቢር ፡ ምክንያት ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ሲል ፡ ነው ። ያለው ፡ ከመንጋው ፤ የሌለው ፡ ከገበያ ፤ ገዝቶ ፡ (አለ ፡) የጌታ ፡ ትውልዱ ፡ ከሕዝብም ፡ ከአሕዛብም ፡ ነውና ።

የሚያዝያ ፡ ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ ባደረገች ፡ ባሥር ፡ አስራችሁ ፡ ባሥራ ፡ አራት ፡ ሰዉ ፡ (አለ) ፡ የጌታ ፡ ምክረ ፡ ሞቱ ፡ ባሥር ፡ ተጀምሮ ፡ ባሥራ ፡ አራት ፡ ተፈጽሟልና ።

ስትበሉትም ፡ ከመዓልቱ ፡ አንዱን ፡ ሰዓት ፡ ነሥታችሁ ፡ ያነን ፡ ከሦስት ፡ ከፍላችሁ ፤ አንዱን ፡ እጅ ፡ ትታችሁ ፡ በኩሌቱ ፡ እጅ ፡ ብርሃን ፡ ከሌሊቱ ፡ አንዱን ፡ ሰዓት ፡ ነሥታችሁ ፡ ያነን ፡ ከሦስት ፡ ከፍሳችሁ ፡ ኩለቱን ፡ እጅ ፡ ትታችሁ ፡ ባንድ ፡ ጨለማ ፡ ሠዉት ፡ አለ ። የጌታ ፡ ነገረ ፡ ሞቱ ፡ በኩለት ፡ እጅ ፡ ብርሃን ፡ ባንድ ፡ እጅ ፡ ጨለማ ፡ ተፈጽሟል ፤ ዓርብ ፡ ከነግህ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ብርሃን ፡ ኾኗል ፤ በቀትር ፡ ጨለማ ፡ ኾኗል ። ወፍኖ ፡ ሠርክ ፡ ይበርህ ፡ ብርሃን ፡ መዓልት ፡ እንዲል ፡ ዘካር ፡ ፲፬ ፡ ፯ ። በሠርክ ፡ ብርሃን ፡ ኾኗል ።

ደሙን ፡ ለመቃን ፡ ለመድረኩ ፡ እርጩት ። ያንን ፡ እያየ ፡ ሞተ ፡ በሰር ፡ ይከለከልላችኋል ፡ (አለ ፡) ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ከሚቀበሉ ፡ ምእመናን ፡ አጋንንት ፡ አይደርሱምና ።

ሐምሳ ፡ ብጎዕ ፡ አረፍርፉበት ፡ (አለ ፡) ለጊዜው ፡ የሚበሉት ፡ ቂጣ ፡ ነውና ፡ ከሆዳቸው ፡ እንዲያጠፋላቸው ፡ ነው ፤ ፍጻሜው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ የሚገባ ፡ የበሉት ፡ ከሆድ ፡ ሲጠፋ ፡ ለአፍ ፡ ምሪት ፡ ሲሰማው ፡ ነውና ።

ሰባት፤ ዐሥር ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፤ እየኾናችሁ ፡ ብሉት ፡ አለ ፡ ሰባት ፡ በነዚያ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ በፍጹም ፡ ቍጥር ፤ አስመ ፡ ጉልቍ ፡ ፯ ፡ ኀበ ፡ ዕብራውያን ፡ ፍጹም ፡ ውአቱ ፡ እንዲል ፡ ዐሥርም ፡ በኛ ፡ ፍጹም ፡ ነውና ፡ የሚቀበለውን ፡ ኹሉ ፡ በፍጹም ፡ ቆጥሮ ፡ ነው ፤ አስራኹለትም ፡ (አለ ፡) ለጊዜው ፡ የሚቀበሉት ፡ ዐሥራኹለቱ ፡ ናቸውና ።

ብርንዶውን ፡ አትብሉ ፡ (አለ ፡) የዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ አትበሉ ፡ ሲል ።

ዝግኑን ፡ ቅቅሉን ፡ አትብሉ ፡ (አለ ፡) ሙስና ፡ መቃብር ፡ አገኘው ፡ አትበሉ ፡ ሲል ።

ጥብሱን ፤ ብሉ ፡ (አለ ፡) ነፍስ ፡ የተለየው ፡ መለኮት ፡ የተዋሐደው ፡ ነው ፡ በሉ ፡ ሲል ።

አትርፋችሁ ፡ አታሳድሩ ፡ (አለ ፡) ካሣ ፡ ሳይፈጸምለት ፡ አደረ ፡ አትበሉ ፡ ሲል ።

የተረፈውንም ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉ ፡ (አለ ፡) ምሥጢር ፡ መርምራችሁ ፡ በተረፈው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያውቃል ፡ በሉ ፡ ሲል ።

ካንዱ ፡ ወደአንዱ ፡ አትውሰዱ ፡ (አለ ፡) ለጊዜው ፡ መካነ ፡ ሞቱ ፡ ለመካነ ፡ መቃብሩ ፤ ቅርብ ፡ ነውና ። ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ካንዱ ፡ ቤተ ፡ እግዘ አብሔር ፡ ሠዉቶ ፡ ወደአንዱ ፡ ቤተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መውሰድ ፡ አይገባም ፡ ሲል ፡ ነው ።

አጥንቱን ፡ አትሰብሩ ፡ (አለ ፡) ለጊዜው ፡ ግብጻውያን ፡ ሲጠፉ ፡ እስራኤል ፡ ላለመጥፋታቸው ፡ ነው ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ኃጥአን ፡ ሲጎዱ ፡ ጻድቃን ፡ ላለመጎዳታቸው ፡ ምሳሌ ።

www.zeyeneta.com

በቁሙም ፡ የኹለቱን ፡ ወንበዶች ፡ ሞን ፡ ሞናቸውን ፡ ሲሰብሩ ፡ አሱን ፡ አይሰብሩትምና ፤ እንደአር
የስም ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ አትበሉ ፡ ሲል ።
ስትበሉም ፡ ኩፈታችሁን ፡ ደፍታችሁ ፡ (አሰ ፡) አክሊለ ፡ ምኩን ፡ አያሰባችሁ ።
በሎታችሁን ፡ ይዛችሁ ፡ (አሰ ፡) ነገረ ፡ መስቀሉን ፡ አያሰባችሁ ።
ዝናራችሁን ፡ ታጥቃችሁ ፡ አለ ፡ ንጽሕናን ፡ ይዛችሁ ።
ጫማችሁን ፡ አዝባችሁ ፡ (አሰ ፡) ምግባረ ፡ ወንጌልን ፡ ይዛችሁ ፡ ተስዕነኒ ፡ ኃይለ ፡ ወንጌል ፡ ዘበሰ
ላም ፡ እንዲል ፡ (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ።)
እየቸኮሳችሁ ፡ ብሉት ፡ (አሰ ፡) ለጊዜው ፡ ዘእት ፡ እንዳሳቸው ፡ ሰግጠየቅ ፡ ነው ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡
ዕለተ ፡ ሞታችሁን ፡ እያሰባችሁ ፡ በትሕትና ፡ ተቀበሉት ፡ ግለቱ ፡ ነው ።
ሳዊሮስ ፡ መስሎታል ፡ ብሎ ፤ ራሱ ፡ የጌታ ፤ ቀንዶቹ ፡ የሥልጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓይናቹ ፡ የነቢያት ፤
ጉሮዎቹ ፡ የጴጥሮስ ፡ የጳውሎስ ፡ ቀኝ ፡ እግሩ ፡ የሐዋርያት ፤ ግራ ፡ እግሩ ፡ የሰብአ ፡ አርዴእት ፤ ቀኝ ፡ ወርቹ ፡
የአምሰቱ ፡ ምእት ፡ ቢጽ ፤ ግራ ፡ ወርቹ ፡ የሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ምሳሌ ፤ ለምለም ፡ ጉበቱ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ኩላሊቱ ፡
የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፤ ንዋየ ፡ ውስጡ ፡ የመጻሕፍት ፡ አነዳው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ጠጉሩ ፡ የሀ
ብቱ ፡ ብዛት ፤ አስትንፋሱ ፡ የሙቀተ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ሳቱ ፡ የደኃርት ፡ ጻድቃን ፡ ምሳሌ ።

ፀፀ ፡ በተአምኖ ፡ ዐደውዋ ፡ ሰባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ከመ ፡ ዘውስተ ፡ ምድር ፡ ይቡስ ። (ዘጸአ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ።)
እስራኤል ፡ በሃይማኖት ፡ እንደየብስ ፡ ኾነላቸው ፡ በየብስ ፡ ኤርትራን ፡ ተሻገሩ ።
መኮነቶሙ ፡ መክራ ፡ ለግብጽ ።
በግብጻውያን ፡ ግን ፡ ጥፋት ፡ ሆነችባቸው ።
ተሠጢዮሙ ።
በሰጠሙ ፡ ጊዜ ፡ እንደሰጠሙ ፡ ሊቀሩ ።

ፀፂ ፡ በተአምኖ ፡ ወድቀ ፡ ዐረፋቲሃ ፡ ሰኢያሪኮ ፡ አመ ፡ የወውድዋ ፡ ስቡኢ ፡ ዕለተ ። (ኢያ ፡ ፮ ፡ ፳ ፡ ፭ ።)
(በተአምኖ ፡ አመ ፡ የወውድዋ ፡) በሃይማኖት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዞሯት ፡ ጊዜ ፡ የኢያሪኮ ፡ ቅጽሯ ፡ በአ
ራት ፡ ወገን ፡ ተናደ ።

ፀፀ ፡ በተአምኖ ፡ ረዓብ ፡ ዘማኒ ፡ ኢተጋጉለት ፡ ምስለ ፡ ዓላውያን ። (ኢያ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ። ያዕ ፡ ፪ ፡ ፳፭ ።
ረዓብ ፡ ዘማም ፡ በሃይማኖቷ ፡ ዳነች ፡ እንጂ ፡ ከዓላውያን ፡ ጋራ ፡ አልጠፋችም ።
እስመ ፡ ተወክፈቶሙ ፡ ሰሰብአ ፡ ዐይን ፡ ወኀብዐቶሙ ፡ በሰላም ።
የእስራኤልን ፡ ጉበኞች ፡ በፍቅር ፡ ተቀብላ ፡ በፍቅር ፡ ሸኝታ ፡ ስለሰደደቻቸው ፡ በሃይማኖቷ ፡ ዳነች ፡
እንጂ ፡ ኢተጋጉለት ። (ሐተታ ፡) ያዕቆብ ፡ በአንቀጸ ፡ ምግባር ፡ ወከማሁ ፡ ረዓብኒ ፡ ዘማ ፡ በምግባሪሃ ፡ ጸድ
ቀት ፡ ሶበ ፡ ተቀበለቶሙ ፡ ለሰብአ ፡ ዐይን ፡ ብሎ ፡ ምግባሯን ፡ መስከሮላታል ፡ ከዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡
በአንቀጸ ፡ አሚን ፡ ሃይማኖቷን ፡ መሰከረላት ። ወምንተ ፡ እንከ ፡ አብል ፡ አስመ ፡ ኀጺር ፡ ዕለትየ ፡ ከመ ፡ እዜ
ኑክሙ ፡ በአንተ ፡ አለ ፡ ጌደዎን ፡ (ዘመሳ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ፡)
አለ ፡ ጌደዎን ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጾኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ እንዳልነገራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡
እላለሁ ። (ሐተታ ፡) ምነው ፡ ሐዋርያ ፡ ደመና ፡ ጠቅሶ ፡ ካሰበው ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ አስተምሮ ፡ እሳምኖ ፡
ይውል ፡ እንጂ ፡ የሰ ፡ ቢሉ፤አሪትን ፡ የምናስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ አልፏል፤ ወንጌልን ፡ የምናስተምርበት ፡
ጊዜ ፡ ነው ፡ ሲል ። (ታሪክ ፡) ጌደዎን ፡ ትውልዱ ፡ ከመንፈቀ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡ ነው ፤ ምድረ ፡ ርስት ፡
ከገቡት ፡ ከዘጠኙ ፡ ነገድ ፡ ተከሊል ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ የምድያማውያን ፡ ሰዎች ፡ በእስራኤል ፡ ሠልጥነውባቸው ፡
ነበር ። በዘርዕ ፡ ወራት ፡ መጥተው ፡ የበቀለውን ፡ አብልተውባቸው ፡ ያልበቀለውን ፡ አስጠቅጥቀውባቸው ፡
ይሔዱ ፡ ነበር ፤ በመከርም ፡ ወራት ፡ መጥተው ፡ የደረሰውን ፡ አብልተውባቸው ፡ የተረፈውን ፤ በእሳት ፡
አቃጥለውባቸው ፡ ይሔዱ ፡ ነበር ።
ወእንዘ ፡ ይዘብጥ ፡ ጌደዎን ፡ ሥርናየ ፡ ከመ ፡ ያምስጥ ፡ ይላል ፤ ሊያሸሽ ፡ ሥንዴ ፡ ሲወቃ ፡ መልእክ ፡
ተገልጦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌከ ፡ ፣ጽንዐ ፡ ኃይል ፡ አለው ። ባባቶቻችን ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፡ ይሉናል ፡ እንጂ ፡
በኛ ፡ ጊዜስ ፡ የለም ፡ አሰው ። ሑር ፡ እንተ ፡ ታድኅኖሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ እስራኤል ፤ ወገኖቹ ፡ አሸሪ ኤልን ፡
ባንት ፡ አድሬ ፡ አድናችዋለሁና ፡ ዝሙት ፡ ፣ሉሃል ፡ አለው ። ቆየኝ ፡ መሥዋዕት ፡ ልሠዋ ፡ ብሎ ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ሠዋ ፡ ሥጋውን ፡ በዕንቅብ ፡ ደሙን ፡ በገበታ ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ ። መልአኩ ፡ በዘንግ ፡ ቢነካው ፡
ተቃጥሏል ። ቆየኝ ፡ ፀምር ፡ ልዘርጋ ፤ መኻል ፡ መኻሉ ፡ ጠል ፡ ይውረድበት ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ ይቡስ ፡ ይኹን፡
አለው ። ይኹንልህ ፡ አለው ፤ መኻል ፡ መኻሉ ፡ ጠል ፡ ወረደበት ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ ይቡስ ፡ ኾነ ፡ መኻል ፡

www.zeveneta.com

መኻሉ ፡ የእስራኤል ፤ ጠል ፡ የረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፤ ዳር ፡ ዳሩ ፡ የእሕዛብ ፤ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለመርዳቱ ፡ አሕዛብን ፡ ላለመርዳቱ ፡ ምሳሌ ፡ ፍጻሜው ፡ ማን ፡ ጸምር ፡ የእመቤታችን ፡ ጠል ፡ የጌታችን ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ የሉሎች ፡ ሴቶች ፡ ጠል ፡ ከመኻል ፡ እንጂ ፡ ከዳር ፡ አለመውረዱ ፡ ጌታችን ፡ ከእመቤታችን ፡ ለመወለዱ ፡ ክሉሎች ፡ ሴቶች ፡ ላለመወለዱ ። ምሳሌ ።

ኹለተኛም ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ ጠል ፡ ይውረድበት ፡ መኻል ፡ መኻሉ ፡ ይቡሰ ፡ ይኹን ፡ አለው ። ይኹንልህ ፡ አለው ። ዳር ፡ ዳሩ ፡ ጠል ፡ ወርዶበት ፡ መኻል ፡ መኻሉ ፡ ይበስ ፡ ኾነ ። ዳር ፡ ዳሩ ፡ የእሕዛብ ፤ ጠል ፡ የመቅሠፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኻል ፡ መኻሉ ፡ የእስራኤል ፤ መቅሠፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ ለማጥፋቱ ፡ እስራኤልን ፡ ላለማጥፋቱ ፡ ምሳሌ ። ፍጻሜው ፡ ማን ፡ ጠል ፡ የዘርዕ ፡ የሩካቤ ፤ ጸምር ፡ የእመቤታችን ፡ ሉሎች ፡ ሴቶች ፡ በዘርዕ ፡ በሩካቤ ፡ ለመውለዳቸው ፤ እመቤታችን ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ለመውለዷ ፡ ምሳሌ ። ጥመቀው ፡ አለው ። ቢጠምቀው ፡ ቂጅ ፡ ምሉ ፡ ኾኗል ፤ ጠጣው ፡ አለው ፡ ቢጠጣው ፡ ኃይል ፡ ኾኖታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦር ፡ ይሰበስብ ፡ ጀመረ ። ሦስት ፡ እልፍ ፡ ከኹለት ፡ ሽህ ፡ ጦር ፡ ሰበሰበ ። ይህማ ፡ በጦራችን ፡ እንደበት ፡ በሠራዊታችን ፡ ብዛት ፡ ልትሉኝ ፡ አይደለምን ፡ ፈሪ ፡ ተለይ ፡ ብለህ ፡ ወዋጅ ፡ ነገር ፡ አለው ፡ ፈሪ ፡ ተለይ ፡ ብሎ ፡ ወዋጅ ፡ ነትረ ። ከኹለት ፡ እልፍ ፡ ኹለት ፡ ሽህ ፡ ተመለሰ ፡ አልፍ ፡ ቀረ ፡ አሁንም ፡ ፍትኖሙ ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ከውኅ ፡ ዳር ፡ ወስደህ ፡ ፍተናቸው ፡ ኃሻ ፡ ጦሩን ፡ ስንቁን ፡ እንደያዘ ፡ ባንድ ፡ እጁ ፡ እንደ ውሻ ፤ አየጠለፈ ፡ የጠጣውን ፡ አስከትል ፤ ኃሻ ፡ ጦሩን ፡ ስንቁን ፡ ትቶ ፡ እንደላም ፡ ተንዘርክኮ ፡ የጠጣውን ፡ መልስ ፤ የዚያን ፡ ስንቅ ፡ የዚያን ፡ ወርኀ ኃሻ ፡ ለዘኃ ፡ ስጥ ፡ አለው ። ምስት ፡ መቶ ፡ ተኀኝ ፡ የቀረው ፡ ተመለሰ ።

ይህን ፡ ይዞ ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ከደጋው ፡ ሰፈረ ፡ አሕዛብ ፡ ከቆላ ፡ ከሚጻው ፡ ላይ ፡ ሰፍረዋል ።

ሌሊት ፡ ወርደህ ፡ ሰልል ፡ ትፈራም ፡ እንደኾነ ። (እንተ ፡ ወፋራን ፡ ቍልዔክ ፡) ፋራን ፡ ብላቴናህ ፡ ይከተልህ ፡ አለው ። ሌሊት ፡ ወርዶ ፡ ሲሰልል ፡ የአንድ ፡ እምሳ ፡ አለቃ ፡ ባለበት ፡ በኩል ፡ ኾለት ፡ ሰዎች ፡ ነቅተው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ እንዱ ፡ የገብስ ፡ ጥረቮ ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወርዳ ፡ እሳት ፡ ኾና ፡ ከተማችንን ፡ ስታገለ ባብጠው ፡ አያለሁ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ገብስ ፡ የደጋ ፡ አህል ፡ ነው ፤ ጌዴዎንም ፡ ሠሩ ፡ ደጋ ፡ ነው ፤ ገብስ ፡ ይቈናቀ ፡ እንደኾነ ፤ እኛም ፡ ንቀ ነዋል ፤ ጦር ፡ ይሰበስባል ፡ እሱ ፡ ምንእልባት ፡ እንዳያዋርደን ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞአታል ።

ይዚን ፡ ሰምቶ ፡ ሐዶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ መለክት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሩኖስ ፡ አበጅቶ ፡ ኃይል ፡ ፋዘእግዚአ ብሔር ፡ ኩናት ፡ ዘጌዴዎን ፡ ብዩ ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ሥራ ፡ አይታችሁ ፡ ሥሩ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።

ከሠፈሩ ፡ ዳር ፡ ሲደርሱ ፡ ኃይል ፡ ዘእግዚአብሔርም ፡ ከኩናት ፡ ዘጌዴዎን ፡ ኣብሎ ፡ ሩኖሱን ፡ ሰበረ ፡ መለ ከቁን ፡ ነፋ ።

ኃይል ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ኩናት ፡ ዘጌዴዎን ፡ እያሉ ፡ ሩኑሳቸውን ፡ ሰበሩ ፤ መለከታቸውን ፡ ነፉ ።

የሩኖሱ ፡ የመለክቱ ፡ ብዛት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያኽን ፡ የሠራዊቱማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቢለው ፡ ኅዛቸውን ፡ ሠፈሪያቸውን ፡ ድንኳናቸውን ፡ ትተው ፡ ሸሽተዋል ፤ ተከትሉ ፡ ድል ፡ አድርጓቸዋልና ፡ አሉ ፡ ጌዴዎን ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ አንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ እላለሁ ፡ አለ ። ወባርቅ ። (ዘመሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ፤ ፲፩ ፡ ፳ ፡)

አለ ። ባርቅ ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ አላለው ።

(ታሪክ ፡) ባርቅ ፡ ትውልዱ ፡ ከነገደ ፡ ንፍታሌም ፡ ነው ። በሱ ፡ ጊዜ ፡ የእሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስ ፡ ቢትወደዱ ፡ ሲማራ ፡ ይባላሉ ፤ ልዒትወደዱ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብረት ፡ ሠረገላ ፡ ነበረው ። በባርቅ ፡ ዘመ ተበት ፡ በዘመኑ ፡ ዲቦራ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ኼዶ ፡ እንደምን ፡ ላድርግ ፡ አላቸ ።

እስክ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ድረስ ፡ ሽሽ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እግላ ፡ መልስ ፡ እያልህ ፡ ተዋጋ ፡ ድል ፡ ታደር ጋለህ ፡ አለችው ። አንች ፡ ካልኼድሽልኝ ፡ ጊዜውን ፡ በምን ፡ አውቀዋለሁ ፡ አላት ።

እኔማ ፡ የኼድሁ ፡ እንደኾነ ፡ ድሉ ፡ የሴት ፡ ይባልብሃል ፡ አለችው ። ኺጅልኝ ፡ አንጂ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ አላት ። ኼደች ፡ ከርእስ ፡ ደብር ፡ ላይ ፡ ኾና ፡ ዋላዋን ፡ አየሠረረች ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሽሽ ፤ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ተዋጋ ፡ እያለች ፡ እየነገረችው ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጎታል ።

ሲማራ ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡ ኾኖ ፡ ሸሸቶ ፡ ኼዶ ፡ ኢያኤል ፡ ብአሲተ ፡ ኮቢር ፡ ቄንያዊ ፡ ይላታል ፤ በእስራኤልና ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያለች ፡ ድንበረኛ ፡ ናት ፤ ሰውሪኝ ፡ አላት ። ሰወረችው ። ውኃ ፡ ጠምቶኛልና ፡ አጠጭኝ ፡ አላት ። ወግሚት ፡ ከነአይገኑ ፡ አቀረበችለት ። ያን ፡ ጠጥቶ ፡ ብርድ ፡ ብርድ ፡ ብሎኛልና ፡ ደራርቦሽ ፡ እልብሰሽ ፡ አስተኝኝ ፡ አላት ። ደራርቦ ፡ አልብሳ ፡ አስተኛችው ፡ ዕንቅልፍ ፡ ሲወ

www.zeyeneta.com

ስጄው ፡ ሒይታ ፡ ጸቀወቶ ፡ ወደመቀቶ ፡ በመትከለ ፡ ደብተራ ፡ ይላል ፡ በሳሪሳራው ፡ መታችበት ። በጎበ ፡ ተራገጸ ፡ ሲሣራ ፡ በሀየ ፡ ጎሥረ ፡ እንዲል ፡ (መላ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ።)

ከዚያው ፡ ጎስቁሎ ፡ ሙታል ። ወዲያው ፡ ባርቅ ፡ ተከታትሎ ፡ ደርሶ ፡ አላየሽም ፡ አላት ። ከማሁስ ፡ ለይኩን ፡ ጸላዕትከ ፡ ብላ ፡ ግዳይ ፡ ጥለታለችና ፡ እለ ፡ ባርቅ ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ አላለሁ ፡ አለ ።

ወዮፍታሔ ። (ዘመሳ ፡ ፲፪ ፡ ፯ ፡

እለ ፡ ዮፍታሔ ፤ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ አላለሁ ።

(ታሪክ ፡) ዮፍታሔ ፡ ትውልዱ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ካልገቡት ፡ ከኹለቱ ፡ ነገድ ፡ ተኩል ፡ ከመንፈቀ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡ ነው ። ወንድሞቹ ፡ ዲቃላ ፡ ነህ ፡ ርስት ፡ መውረስ ፡ አይገባህም ፡ ብለው ፡ ከልከለውት ፡ ነበር ፡ የእናቱ ፡ ሀገር ፡ ጣፍ ፡ ትባላለች ፡ ከዚያ ፡ ሔዶ ፡ ፫ ፡ ያህል ፡ ቦለድ ፡ ኾኖ ፡ ሀገር ፡ አቅንቶ ፡ ሲኖር ፡ ንጉሠ ፡ ሞዓብ ፡ በእስራኤል ፡ ዘመተባቸው ። ርዳን ፡ ብለው ፡ ላኩበት ፤ አንግዲህስ ፡ ቀድሞ ፡ ሰርስት ፡ ሳስታችሁ ፡ ከልከላችሁኛልና ፡ አይኾንም ፡ አላቸው ። ግድ ፡ የለም ፡ ትወርሳለህ ፡ አሉት ።

ምስፍናውን ፡ ትለጡኝ ፡ እንደኾነ ፡ አላቸው ። ይህማ ፡ የምንሻውን ፡ አሉት ። ማሉልኝ ፡ አላቸው ፡ ማሉለት ።

ተመለስልኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። ርስቱን ፡ ሰጠኝና ፡ ልመለስ ፡ ያለዚያ ፡ እንደምን ፡ አመለሳለሁ ፡ አለው ፡ ምን ፡ ርስት ፡ አለህ ፡ ንጉሠ ፡ አሞሬዎን ፡ ካንተ ፡ አባት ፡ ወስዶታል ፤ የኔ ፡ አባት ፡ ከንጉሠ ፡ አሞሬዎን ፡ አምጥቷታል ፤ በዚያው ፡ ላይ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ርስት ፡ ይገኛልን ፡ ተመለስ ፡ አለው ። እሱም ፡ አልመለስም ፡ አለው ። እንኪያስ ፡ አንተም ፡ እምላክህ ፡ ኩሞስ ፡ ያወረሰህን ፡ ትወርሳለህ ፡ እኔም ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያወረሰኝን ፡ እወርሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ዘመተ ። ሲኼድ ፡ ተስሎ ፡ ይኼዳል ፡ ድል ፡ ነሥቼ ፡ የተመለስሁ ፡ እንደኾነ ፡ በመጀመሪያ ፡ ያገኘሁትን ፡ አሠዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስሎ ፡ ይሔዳል ። ገጠሙ ፡ ዮፍታሔ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ልጁ ፡ ድል ፡ ማድረጉን ፡ ሰምታ ፡ ባልንጀሮቿን ፡ ይዛ ፡ ልትቀበለው ። ወጣች ።

ከፈረስ ፡ ከሠረገላ ፡ ወርዶ ፡ አዕቀጽከኒ ፡ ወለትየ ፡ ብሎ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ ቆመ ። ለልማዱ ፡ ከዋለበት ፡ ሲገባ ፡ የሚቀበለው ፡ ለማዳ ፡ ነጭ ፡ በግ ፡ ነበረ ፤ ያ ፡ ይቀበለኛል ፡ ያን ፡ እሠዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበረ ። ተወው አንተም ፡ የተሳልህበትን ፡ ታደርጋለህ ፡ ለኔም ፡ ለድንግልናዬ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ ስጠኝ ፡ ላልቅስለት ፡ እለችው ፡ ሰጣት ። ቀን ፡ ቀን ፡ ባልንጀሮቿን ፡ እየያዘች ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ እየወጣች ፡ ስታለቅስ ፡ ትውላለች ፡ ሌሊት ፡ አየገባች ፡ ታድራለች ። አንዲህ ፡ እያለች ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ ሲኾናት ፡ ሠውቷታልና ፤ እለ ፡ ዮፍታሔ ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛል ፡ ምን ፡ እላለሁ ፡ አለ ።

ወሶምሶን ፡ (ዘመሳ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፳ ።)

እለ ፡ ሶምሶን ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀን ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ እላለሁ ፤ (ታሪክ) ፡ ሶምሶን ፡ ትውልዱ ፡ ክነገደ ፡ ዳን ፡ ነው ፡ እባቱ ፡ ማኑሄ ፡ እናቱ ፡ እንትኩይ ፡ ይባላሉ ፡ ዕንጨት ፡ ስትሰቅም ፡ መልአከ ፡ ተገልጦ ፡ ደግ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳላችሁና ፡ መሥዋዕት ፡ የማይኾን ፡ መጣጣ ፡ ነገር ፡ ከመመገብ ፡ ተከልከሉ ፡ ለባልሽም ፡ ንገሪው ፡ አላት ። ኼዳ ፡ ነፃረችው ። ኹለተኛ ፡ ያገኘሽው ፡ እንደኾነ ፡ መጥተሽ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ። ኹለተኛ ፡ ተገልጦ ፡ ደግ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳላችሁና ፡ መሥዋዕት ፡ የማይኾን ፡ መጣጣ ፡ ነገር ፡ ተመመገብ ፡ ተከልከሉ ፡ አላት ። ቆየኝ ፡ ባሌን ፡ ልጥራው ፡ ብላ ፡ ጠርታ ፡ ይዛው ፡ መጣች ። ለምሽቱ ፡ የነገርሃት ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ። አዎን ፡ አለው ። በል ፡ እንደ ነገርሃት ፡ እድርገህ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ደግ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳላችሁና ፡ መሥዋዕት ፡ የማይኾን ፡ መጣጣ ፡ ነገር ፡ ከመመገብ ፡ ተከልከሉ ፡ አለው ። ቆየኝ ፡ መሥዋዕት ፡ ልሠዋ ፡ ብሎ ፡ ሥጋውን ፡ በዕንቅብ ፤ ደሙን ፡ በገበታ ፡ እድርጎ ፡ አቀረበ ። መልእኩ ፡ በዘንግ ፡ ቢነካው ፡ ተቃጥሏል ፤ በጢሱ ፡ መልእኩ ፡ ዐርጓል ። መልእክ ፡ አይተው ፡ አያውቁም ፡ ነበርና ፡ መልእክ ፡ እይተናልና ፡ እንሞታለን ፡ አላት ። እሺ ፡ ከሞት ፡ ልጁን ፡ ግን ፡ ይወልደዋል ፤ አንሞትም ፡ እለችው ። ወዲያው ፡ ሶምሶን ፡ ተፀነሰ ፡ ተወለደ ፤ እደገ ፤ ምሁረ ፤ ጸብዕ ፡ ኾነ ። ዐሥራ ፡ እምስት ፡ ዓመት ፡ ሲኾነው ፡ እባቱ ፡ ለጉዳዩ ፡ ወደምድረ ፡ ኢሎፍሊ ፡ አስከትሎት ፡ ሔደ ። ሲሔድ ፡ በመንገድ ፡ አንበሳ ፡ መደብ ፡ ለመቀመጥ ፤ አውሬ ፡ ለመቀስቀስ ፤

www.zeyeneta.com

ቢሉ፡ ዱር ፡ ቢገባ ፡ እንበሳ ፡ አገኘ ። በጡጫ ፡ መቶ ፡ ገሎት ፡ ሐዲል ። ከዚያ ፡ ኑሮ ፡ ሲመለስ ፡ እንበሳ ፡ መደብ ፡ ለመቀመጥ ፤ አውሬ ፡ ለመቀስቀስ ፡ ቢሉ ። እንድም ፡ ከዚህ ፡ እንበሳ ፡ ገድዬ ፡ ነበረ ፡ እንደምን ፡ ኾኖ ፡ ይኾን ፡ ብሎ ፡ ቢገባ ፡ ንብ ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ማር ፡ ሠርታ ፡ አገኘ ። ቆርጦ ፡ በልቶ ፡ ለእናት፡ ለአባቱ ፡ ይዞላቸው ፡ ሐዲል ። ምሳሌ ፡ ነው ፡ ሶምሶን ፡ የጌታ፡ እንበሳ ፡ የአሕዛብ ፤ ካንበሳው ፡ አፍ ፡ የተገኘውን ፡ መብላቱ ፡ ጌታ ፡ ቅርባኑ ፡ አሕዛብን ፡ መሥዋዕተ ፡ አሕዛብን ፡ ለመቀበሉ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

በኢሉፍሊ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ብላቴና ፡ አይቶ ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፡ አባቱን ፡ አጋባኝ ፡ አለው ። የኔ ፡ ልጅ ፡ ተስፋ ፡ ከተነገረላቸው ፡ ከኃያላኑ ፡ ከእስራኤል ፡ ታግባለህ ፡ እንጂ ፡ ተስፋ ፡ ካልተነገረላቸው ፡ ከድኩማኑ ፡ ከአሕዛብ ፡ ታግባለህን ፡ አለው ። ግድ ፡ የለም ፡ ወድጃታለሁና ፡ አጋባኝ ፡ አለው ፤ አሞቶ ፡ አጋባው ። ሠላሳ ፡ ያህል ፡ ሚዛዝት ፡ አበጅተውለት ፡ ሲጨዋወቱ ፤ ምሳሌ ፡ መስዬ ፡ ልንገራችሁ ፤ ያገኛችሁት፡ እንደኾነ ፡ ሠላሳ ፡ መጐናጸፊያ ፤ ሠላሳ ፡ ቀሚስ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ እናንተስ ፡ አላቸው ። እኛም ፡ ሠላሳ ፡ ቀሚስ ፡ ሠላሳ ፡ መጐናጸፊያ ፡ እንሰጥሃለን ፡ አሉት ።

እምአፈ ፡ በሳሚ ፡ ተረከበ ፡ መብልዕ ፡ ወእምአፈ ፡ ግሩም ፡ ወፅአ ፡ ጥዑም ፡ አላቸው ። ቢፈልጉም ፡የማያገኙት ፡ ኾነ ። ቀን ፡ ስጠን ፡ አሉት ። ምስት ፡ ቀን ፡ ሰጣቸው ። እሱ ፡ በሌለበት ፡ ገብተው ፡ ምሽቱን ፡ እኛ ፡ የሰበሰባችሁን ፡ ለፍቅር ፡ መስሎን ፡ ነበር ፡ አንጂ ፡ ለጠብ ፡ ነውን ፤ ትነግሪን ፡ እንደኾነ ፡ ጠይቀሽ፡ ንገሪን ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ጠባችን ፡ ካንች ፡ ነው ፡ አሏት ። ሶምሶን ፤ ምሳሌህን ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ። ከእንበሳ የተፈራ ፡ ከማር ፡ የጣፈጠ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ከአፈ ፡ አንበሳ ፡ ማር ፡ አግኝቼ ፡ በልቻለሁ ፡ አላት ፡ ይህን ፡ነገረቻቸው ። በተቃጠሩበት ፡ ቀን ፡ ቀርበው ፡ ሶምሶን ፡ ምሳሌህን ፡ እንንገርህ ፡ አሉት ። በሉ ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ከአንበሳ ፡ የተፈራ ፡ ከማር ፡ የጣፈጠ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ከአፈ ፡ አንበሳ ፡ ማር ፡ አግኝተህ ፡ በልተሃል ፡ አሉት። (ሶበሰ ፡ ኢያሥራህከምዋ ፡ ለዕጕልትየ ፡ እምኢረከብክምዋ ፡ ለምሳሌየ ፡) ምሽቱን ፡ ባታደከሚትስ ፡ ምሳሌዬን ፡ ባላገኛችኋትም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፤ እንደቆብ ፡ አስጥል ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ ሔዶ ፤ ሠላሳ ፡ ያህል ፡ነጋድያን ፡ አልፈው ፡ ሲሔዱ ፡ ሚን ፡ ሚናቸውን ፡ ሰብሮ ፡ ልብስ ፡ ልብሳቸውን ፡ ገፎ ፡ ያውሳችሁ ፤ ባላገኝ ፡ እንጂ ፡ ልትጣሉኝ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ በዚህ ፡ አዝኖ ፡ ሀገሩ ፡ ሔደ ። ሔደ ፡ ብሎ ፡ አማቹ ፡ ምሽቱን፡ ለሥር፡ ሚዜው ፡ አጋብቶታል ፤ ፫ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ኑሮ ፡ ሙከቱን ፡ እየሳበ ፡ ሲመጣ ፡ አማቹን ፡ በመንገድ ፡ አገኘው ። ወዴት ፡ ትሔዳለህ ፡ አለው ፡ ከሚስቱ ፡ ዘንድ ፡ አለው ።

አፏንማ ፡ ሔድኽ ፡ ብለን ፡ አጋብተናት ፡ ቦመልክም ፡ በሙያም ፡ ከሷ ፡ የምትበልጥ ፡ ታናሽ ፡ እኅቷ፡ አለች ፤ አሷን ፡ ታገባ ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለው ። ምሽቱን ፡ እንጂ ፡ ሌሳማ ፡ ለምኔ ፡ አለው ። እሷ ንስ ፡ ቀረህ ፡ ብለን ፡ አጋብተናታል ፡ አለው ። ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ በሩጫ ፡ ምስት፡መቶ ፡ ቀበሮ ፡ ያዘ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡የጭራሮ ፡ መብራት ፡ አበጅቶ ፡ አንዱን ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱን ፡ ከኹለቱ ፡ ጅራት ፡ እያስተሳሰረ ፡ አሳት ፡ እያቃጠለ ፡ ለቀቃቸው ። ምን ፡ መጣብን ፡ እያሉ ፡ ሲሮጡ ፡ የነጋሪት ፡ ሀገር ፡ አዝመራ፡ አቃጥለው ፡ ውለዋል ። ይህን ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ። ሶምሶን ። በምን ፡ ነገር ። ምሽቱን ፡ ለሌላ ፡ አጋብቶበት ። ቀድሞ ፡ ያላቸው ፡ ይጋባ ፡ በኋላ ፡ የሰው ፡ ምሽት ፡ ለሌላ ፡ ይሰጥ ፡ ብለው ፡ ከነጓዙ ፡ከነከብቱ ፡ ደጅ ፡ ዘግተው ፡ በአሳት ፡ አቃጥለውታል ። በጎ ፡ አደረጋችሁ ፡ ይህን ፡ ባታደርጉ ፡ ጠቤ ፡ ከሱ ፡ ብቻ ፡አል ነበረም ፡ ከናንተም ፡ ነበር ፡ አሳቸው ። ይህን ፡ ዋሾ ፡ ማን ፡ ከማን ፡ ሰንፍ ፡ ብለው ፡ አርብዓ ፡ ያህል ፡ኃያላን ፡ ተመራርጠው ፡ ገጠሙት ። ሚን ፡ ሚናቸውን ፡ ሰብሯቸው ፡ በእተ ፡ ኤጣም ፡ ገብቷል ። ሐደው፡ አስራኤልን ፤ ሶምሶንን ፡ ይዛችሁ ፡ ትሰጡን ፡ እንዳኾነ ፡ ይዛችሁ ፡ ስጡን ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ጠባችን ፡ከናንት ፡ ነው ፡ አሏቸው ፡ ሔደው ፡ ነገሩት ። አናንት ፡ አትጣሉኝ ፡ እንጂ ፡ ለነዚያስ፡ ይዛችሁ ፡ ስጡኝ ፡ አሳቸው ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ኃይል ፡ በአሕዛብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአስራኤል ፡ አልተሰጠውም፡ ነበርና። ኃይሉስ አልተከፈለበትም ፡ ብሎ ፡ ዘመዶቹ ፡ ናቸውና ፡ አዝናኳቸው ። ዐስረው ፡ እንደ ፡ እንጅባ ፡ ካለሚዳ ፡ ጣሉ ፡ ላቸው ። እንይዘዋለን ፡ ብለው ፡ ሲሔዱ ፡ ጕማምዶት ፡ ተኑግ ። ቢፈልግ ፡ መንሰክ ፡ አድግ ፡ አገኘ ፤ ቢወረውር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሽህ ፡ ሰው ፡ ፈጅቷል ፡ ወዲያው ፡ ውጎ ፡ ጥም ፡ ተሰማው ፡ ጌታዬ ፡ ኃይል ፡ ባደረግህልኝ ፡ ቀን ፡ በውጎ ፡ ጥም ፡ ትገለኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር ፡ በያመለክት ፡ ከመንታው ፡ላይ፡ ነቅቶለት ፡ ጠጥቷል ።

ምሳሌ ፡ ነው ፡ ሶምሶን ፡ የጌታ ፡ መንሰክ ፡ አድግ ፡ የአሕዛብ ፤ ክመንሰክ ፡ አድግ ፡ የተገኘውን ፡ ሳይጸየፍ፡ መጠጣቱ ፡ ጌታ ፡ መሥዋዕተ ፡ አሕዛብን ፡ ቅርባኑ ፡ አሕዛብን ፡ ለመቀበሉ ፡ ምሳሌ ። ከዚያ ፡ አልፎ፡ ጋዛ ከምትባል ፡ ሀገር ፡ ገብቶ ፡ ሴት ፡ ስመደ ፤ ቀን ፡ ቀን ፡ እንደሰሚን ፡ ካለ ፡ ተራራ ፡ ይውላል ፤ ሌሊት ፡እየ ገባ ፡ ያድራል ።

www.zeyeneta.com

ጠላቶቹ ፡ ሲወጣ ፡ እንገለዋለን ፡ ብለው ፡ ከደጀሰላሙ ፡ ደርብ ፡ ላይ ፡ ሽምቀው ፡ ሲጠብቁት ፡ ያድራሉ ፡ ሲወጣ ከዚያ ፡ አንዳሉ ፡ አውቆ ፡ ወጸረ ፡ ራግዛተ ፡ ጋዛ ፡ በመትከፉ ፡ ይላል ፡ ክነደርቡ ፡ ተሸከሞ ፡ ወስዶ ፡ በሚው ልበት ፡ አፋፍ ፡ ገደል ፡ ሰደቸዋል ።

ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ደሊላ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ለመደ ። ከዐሥር ፤ አንድ ፡ ከመቶ ፡ አሥር ፡ ከሽህ ፡ መቶ ፡ ብር እንሰጥሻለንና ፡ ኃይሉ ፡ የሚደክምበትን ፡ ጠይቀሽ ፡ ንገሪን ፡ አሏት ። ሶምሶን ፡ ኃይልኽ ፡ የሚደክምበትን ንገረኝ ፡ አለችው ፡ በሰባት ፡ አውታር ፡ ቢያሰሩኝ ፡ ይደክማል ፡ አላት ። በሰባት ፡ አውታር ፡ አሰራ ፡ ሶምሶን ፡ ኢሎፍላውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ። ጕማምዷት ፡ ተነሣ ። አታለልኸኝ ፡ ኧረ ፡ ንገረኝ ፡ አሪችው በሰባት ፡ ምራን ፡ ቢያሰሩኝ ፡ ይደክማል ፡ አላት ፡ በሰባት ፡ ምራን ፡ አሰራ ፡ ሶምሶን ፤ ኢሎፍላውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ። ጕማምዶት ፡ ተነሣ ። ስታታልለኝ ፡ ኹለተኛህ ፡ ነው ፤ ኧረ ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ። ሰባቱን ፡ ቢርንጕዎቼን ፡ ከምድር ፡ በካስማ ፡ መተው ፡ ቢይዛቸው ፡ ይደክማል ፡ አላት ፡ ሰባቱን ፡ ቢርን ጕዎቹን ፡ ከምድር ፡ በካስማ ፡ መታ ፡ ሶምሶን ፡ ኢሎፍላውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ። ንቃቅሎት ፡ ተነሣ ፡ ወንዝሆሙ ፡ በቆናዝሊው ፡ ይላል ፤ ከኃይሉ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ የደረሱበት ፡ አልታወቀም ።

ስታታልለኝ ፡ ሦስተኛህ ፡ ነው ፡ አወድሻለሁ ፡ ትላለህ ፡ አንጂ ፡ አትወደኝም ፤ ኧረ ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ። ከተወስድሁ ፡ ጀምሮ ፡ ኃይሌ ፡ በጠንሬ ፡ ነው ፡ ተላጭቸው ፡ አላውቅም ፡ እስመ ፡ ናዝራዊ ፡ ሐዲሱ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ የተባልሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላት ፡ የልቡን ፡ አንደነገራት ፡ አውቃ ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አጠጥታ ፡ አስከራ ፡ ከጭኒ ፡ ላይ ፡ አስተኝታ ፡ ጠጉሩን ፡ በመቀስ ፡ እያረፈች ፡ እያረፈች ፡ ጣለችው ፡ ሶምሶን ፡ ኢሎ ፍላውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ። ኃይል ፡ ተነሥቶታልና ፡ ወደታች ፡ እንጂ ፡ ወደላይ ፡ መነሣት ፡ የማይ ቻለው ፡ ኾነ ።

ኑ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ደከምላችኋል ፡ አለቻቸው ። መጥተው ፡ ኹለት ፡ ዐይኑን ፡ አጥፍተው ፡ ባቄላ ፡ ሲያስፈጩት ፡ ኑረዋል ፡ ዓይን ፡ አይመለስም ፡ እንጂ ፡ ጠጉር ፡ እያደገ ፡ ኃይል ፡ እየተመለሰ ፡ ሔደ ፡ በዓል ፡ ባደረጉበት ፡ ቀን ፡ አስቲ ፡ ያን ፡ ዕውር ፡ ጥሩት ፡ ያጫውተን ፡ ብለው ፡ ብላቴና ፡ ላኩ ። በፊት ፡ በፊት ፡ እየመራ ፡ ይዞት ፡ መጣ ። ከመካከል ፡ አግብተህ ፡ አቁመኝ ፡ አለው ። አግብቶ ፡ አቆመው ።

ምሶሖን ፡ አስይዘኝ ፡ አለው ፡ አንዱን ፡ ምሶሖ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ አንዱን ፡ ምሶሖ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ አስያ ዘው ፡ ኹሉም ፡ ተከተው ፡ ገብተዋልን ፡ የቀረ ፡ የለምን ፡ አለው ። አዎን ፡ አለው ። አ እግዚኦ ፡ እሑተ ፡ ሰእ ለተ ፡ አስእለከ ፡ ሀየንተ ፡ ከልኤሆን ፡ አዕይንትየ ፡ ትግእ ፡ ነፍሰየ ፡ ምስለ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ ብሎ ፡ አንዱን ዓምድ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ አንዱን ፡ ዓምድ ፡ በእግራ ፡ እጁ ፡ ቢመታው ፡ የታቹም ፡ የላዩም ፡ አንድ ፡ ኾነው አልቀሞል ። ምሳሌ ፡ ነው ፤ ሶምሶን ፡ የጌታ ፡ ሶምሶን ፡ በብሠራቱ ፡ መልአክ ፡ ተወልዷል ፡ ጌታም ፡ በብ ሥራቱ ፡ መልአክ ፡ ተወልዷልና ፡ ሶሞሶን ፡ በተናቀች ፡ መንሰክ ፡ አድግ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አጥፍቷል ፤ የጌታም አይሁድ ፡ በናቋት ፡ በሞቱ ፡ ብዙ ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቷልና ።

አንድም ፡ ሶምሶን ፡ በሕይወቱ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ካጠፋቸው ፡ ጠላቶቹ ፡ በሞቱ ፡ ያጠፋቸው ፡ ጠላቶቹ ፡ ይበዛሉ ፡ የጌታም ፡ በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ካጠፋቸው ፡ አጋንንት ፡ በሞቱ ፡ ያጠፋቸው ፡ አጋንንት ፡ ይበዛሉና ።

ወዳዊት ፡ ፪ (ሳሙ ፡ ፪ ፡፭ ።)

እለ ፡ ዳዊት ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮኛልና ፡ ምን አላለሁ ። የጎልያድን ፡ ያስተርካል ።

ወሳሙኤል ።

እለ ፡ ሳሙኤል ፡ በሃይማኖት ፡ ቢጸኑ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮኛልና ፡ ምን ፡ አላለሁ ፡ የአጋግን ፡ ያስተርካል ።

፴፫ ፡ ወባዕዳንሂ ፡ ነቢያት ፡ አለ ፡ በተአምኖ ፡ ተጋደሉ ።

ነሚሣለትና ፡ ባዕዳንሂ ፡ ነቢያት ፡ አለ ፤ አምነው ፡ መከራ ፡ ለተቀበሉ ፡ ለሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ የተደረ ገላቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ቀኑ ፡ አጥሮብኛልና ፡ ምን ፡ አላለሁ ።

ወሞኡ ፡ ንጉሥተ ፡(፪ ሳሙ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ፲፬)

ሰብአ ፡ ኢያሱ ፡ ነገሥተ ፡ ከነዓንን ፤ ሰብአ ፡ ጌዴዎን ፡ ነገሥተ ፡ ምድያምን ፡ ድል ፡ ነሡ ።

ወአድምዑ ፡ ፍናዊሆሙ ።

ዋጋቸው ፡ መዊአ ፡ ፀርን ፡ አገኙ ።

www.zeyeneta.com

ተገበሩ ፡ ጽድቀ ።
ትሩፋት ፡ ሠሩ ፡ (አለ ፡) አለ ፡ ዳዊት ።
ወረከቡ ፡ ተስፋሆሙ ።
ተስፋቸውንም ፡ አገኙ ።
ወፈጸሙ ፡ አፈ ፡ አናብስት ። (ዳን ፡ ፮ ፡ ፳፪)
አፈ ፡ አናብስትን ፡ ዘጉ ፡ (አለ ፡) አለ ፡ ዳንኤል ።
ፀዊዐ ፡ ወአጥፍኡ ፡ ኃይለ ፡ እሳት ፡(ዳን ፡ ፫ ፡ ፳፯ ፡)፡
ዋዕየ ፡ እሳት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ዋዕየ ፡ እሳትን አጠፋ ፡(አለ ፡) ፫ቱ ፡ ደቂቅ ።
ወድኅኑ ፡ አምአፈ ፡ ኩናት ።
ከሮር ፡ አንደበት ፡ ዳኑ ፡ (አለ ፡) ፫ቱ ፡ ደቂቅ ።(ሐተታ) ፡ላስወጋቸው ፡ ቢል ፡ ይቻለው ፡ ነበርና ፡ አን
ድም ፡ ደቂቀ ፡ መቃቢስ ፡ ናቸው ።
ወጸንዑ ፡ በሕማሞሙ ።
በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ በረቱ ።
ወጎየሱ ፡ በውስተ ፡ ጸብዕ ።
በሰልፍም ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ነሡ ።
ወሰደዱ ፡ ተዐይነ ፡ ፀር ።
መቃብያን ፡ ጽርዓውያንን ፤ ትሩፋን ፡ ኀጣ ፡ ማኅጣን ፡ ድል ፡ ነሡ ።
ፀፍጹ ፡ ወንሥአ ፡ አንስት ፡ ምውታኒሆን ፡ አሕይዎሙ ፡ ከመ፡ዘትንሣኤ ፡ ፭ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ፡ ፱ ፡ ነገ ፡ ፬ ፡ ፀፍጹ ።
እንደትንሣኤ፡ ዘጉባኤ ፤ አለ ፡ ኤልያስ ፤ አለ ፡ ኤልሳዕ ፡ ልጆቻቸውን፡ አሥነሥተውላቸው፤ (ሐይዎሙ)
ቢል ፡ ልጆቻቸው ፡ ተነሥተውላቸው ፡ ሴቶች ፡ ይዘው ፡ ሔዱ ።
ወቦ ፡ አለ ፡ ሞቱሂ ፡ ተኰነኖሙ ።
ይሞት ፡ በቃ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ የሞቱም ፡ አሉ ።
አስመ ፡ ኢፈቀዱ ፡ ድኀነ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሕይወት ፡ መኖርን ፡ አልወደዱምና ።
ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ እንተ ፡ ትኄይስ ።
የበለጠች ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለክብርን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ።
ፀፂ ፡ ወቦ ፡ አለሂ ፡ ቀሠፍዎሙ ።
ገርፈው ፡ የገደሏቸውም ፡ አሉ ፡ (አለ) አለ ፡ አሞጽ፡ ወዲያ ፤ በለስህን ፡ ሸጠህ ፡ ብላ ፡ እንጂ ፡ ከትምህ
ርት ፡ ከትንቢት ፡ ምን ፡ አገባህ ፡ ብለው ።
ወተግለፁ ፡ ላዕሌሆሙ ።
የዘበቱባቸውም ፡ አሉ ።
ወሐመይዎሙ ፡ ወሞቅሕዎሙ ። (ኤር ፡ ፳፪ ፡
አስረው ፡ ያገዟቸውም ፡ አሉ ።
ፀፃ ፡ ወቦ ፡ አለ ፡ ወሠርዎሙ ፡ በሞሠርጉ ።
በመጋዝ ፡ ተርትረው ፡ የገደሏቸውም ፡ አሉ ፡ (አለ) ፡ አለ ፡ ኢሳይያስ ፡
ወወገርዎሙ ። (ግብ፡ ሐዋ ፡ ፯፡ ፶፱)
በደንጊያ ፡ ወግረው ፡ የገደሏቸውም ፡ አሉ ፡ (አለ) አለ ፡ ኤርምያስን ፡ አለ ፡ አስጢፋኖስን ።
ወቀተልዎሙ ፡ በአረ ፡ መጥባሕት ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰ ።)
በሰይፍ ፡ መትተው ፡ የገደሏቸውም ፡ አሉ፡ (አለ)አለ ፡ ዘካርያስን ፡ አለ ፡ ዮሐንስን ፡ አለ ፡ ያዕቆብን ።
ወዓሉ ፡ በሠቅ ።
ምንጣፍ ፡ ለብሰው ።
ወበሐሜለት ።
የተልባ ፡ አግር ።
ወበዘብድው ፡ ጠሊ ።
ዐጽፍ ። አንድም ፡ ሐሜለት ፡ ዐጽፍ ፤ ዘበድው ፡ ጠሊ ፤ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ ለብሰው ፡ የዞሩ ፡ አሉ ፡ (አለ
አለ ፡ ኤልያስ ፡ ናቸው ።
ተፀነሱ ። ተቸገሩ ።

www.zeyeneta.com

ተመንደቡ ተጨነቁ ።

ፀጋ ፡ ሐሙ ፡ አሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዘአይደልሙ ፡ ዓለም ።

የወዲያው ፡ ዓለም ፡ እንጂ ፡ የወዲሁ ፡ ዓለም ፡ የማይገባቸው ፡ እሊህ ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ። እንድም ፡ ዘአይዳለሙ ፡ ዓለም ፤ ዓለሙ ፡ የማይመጣጠናቸው ፡ እሊህ ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ።አንድም፡(ዘአይደለም ፡ ለዓለም ፡) ረክቡ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ለዓለም ፡ የማይገባውን ፡ ዋጋ ፡ አገኙ ።

ወዓሉ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ።

ዱር ፡ ለዱር ።

ውስተ ፡ አድባር ።

ተራራ ፡ ለተራራ ፡

ወበአታት ።

ዋሻ ፡ ለዋሻ ።

ወግበበ ምድር ። ፡ (፩ ፡ ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፬) ።

ፍርክታ ፡ ለፍርክታ ፡ ዞሩ ፤ የዞሩ ፡ አሉ ።

ፀፀ ፡ ወሶሎሙ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅኑ ፡ በሃይማኖት ።

ኹሉም ፡ አምነው ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ።

ወኢያድምዑ ፡ ዘእሰረዎሙ ።

ተሰፋ ፡ ያናገረላቸውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ግን ፡ አላገኙም ።

፵ ፡ እስመ ፡ አቅደመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርእየ ፡ በእንቲአነ ።

እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ስለኛ ፡ በይኒልና ፡ ወርሲን ፡ እምድኅረ ፡ ተጋባእነ ፡ እንዲል ፡(ግብ ፡ ሐዋ፡ ፲፭ ፡ ፵፩ ።)

እንተ ፡ ትሔይስ ፡ ከመ ፡ አይሠለጡ ፡ ዘእንበሌነ ።(ም ፡፲፪ ፡ ፵፫ ።)

የበለጠች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ያለኛ ፡ እንዳይወርሱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ትኹን ፡ ብሎ ፡ በይኒልና ።ወወሰን ፡ እሐደ ፡ ዕለተ ፡ ለነሢአ ፡ እክሊል ፡ ቀደሙን ፡ በተጋድሎ ፡ ወኢቀደሙን ፡ በነሢአ ፡ እክሊል ፡ወሶሎኔ ፡ ረሰይክዋ ፡ ከመ ፡ ኅልቀት ፡ እንዲል ። ዕዝ ፡ ፭ ፡ ፵፪ ፡(አፈ፡ ወር ፡)(ሐተታ ፡)ላንድ፡ ሽማግሌ፡ዐሥር ልጆች ፡ ይኖሩታል፤ እምስቱ ፡ ደጋ፡ አምስቱ፡ ቄላ ፡ ይሰማራሉ፡ ከነዚያ፡ እንዳቸው፡ ቀድመው፡ ቢመጡ፡ መቆያቸውን ፡ ሰዋቶ ፡ ያቆያቸዋል ፡ እንጂ ፡ ቀድሞ ፡ ግብር ፡ እንዳያገባላቸው ፤ ጌታም፡ የዐረቦኑን ፡ ከብር፡ ሰዋቶ ፡ ያቆያቸዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

ክፍል ፡ ፲፪ ፡

፩ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንሕነኒ ፡ እለ ፡ ብነ ፡ እሙንቱ ፡ ሰማዕት ፡ ሶሎሙ ፡ ዘየዐውዱን ፡ ከመ ፡ ደመና፡ ንግድፍ፡ እምላዕሌነ ፡ ሶሎ ፡ ክበደ ፡ ወሁከተ ፡ ኃጢአት ፡ (ሮሜ ፡፯ ፡፳፭ ፡)

እንደ ፡ ደመና ፡ የሚከቡን ፡ እሊህ ፡ እብነቶች ፡ አሉና ፡ እሊህ ፡ ስላሉ ፡ (ሐተታ ፡) የዐውዱን ፡ አለ ፡ ይጸልሉን ፡ አላለም ፡ መጋረድ ፡ እንድ ፡ ወግ ፡ ነው ፡

መክበብ ፡ ግን ፡ ዙሪያውን ፡ ነው ፤ አብነትነታቸውም ፡ በብዙ፡ወግ ፡ ነውና ፡ የዐውዱን ፡ አለ።ክበደ ኃጢአትን ፡ ሁከተ ፡ ኃጢአትን ፡ ክኖ ፡ እናርቅ ፡ ማለት ፡ የመከራ ፡ ጽናት ፡ ያመጣብንን ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፋን ፡ ክኖ ፡ እናርቅ ፡

ወንሩጽ ፡ በትዕግሥት ፡ ኀበ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ለነ ፡ ተስፋን ፡(፩ ፡ ቆሮ ፡፱ ፡ ፳፬ ።)

መከራውን ፡ በመታገሥ ፡ ኾነን ፡ በሃይማኖት ፡ ተጠብቆልን ፡ ወዳለ ፡ ተስፋችን ፡ እንገሥግሥ ።

፪ ፡ ወንትልም ፡ ለፍጹም ፡ መልእክነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ፍጹም ፡ አበጋዛችን ፡ ፊታውራሪያችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ እንከተለው ፡ (አለ) ፡ እንምሰለው፡ አብነት ፡ እናድርገው ።

ዘተወገሠ ፡ ኃፍረተ ፡ መስቀል ።

መከራ ፡ መስቀልን ፡ ታግሦ ፡ የተቀበለ ።

www.zeyeneta.com

አናኅሰዮ ፡ በእንተ ፡ ፍሥሐሁ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ሎቱ ።
ተጠብቆለት ፡ ሰላለ ፡ ድኅነተ ፡ ምእመናን ፡ መከራውን ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ፡ ምን ፡ ትጐዳኛለች ፡ ብሎ ።
ወመነና ፡ ለኅፍረት ።
ኃፍረተ ፡ መስቀልን ፡ ይኹንብኝ ፡ ያለ ፡
ወነበረ ፡ በየማነ ፡ መንበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፪ ፤ ፲፫ ፡ ፊል ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ በእብ ፡ ዕሪና ፡ የተቀመጠ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አብነት ፡ እናድርገው ።

፫ ፡ ሐልይዎ ፡ እስኩ ፡ ስዘከመዝ ፡ ተዐገሠ ፡ እምኃጥኣን ፡ (ሉቃ ፡፪ ፡፴፬ ፡፲፭ ፡፲፰ ፡፭ ፡)
ከኃጥአን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ አሱን ፡ አስኪ ፡ አስቡት ። አንድም ፡ ከኃጥአን ፡ ይህን ያህል ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ እስኪ ፡ አስተውሉት ፤ ወተናገርዎ ፡ በበይናቲከሙ ። እርስ ፡ በርሳችሁ፡ ተጨዋወቱት ።
ከመ ፡ ኢትሥራህ ፡ ነፍስከሙ ፡ ወኢትድክም ።
ድካመ ፡ ነፍስ ፡ ሥራኅ ፡ ነፍስ ፡ እንዳያገኛችሁ ።

፬ ፡ እስመ ፡ ዓዲከሙ ፡ ኢጸናእክሙ ፡ እስከ ፡ ስደም ፡ ትበጽሑ ፡ (ም ፡ ፲ ፡ ፴፫ ፡)
ደማችሁን ፡ እስከ ፡ ማፍሰስ ፡ ድረስ ፡ ደርሳችሁ ፡ ገና ፡ ከፍጹምነት ፡ አልደረሳችሁምና ፡ ከመ ፡ ኢትሥራህ ። ተጋደልዎ ፡ ግንሸ ።

፭ ፡ ተጋደልዎ ፡ ለኃጢአት ፡ ወዕበይዎ ።
እንድም ፡ ደማችሁን ፡ እስከማፍሰስ ፡ ድረስ ፡ ደረሳችሁ ፡ ገና ፡ ከፍጹምነት ፡ አልደረሳችሁምና ኃጢአት ፡ እገባ ፡ እገባ ፡ እናንት ፡ አናስገባ ፡ እናስገባ ፡ በማለት ፡ ተመካክቱ ።
ወአብድርዋ ፡ ለትምህርተ ፡ ተሰፋህሙ ።
ተሰፋችሁን ፡ የምታገኙበት ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ ውደጂት ፡ (አል) ወበትዕግሥትከሙ፡ ታጠርይዋ ለነፍስከሙ ፡ የምትል ፡ ማለት ፡ ነው ።
እስመ ፡ ከመ ፡ ውሉድ ፡ ይብሉከሙ ።
ልጆቹ ፡ እንደመኾናችሁ ፡ ለልጆቹ ፡ እንዲመክር ፡ ይመከራችኋልና ።
ወልድየ ፡ ኢታስተጽሕብ ፡ ተግሣጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ምሳ ፡፫ ፡፲፩ ፡፲፪ ።)
ልጄ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያመጣብህን ፡ መከራ ፡ አትሰልች ፤ አትሰቀቅ ፡ አትመረር ።
ወኢትትገኃሥ ፡ እምኔሁ ፡ ሶበ ፡ ይዘልፈከ ፡ አመ ፡ ገሠጸከ ።
በመከረህም ፡ ጊዜ ፡ በመከራው ፡ ቢዘልፍህ ፡ ከሱ ፡ አትራቅ ፡(አስ) ኃጢአት ፡ ሳልሠራ ፡ መከራ ፡ አመጣብኝ ፡ አትበል ።

፮ ፡ እስመ ፡ ዘአፍቀረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጌሥጾ ።
እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ በመከራ ፡ ይገሥጻልና ።
ወይቀሥፍዎ ፡ ለኵሉ ፡ ውሉድ ፡ ዘይትፈቀድ ፡(ራእ ፡፫ ፡፲፱ ።)
የሚወዱትን ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ይሠሩታል ፡ ይቀጡታል ።

፯ ፡ ለተግሣጽከሙ ፡ ተዓገሡ ።
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ መከራውን ፡ ታግሣችሁ ፡ ተቀበሉ ።
እስመ ፡ ከመ ፡ ውሉዱ ፡ ያፈቅረከሙ ፡ እግዚአብሔር ።
ልጆቹ ፡ እንደመኾናችሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ እንደሚወድ ፡ ይወዳችኋልና ።
መኑ ፡ ውሉድ ፡ ዘኢይጌሥጾ ፡ አቡሁ ፡(ዘዳግ ፡ ፰ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡)
አባቱ ፡ የማይሠራው ፡ የማይቀጣው ፡ ልጅ ፡ ማነው ።

፰ ፡ ወእመሰ ፡ ኢገሠጹከሙ ፡ አንደበራ ፡ አንትሙ ።
ካልሠሩዋችሁ ፡ ካልቀጡዋቸሁስ ፡ ባዕዳን ፡ ናችሁ ።
ወኢከንከሙ ፡ ውሉደ ።
ልጆች ፡ አትባሉም ።
ወበረይከሙ ፡ ዝሉከሙ ። (መዝ ፡ ፸፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ፡)
ትከክል ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ፡ (አለ ፡) ባልንጀራ ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ።

www.zeyeneta.com

፱ ፡ ወእመሰ ፡ እበዊነ ፡ እለ ፡ ወለዱነ ፡ በሥጋ ፡ ይጌሥጹነ ።
ሥጋውያን ፡ አባቶቻችን ፡ የሚሠሩን ፡ የሚቀጡን ፡ ከኾነ ።
ወነኀፍሮሙ ።
እኛም ፡ የምንናፍራቸው ፡ ከኾነ ።
እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ንግነይ ፡ ወንትአዘዝ ፡ ለአቡ ፡ መንፈስነ ፡ ይደልወነ ፡(ዘጕል ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯ ፡)
በሀብት ፡ ለሚወልደን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለሚያጸልየን ፤ በመልእክ ፡ ውቃቢ ፡ ለሚያስጠብቀን ፤ ለሰ
ማያዊ ፡ አባታችንማ ፡ መገዛት ፡ እንደምን ፡ አይገባን ፡(ወንሕየው ፡)፤ በመገዛት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ እንደምን ፡
አይገባን ።

፲ ፡ ወእሙንቱሰ ፡ ለሥላጤ ፡ ለጎዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ይጌሥጹነ ፡ በከመ ፡ ፈቀዱ ።
ሥጋውያን ፡ አባቶቻችንስ ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ የራሳቸውን ፡ ግዳጅ ፡ ለመፈጸም ፡ እንደወደዱ ፡ ይሠሩናል
ይቀጡናል ።
ወውእቱሰ ፡ ለእንተ ፡ ትኄይስ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ንርከብ ፡ ቅድሳቲሁ ፡ ። (፩ ፡ ጴጥ ፡፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮)
እሱ ፡ ግን ፡ ከብሩን ፡ እንወርስ ፡ ዘንድ ፡ ለኛ ፡ ብሎ ፡ በመከራ ፡ ይገሥጸናል ።
፲፩ ፡ ኵሉ ፡ ተግሣጽ ፡ ኢይመስል ፡ ትፍሥሕተ ፡ በጊዜሁ ።
መከራ ፡ ለጊዜው ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ።
ዳዕሙ ፡ ኀዘን ፡ ውእቱ ።
ያሳዝናል ፡ እንጂ ።
ወድኅረሰ ፡ ትፈሪ ፡ ሰላመ ፡ ለእለ ፡ ተገሥጹ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፭ ፡ ያዕ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።)
ኋላ ፡ ግን ፡ ታግሠው ፡ ለተቀበሏት ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አንድነትን ፡ ታመጣለች ።
ወተዐበዮሙ ፡ ጽድቀ ።
ዋጋቸውንም ፡ ትሰጣቸዋለች ።

፲፪ ፡ ወበእንተዝ ፡ እርትዑ ፡ እደ ፡ ፅውስተ ፡ ወእግረ ፡ ፅቡሳተ ። (ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፫ ።)
ልምሾ ፡ እደ ፡ ልቡናችሁን ፡ ልምሾ ፡ እግረ ፡ ልቡናችሁን ፡ የቀና ፡ እድርጉ ።
፲፫ ፡ ወግበሩ ፡ መንኰራኵረ ፡ ርቱዐ ፡ ለእገሪክሙ ።
ለእግረ ፡ ልቡናችሁ ፡ የቀና ፡ የሠረገላ ፡ መንኰራኵርን ፡ ያዙ ፡ (አለ ፡) ሃይማኖትን ።
ከመ ፡ ይሕየው ፡ ሕንካሴ ፡ ልብከሙ ።
የልቡናችሁ ፡ ጥርጥር ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ።
ወኢትትዐቀፉ ።
እንዳትጠራጠሩ ።

፲፬ ፡ ወሩጹ ፡ ኀበ ፡ ሰላም ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ።
ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ ፍቅርን ፤ እንድነትን ፡ ወደመያዝ ፡ ገሥግሡ ።
ወኢትኅድጉ ፡ ቅድሳቲክሙ ።
ንጽሕናችሁንም ፡ አታፍርሱ ።
ወዘእንበሌሁሰ ፡ አልቦ ፡ ዘይሬእዮ ፡ ለእግዚአብሔር ። (መዝ ፡ ፴፬ ፡ ፲፭ ፡ ሮሚ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ፡)
ያለንጽሕናስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያየው ፡ የለም ። እስመ ፡ በእንጽሐ ፡ መንፈስ ፡ ርእይዎ ፡ ነቢያት ፡
ለእግዚአብሔር ፡ እንዲል ።
ያለንጽሕና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያየው ፡ የለምና ፡ ኢትኅድጉ ።

፲፭ ፡ እስተሐይጹ ።
እስተውሉ ።
አልቦ ፡ ዘያሰትት ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ።
ሃይማኖት ፡ ወንጌላዊትን ፤ ገድል ፡ ትርፍትን ፤ ተድላ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ የሚንቅ ፡ የሚያ
ታልል ፡ ሰው ፡ አይኑር ።
ወአልቦ ፡ ዘይትረከብ ፡ ሥርወ ፡ መሪር ። (ዘዳግ ፡ ፳፱ ፡ ፲፰ ።)
ክፉ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ያለው ፡ መምህር ፡ አይኑር ፡ (መሪረ ፡ ሥርው ፡) ክፉ ፡ መምህር ፡ ያለው ፡
ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አይኑር ፡ (መሪር ፡ ሥርው ፡) ይላል ፡ ክፉ ፡ መምህር ፡ አይኑር ።

www.zeyeneta.com

እንተ ፡ ታሠርጽ ፡ ሕግመ ፡ እንተ ፡ ታስሕቶሙ ፡ ወታረሲሶሙ ፡ ለብዙኃን ።
ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ የምትነዳ ፡ ክህደትን ፡ ኑፋቄን ፡ የምታሳማ ፡ ብሎ ፡ ለሥርው ፡ መሪር ፡ ቀጠለ ።

፲፯ ፡ እልቦ ፡ ዘይከውን ፡ ዘማዌ ፡ ወርዙሰ ፡ ከመ ፡ ዔሳው ፡ ዘኒጠ ፡ ብኩርናሁ ፡ ለአሐዱ ፡ መብልዕ ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፫ ፡ ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፳ ፡ ዘፍጥ ፡ ፳፭ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ።)
ብዙርናውን ፡ ለምስር ፡ ንፍሮ ፡ ለዳቦ ፡ ሽሮ ፡ እንደሸጠ ፡ እንደዔሳው ፡ ያልሰጡትን ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ እይኑር ።

፲፯ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ድኅሬሃ ፡ ፈቀደ ፡ ይረስ ፡ በረከተ ። (ዘፍጥ ፡ ፳፯ ፡ ፴ ፡ ፴፭ ።)
ኋላ ፡ ግን ፡ በረከትን ፡ ይወርስ ፡ ዘንድ ፡ እንደሻ ፡ ታውቃላችሁ ።

ወአውፅአዎ ።
ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ነሥት ፡ እንጂ ።

አስመ ፡ ተስዕኖ ።
መመለስ ፡ አልተቻለውምና ።

ወኃየአ ፡ ፍናተ ፡ በዘይኔስሕ ።
በሚመለስ ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለስበትን ፡ ምክንያት ፡ አላገኘምና ።

ወኃሠሠ ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ።
መሻቱንስ ፡ እያለቀሰ ፡ ሻ ፤ አላገኘም ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ኢመጻእክሙ ፡ ኀበ ፡ እሳት ፡ ዘያስተርኢ ፡ ዘይነድድ ።
የሚነድ ፡ እሳት ፡ ወደሚታይበት ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አልወጣችሁምና ፤ አንድም ፡ እየነደደ ፡ የሚታይ ፡ እሳት ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አልወጣችሁምና ።

ወጽልመት ፡ ግፍጉዕት ።
ይያዝ ፡ የመሰለ ፡ ጨለማ ፡ ወዳለበት ።

ወቆባር ። ጽጋግ ።
ወዐውሎ ። ጥቅል ፡ ነፋስ ።
ወጣቃ ። (ዘፀአ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ፡ ዘዳግ ። ፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።)
እንደ ፡ ግድግዳ ፡ የቆመ ፡ ጨለማ ።

፲፱ ፡ ወድምፀ ፡ መጥቅዕ ።
የነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ ወደተሰማበት ።

ወቃለ ፡ ነገር ፡ ዘሰምዑ ፡ እሙንቱ ፡ ወኢፈቀዱ ፡ ዳግመ ፡ ይትነገሮሙ ። (ዘጸአ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ፡)
እስራኤል ፡ ሰምተው ፡ ዝለተኛ ፡ ሊነግራቸው ፡ ያልወደዱት ፡ ቃል ፡ ወደተሰማበት ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አልወጣችሁምና ። ኢይትነገረነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላ ፡ ይትነገረነ ፤ ሙሴ ፡ ብለዋል ።

ኀ ፡ አስመ ፡ ስዕንዎ ፡ አጽምዖቶ ፡ ለዘተነገሮሙ ።
የተነጋገራቸውን ፡ ነገር ፤ የተነጋገራቸው ፡ አሱን ፤ መስማት ፤ ስላልተቻላቸው ።
ወእመኒ ፡ እንስሳ ፡ ቀሪበ ፡ ለውእቱ ፡ ደብር ፡ ይቄግርዎ ። (ዘፀአ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡)
ከብትም ፡ ወደተራራው ፡ ቢቀርብ ፡ ወግረው ፡ ይገሉት ፡ ነበር ፤ አከብረው ። አንድም ፡ ሊያመጣብን ፡ ብለው ፡ ፈርተው ።

ኀ፩ ፡ ወዝንቱ ፡ ዙሉ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ግሩም ፡ ዘአስተርአዮ ።
ይህ ፡ ኹሉ ፡ ስለታያቸው ፡ ግሩም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ግሩም ፡ ነገር ፡ ስለታያቸው ፡ ነው ።
ወሙሴኒ ፡ ይቤ ፡ ርዑድ ፡ ወድንጉፅ ፡ እነ ። (ዘዳግ ፡ ፱ ፡ ፲፱ ፡)
ሙሴም ፡ ርዑድ ፡ ነኝ ፡ ድንጉፅ ፡ ነኝ ፡ ብሏል ።

ኀ፪ ፡ ወእንትሙሰ ፡ በጸሕክሙ ፡ ኀበ ፡ ጽዮን ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንቲ ፡ በሰማያት ።
(መዝ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ ፻፲ ፡ ፪ ። ራእ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ፡ ፯ ፡ መዝ ፡ ፵፰ ። ፲፮ ፡ ዳን ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ራእ ፡ ፯ ፡ ፵ ፡ ፲፭ ።)
(ኀበ ፡ ጽዮንሰ ፡) የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ወደምትኾን ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ ግን ፡ ገብታችኋልና ።

ውኅበ ፡ አእላፍ ፡ መላእክት ፡ ፍሡሓን ።
ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የሚኖሩ ፡ መላእክት ፡ ወዳሉባት ። አንድም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ከሚኖሩ ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ወደመኾን ፡ ደርሳችኋልና ።

www.zeyeneta.com

ሸኸ ፡ ወማኅበረ ፡ በሰር ። (ሱቃ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ራሕ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ፡)
ማኅበረ ፡ በሰር ፡ ወዳሱበት ፡ ወደመንግሥተ ፡ ሰማይ ። አንድም ፡ ከማኅበረ ፡ በሰር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ወደ መኾን ፡ ደርሳችኋልና ። (ሐተታ ፡) በሰር ፡ ጌታ ፡ ማኅበር ፤ ከአቤል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

እለ ፡ ጽሑፍ ፡ አስማቲሆሙ ፡ በስማያት ።
ስማቸው ፡ በልበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለበጎ ፡ የታወቀ ።

ውኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ሱሉ ፡ (ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ። (መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
በኹሉ ፡ ከሚፈርድ ፡ ኹሉን ፡ ከሚገዛ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ወደመኾን ፡ ፤ደርሳችኋልና ፡

ወኅበ ፡ መንፈስ ፡ ጸድቃን ፡ ፍጹማን ፡ (ም ፡ ፲፩ ፡ ፵ ።)
በፍጹማን ፡ ጸድቃን ፡ አድሮ ፡ ከሚኖር ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ደርሳችኋልና ።

ጽፀ ፡ ወኅበ ፡ ኢየሱስ ፡ ኅሩይ ፡ ወመርሀ ፡ ለሐዳስ ፡ ሥርዓት ።
ለሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ መምህር ፤ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አስታራቂ ፡ ከሚኾን ፡ ከኢየሱስ ጋራ ፡ አንድ ፡ ወደመኾን ፡ ደርሳችኋልና ።

ወለንዝኅተ ፡ ደም ፡ ነባቢ ።
(መርሀ ፡ ለንዝኅተ ፡ ደም ፡) ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ ፊታውራሪ ፡ ከሚኾን ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ወደ መኾን ፡ ደርሳችኋልና ። (ሐተታ ፡) ነባቢ ፡ አለው ። እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ርስታችን ፡ ብለው ፡ የሚመኩበት ፡ ስለኾነ ። አንድም ፡ ወሰበ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ንጹሕ ፡ ያንቅሆ ፡ ለተናግሮ ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወር ፡) አድሮ ፡ ምሥጢር ፡ የሚያናግር ፡ ስለሆነ ።

ዘይኄይስ ፡ ተናግሮ ፡ እምዘ ፡ አቤል ፡ (ም ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። ዘፍጥ ፡ ፬ ፡ ፲ ።)
በመናገር ፡ ከአቤል ፡ ደም ፡ የሚበልጥ ፡ (አለ ፡) ያ ፡ ደመ ፡ ስከየት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ግን ፡ ደመ ፡ ስር የት ፡ ነውና ።

ጽሬ ፡ ውቁ ፡ እንከ ፡ ኢትዕበይዎ ፡ ለዘተናገረከሙ ፡ እምሰማይ ።
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ከወደሰማይ ፡ መጥቶ ፡ የተናገራችሁን ፡ ነገር ፤ የተናገራችሁ ፡ እሱን ፡ አንቀበልም ፡ እንዳትሉ ፡ ዕወቁ ።

ሶበ ፡ አመንቱ ፡ ኢድኅኑ ፡ አስመ ፡ ዐበይዎ ፡ ለዘአስተርአዮሙ ፡ በደብር ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፪ ። ፲ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ።)
አስራኤል ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ የተናገራቸውን ፡ ነገር ፡ የተናገራቸው ፡ ሙሴን ፡ አንቀበልም ፡ ስላሉ ፡ ከመከራው ፡ ካልዳኑ ።

እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ንሕነሰ ፡ ለእመ ፡ ሜጥን ፡ ገጸነ ፡ እምኔሁ ፡ ለዘመጽአ ፡ እምሰማያት ።
እኛማ ፡ ከወደሰማይ ፡ መጥቶ ፡ ከተነጋገረን ፡ ከሱ ፡ ገጹ ፡ ልቡናችንን ። ብንመልስ ፡ ከመከራው ፡ እንደ ምን ፡ እንድናለን ።

ጽኂ ፡ ወኢድለቅለቃ ፡ ለምድር ፡ ቃሉ ፡ ይእተ ፡ አሚረ ።
ያንጊዜ ፡ ቃሉ ፡ ደብረ ፡ ሲናን ፡ ካነዋወጣት ፡ ከሱ ።

ወይእዜኒ ፡ ነገረ ፡ ወይቤ ፡ ዓዲ ፡ ምዕረ ፡ አነ ፡ አድለቅለቃ ፡ ለምድር ፡ (ሐጌ ፡ ፪ ፡ ፮ ።)
ዛሬም ፡ ዳግመኛ ፡ ምድርን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እነዋውጣታለሁ ፡ ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ ከሱ ፡ ገጸ ፡ ልቡናችንን ፡ ብንመልስ ፡ ከመከራው ፡ እንደምን ፡ እንድናለን ።

ወአኮ ፡ ለምድር ፡ ባሕቲታ ።
የማነዋውጣትም ፡ ምድርን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ዓዲ ፡ ለሰማይኒ ።
ሰማይንም ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ጽኂ ፡ ወዘይቤ ፡ ዓዲ ፡ ምዕረ ።
ወይቤ ፡ ዓዲ ፡ ምዕረ ፡ አነ ፡ አድለቅለቃ ፡ ለምድር ፡ ያለውም ።

ያሬኢ ፡ ከመ ፡ ያፍልሶ ፡ ወያሕልፎ ፡ ለዘያንቀለቅል ።
የሚያልፈውን ፡ ዓለም ፡ ያሳልፈው ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ያስረዳል ።
(ያፈልሶ ፡ ወያሐልፎ ፡) ይላል ፡ የሚያልፈውን ፡ ዓለም ፡ እንዲያሳልፈው ፡ ያስረዳል ።

www.zeyeneta.com

አስመ ፡ ፍጡራን ፡ እመንቱ ።
ጥንቱን ፡ ለኅለፍት ፡ ተፈጥረዋልና ።

ከመ ፡ ይንበር ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡ (መዝ ፡፻፱ ፡፭፯ ።)
የማያልፈው ፡ በመወረስ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።

፭፭ ። ወበእንተዝ ፡ ንነሥእ ፡ ንሕን ፡ መንግሥተ ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡(ዳን ፡ ፪ ፡፵፬ ፡፯ ፡፲፬ ።)
ስለዚህ ፡ እኛ ፡ የማታልፍ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይን ፡ ወርሰን ፡ እንኖራለን ።

ወብነ ፡ ጸጋሁ ፡ እንተ ፡ በእንቲአሁ ፡ ንሠውዕ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ስውነታችንን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ እድርገን ፡ የምናቀርብበት ፡ ልጅነት ፡ አለን ።

ወናሠምሮ ፡ በጸሎት ፡ ወበስኢል ።
በጸሎት ፡ በስኢል ፡ ኾነን ፡ ደስ ፡ የምናሰኝበት ።

በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡(መዝ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ። ፊል ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)
በፍርሃት ፡ በረዓድ ፡ ኾነን ፡ ደስ ፡ የምናሰኝበት ።

፭፱ ፡ እስመ ፡ አምላክነ ፡ እሳት ፡ በላዒ ፡ ውእቱ ፡(ዘዳግ ፡፬ ፡፭፫ ።ኢሳ ፡፷፮ ፡፲፭ ።)
ፈጣሪያችን ፡ ተወካፌ ፡ መሥዋዕት ፡ ነውና ።

አንድም ፡ ወብነ ፡ ጸጋሁ ፡ እንተ ፡ በእንቲአሁ ፡ ንሠውዕ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ተሹመን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምናገለግልበት ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ አለን ።

ወናሠምሮ ፡ በጸሎት ፡ ወበስኢል ።
በጸሎት ፡ በስኢል ፡ ኾነን ፡ ደስ ፡ የምናሰኝበት ።

በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ።
በፍርሃት ፡ በረዓድ ፡ ኾነን ፡ ደስ ፡ የምናሰኝበት ።

እስመ ፡ አምላክነ ፡ እሳት ፡ በላዒ ፡ ውእቱ ።
ተሹመን ፡ ባናገለግል ፡ ፈጣሪያችን ፡ ፈታሒ ፡ ነውና ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ክፍል ፡ ፲፫ ።

፩ ፡ ወይኅልዉ ፡ በተፋቅሮ ፡ ምስለ ፡ ቢጽክሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፯ ።)
በሃይማኖት ፡ ከመሰሏችሁም ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ጋራ ፡ ስትኖሩ ፡ በፍቅር ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ።

፪ ፡ ወኢትርሥዑ ፡ ተቀብሎ ፡ ነግድ ።
እንግዳ ፡ መቀበልንም ፡ አትተዉ ።

እስመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ከፈሉሙ ፡ ከመ ፡ ይትቀበሉ ፡ ነግደ ፡ መላእክት ፡ እንዘ ፡ ኢያእምሩ ፡(ሮሜ ፡፲፪ ፡ ፫ ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፰ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፡ ፪ ፡ ፫ ።)
እንግዳ ፡ መቀበልን ፡ ሰለወደዱ ፡ ሳያውቁ ፡ የመላእክትን ፡ እንግድነት ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ያደላቸው ፡ አሉና ፡ (አለ ፡) እለ ፡ ሎጥ ፡ እለ ፡ አብርሃም ።

፫ ፡ ተዘከሩ ፡ ሙቁሓን ፡ ዘከመ ፡ ተሞቃሕክሙ ፡ ምስሌሆሙ ።
እስረኞችንም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳላችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ አስቡ ።

ወእለ ፡ ተሣቀዩ ፡ ከመ ፡ ዘህለውክሙ ፡ በሥጋክሙ ፡ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፮ ።)
በደዌ ፡ ያሉትንም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳላችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ አስቡ ።

፬ ፡ ክቡር ፡ አውስቦ ፡ በኵሉሄ ፡
ኀሡ ፡ ሰላመ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ብሎ ፡ ኢትኔድኑ ፡ ቅድሳቲክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ግቢ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡

www.zeyeneta.com

እንዳይሉበት ፡ ግቢ ፡ በሕዝቡም ፡ በእሕዛቡም ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነው ። እንድም ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ በሐዲስም ፡ የታዘዘ ፡ ነው ።

ወለምስካቦሙኒ ፡ እልቦቱ ፡ ስዕበት ።

ለምንጠሩትው ፡ እያፍ ፡ ርኩሰት ፡ የለውም ።

ለዘማውያንሰ ።

ዘማውያንን ፡ ግን ።

ወለእለ ፡ ያረኩሱ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ይኬንኖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዘወእ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ፡ ፩ቆሮ ፡፮ ፡ ፱ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፭ ።)

ሥጋቸውን ፡ በኃጢአት ፡ የሚያሳድፉትን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈርዶ ፡ ያጠፋቸዋል ።

፭ ፡ እንዘ ፡ ኢታረቅሩ ፡ ንዋየ ፡ ሀልዉ ።

ወሀልዉ ፡ በተሩቅሮ ፡ ምስለ ፡ ቢጽክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከወንድሞቻችሁም ፡ ጋራ ፡ ስትኖሩ ፡ ከብት፡ እትውደዱ ።

ወባሕቱ ፡ የእክለክሙ ፡ ዘብክሙ ።

ያላችሁ ፡ ይበቃችኋል ፡ እንጂ ። እንድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያላችሁ ፡ ይበቃችኋል ።

(ሐተታ ፡ ምን ፡ አላቸው ፡ ቢሉ ፡ የዕለት ፡ እራት ፤ ተገብሮ ፤ ሃይማኖት ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ኢይኅድገከ ፡ ወኢይትሐየየከ ፡ (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፭ ።)

እልጥልህም ፡ ቸል ፡ እልልህም ፡ ብሏልና ።

፮ ፡ ወይእዜኒ ፡ ተእሚነነ ፡ ንበል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድእኒ ።

አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ እምነን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳናል ።

ወኢይፈርህ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምንተ ፡ ይፈሰየኒ ፡ (መዝ ፡ ፶፯ ፡ ፭ ፡ ፻፲፰ ፡ ፮ ።)

ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገናል ፡ እንፈራም ፡ እንበል ። አንድም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገናል ፡ ብለን ፡ እንፈራለን ? አንፈራም ፡ እንበል ።

፯ ፡ ተዘከሩ ፡ መኳንንቲክሙ ፡ ዘነገሩክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡(ቊ ፡ ፲፯ ።)

ወንጌልን ፡ ያስተማሯችሁ ፡ መምህሮቻችሁንም ፡ አርዱ ።

እንዘ ፡ ትሬእዩ ፡ ሠናየ ፡ ግዕዘሙ ፡ ወተመሰሉ ፡ በሃይማኖቶሙ ፡(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)

በጐ ፡ግብራቸውንም ፡ እይታችሁ ፡ በሃይማኖት ፡ ምሰሏቸው ። መምህር ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ ምግባሩ፡ ያልቀና ፡ እንደኾነ ፡ መምሰል ፡ ይገባል ፤ የምግባር ፡ ነገር ፡ እያደረ ፡ ይኾናልና ። ሃይማኖቱ ፡ ያልቀና ። ምግባሩ ፡ የቀና ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ መምሰል ፡ አይገባም ፡ በጐ፡ ምግባሩን ፡ እያሳየ ፡ ወደክፉ ፡ሃይማኖት ፡ ይስባልና ፡ ሃይማኖቱም ፡ ምግባሩም ፡ የቀና ፡ እንደኾነ ፡ መምሰል ፡ ይገባል ።

፰ ፡ እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ዘትማልም ፡ ወየም ።

አስቀድመው ፡ በነበሩ ፡ ዛሬም ፡ ባሉ ።

ወኩመ ፡ ውእቱ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡፫ ፡፲፩ ፡ ራሔ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።)

እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ በሚነሡ ፡ መምህራን ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ።

፱ ፡ ኢታምጽኡ ፡ ካልእ ፡ ነኪረ ፡ ትምህርተ ፡(ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ።)

እኛ ፡ ካስተማርነው ፡ ትምህርት ፡ ሌላ ፡ አሪትን ፡ እንዳታስተምሩ ።

እስመ ፡ ይኄይስ ፡ ጸጋሁ ፡ ያስተፍሥሕ ፡ ልበክሙ ፡(ምሳ ፡ ፳፭ ፡ ፪ ።)

ጸጋው ፡ ወንጌል ፡ ልባችሁን ፡ ደስ ፡ ቢያሰኛችሁ ፡ ይሻላልና ።

ወእኩ ፡ በመባልዕት ፡ ዘኢይበቍዖሙ ፡ ለእለ ፡ ያንሶስዉ ፡ ቦቱ ።(ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ።)

ደስ ፡ ማሰኘቱም ፡ የሚኖሩበትን ፡ ሰዎች ፡ በማይረባቸው ፡ በማይጠቅማቸው ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡አይ ደለም ።

፲ ፡ ወብነ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘኢይክውኖሙ ፡ ይብልዉ ፡ እምኔሁ ፡ እለ ፡ የሐርምዋ ፡ ለደብተራ ።(ም ፡፳ ፡፪ ፡፭ ።

ወእኩ ፡ በመባልዕት ፡ ዘኢይበቍዖሙ ፡ ለእለ ፡ ያንሶስዉ ፡ ቦቱ ፡ ማለትህ ፡ እንደምነዋ ፤ ትሉኝ ፡ እን ደኾን ፤ ደብተራ ፡ አሪትን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ሰዎች ፡ ከሱ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ የማይገባቸው ፡ መሥዋዕት ፡ አለን ፡ (እለ ፡) ሥጋው ፡ ደሙ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ዘይሠውዑ ፡ እንስሳ ።

የሚሠዉት ፡ ላም ፡ በግ ፡ ነበርና ።

www.zeyeneta.com

ደመ ፡ ያበውዕ ፡ ሊቁ ፡ ካህናት ፡ ውስተ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ።(ዘሌዋ ፡፲፮ ፡፳፯ ።)
ሊቁ ፡ ካህናቱ ፡ ኃጢአት ፡ ስለማስተሰረይ ፡ ደሙን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይገባ ፡ ነበር ።
ወያውዕይዎ ፡ ሥጋሁ ፡ በአፍአ ፤ እም ፡ ትዕይንት ።(ዘፀአ ፡ ፳፱ ፡ ፲፬ ።)
ሥጋውን ፡ ግን ፡ ከከተማ ፡ በአፍአ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉት ፡ ነበር ።

፲፪ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኢየሱስኒ ፡ ከመ ፡ ይቀድሶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በደሙ ፡ በአፍአ ፡ እምትዕይንት ፡ ተቀትለ ።(ዮሐ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ።)
(ወበእንተዝ) ፡ ምሳሌውን ፡ ለመፈጸም ። እንድም ፡ ደም ፡ አፍሰው ፡ ስብ ፡ አጢሰው ፡ አስተራኩሰው፡ ነበርና ፤ ሕዝቡን ፡ በደሙ ፡ ያከብራቸው ፡ ዘንድ ፡ ከከተማ ፡ በአፍአ ፡ ተሰቀለ ።

፲፫ ፡ ወይእዜኒ ፡ ንፃእ ፡ ኀቤሁ ፡ አፍአ ፡ እምትዕይንት ፡ እንዘ ፡ ንጸውር ፡ ትዕይርቶ ። (ም፡ ፲፭ ፡ ፳፯ ።)
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ እሱ ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ እየተቀበልን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በምናኔ ፡ ተለይተን።
እሱ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ እንገሥግሥ ።

፲፬ ፡ ዘእኮ ፡ ብነ ፡ ዝየ ፡ ሀገር ፡ ዘይነብር ።
ይህን ፡ ኃላፊውን ፡ ዓለም ፡ ወርሰን ፡ ያምንቀር ፡ አይደለምና ።
አላ ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ መንግሥተ ፡ ነኃሥሥ ፡(ም ፡ ፲፩ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ።)
የምትመጣውን ፡ መንግሥተ ፡ ስማይን ፡ እንሻለን ፡ እንጂ ።

፲፭ ፡ ቦኑ ፡ እንከ ፡ ኢይከውነነ ፡ ናብዕ፡ መሥዋዕተ፡ ስብሐት ፡ በሰሉ ፡ ጊዜ፡ ለእግዚአብሔር፡ (፩፡ ጴጥ፡ ፪፡ ፭ ።)
በውኑ ፡ ዅል ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምስጋና ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ እይገባንምን ።
ፍሬ ፡ ከናፍሪነ ።(ሆሴ ፡ ፲ ፬ ፡ ፫ ።)
ያንደበታችን ፡ ፍሬ ፡ የሚኾን ፡(አለ ፡) የላይ ፡ ከንፈር ፡ የታች ፡ ከንፈር ፡ ደክሞ ፡ የሚያቀርበው፡ ስለ ኾነ ፡ ፍሬ ፡ ከናፍሪነ ፡ አለ ።
ከመ ፡ ንእመን ፡ በስሙ ።
ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደኾነ ፡ እምነን ፡ የምስጋና ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ አይገባንምን፡

፲፮ ፡ ወኢትርሥዑ ፡ ምሕረ ፡ ነዳያን ።
ለነዳያን ፡ መመጽወትንም ፡ እትተዉ፡
ወተሳትፎሙ ።
እናንተ ፡ በመስጠት ፡ እነሱ ፡ በመቀበል ፤ በጸሎት ፡ አንድ ፡ መኾንንም ፡ እትተዉ ።
አስመ ፡ ዘከማሁ ፡ መሥዋዕት ፡ ይኤድሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ፊል ፡ ፬ ፡ ፲፰ ።)
እንዲህ ፡ ያለ ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋልና ።

፲፯ ፡ ተአዘዙ ፡ ለመኳንንቲከሙ ።
መምህሮቻችሁንም ፡ እርዱ ።
ወተኩነኑ ፡ ሎሙ ።
ተገዙላቸው ።
እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይተግሁ ፡ በእንተ ፡ ነፍስክሙ ።(ቈ ፡ ፯ ።)
ነፍሳችሁን ፡ ለማዳን ፡ ተግተው ፡ ያስተምሯችኋልና ።
ከመ ፡ ዘይትሐሰብዎሙ ፡ በእንቲአከሙ ።(ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ። ፴፫ ፡ ፪ ፡ ፰ ።)
ፍትሐ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ስለናንተ ፡ የሚቈጣጠሯቸው ፡ እንደመኾናቸው ። ጉበር ፡ ሀካይ ፡ ለምንት፡ ኢያግባዕከ ፡ ወርቅየ ፡ ወስተ ፡ ማዕድየ ፡ ብለው ።
ዘመ ፡ በፍሥሐ ፡ ይግበርዎ ፡ ለዝንቱ ።
ይህን ፡ ማስተማሩን ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ።
ወኢይንሀከ ።
እንዳያዝኑ ።

፲፰ ፡ ወዝንቱ ፡ ይደልወክሙ ።
ይህም ፡ ይገባችኋል ፦ ዝንቱ ፡ ያለውን ፡ ያምጣው ።
ከመ ፡ ትጸልዩ ፡ በእንቲአነ ።
ስለኛ ፡ ትጸልዩልን ፡ ዘንድ ።

www.zeyeneta.com

ንትአመን ፡ ከመ ፡ ታፈቅሩ ፡ ወትፈቅዱ ፡ ሠናየ ፡ ለዝሉ ። (፱፡ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ፡ ።)
ለሰው ፡ ኹሉ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ መሥራትን ፡ እንድትወዱ ፡ እናምናለንና ።

፲፱ ፡ ወፈድፋደ ፡ ትግበሩ ፡ አስተበቍዓክሙ ፡ ዘንተ ።
ይልቁንም ፡ ይህንን ፡ ትሠሩት ፡ ዘንድ ፡ እማልዳችኋለሁ ፡ (አለ ፡) ዐውቆ ፡ መቅረት ፡ አይረባምና ።
ከመ ፡ ፍጡነ ፡ እበጽሐክሙ ።
ፈጥኜ ፡ ወደናንት ፡ እንድ ፡ መጣ ፡ መጠን ።

፳ ፡ ወአምላክ ፡ ሰላም ፡ ዘአንሥአ፡እምውታን፡ ለሊቀ ፡ ኖሎት፡ አባግዕ ።(ኢሳ፡ ፶፫፡ ፲፩፡ ሕዝ፡ ፴፬፡ ፳፪፡ ዕብ፡ ፲ ፲፫ ።)
አባግዕ ፤ ምእመናን ፡ ኖሎት ፡ ቀሳውስት ። ሊቅ ፤ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ የምእመናን ፡ ጠባቆች ፡ የሚኾኑ፡ የቀሳውስት ፡ እለቃ ፡ የሚኾን ፡ ክርስቶስን ፡ ክሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያሥነሣው ፡ የፍቅር ፡ የአንድት ፡ ባለቤት እግዚእብሔር ።
በደመ ፡ ሥርዓት ፡ ዘለዓለም ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያጽንዕክሙ ።
የዘለዓለም ፡ ሕግ ፡ የወንጌል ፡ የዘለዓለም ፡ ርስት ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ። መጽኖ ፡ በሚኾን ፡ በደሙ ።
፳፩ ፡ ያጽንዕክሙ ።
ክጌታችን ፡ ክኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በመኾን ፡ አንድትጸኑ ፡ ያድርጋችሁ ።
ከመ ፡ ትግበሩ ፡ ፈቃዶ ፡ በዙሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እሱ ፡ የሚሻውን ፡ ነገር ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ።
እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ይገብር ፡ ለክሙ ፡ ሥምረቶ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጋዥነት ፡ ፈቃዱን ፡ ለማሠራት ፡ እሱ ፡ እያገዛችሁ ።
ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ለዘለዓለሙ ፡ ክብር ፡ ጌትነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።
አሜን ። በውነት ።

፳፪ ፡ እስተበቍዓክሙ ፡ እኃዊነ ፡ ተወክፉ ፡ ቃለ ፡ ትምህርትክሙ ።
ወንድሞቻችን ፡ ያስተማርኋችሁን ፡ ትምህርት ፡ ተቀበሉ ፡ ብዬ ፡ እማልዳችኋለሁ ።
እስመ ፡ ቦኑሮ ፡ እዘዝኩክሙ ።
ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ክብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ጸፈላችኋለሁና ።

፳፫ ፡ ወእእምሩ ፡ ከመ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እኁነ ፡ ዘተፈነወ ፡ አምኀቤነ ፡ ኀቤክሙ ፡
ከእኛም ፡ ዘንድ ፡ ተልኮ ፡ ወደናንተ ፡ የመጣ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከመ ጀመሪያ ፡ እስክ ፡ መጨረሻ ፡ ተመልክተው ፡ የርሱ ፡ መኾንን ፡ በዚህ ፡ ያውቁታል ።
ወእመሰ ፡ አፍጠነ ፡ መጺእ ፡ እሬእየክሙ ።
ፈጥኖም ፡ ቢመጣ ፡ እያችኋለሁ ።(ሐተታ ፡)ከወደፊት ፡ መጥቶ ፡ ያያቸዋል ፡ ቢሉ ፡ ከእንድልስ ፡ መጥቶ፡ ያያቸዋል ።

፳፬ ፡ አምኑ ፡ ዙሉ ፡ መኳንንቲክሙ ።
መምህሮቻችሁን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ እላችሁን ፡ በሉ ።
ወዙሉ ፡ ቅዱሳነ ።
ምእመናንን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ በሉ ።
አምኑክሙ ፡ እለ ፡ በአጣልያ ።
በአጣልያ ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አላችኑን ፡ ይሏችኋል ።

፳፭ ፡ ወጸጋሁ ፡ ምስለ ፡ ዙልክሙ ።
ጸጋው ፡ በኹላችሁ ፡ እድሮ ፡ ይኑር ።
አሜን ።
በውነት ።

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ዕብራውያን ፡ ወተፈነወት ፡ በእደ፡ ጢሞቴዎስ፡ ወተጽሕፈት ፡ በአጣልያ
በአጣልያ ፡ የተጻፈች ፡ ከጳውሎስ ፡ በጢሞቴዎስ ፡ እጅ ፡ ለዕብራውያን ፡ ሰዎች ፡ የተላከች ፡ ክታብ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።
አንግሥቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ለአስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።